# ምዕራፍ 16
## የብጹዕ አቡነ መልከ ጼዴቅ መንፈሳዊ ትግል

ሊቀ ሥልጣናት አባ ሃብተ ማርያም ወርቅነህ (አባ መልከ ጼዴቅ) አዲስ አበባ የቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ አስተዳዳሪ በነበሩ ግዜ በመጠኑ አውቃቸው ነበር፡፡ የዓፄ ኃይለ ሥላሴ ወዳጅ ናቸው ይባልላቸው ስለነበር የማያቸው ንጉሡን በማይበት መነጽር ነበር፡፡ ምክንያቱም ከንጉሡ ጋር በነበራቸው የቅርብ ግንኙነት መጠቀሚያ ያደርጓቸዋል የሚል አስተሳሰብ ነበረኝ፡፡

ነገሮችን ከሁኔታዎች ጋር ሳያገናዝቡና ሳያጠኑ በጭፍን ያለ አገባብ በጠማማነት አወላግዶ መፈረጅ ትልቅ ስህተት መሆኑን የተረዳሁት የብጹዕ አቡነ መልከ ጼዴቅን ምንነት ቀርቤ ካወቅኩ በኋላ ነው፡፡ ከውስጥ የተደበቀ መሰሪነት የላቸውም፤ ግልጽ የግንባር ሰው ናቸው፡፡ዓይን አፋር አይደሉም፤ ከይሉኝታና ከፍርሃት እራሳቸውን ነፃ ያደረጉ ሰው ናቸው፡፡ የሰውን ባሕርይ አውቆ ለመውደድም ሆነ ለመጥላት፤ ለማመስገንም ሆነ ለመንቀፍ የሚቻለው ቀርቦ የሚሠራውን በዓይን በማየት ተጨባጭ መረጃዎችን በመያዝ ያውም ረዘም ያለ ግዚያት አብሮ በመኖር መሆን ሲገባ እንዲያው በወሬ በመረበሽ ከነ እገሌ ጋራ ወዳጅ ከሆነ የጥፋታቸው ተካፋይ ነው ብሎ እነርሱ በሚታዩበት መነጽር ማየት ሕሊናዊ ሚዛን የጎደለው ስህተት ነው፡፡

ያንድን ሰው ምንነት በአንድ ጊዜ ግንኙነት ወይም በወሬ ማወቅ አይቻልም፡፡ ቢያንስ ለርኸርም ጊዜ አብሮ መኖር ያስፈልጋል፡፡ አብዛኛውን ግዜ አንዳንድ ሰዎች ምንም ዓይነት ተጨባጭ በሌለው ነገር በወሬ (አሉ ባልታ) ተመርተው ውስጡን መርምረው በማያውቁት ሰው ላይ የሚያካሄዱት የስም ማጥፋት ዘመቻ አድሮ ውሎ እውነተኛው ነገር ሲገለጽ እያሳፈራቸው በጸጸት እራሳቸውን የጎዱ ሰዎች አውቃለሁ፡፡

ብጹዕ አቡነ መልከ ጼዴቅን በሚገባ ያወቅኋው ከሱዳን ወደ አሜሪካ መጥቼ እርሳቸውም ከኢትዮጵያ ወደ አሜሪካ መጥተው የኢትዮጵያ ጉዳይ ከአገናኘን በኋላ ነው፡፡ ስለ ኢትዮጵያ ጉዳይ ምን ማድረግ እንደሚገባን ተወያይተን የተስማማንበት አቋም ለግዜው ልንሰራው የሚገባ ባሜሪካ ውስጥ የትም የተበታተኑትን ኢትዮጵያዊያን ስደተኞችን በተለይም ተቃዋሚ ኃይላትን የተራራቁትን በማቀራረብ፤ የተቀያየሙትን በማስማማት የመወያያ መድረኮችን በማዘጋጀት በመዕከላዊነት ለማገልገል እንዲሁም ወጣቶች በኢትዮጵያዊነት ታንጸው የሚያድጉበትን የመገናኛና የመወያያ ክበቦችን በማመቻቸት በምክር ለመርዳት ጉባዔ አበውን መስርተን አብረን ስንሰራ ነው የብጹዕነታቸውን ምንነት ለማወቅ ዕድል ያገኘሁት፡፡



ብጹዕ ወቅዱስ አቡነ መልከ ጸዴቅ



ብጹዕ ወቅዱስ አቡነ መልከ ጼዴቅ

የሰው መለኪያው ሥራው ነው። ከሚፈጽመው ተግባር ውጭ ሌላ መለኪያ የለውም። ሥጋና ደም፣ ሃይማኖትና ፖለቲካ እንደማይነጣጠሉ የሰው ባሕሪዩም ከሥራው ጋር የተያያዘ ነው።

የዱሮው ሊቀ ሥልጣናት አባ ሀብተ ማርያም ወርቅነህ የዛሬው ብፁዕ አቡነ መልከ ጼዴቅ ማናቸው? ብሎ መጠየቅም የተገባ ነው። ቆብ የጫነ ሁሉ መነኩሴ፣ የጠመጠመ ቄስ አይደለም " ተብሏል። ብፁዕ አቡነ መልከ ጼዴቅ ግራና ቀኝ ስለት ያለው እውነተኛ አንድ ወጥ ሠይፍ ታጥቀዋል። ሠይፋቸው በአንደኛው ወገን ያለው የሃይማኖት መንፈሳዊ ስለት፣ በሌላው ወገን ያለው ፖለቲካዊ ስለት ሲሆን በሁለቱም ሳይጠራጠሩ ይቆርጡበታል። ሠይፋቸው እንደ ልፍስፍሱ የዶሮ ላባ አይደለም የዶሮ ላባ ግራና ቀኝ ሠይፍ ቢኖረውም አይቆርጥበትም። ሥልጣን ያላቸው በሥልጣናቸው እንደማይቆርጡበት ማለት ነው።

የብፅዕ አቡነ መልከ ጼዴቅ ሠይፍ ግን ነበልባላ ስለቱ የማይበርድ ከሃዲን በጣጥሶ የሚጥል በዕምነት የተሳለ እውነተኛ ሰይፍ ነው። እርቱዕ ሃይማኖት ያላቸው አቡነ መልከ ጼዴቅ እምነታችን አንክድም ለጣዖት አንሰግድም ብለው በዕሳት እንደ ተጣሉት ሰልስቱ ደቂቅ ወደ አንበሳ ጎሬ እንደ ተወረወረው ዳንኤል እምነታቸውን የሚጻረር ፈተና ተፈትነዋል።

ደርግ አስሮ መስቀላቸውን እንዲያስረክቡ ቢያስገድዳቸው የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስን የመስቀሉን ምልክት ግደሉኝ እንጂ አላስረክብም፣ የምንኩስና ቆባቸውንም እንዲያወርዱ ቢያስገዱዷቸውም በአምላኬ በእግዚአብሔር ስም የተባረከውን የዕምነት ምልክቴን አልጥልም ብለው የተቃወሙ፣ ጸጉራቸውንም እንዲላጩ ቢገደዱም ራሴን ከእግዚአብሔር ምላጭ በቀር ሌላ አይነካውም ብለው በመቃወማቸውና በኃይል ቢያስገዱዷቸውም ሞትን ፈርቼ ከዕምነቴ ፈቀቅ አልልም ብለው እስከ መጨረሻ በዕምነት ጸንተው በመቆም መስቀላቸውንና ቆባቸውን ሳይጥሉ፣ ጸጉራቸውንም ሳያስነኩ ስምንት ዓመት ታስረው ከነ ክብራቸው የወጡ መንፈሳዊ ጀግና ቆራጥና ደፋር መሆናቸውን አብርው ታስረው የነበሩ ሁሉ መስክረውላቸዋል። "ሰውን መፍራት ወጥመድ ያመጣል፡ በእግዚአብሔር የሚያምን እርሱ ይታደገዋል" ( ምሣ.29፤17) የመጀመሪያውን ፈተና ባስደናቂ ሁኔታ በድፍረት በእግዚአብሔር ጸጋ ተቋቁመው አልፈውታል።" ሕይወቴ ለእኔ ክርስቶስ ነው ሞትም ለእኔ ጥቅሜ ነው" (ፊሊ 1፤ 21) ብለው ታግለዋል።

የእግዚአብሔር ቃል አይታሠርም ብለው ብዙ የትግል መሰናክሎችን አልፈዋል። በተለይ በደብተራዎች መካከል ምቀኛ የተባለ ጦር አለ። ሊቀ ሥልጣናት አባ ሀብተ ማርያም ወርቅነህ የመንፈሳዊ ኮሌጅ ዋና አስተዳዳሪ (ዲን) በነበሩበት ግዚያት ብዙ ወጣቶችን አስተምረዋል፣ ለከፍተኛ ትምህርት ወደ ውጭ እየላኩ ካስተማሯቸው ውስጥ የጵጵስና ማዕረግ ያገኙ ብዙ ናቸው።

እንደ ሊቀ ሥልጣናት አባ ሀብተማርያም ያለ ንቁና ታታሪ



አርቆ ተመልካች ጳጳስ ሁኖ ክህነት በመስጠትና በመባረክ በሃገረ ስብከት ተወስኖ ተሾሞንሙኖ ከመቀመጥ ይልቅ እየተዘዋወሩ ማስተማርን መርጠው የጵጵስና ማዕረግ ቢሰጣቸው አልተቀበሉትም ነበር። በማስተማር ቀጥለው ድንቁርናን ለመዋጋት በአዲስ አበባ ዙሪያ ሰበታ የደናግል ትምህርት ቤት ከፍተው ትምህርት የጠማቸውን ወጣቶች አስተምረዋል።

"ነቢይ በአገሩ አይከበርም" እንደተባለው ሆነና ነገሩ የሊቀ ሥልጣናትን መልካም አርአያነት ተከትለው ለማስተማር መንፈሳዊ ቅንዓት አድሮባቸው ጋሬጣ እየሆኑ የሚወጓቸው የሠሩትን ሁሉ ለማፍረስ የሚጥሩ ከመንደራቸው አልፈው ማየት የማይችሉ ይጠናዎቷቸው ነበር። (በተለይም ወያኔ ሥልጣን ከያዘ በኋላ) ሊቀ ሥልጣናት አባ ሀብተማርያም ከእስር ቤት ከውጡ በኋላም ድንቁርናን ለመዋጋት ዓቅደውት የነበረውን ዘመቻ ለማካሄድ ቢሞክሩም አልተሳካላቸውም። እምነታቸውን የከዱ እቅዳቸውን ሁሉ አሰናክለውባቸዋል። "የፈሩት ይደርሳል የጠሉት ይወርሳል" እንደ ተባለው በተደረገባቸው ተጽዕኖ ዕቅዳቸው ሁሉ በመሰናከሉ ቀደም ብሎ አልቀበልም ያሉትን ሹመተ ጵጵስና መቀበል ግድ ሆኖባቸው አባ መልክ ጼዴቅ ሊቀ ጳጳስ ተብለው ተሾሙ።

ሊቀ ጳጳስ ተብለው ከተሾሙም በኋላ ብዙ ሳይቆዩ ሌላው ትልቁ ሁለተኛው ፈተና ተደቀነባቸው። የፊተኛው ፈተና አገር ስለነበር በአገራቸው ሁነው ተከራክረው አለፉት። የተደቀነባቸውን ሁለተኛውን ፈተና ግን ተከራክረው የሚያቸንፉባት አገራቸውን ተገንጣይ ወያኔ ትግራይ በጎሣ በጣጥሶ በሃይማኖትም ውስጥ ገብቶ በድንበርና ክልል ከፋፍሎ ጎሣዊ መስመር እንድትከተል በማድረግ በካድሬነት ያገለግሉት የነበሩትን አቡነ ጳውሎስን ፓትሪያርክ አድርጎ በመሾሙ በፓትሪያርክ ላይ ፓትሪያርክ አይሾምም፣ ከካህናት መተዳደሪያ ደንብ ከቅዱስ ሲኖዶስ ድንጋጌ ውጭ ነው በማለት በድፍረት ቢከራከሩም ሰሚ አላገኙም። ስለዚህ ከሃይማኖት ድንጋጌ ውጭ የእግዚአብሔር የአምልኮት ሥርዓት ተጥሶ በጦር መሳሪያ አገዛዝ ውስጥ በመውደቁ አገርም በጎሣና በቋንቋ መከፋፈሉን በማውገዝ የወያኔን የጥፋት እርምጃ ለዓለም ሕዝብ በማስታወቅ ትግላቸውን ቀጥለዋል።

ብፁዕ አቡነ መልከ ጼዴቅ በንቃታቸው ላይ ያልተኙ ከግብዝነት ወጥመድ ያመለጡ ለዩልኝታ ያልተገዙ እውነተኛ የስነ መለኮት ምሁር ናቸው። አንዳንድ የዋሆች ጥልቅ የፍልስፍና ትምህርት የሚጎድላቸው ሃይማኖት ከፖለቲካ አያገባውም እያሉ የፖለቲካ ጉዳይ ሲነሳ የሚበረግጉ አሉ። እንደነዚህ ያሉ ሃይማኖት ለምን እንደተመሠረተ የሚያውቁ አይመስለኝም። ሃይማኖትን እኔ እንደ መሰለኝ ግድግዳና ምሰሶ ሁነው ያቆሙት ሁለት ትዕዛዞች ናቸው። እነርሱም አንደኛው " ጌታ አምላክህን በፍፁም ልብህ፣ በፍፁም ነፍስህ፣ በፍፁም ኃይልህም በፍፁም አሳብህም፣ ውደድ ባልንጀራህንም እንደ ራስህ ውደድ፣" (ሉቃ. 10፡27) የሚሉ ናቸው። ማንኛውም ሰው እንደራሱ አድርጎ እንዲወድ የተሰጡ ትዕዛዞች እነዚህ ሲሆኑ ሌሎች

ትዕዛዛት ግን እነዚህን መመሪያዎች ለማጥበቅ የተሳኑ ጨፈቃዎች ወይንም አጃቢዎች ናቸው። በእነዚህ ሁለት ትዕዛዞች ማናቸውም ነገሮች ሲጠቃለሉ ግባቸው አንድ ይሆናል። የኃጢአትን መንገዶች ሁሉ ይዘጋሉና ።

እግዚአብሔር በፍፁም ልብ መውደድና ማክበር በጉልበት እኔ አምላክ ነኝ ስገዱልኝ ገብሩልኝ ከሚል ተከላክሎ እንደሚያድን ቅዱስ መጽሐፍ ምሳሌዎችን እየደረደረ ይናገራል። እግዚአብሔር ፈጣሪያችን "ሁሉን አድራጊ" አመለከቱም አላመለከቱ ሥልጣኑ አይቀነስም፤ ቢያመለክቱም አይጨመርለትም። ሰጭም ነሽም ለዘለዓለም የማይጎልና የማይቀንስ በሙላቱ የሚኖር የኃይልና የጥበብ ምንጭ በፍጡር ህሌና የማይዳሰስ አምላክ ፍጥረቱን የሚወድለትና (የሚያከብርለት) የሚረዳለትን ይደግፈዋል።

ሁለተኛይቱ ዋና ትዕዛዝ ጓደኛህን እንደራስህ ውደድ የምትለው ናት። ጓደኛ ሲል ሁሉን የሰው ልጅ ማለቱ ነው። እንግዲህ በዛሬው ዘመን ፖለቲካ እየተባለ የሚጠራው የሰው ልጆች የዕለት ከዕለት ኑሮ መምሪያ ነው። በአንድ ቃል ሲጠቃለል የሕዝብ አስተዳደር ወደ ሚባለው ይመራል። የሕዝብን መልካም አኗኗር የሚያደራጀው የሕዝብን ሰላምና ደኅንነት የሚጠብቅ ነው። በጭቆናና በብዝበዛ በግፍ ሥራዎችም ሰብአዊ መብቶች እንዳይረገጡ የሚከላከል ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ነው። ፍትህና ሕግ ሲጓደል ሕዝብ ሲጨቆንና ሲበዘበዝ ሲገደልና ሲታሰር የግፍ ድርጊት ጭቆና ሲካሄድበት እያዩ ከፖለቲካ አያገባኝም ማለት " ወንድምህን እንደ ራስህ ውደድ የሚለውን " አምላካዊ ትዕዛዝ መተላለፍ ነው።

እግዚአብሔርን ማገልገል ማለት በስቃይ ያለን ሰው መርዳት ነው። ከችግሩና ከስቃዩ እንዲላቀቅ መታገል ነው።ያነው አግዚአብሔርን መውደድ። ሁሉም ነገር ጓደኛህን እንደራስህ አድርገህ ውደድ በሚለው ትዕዛዝ ተጠቃሏል። በሰዎች መካከል ፍቅር ካለ እርስ በርስ መገዳደል ዝርፊያና ጭቆና ምቀኝነትና ስስት ዘረኝነትና ጎሰኝነት አድላዊነትና ጣዖትነት የመሳሰሉ ይቋረጣሉ።

እስራኤላዊያን ከግብፅ ወጥተው ወደ ከንዓን በሚያልፉበት ግዚያት የአማሌቃውያን ንጉሥ አጋግ የእስራኤላውያንን ደም አፍስሶ ነበርና ደሙ መመለስ ነበረበት። ነብዩ ሳሙኤል የእስራኤልን ንጉሥ ሳዖልን "ሂደህ አማሌቃውያንን ምታ፤ ያላቸውን ሁሉ ፈጽመህ አጥፋ፤ አትማራቸው፤ ወንዱንና ሴቱን፤ ብላቴናውንና ህፃኑን፤ በሬውንና ግመሉን፤ በጉንና አህያውን፤ ግደል" ብሎ ከእግዚአብሔር የተገለጸለትን ይነግረዋል። አጋግም ከእስራኤላውያን ጋር ተዋግቶ በጦር ሜዳ ሲማረክ የእስራኤል ንጉስ ሳዖል በነብዩ የተነገረውን ሳይፈጽም በመቅረቱና ምሕረት ስላአደረገለት ነብዩ ሳሙኤል ተቆጥቶ አጋግን ወደ እርሱ እንዲያቀርቡት አድርጎ ንጉሡ አጋግ ከነብዩ ሳሙኤል ፊት ሲቀርብ "በውኑ ሞት እንዲህ መራራ ነውን?" አለ። ሳሙኤልም ሲመልስለት "ሠይፍህ ሴቶችን ልጆች አልባ እንዳደረጋቸው እናትህ



በሴቶች መካከል ልጅ አልባ ትሆናለች።" ብሎ ሳሙኤልም አጋግን በእግዚአብሔር ፊት በጌገላ ቆራረጠው። (ሳሙ፡ ቀዳ. 15፡ 33) ይላል። ታዲያ ይህ ምንን ያመለክታል? ነፍስ ገዳዮችንና ግፍ ሰሪዎችን መቃወም ነው። የእግዚአብሔር ፀጋ ያደረበት ነብዩ ሳሙኤል በሃይማኖት መሪነቱ ትንቢት በመናገር ብቻ አልተወሰነም። በነፍስ ገዳዩ ላይ እራሱ ርምጃ ወሰደ እንጂ ፖለቲካ ነው ብሎ አያገባኝም ብሎ አላለፈውም። ኢትዮጵያዊው አቡነ ጴጥሮስም ወራሪውን ፋሽስት አውግዘዋል። ይህን ነብዩ ሳሙኤል የወሰደውን ርምጃ ዓይነት ማንም ሃይማኖት አለኝ የሚል ሊያደርገው የሚገባ መልካም አርአያ ነው። ምንም እንኳን ሁሉን አድራጊ በሆነ እግዚአብሔር ላይ ጠላት ሊኖር ባይችልም እግዚአብሔር የፈጠረውን የሚገድል ሁሉ የትዕዛዙ ተቀዋሚው በመሆኑ ማንም የእግዚአብሔር አማኝ የሆነ ነፍስ ገዳይ፤ ቀማኛ፤ ዘራፊን፤ መቃወም አለበት። የማይቃወም ከሆነ ግን ከከሃዲው የበለጠ ጥፋተኛ ነው። አንዳንድ የዋሆች ወይም ሠነፎች ከሃዲን ወንጀለኛ ከእግዚአብሔር ካልተሰጠው በቀር ሥልጣን መያዝ አይችልም የሚሉ ወንጀለኞች፤ ወንጀለኛን መቃወም እንደ ኃጢአት እየቆጠሩ ሕዝብ ሲሰቃይ ዝም ብለው በማየት " ወንድምህን እንደራስህ ውደድ " የምትለውን ዋነኛዋን የእምነት ሁሉ ማሳረጊያዋን ትዕዛዝ የሚገድሉ ብዙ ናቸው። የሚያሳዝነው ራሳቸው በባዕዳን ሰብከት መተው ሌላውን መግደላቸው ነው።

በማህበራዊ ኑሮ በሰላም ተስማምቶ የሚኖርን ሕዝብ በጎሳና ቋንቋ መከፋፈል፤ ሰብአዊ ፍጡርን ማሰቃየትና መግደል፤ የደከመበትን ሃብቱንና ርስቱን መዝረፍ የለየለት ድንቁርና በመሆኑ ዳግማዊ ሳሙኤል ብፁዕ አቡነ መልከ ጼዴቅ የእግዚአብሔር እውነተኛ አገልጋይ ምሁር ድንቁርናን በሄዱበት ሁሉ ያለ እለዕረፍት በመዋጋታቸው አንዳንድ ስግብግቦችና የመንደር ሰዎች ቢቀኑባቸውም በእነርሱ ላይ እየተራመዱ አልፈዋል።

ብፁዕ አቡነ መልከ ጼዴቅ በውጪ አገር የፈጸሟቸው ተግባራት

1. ነሐሴ 30.1991 (እ.አ.አ.) ጉባኤ አበውን አበረው በመመስረት መርቀው ከፍተዋል።
2. የኤርትራን መገንጠል በመቃወም ወደ ተባበሩት መንግሥታት ጠቅላይ ሠፈር ኒውዮርክ በመሔድ በተደጋጋሚ በተደረጉት የተቃውሞ ሰልፎች ግንባር ቀደም በመሆን የተቃውሞ ድምፅ አሰምተዋል።
3. በዋሽንግተን ዲሲ የኤርትራን መገንጠል በመቃወም በተደረጉት ሠላማዊ ሰልፎች በየግዜው እየተገኙ ለአሜሪካ መንግሥት የተቃውሞ ድምፅ አሰምተዋል።
4. የወያኔን የጎሳ መመሪያ/ ፖሊሲ በመቃወም በዋሽንቶን ዲሲ በየግዜው በተካሄዱት የተቃውሞ ሰልፎች እየተገኙ ንግግር አድርገዋል። ወያኔ ዴሞክራሲን አፍኖ ሰብአዊ መብትን በመርገጡ የዓለም ሕዝብ ድርጊቱን እንዲያወግዝ በጽሁፍ አሳስበዋል።
5. የአሜሪካ መንግሥትና የዓለም ባንክ ለወያኔ መንግሥት በሚሰጡት

ዕርዳታ ዴሞክራሲን አፍኖ ሰበአዊ መብትን የረገጠ በመሆኑ የሚያደርጉትን ማናቸውንም ዕርዳታ እንዲያቆሙ በኋይት ሀውስ በስቴት ድፓርትመንትና በዓለም ባንክ በተደረጉት የተቃውሞ ሰልፎች ተገኝተው የተቃውሞ ጽሁፎችን ያቀረቡ ብፁዕ አቡነ መልከ ጼዴቅ ናቸው፡፡

6. በዩናይትድ ስቴትና በካናዳ በየስቴቱ ቤተ ክርስቲያን በማቋቋም እያገለገሉና እያስተማሩ የምዕመናንን መንፈሳዊ ሕይወት አድሰውታል፡፡

በአጠቃላይ ብፁዕ አቡነ መልከ ጼዴቅ የሰው ልጅ በነፍሱ መንፈሳዊ ሕይወት ሳይጓደልበት በስጋው ጉዳት ሳይደርስበት፣ በሰላምና ጤና የደኅንነት ኑሮ እንዲያገኝ የተቻላቸውን ከማድረግ በዝነው አያውቁምና ሁሉን አድራጊ ልዑል እግዚአብሔር ሆይ ብፁዕ አቡነ መልከ ጼዴቅን ጠብቃቸው በሕግሕ ላይ አምፀው በመቅደስህ ደም በማፍሰስ ያረከሱ የወያኔ ትዕቢተኛ (ደንቆሮ) አምባ ገነን መሪዎችን ሲዋጉ አንተ ደግሞ ኃይልና ብርታት ስጣቸው፡፡ አንተ በመረጥካቸው በሙሴና ሐሮን ላይ ቀንተው በምቀኝነት የተነሱባቸውን ቆሬን፤ ዳታንና አቢራምን ምድር አፍዋን ከፍታ እንደ ዋጠቻቸውና ወደ ሲዖል እንዲወርዱ እንደአደረክሀአቸው ሳይሆን ምህረትህ የበዛችው ይቅርባይ፤ ቻይ፤ ሩኅሩኅ አምላክ ስለሆንክ የብፁዕ አቡነ መልከ ጼዴቅን ምቀኞችና ስም አጥፊዎች ዓይነ ልቦናቸውን ከፍተህ ስህተታቸውን እንዲያርሙ በቅዱስ መንፈስህ ዳስሳቸው፤ የአድማ መድረኮችንም ወደ መንፈሳዊ መድረክ ለውጣቸው፡፡ በክፋት የጠጠረውን አለሎ ልብም አልዝበው፡፡ ጠልፎ ለመጣል የተዘረጉትንም አሽንካላዎች በጣጥሳቸው፡፡ ጌታ ኢየሱስ ሆይ!! ባለ ማወቅ ያንተን ደቀ መዛሙርት ያሳድድ የነበረው የሳኦልን (ጳውሎስ) ሕሌና እንደለወጥህ እንዲሁም በእኩይ መንፈስ ወደ ጥልና ክርክር የሚያመሩትን "ሲቻለው ማረ" ነህና ፍቅርንና ሠላም ሰጥተህ ለመቅደስህ ታማኝ አገልጋይ አድርገህ ለውጣቸው፡፡ ምዕመናንንም ከጮሌዎች (ሐሳይ መሲሆች) ሸንገላ ጠብቃቸው፡፡ እግዚአብሔር በምሕረቱ ባለ ጠጋ ስለሆነ ከወደደን ከትልቅ ፍቅሩ የተነሳ በበደላችን ሙታን እንኳን ብንሆን ግዜ ከክርስቶስ ጋር ሕይወት ሰጠን፡፡ (ኤፌ. 2፡ 4፤5) ተብሏልና፡፡

የግሪኩ የፕላቶን ፍልስፍና አርስቶትል አቀነባብሮና ቅርፅ ስጥቶ ያስፋፋውን የጀርመኑ ሄግል ደግሞ ኃሳቡን ወስዶ በሜታፊዝክስ ጥናቱ በመኖርና በሞት ፍልስፍናው መንፈስን ገድሎ ሳይንስን ሕያው ባደረገበት ፍልስፍናው ሃይማኖትና ማሕበራዊ ሳይንስ ኅብረት የሌላቸው በተለያየ መንገድ እንደሚሄዱ አድርጎ የፈረጀውን ካርል ማርክስ ደግሞ የሂግልን ፍልስፍና እንዳለ ወርሶ በሃይማኖት ፈንታ ማርክሲዝምን አምላክ አድርጎ የቀረፀውን ብዙ የፍልስፍና ምሁራን (አይዲያሊስትን) ሰቦ አስገብቶ ዓለምን ከውዥንብር ውስጥ ከትቶት ነበር፡፡ እነ ማርክስ አንድ አቅጣጫ ይዘው በመጓዝ የሳይንስ ፈጣሪ የሆነውን ታለቁን አምላክ እግዚአብሔርን ረስተው ያስፋፉትን ፍልስፍና የተቀበሉ ጥራዝ ነጠቆች በሃይማኖት ላይ ባደረጉት ተፅዕኖ ብዙዎችን ከአደጋ ላይ በጣሉበት ግዜ ለታላቁ የስነ መለኮት ምሁር



ለአባ መልከ ጼዴቅ ብርታትና ቆራጥነት ሰጥቶ የእግዚአብሔርን ታላቅነት ወህኒ ቤት ሳይቀር አስተምረዋል፡፡ " ምድርም ከሚቀመጡባት በታች ረክሳለች፤ ሕጉን ተላልፈዋልና፤ ሥርዓቱንም ለውጠዋልና፤ የዘለዓለሙንም ቃል ኪዳን አፍርሰዋልና " (ኢሳ. 24፤5) "ስለዚህ መርገም ምድርን ትበላለች፤ በእርሷም የተቀመጡ ይቀጣሉ" (ኢሳ. 24፤6) ተብሎ በነብዩ የተነገረው ትንቢት ተፈጽሟል፡፡

የሶቬየት ሕብረትና የደርግ (ኢሠፓ) አወዳደቅ በጣም አስገራሚና ያልተጠበቀ ነበር፡፡ ኃያሉ አምላክ ልዑል እግዚአብሔር መለኮታዊ ሥልጣኑን የተጋፉትን ሁሉ አንኮትኩቷቸዋል፡፡ የትግራይ ማርኪሲስት ሌኒኒስት ሊግ ትግራይ ማሌሊት የነገ እድል ፈንታቸው መጥፋት ነው፡፡ ሃይማኖትና ሳይንስ በተለያዩ መንገዶች እንደሚሔዱ ሄግልስ በራሱ እቅድ (ሲስተም) ፈርጇል፡፡ ሳይንስ ንጥረ ነገሮችን እያገጣጠመ በመሥራት የሚጨበጡና የሚታዩ ነገሮችን የከሰተ ቢሆንም፤ ሃይማኖት ደግሞ ሁሉን አስገኝ የሆነውን የልዑል እግዚአብሔርን በፍጡር አቅም ሊመረመርና ሊደረስበት የማይችልበት ድንቅ መለኮታዊ ኃይል የገለጠ በመሆኑ ወደ አንድ የእውነት ግብ ያቀራርባቸዋል፡፡ ለማርክሲዝም ፍልስፍና መንደርደሪያ የሆኑት የሃይማኖት መጽሐፍት መሆናቸው የማይካድ ሃቅ ነው፡፡ ለዘመናዊ ሳይንስ መሠረትና መንደርደሪያ የሆኑ የሃይማኖት ሰዎች መሆናቸው የሚካድ አይደለም፡፡

ካርል ማርክስ በአዲሱ ቲዎሪ (ማቴሪያሊዝም አይዳሊዝም በቅራኔ መልክ ለያይቶ ቢፈርጃቸውም) ሃይማኖትና ማኅበራዊ ሳይንስ በብዙ ነገሮች ይገናኛሉ፡፡ ሁኖም ይህ የሚከፋፍል ቲዎሪ ታዳጊ አገሮችን በማመሰቃቀል ለማኅበራዊ ኑሮ ብርቱ እንቅፋት መሆኑ አልቀረም፡፡ ደርግ ኢትዮጵያዊያንን በመደብ ከፋፍሎ በመለያየቱ የኢትዮጵያዊያንን አገር ወዳድነት ሸርሽሯል፡፡ የቀደሙ ኢትዮጵያዊያን ወላጆች ሲበዛ ኩሩዎችና በራሳቸው ሥራ ይመኩ ስለ ነበር የባዕዳን ፍልስፍና መመጽወት እንደ ውርደት እየቆጠሩ በራሳቸው ፍልስፍና ሲመሩ ኑረዋል፡፡ በአራተኛው ምዕተ ዓመት ወደ ኢትዮጵያ ገባ የተባለውን ክርስትናም ቢሆን ወዲያውኑ ኢትዮጵያዊ አድርገው ለውጠውታል፡፡ ልዩልዩ የፈጠራ ሥራዎችም ከባዕድ ያልተወረሱ አገር በቀል ናቸው፡፡ የአሁኑም አዲሱ ትውልድ በራሱ የሚመካ ነፃ ሕዝብ በመሆኑ የውጭ አገር የፈጠራ ሥራዎች ወደ አገራዊ አስተሳሰብ በመለወጥ በራሱ ሥራዎች መካከል ያስፈጽመዋል፡፡

የሃይማኖት ተቋማት ማኅበረ ሰቡን ምሶሶና ዋልታ በመሆን ሲያስተባብሩና ሲያደራጁ መኖራቸውን ሁሉም ያውቀዋል፡፡ ስለዚህ ከጥንት ጀምሮ ሲያያዝ የወረደውን በባህል ላይ የተመሠረተውን መሠረታዊ ጥንካሬ አጥብቆ በመያዝ በዘመናዊ አስተሳሰቦች የባህል ተቋማትንና ልምዶችን ተገቢነት ባለው አኳኋን ዘመናዩንና ነባሩን ሥልጣኔ በማዋሃድ ማኅበረሰቡን ወደ እድገት መምራት አስፈላጊ ነው፡፡ የራስን እየለቀቁ በባዕድ ባህል ዕምነትና ፍልስፍና መዋጥ ግን " የሰው ሲቀላውጡ የራስን ያጡ" እንደ ተባለው እንዳይሆን ብርቱ ጥንቃቄ

ማድረግ ያስፈልጋል።

የኢትዮጵያ ሥነ መለኮታዊ ትምህርት እንደማይንቀሳቀስ የደም ሥር (ሕልውና) እንደ ሌለው ሆኖ መታየት የለበትም። ብዙ ትሩፋት፤ ያስገኘ፤ የነፃነት ጋሻ፤ የማንነት መታወቂያ ነው። ልዩ የሆነው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተወሕዶ ዕምነት ለጥቁር ሕዝብ ሁሉ መመኪያና አልኝታ ነው። ለወደፊትም በሳይንሳዊ ዘመን ካለ ትውልድ ጋር አብሮ የሚሔድ ኢትዮጵያዊ መሠረቱን ሳይለቅ የስሜት ስሮችን (ነርቮችን) የሚያንቀሳቅስ ስነ መለኮታዊ ትምህርት አዘጋጅቶ (ስነ ልቦናዊ) ኢትዮጵያዊ አገር ወዳድነት ምግብ መመገብ አስፈላጊ ነው። የኢትዮጵያ መንፈሳዊ ትምህርት የማያስተነፍስና የማያንቀሳቅስ ቀይዶና አፍኖ በጭቆና የሚይዝ አይደለም። እያንዳንዱ ምእምን አርነት አለው። እንደፈለገው በራሱ ቋንቋ ሊፀልይ ይችላል፤ በፈለገው ስም መጠራት መብት አለው። ያለ ምንም ተፅዕኖ የራሱን ባህል መከተል ይችላል። ይህም ሲባል ልማዳዊ ሸክሞች የሉም ማለት አይደለም፤ ተዝካር፣ ሙት ዓመት፤ ዝክር፤ ግብረሠላምን የመሳሰሉ ኅተራን የሚበሉ ነቀዞች መኖራቸው አይካድም። እነዚህንም ህብረተሰቡ ነቃቅሎ ሊያስወግዳቸው ይገባል። ለቤተ ተክርስቲያን በሕጉ ምሥረት ከአስር አንድ ከተሰጠ ይቀላል። እውነተኛው ኢትዮጵያዊ የስነ መለኮት ምሁር ኢትዮጵያ በማናቸውም ረገድ እየተበለጠች፤ ባህሏም ዕምነቷምን እየተበዘበዘች፤ መንፈሳዊ ፀጋዋን እየተገፈፈች ባለችበት በአሁኑ ወቅት ወደ አለመኖር ስትገፋ ዝም ብሎ እያዩ ሃይማኖት ከፖለቲካ አያገባውም ብሎ የሞኝነት ፈሊጥ አይከተልም። ነፍስና ሥጋንም እንደማይገናኙ ተቃራኒ አድርጎ አይፈርጃቸውም። ነፍስና ሥጋ ከማኅጸን ጀምሮ የተያያዙ ናቸውና እስከ ሞት ድረስ አብረው ይኖራሉ። በሞት ግዜ ብቻ ይለያያሉ፤ ሥጋ ወደ መሬት መንፈስ ወደ መጣችበት (ታርጋለች) ትሄዳለች። ሥጋና ነፍስ ከፖለቲካና ከሃይማኖት በፊት አብረው የነበሩ ስለሆኑ ለያይቶ መፈረጅ አስፈላጊ አይደለም። ሃይማኖት ለሰዎች መተዳደሪያ የተፈጠረ በመሆኑ ከሰዎች የዕለት ከእለት ኑሮ ጋር ተቆራኝቶና ተያይዞ የኖረና የሚኖርም ነው። ከሃይማኖት እምነት ውጭ የሆኑትን ሞራል የካዳቸውን ሰዎች አላከብርም። ማመን የሞራል ግዴታ ነውና በሃይማኖቱ የማይጸና ወላዋይ ውዳቂ ነውና ክብር አያስፈልገውም።

የሃይማኖት መሪ ከቄስ ጀምሮ እስከ ጳጳስ ለሕዝብ ደኅንነትና ሰላም፤ ሕልውናና ሰባአዊ መብት መታገልና መሟገት ተቀዳሚ ግዴታ ነው። የኢትዮጵያ ሕዝብ በመካከሉ ያሉትን ልዩነቶች አስወግዶ የአንድነት ራዕዩን ማለትም የተስፋውን ድምፅ መስማት የሚችልበትን ስልት ቀይሶ በደወል ማስነሳት የሃይማኖት መሪዎች ትልቁ ሚናቸው ነውና ደወል ደውለው የማስነሳት ግዴታ አለባቸው። ምክንያቱም የሃይማኖት መሪ ሕይወቱን ለሕዝብ ጥቅም የለገሰ በመሆኑ ሕዝብ ወደ ነፃ ሕይወት የመምራት ኃላፊነት አለበትና ብፁዕ አቡነ መልከ ጼዴቅ በአዲስ አበባ በኒውዮርክና በዋሽንግቶን ዲሲ ያሰሙትን የነፃነት ደወል በየትኛውም ቦታ መደወል አለበት፤ እግዚአብሔር ምድርን ፈጥሮ በላይዋ "ሕያዋንና ፍጥረታት እንደ ወገኑ እንስሳትን ተንቀሳቃሽን፤



የምድር አራዊትን የባሕር አሦችን የሰማይ ወፎችንም ሰውንም " ፈጥሮ የማያቋርጥ ዘለዓለማዊ የሕይወት ምግብ እንደሰጠ (ዘፍ. 1፤24-27) እንዲሁም ሰው "እነሆ አዳም መልካሙንና ክፉውን ለማወቅ ከእኛ እንደ አንዱ ሆነ " (ዘፍ.፤22) እንደ ተባለለት የሰው ልጅ አእምሮ በዕውቀት እየተለጠጠ ሠፍቶ ሥልጣኔን ፈጥሮ ከብዙ ሺህ ዓመት ጀምሮ በለውጥ እንቅስቃሴዎች ተጉዞ አሁን ካለበት ደርሶ ለሕይወት አስፈላጊ የሆኑትን ሁሉ እየፈጠረ ምርቱን በማሻሻል ድካሙን እያቃለለ ሕይወቱን በተሻለ ሁኔታ የመራበት በትጉሃን ምሁራን ጥረት ነው። የሰው ልጅ ማንኛውንም ሁኔታ ለመለወጥ ችሎታና ዕውቀት ቢኖረውም ለራሱም ሆነ ለሌሎች ሕይወት ጠቃሚ ነገሮችን ለመፍጠር ኖኅ ዘመንን ውስዶበታል። ለሕዝብ መንፈሳዊና ሥጋዊ ሕይወት የሚያስቡ እንደ አቡነ መልከ ጼዴቅ የመሳሰሉ ምሁራን ጅረት በመሆን ለሰው ማሕበራዊ ኑሮ እውቀትን በመመገብ ድንቁርናን ለማስወገድ ታላቅ ተጋድሎ አድርገዋል።

ለሕዝብ መልካም አኗኗር፤ ለእድገቱና ብልጽግናው ለሰብአዊ መብቱ፤እንዲሁም ለመንፈሳዊ ሕይወት የታገሉና በመታገል ላይ ላሉ ወገንና አገር ወዳድ ሁሉ ትንሿን ሰኮንድ እንኳን በከንቱ በዋዛ ፈዛዛ ላላሳለፉ ክብር ይገባቸዋል። ሃይማኖትና ባሕል በትክክል በንቃት ሁኔታ አብሮ ይዳብራል። እነዚህ ነገሮች በንቃት ላይ በሚያደርጉት ተፅዕኖ ሥልጣኔን ወደኋላ ጎትተውታል። አንዳንድ የሃይማኖት አስተማሪዎች እግዚአብሔር የፈጠረውን ሰው መግደል ያፀድቃል እያሉ በማስተማራቸው ሕዝብ እርስበርስ እየተጋጨ ሥልጣኔን (ዕውቀትን) በመግደሉ ለማያቋርጥ ድህነትና በሽታ ተጋልጧል።

ታሪክ በፀረ ምሁርነት የሚያውቃቸው ደርግ፤ ወያኔና ሻዕቢያ ምሁራንን ሲገድሉ ለኢትዮጵያ ዕድገት 30 ዓመት ያህል ሰብስበው ያከማቹትን ዕውቀት በጉድጓድ ውስጥ አስገብተው አገሪቱን ለከፋ ረኃብና በሽታ አሳልፈው የሰጡ አቅማቸውን የማያውቁ ቡድኖች ናቸው። እግዚአብሔር በፈጠራት ምድር መለኮታዊ መንግሥት በአእምሮ ውስጥ የሚታወቅ የማይሻርና የማይለወጥ ዘለዓለማዊ መንግሥቱ ላይ ሁኖ ከዘለዓለም እስከ ዘለዓለም በሥራ ላይ ነው። ምን ግዜም ቦዝኖ አያውቅም። ትጉህና ንቁ አምላክ ነው። ሁሉንም በየቁናው ይሰፍረዋል። ወንጀለኛውን ከሥልጣን ሲያወርድ፤ ሌላውን ወደ ሥልጣን ሲያወጣ፤ የተራበውን ሲያጠግብ፤ ጥጋበኛውን ሲያዋርድ፤ ከኃብታሙ ነጥቆ፤ ድኃውን ባለፀጋ ሲያደርግ፤ ደንቆሮውን ሲያነቃ፤ ዓዋቂውን የማስተዋል ኃይሉን ሲነጥቀው፤ (ቅዱስ መንፈሱን ወስዶ የሚያስጨንቅ ርኩስ መንፈስ ያገባበታል ማለት ነው) ከአንዱ የነበረውን ሥልጣኔ ወደሌላው ሲያዛውር፤ በሽረት ሽረት ሕጉ ላይ ዓለምን ሲያሽከረክር የኖረ ነው። የሰው ልጅ ከሁሉ ቀድሞ ሊያገኝ የሚፈልገው አርነቱን ነው። የኢትዮጵያ ሕዝብ እግዚአብሔርን በማምለክ ቀዳሚነቱን ይዞ በመንፈሳዊ አርነት የኖረ ነው።

ሰው በምድር ላይ ነፃ ሁኖ እንደተወለደ እንደዚሁም በሚያምነው አምልኮት ነፍሱ በመንግሥተ ሰማያት የዘለዓለም ነፃነት አላት ብሎ በማመን እምነቱን ከሚፃረሩት አረማውያን ጋር እየተዋጋ እምነቱን ሳያስደፍር ኖሯል። የኢትዮጵያ ሕዝብ ለምድራዊ ሕይወቱና ለሰማዊ ሕይወቱ (ያገር ወዳድ ሊቃውንት ትውልድ ከማለፉ በፊት) እኩል ታግሏል። እኩል ኑሯል። በመንፈሳዊ አምልኮት በኩል አለቃና ምንዝር አልነበረም። ሰው ከሞተ በኋላ እየተነሳ ባያየውም የኢየሱስ ክርስቶስን ትንሣዔ ሙታን አብነት አድርጎ "ተሠራ በምድር ተሠራ በሰማይ" በሚል መርሆ ለምድራዊው ነፃነት መሄጃ መንገድ፤ መሸጋገሪያ ድልድይ ወደ ላይ መውጫ መሰላል ይሆናል ብሎ ሳይጠራጠር ያምንበታል። ምክንያት የሚሰጠው በባርነት ተገዝቶ ያልረከሰ ሰውነት (ቅዱስ መንፈስ) ሉዓላዊ ክብር አለው ከሚል ነው።

አሁንም ቢሆን ኢትዮጵያዊ ሁሉ አበው አውርሰውት እንዳለፉት ለምድራዊና ለሰማያዊው ነፃነቱ ተግቶ ካልታገለ "ምድር በኃጥዓን እጅ ትጠፋለች" (ኢዮ.9፡ 24) እንዳለው ፃድቁ ኢዮብ ትጠፋለች። እምነት ባልነበራቸው አረመኔ አገሮች ፖለቲካና ሃይማኖት እንደማይገናኙ ባላንጣ አድርገው የከፋፈሉት በኢትዮጵያ አይሰራም።

ምክንያቱም የኢትዮጵያ ሉዓላዊነት ተጠብቆ የኖረው በእግዚአብሔር ኃይል በመሆኑ ነው። "ኢትዮጵያ እጆቿን ወደ እግዚአብሔር መዘርጋቷን" ካቆመች የእግዚአብሔር ቅዱስ መንፈስ ሲለያት ሌላ ምድራዊረዳትና ደጋፊ ስለሌላት ትጠፋለች። የመንፈሳዊ ዓላማ ሕግ ስስትን አስወግዶ እውነትንና ፍቅርን ተላብሶ ለመብት መታገል ነው። እውነተኛ ሃይማኖት በሌላቸው በሃይማኖት ስም ብዙ ማጭበርበር ተደርጓል። መንፈሳዊ ሃቅ በመንግሥት አስተዳደር ውስጥ ኑሮ አያውቅም። ሕዝቡ የፖለቲካ ሕይወት፤ የማሕበረሰብ ሞራል እንዳይኖረው አንድ አካል ሁኖ በመንፈሳዊነቱ እንዳይቆም ተጽዕኖ ተደርጎበታል። እግዚአብሔር በሰዎች መካከል ያቆመው ኪዳን የያንዳዱን መብትና ጥቅም ሳይነካ ሁሉም ተስማምቶ በመንፈሳዊ ሕይወት ተጣምሮ እንዲኖር ነው።

## ኃያሉ እግዚአብሔር የኢትዮጵያን ጠላቶች ተበቀለ

ለዓለም ሰላምና ጸጥታ ጥበቃ (Collective Security) ተቋቋመ የተባለለት የተባበሩት መንግሥታት ድርጅትና በኃይሌ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን በዓለም ሁሉ አስከብራለሁ የምትለው ዩናይትድ ስቴት ኦፍ አሜሪካ የኤርትራን መገንጠል ደግፈው የኢትዮጵያን ተቃዋሚ ኃይሎች በሰላማዊ ሰልፍና በደብዳቤም ያቀረቡላቸውን የተቃውሞ ድምፅ ከምንም አልቆጠሩትም ነበር።

እንዲያው ሕይወት የሌላቸው መሰንቆና በገና፤ ከበሮና ክራር እንደሚያሰሙት ድምፅ በጆሯቸው ከማለፉ በቀር የኒውዮርክና የዲሲ ባለሥልጣናት ኢትዮጵያዊያን የሚያሰሙትን ጩኸት ሰምተው የወሰዱት እርምጃ የለም። የኢትዮጵያውያን ጩኸት በሰው ዘንድ ሰሚ አልነበረውም። ሁሉን አድራጊ እግዚአብሔር ግን በብፁዕ አቡነ መልከ



ጸዴቅ የተመራውን ጩኸት ከንቱ አላስቀረውም። የራሳቸውን አገር ኢትዮጵያን ለማጥፋት ከኢትዮጵያ ጠላቶች ጋር አብረው የዶሎቱትን ሻዕቢያንና ወያኔን አጋጭቶ እርስ በርሳቸው እንዲዋጉ አድርጓል። ዱሮውንም ቢሆን ለኢትዮጵያ ከእግዚአብሔር በቀር ደጋፊና ረዳት ኑሮአት የማያውቅ ሲሆን ወደ መንግሥታት ጩኸት መሔድ አስፈላጊ አልነበረም።

ኃያሉ አምላክ እግሒአብሔር መቶ ዓመት ባልሞላ ግዚያት ውስጥ በኢትዮጵያ ትላልቅ አስደናቂ ታምራት አድርጓል። ኢጣሊያ በ1928 ዓ.ም. የሊግ ኦፍ ኔሺንን ድንጋጌ ጥሳ ኢትዮጵያን ስትወር፤ ኢትዮጵያ ለዚሁ ሊግ ኦፍ ኔሺን በመባል ይታወቅ ለነረው የዓለም ማኅበር አቤቱታ ብታቀርብ የማኅበሩ አባላት አፌዙባት እንጂ አቤቱታዋን አልተቀበሉትም ነበር። ኃያሉ የኢትዮጵያ አምላክ እግዚአብሔር ግን ሁለተኛውን የዓለም ጦርነት አስነስቶ እርስ በርሳቸው እንዲተላለቁ አድርጎ ተበቅሎላታል። እንዲሁም ጠላቷ ኢጣሊያ ተንኮታኩታ ወደቀች። ኢጣሊያ ኢትዮጵያን እንደወረረችና ኢትዮጵያን እንዳዋረደች ተዋረደች።

በ1935 ዓ.ም. ኢትዮጵያን ለመከፋፈል የምሥራቅ ትግራይ የመጀመሪያውን ወያኔን ያነሳሳች እንግሊዝም በአገሯ ውስጥ የሰሜን አየርላንድ ተገንጣዮች ተነስተውባት በዋናዋ ከተማ ለንደን ውስጥ ቦምብ እያፈነዱባት ለብዙ ዓመታት እየተሰቃየች ቆይታለች።

ወያኔና ሻዕቢያ ለጠላት መሣሪያ በመሆን አገራቸው ኢትዮጵያን ክደው በነሳ ከፋፍለው ሕልውናዋን ለማጥፋት ባካሄዱት ሤራ እግዜር ተቆጥቶ በመካከላቸው የለኮሰው እሣት ሲያንገበግባቸው እየታዩ ነው። ገናም የሚከፍሉት ፍዳ ይጠብቃቸዋል "የኃጢአተኞች ወገናቸው የገለባ ክምር ነው፡ ፍጻሜያቸውም ለገሃነም ይሆናል" (ሲራ. 21፡9) ኢትዮጵያን ለማጥፋት የሚተናኮላትን ሁሉ ታላቁ አምላክ እግዚአብሔር ተበቅሎላታል።

የኢትዮጵያን ነጻነት የደፈሩ የሱዳን ድርቡሾችና ግብፆች አገራቸውን እንግሊዝ ወርራ ቅኝ አድርጋ ገዝታቸዋለች። ቱርክም የኢትዮጵያን ልዓላዊነት በመተናኮሏ ትልቁን የቅኝ ግዛቷን አጥታ ተንኮታኩታ ወድቃ ትንሽ አገር ሁናለች። የሱማሌው አምባገነን ዚያድ ባሬ የኢትዮጵያን ሉዓላዊነት በመዳፈሩ በአሳፋሪ ሁኔታ ካገሩ ተባሯል። ኢትዮጵያን ሃይማኖቷንም ሆነ ግዛቷን የተተናኮለ ሁሉ ምንግዜም አይቀናውም። እግዚአብሔር የበቀል እርምጃውን በግልፅ አሳይቷል።

ለሰው ሕይወት ደንታ የሌለውን ጨካኝ ነፍሰ ገዳይ ቡድን በቆራጡ ርቱዓዊ ሃይማኖት በፅኑ ሞራል የተቋቋሙ አይበገሬ ብፁዕ አቡነ መልከ ጼዴቅ የዘመኑ ትልቅ ሐዋሪያ፤ ዘለዓለማዊ ሕይወት የሚገኝበትን ሕዝብን ለዕምነቱ መሿይት እንዲደፍርና በቆራጥነት እንዲታገል ያስተማሩ ትውልድ የሚኮራባቸው ናቸው። ኤርትራን ከኢትዮጵያ ለመገንጠል ሻዕቢያ ያደረገው (ሬፌረንደም) በመቃወም ለተባበሩት መንግሥታት 47ኛው ጠቅላላ ጉባዔ በኅዳር 2 ቀን 1992 ዓ.ም (እንደ ፈረንጆች አቆጣጠር) ከኢትዮጵያ ማኅበረሰብ 10 አባሎች ጋር በመሆን የተጻፈውን 2 ገጽ ደብዳቤ ካቀረቡት አንዱ አገር ወዳዱ

ብፁዕ አቡነ መልከ ጼዴቅ ነበሩ። ለተባበሩት መንግሥታት ልዩ ጉባኤ ሊቀመንበር የተጻፈው ደብዳቤና የተሰጠው መልስ ግልባጭ በአባሪ ተመልክቷል።

በጥንታዊቷ ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ሃይማኖት እኩልነት፡ አንድነትና ወንድምአማችነት አገራዊ ሉዓላዊነትን የያዘች ነበረች። ሃይማኖትን ማክበርና በሃይማኖት ህልውናን መግለጽ እንዲሁም በሃይማኖት ሕይወት ውስጥ ኢትዮጵያዊያን በሚኖሩበት ግዜያት ሕዝብ ሠላምና ጤና ፍቅርና አንድነት ነበረው። ምንም እንኳ እግዚአብሔር አንድ ብቻ መሆኑ ቢታወቅም ብዙ የሃይማኖት ቡድኖች ቢፈለፈሉና ሃይማኖትን የመምረጥ ነጻነት ቢኖርም፡ በሃይማኖቶች መካከል መፈቃቀድ፡ ሕጋዊ እኩልነትና ሠላም ማስፈን ይገባል።

በአንጻራዊነት የሕዝብን አንድነት የሚንድ በሃይማኖቶች መካከል የቃላት መተቻቸት፡ አንዱ ሌላውን ማጥላላትና መንቀፍ ሃይማኖት ሳይሆን ለሥልጣን የሚወዳደር የፖለቲካ ጭራቅነት ነው። እንደሚታወቀው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን እራሷን ችላ ከማንኛውም የውጭ ሃይማኖቶች ያልተደቀለች በብሔራዊ ወጥነት የውጭ ሃይማኖት ተጽዕኖ ሳይኖርባት በተወሰኑ ክልሎች ሕልውናዋን ይዛ ቆይታለች። ይህችው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን የአገሪቱ የሕልውና መሠረት፡ የነፃነት፡ ጋሻ፡ የታሪክ መነሻ፡ በመሆኗ የዕምነት ዴሞክራሲያዊ አማራጭ የማይፈለግባት እናት ሃይማኖት ናት። ከፖለቲካ ነፃ ሁና በራሷ መመሪያ ታሪካዊ እምነቷን ይዛ ቆይታለች።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ከራሷ እየተፈለፈሉ በወጡ እስላሞችና አይሁዳዊያን፡ ካቶሊኮችና ፕሮቴስታንቶች ላይ ተጽዕኖ ሳታደርግ በራሷ የሞራል ጥንካሬ ሕልውናዋን ይዛ ቆይታለች። ማንኛውም መጤ ሃይማኖት በራሱ ቀኖናዊነት እምርታውን ሲቀጥል በሁሉም ተከታዮቹ ላይ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ምንም ዓይነት ተጽዕኖ ያላደረገች፡ የበላይነት ስሜት ያላሳየች በመሆኗ ሁሉም የመነጨባት ለባህሉና ለወጉ መሠረት ለሆነች ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ሃይማኖት ብሎም ለቅርሱና ለማንነቱ መታወቂያ ሲል ማንኛውም የሃይማኖት ክፍል አክብሮት ሊሰጣት ይገባዋል እንጂ ተቀናቃኝ በመሆን ሊያዳክማት አይገባውም።

በኢትዮጵያ ማንኛውም ሃይማኖት አመሠራረቱ በፍላጎት እንጂ በኃይል በማስገደድ አይደለም። በ16ኛው ምዕተ ዓመት ግራኝ ሙሐመድ ክርስቲያን አጥፍቶ እስልምናን ለማስፋፋት ያደረገው ሙከራ ከሽፎበታል። በ19ኛው ምዕተ ዓመት አጋማሽ በኋላ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት የነበሩት ዓፄ ዮሐንስ 4ኛ በአንድ አገር አንድ ሃይማኖት ብለው በመነሳት ያደረጉት ሙከራም አልተሳካም። ስለዚህ ሃይማኖት የፍላጎት እንጂ ግዴታ ስላልሆነ አንዱ ሌላውን ለመሰርጀት የሚያደርገውን ሰም ለበስ ተንኮል አስወግዶ በእኩልነትና በመከባበር አብሮ በሰላም ለመኖር መጣር ያስፈልጋል።



## የእግዚአብሔር መንፈስ፤ ጥበብና ኃይል በሰዎች ሚሠራ

(እግዚ ጌታ፡ አብ አባት፡ ሔር ቸር።)

ኢትዮጵያ በ18ኛው ምዕተ ዓመት መጨረሻዎቹ ዓመታት እስከ 19ኛው ምዕት ዓመት አጋማሽ ማዕከላዊ መንግሥቷ ተዳክሞ በመሳፍንታዊ አገዛዝ ሥር በመከፋፈሏ ኢትዮጵያን ለመውረር ሲያደቡ ለነበሩ የውጭ ወራሪ ኃይሎች ሁኔታው ስለተመቻቸላቸው በሰሜን ምዕራብ 12 ግዜ በሰሜን 4 ግዜ በሰሜን ምሥራቅ 16 ግዜ (ኤርትራ) በደቡብ ምሥራቅ 2 ግዜ በድምሩ 36 ግዜ ከዘመቱባት የውጭ አገር ወራሪዎች ጋር የመከላከል ጦርነት አድርጋለች። እነርሱም ቅኝ ግዛት በማስፋፋት ላይ የነበረች ቱርክ የቅኝ ግዛት ጥም ያንገበገባት ኢጣሊያ የቱርክ ወኪል የነበረችው ግብፅና የሱዳን ድርቡሾች ናቸው።

ኢትዮጵያዊያን ቅድሚያ ለአገር ሉዐላዊነትና ነፃነት በመስጠት እነዚያኑ ወራሪዎች በመከላከል ብዙ መስዋዕት ከፍለዋል። ይኸው ያለአሰለሰ ጦርነት የዕድገቷን ርምጃ አሰናክሎታል። በተጨማሪም ጠባብ አስተሳሰብ የነበራቸው መሳፍንት እርስ በርስ መጋጨትና የማዕከላዊው መንግሥትን መዳከም በብርቱ በብርቱ ጎድቶታል።

ኢትዮጵያን ሁልግዜ የሚጠብቃት ኃያሉ ዓምላክ ልዑል እግዚአብሔር አፄ ቴዎድሮስን ከትቢያ አንስቶ በየጎጡ የገነኑትን መሳፍንት አስወግዷል። አንዲት ኢትዮጵያ እንዲያቋቁሙ ኃይልና መላ ድፍረትና ብሩህ ሕሊና ስለሰጣቸው የጎጥ መሳፍንትን አስወግደው አንድ ወጥ አመራር መሥርተው ኢትዮጵያ በተበለጠችባቸው በሳይንስና ቴክኖሎጂ ለማራመድ የጣሉት መሠረት ከእርሳቸው በኋላ ተከታትለው ሥልጣን የያዙት (ዮሓንስና ምኒልክ) እንደ አይጥና ድመት እርስ በርሳቸው በሥልጣን ከመወዳደር አልፎ ኢትዮጵያን የሚገባትን ያህል በዘመናዊ ሥልጣኔ አላራመዷትም።

አፄ ቴዎድሮስ ጋፋት የጦር መሣሪያ ማምረቻ ባቋቋሙበት ወቅት ሀ ብለው የጀመሩ ጃፓንን የመሳሰሉ አገሮች ዛሬ በሳይንስና ቴክኖሎጂ ተአምራዊ ዕድገት አድርገዋል።

በቅርቡ በ20ኛው ምዕተ ዓመት በራሱ ገፍቶ የመጣውን ሳይንስና ቴክኖሎጂ የቀዳማዊ ሃይለ ሥላሴ መንግሥት በሚገባ ባያስተናግደውም በኤሊ ጉዞ የጀመረው ረጅም ጎዳና የሚያስኬድ ቢሆንም የሚከፋ አልነበረም። ኅብረተሰባዊነትን ለማራመድ ሙከራ ያደረገው ደርግም ከተገንጣይ ጎሰኞችና ከሶማሊያ ወራሪዎች ጋር ከሚያደርገው ጦርነት ጎን ለጎን የልማት መርሃ ግብሮችን ዘርግቶ የማይናቁ ሥራዎችን ሠርቷል።

ኢትዮጵያ በዚሁ ዘገምታ እንቅስቃሴዋ እንዳትጓዝ ኢትዮጵያዊነቱን የካደየትግራይ ተገንጣይ አድሃሪ ኋላ ቀር ቡድን ወያኔ ሥልጣን ይዞ ወደኋላ አጥብቆ እየጎተታት ነው። ኢትዮጵያ ከአንድ ጎታች ሃይል ስትላቀቅ ሌላው የባሰ እየተተካ ወደፊት እንዳትራመድ እያደረጋት ከነበራት ክብርና ገናናነት ወርዳ ስትታይ እጅግ በጣም ያሳዝናል ያስቆጫል፡ ያናድዳልም።

የትግራይ ሪፑብሊክ መንግሥት መስራቹ ወያኔ የራሱን ጎጥ ለማልማት

የዘረጋው መርሃ ግብር ከግብረ አበሩ ከሻዕቢያ ጋር ጦር አማዞት የብዙ ሰው ሕይወት በከንቱ ጠፍቷል፡፡ ነገ ደግሞ ከሙሉ ኢትዮጵያ ጋር ቅራኔ ውስጥ የሚያስገባ ነው፡፡ ወያኔ የትግራይ ህዝብ ቁርጠኛ ወገኖቹ ከኢትዮጵያዊያን ጋር አብሮ በሰላም እንዳይኖር የሚያደርገው ማራራቅ ለትግራይ ህዝብ መቅሰፍት ነው፡፡ ምንም እንኳ የወያኔ የግፍ ሂደት እስኪያልፍ የትግራይ ሪፑብሊክ መንግሥትን በእንዱስትሪ ለማበልፀግ ግንባታው የሚቀጥል ቢሆንም በሃቅ ላይ ያልተመሰረተ (በአጭበርባሪነት) በመሆኑ ለአደጋ የተጋለጠ ነው፡፡

## ህሊናዊ ንቃት

«መንፈስ የእግዚአብሄርን ጥልቅ (ረቂቅ) ነገሮችን እንኳ ሳይቀር ይመረምራልና ለእኛ እግዚአብሄር በመንፈሱ በኩል ገለፀው»(፩ ቆሮ.፪-፲) የሚለውን የሃዋሪያው ጳውሎስ መልዕክት መሠረት በማድረግ አንድ የክርስቲያን ድርጅት በመጽሄቱ "በእጅ የማይዳሰሱበዓይን የማይታዩ የእግዚአብሄር ክስተቶች" በሚል አርዕስት «ምንም ዓይነት የቴክኖሎጂ ማስረጃ ባልነበረበት ዘመን ሐዋሪያት በእጅ የማይዳሰሱ በዓይን የማይታዩ የእግዚአብሄር ፍጥረቶች መኖራቸውን አስተምረዋል፡፡ ዛሬ ቴክኖሎጂ እነኚህን የአምላክ ሚስጢራዊ ሥራዎች በትንሹ እንድናውቅ ቢያደርግም የሰው ልጅ ብዙ የረቀቁ ምሥጢሮችን ሊደርስባቸው አልቻለም፡፡» ጉዳዩ ውቅያኖስን በጭልፋ ማለት ነውና፡፡

መጽሄቱ ከዚህ ቀጥሎ አንዳንድ ለምሳሌ የሚሆኑ ከፊታችን የምናያቸው ነገሮች እንዴት እንደተሰሩ ይገልጽልናል፡፡ «ውሃ የሚዳሰስም የሚዘገንም ነው፡፡ ነገር ግን ውሃ የተሰራው ከሁለት በዓይን በማይታዩ ከማይጨበጡ የአየር ንጥረ ነገሮች ነው፡፡ ይኸውም ሁለትእጁ ሃይድሮጂን አንድእጁ ደግሞ ለእስትንፋስ ከምንወስደው ኦክስጂን ከተባለው አየር ንጥረ ነገር ነው፡፡ ኦክስጂን የሚባለው አየር የሚገኘው ዕፅዋት ከሚተነፍሱት (ከሚተነው) አየር ሲሆን ሰው የሚተነፍሰው አየር ደግሞ ዕፅዋትን መልሶ ይመግባል፡፡ ዕፅዋት ያለእንሰሳ እንሰሳም ያለ ዕፅዋት መኖር አይችሉም፡፡ ሰው ዕፅዋትን ካጠፋ እራሱን እንዳጠፋ ይቆጠራል፡፡ ይህም የሚያስረዳው አንድ ነገር ብቻውን መኖር እንደማይችል ነው፡፡ የአንዱ መኖር ለሌላው ለህላዌነቱ ዋስትና በመሆኑ ነው፡፡

የነቃ የሰው ልጅ አእምሮው በእግዚአብሄር መንፈስ የተሞላው ፈላስፋ (ሳይንቲስት) የፈጣሪን ምስጢራዊ ሥራዎች በመመርመር የሰው ልጅ ድካም የሚቃለልበትን አጋዥ መሣሪያዎች ፈልስፎ ሰማየ ሰማያትን የሚዳስሰው በትንሿ ምድር ላይ በድንቁርና ጭለማ ውስጥ ተውጦ በመደናበር ላይ ያለውን የሰው ልጅ ነትጉቶ በማንቃት የእርስ በርስ መጠፋፋትን አስወግዶ የእግዚ - አብ - ሄርን ድንቅ ሥራዎች እንዲያከብርና በሥርዓት ተስማምቶ እንዲኖር ነው፡፡

«ሰው የእግዚአብሄር ቤተ መቅደስ እንደሆነ የእግዚ - አብ - ሄር መንፈስ እንዳለበት አታውቅምን?» ብሎ ቅዱስ ጳውሎስ የመሰከረለትን ሰብአዊ ፍጡር ከመቅጽበት ለሚያልፍ ሥልጣን ፍትህንና ርዕትን በሳጥን



ውስጥ አሽጎ ሰብዓዊ መብትን ረግጦ ማስቃዬትና ማስጨነቅ ንብረት ዘርፎ በረሃብ አለንጋ መግረፍ ሃይማኖታዊና መንፈሳዊ ፀጋን መግፈፍ ከድንቁርና ያለፈ እብደት ነው፡፡ በግል ለመበልጸግ የሚደረገው ማጭበርበርም ግዜ ጠብቆ በሚፈነዳ ቦምብ ላይ መቀመጥ ነው፡፡

የህይወታችን ዋስትና የሆነው ውሃ አብዛኛውን የሰውነታችንን ክብደት የያዘው በአብዛኛው ምድርን ከየብስ ይልቅ አብዛኛውን የመሬት ወለል (የሸፈነው) የሞላው ውሃ ሦስት ዓይነት ባህሪያት ያለው መሆኑን ስንመለከት አያስደንቅም? ውሃ ሲሞቅ አየር ሆኖ ይተናል፡ ሲቀዘቅዝ ደግሞ (እንደ ድንጋይ ይጋገራል) ዓለት ይሆናል ተመጣጣኝ ሙቀት ሲያገኝ ደግሞ ፈሳሽ ይሆናል፡፡ የእኛስ ህይወት ተመሳሳይ ባህሪይ ይኖረው ይሆን?፡፡

የነቁ ምሁራን በሰማይ ሆነ በምድር ተመራምረው የደረሱበት ተአምር ሁሉ በአጋጣሚ የተሰበሰበ ሳይሆን እጅግ ረቂቅ በሆነ ህግና ሥርዓት የተዋቀረ መሆኑን በማስረጃ በተደገፈ ጥናት በየዘመኑ ያለማቋረጥ አስረድተዋል፡፡ ይሁን እንጂ የሰው ልጅ ከጥፋት የሚድንበት ቢነገረውም ህሊናዊ ንቃቱን ባለማዳበሩ ከመመራመርና ከማስተዋል ጉድለት የተነሳ እርስ በርሱ ከመበላላትና ከመጠፋፋት የቦዘነበት ግዜአት የለም፡፡

ሰው አንድ ግዜ ሰውነቱ ሲግል ሁኔታዎችን ሳያመዛዝን በስሜት እየተገፋ በአረመኔአዊነት ከቁጥር የበዙ ስህተቶችንና በደሎችን በጭካኔ ባልሰከነ ህሊና ይፈጽማል፡፡ ሰውነቱ ሲቀዘቅዝ ደግሞ ከማናቸውም ህግ ወጥ ድርጊቶች እርቆ ፍትሀዊነትና ሰብዓዊነት በሞላበት ርህራሄና ደግነት በመልካም ርምጃ ይንቀሳቀሳል፡፡ እንደዚህ ያለውን የተመሰቃቀለ ባህሪያት (ለማስወገድ) ለማስተካከል በንቃታቸው ላይ ያልተኙ የነቁ የህብረተሰብ ክፍሎች ታላቅ ተጋድሎ አድርገዋል፡፡ እያደረጉም ነው፡፡

«ለምኑ ይሰጣችኋል፤ ፈልጉ ታገኙማላችሁ፤ መዝጊያ አንኳኩ ይከፈትላችኋል» (ሜቴ. 7:7) በተባለው መሠረት ጥበብን ለፈለጉ ሁሉ ሰጥቷቸዋል፡፡ ጥል ክርክርና መጋደልን ለፈለጉም የሚጠፋበትን ጥበብ አልነፈጋቸውም፡፡

የሰው ልጅ ሥልጣኔን የማናውቃቸውን የእግዚአብሄር ረቂቅ ሥራዎች በትንሹም ቢሆን እንዲገለጽ አድርጎታል፡፡ በአሁኑ ግዜ የእጣት ጥፍር የምታህለውን መሬት አንድ ትልቅ አገር አድርጎ አጉልቶ የሚያሳይ መሣሪያ ተፈልስፏል፡፡ ዛሬ የተከሰተው ቴክኖሎጂ አንዲቷን ፀጉር የማን እንደ ሆነች መቶ በመቶ ለይቶ ያረጋግጣል፡፡ ወደፊት ካሁኑ ዘመን የተሻለ መሣሪያ ሢሰራ ደግሞ በጣም ረቂቅ የሆኑትን ያልታዩትንና የማይታወቁትን እንዲገለጹ ያደርጋቸዋል፡፡

ከሠማየ ሠማያት በላይ ብዙ ሰማዮች መኖራቸው የተገለጸለትና የተነገ ይሆን? ከአራት መቶ ዓመት በፊት የኖሩ አዋቂዎችና ፈላስፎች አቅርቦ የሚያሳየውን መነጽር (ቴሌስኮፕ) ሠርተው ወደ ሠማይ ሲመለከቱ ለቁጥር አዳጋች የሆኑ ከዋክብት መኖራቸውን ገልጸው ነበር፡፡

«ዓይን ያላያቸው ጆሮም ያልሰማው በሰው ልብ ያልታሰበ እግዚአብሄር ለሚወዱት ያዘጋጀው» (፩ ቆሮ. 2:9) ሲል ሃዋሪያው ጳውሎስ በመልዕክቱ እንደ ገለጸው በዚህ በያዝነው ክፍለ ዘመን ደግሞ ከዱሮው የተሻለ ዘመናዊ

የሆነ አቅርቦ የሚያሳይ መነፅር ተሠራ። ይህንኑ አዲስ የተሰራ ግዙፍ መነጽር ወደ ህዋው በመንኮራኩር አምጥቀው የበለጠ ሠማየ ሠማያትን በመዳሰስ ሰዎች ከምድር መነጽሩ ከሰማይ ሁኖ በኮምፒዩተር አጋዥነት ሌላ ተዓምር መመልከት ቻሉ። ይኸውና እኛ ካለንበት ሠማይ (ጋላክሲ) ሌላ በሠማይ ላይ ሠማይ የተደራረቡ እያንዳንዳቸው 10 ቢሊዮን ኮኮቦች የያዙ 10 ቢሊዮን ሠማዮች (ጋላክሲዎች) መኖራቸው ተገለጸ። በጣም ተራርቀው በሠማይ ላይ ሠማይ እየተደራረቡ ያሉትን ሠማዮች (ጋላስኪዎች)ብዛትና የከዋክብት ብዛት ቆጥሮ ለመድረስ በአንድ ቢሊዮን ዳውላ ውስጥ ያለ ጤፍን ብዛት ቆጥሮ የመጨረስ ያህል ነው። መጀመሪያና መጨረሻም የለውም።

እንግዲህ አውሮጳውያን ፈላስፎች ለሰው ልጅ አገልግሎት የሚውል አጉልቶ የሚያሳይ መነጽር ሰርተው ባካሄዱት ስሌት ከምድር ከርስ ምርመራ አልፈው ሠማያት በመመርመር ወደ ጨረቃና ማርስ መንኮራኮሮችን እያመጠቁ ተዓምር እያደረጉ ነው። ለእኛ ለኢትዮጵያዊያንስ ጥፋታችንን አጉልቶ የሚያሳይ መነጽር ማን ይሥራልን? እኛ ኢትዮጵያዊያን ግን ህሊናዊ መነጽር ለመሥራት የጎሣው ትርምስ ግዜ አልሰጠን ብሎ ይሆን? ኢትዮጵያዊያን በነፃነት ካሳለፏቸው 5 ሺህ ዓመታት ውስጥ ሁለት ሺህ ተቀንሶ ሦስት ሺህ የነፃነት ዘመን እንኳ ቢታሰብ ከኋላ በተነሱ ፈረንጆች በእጅጉ እንቀዳደም ነበር። በዚህ ባለንበት ዘመን በየቀኑ የምናዩው አዳዲስ ፍልስፍና ጥበብ እጅግ የሚያስደስትና የሚያስቀና ነው።

ዓለም ባልነቃበትና ባልሠለጠነበት በጨለማው ዘምን የነበሩ ቀደምት ኢትዮጵያዊያን አበው በዘመኑ በነበረው በሳይንስና ቴክኖሎጂ ተራምደው አሁን የምንገለገልባቸውን በመሥራት የተጓዙት ከእግዚአብሄር ጋር በነበራቸው የቅርብ ግንኙነት ብሩህ ህሊና አስተዋይ አእምሮ በማይመረመር ጥልቅ ምስጢሩ ስለሰጣቸው እርሱን ጋሻ በማድረግ ያለምንም ፍርሃትና ሥጋት በድፍረትና ቆራጥነት እየተንቀሳቀሱ እምነታቸውንና ነፃነታቸውን አስከብረው በክብር ኖሩ። በእግዚአብሄር ሙሉ እምነት ያለው አይሰናከልምና።

ቅዱስ ጳውሎስ ወደ ጢሞቴዎስ ሰዎች በላከው መልዕክቱ (ጢሞ. 4:1) «በኋለኛው ዘመናት አንዳንዶች የሚስቱ መናፍስንትንና በውሸተኞች ግብዝነት የተሰጠውን የአጋንትን ትምህርት እያዳመጡ ሃይማኖትን ይክዳሉ» እንዳለው የቅርብ ግዜ ትውልድ በተለይ ከ20ኛው ምዕተ ዓመት አጋማሽ ወዲህ ካለው ትውልድ ውስጥ በአመዛኙ የቁሳቁስ ተገዥ በመሆኑና ከእግዚ-አብ-ሄር አምልኮ በመንሸራተቱ ፍቅርና አንድነት አጥቶ በመንደርና ጎጥ በመከፋፈሉ ዓይኑ በዳፍንት የተጋረደው በጎሰኝነትና በዘረኝነት እርስ በርሱ የሚተራመሰው የጥላቻ ዘር የሚዘራው የግል ፍላጎቱን ለማርካት የሚስገበገበው ግብዝ የእርግማን ናዳ በላዩ ላይ ወርዶበታል።

«ጠማማ ይቀና ዘንድ ጎዶሎም ይቆጠር ዘንድ አይችልም» እንደተባለው እርስ በርሱ በሚያደርገው ሽኩቻ ከባህር ውስጥ ተለቅሞ እንደሚበላው ክራብ (ቀንድ አውጣ መሳይ) ማለት ነው። ክራብ ለሚበሉት ጣፋጭ ነው። ምግብ ቤቶችም በውድ ዋጋ ይሸጡታል። ይህንኑ ክራብ



ሰብስቦ በቅርጫት ውስጥ አስቀምጦ ቢመለከቱት አንዱም ክራብ ከቅርጫቱ ለመውጣት አይችልም። ጠባቂም አያስፈልገውም። አንዱ ክራብ ከቅርጫቱ ለመውጣት ሲታገል ሌላው ጎትቶ ያስቀረዋል። እንደዚያ ያሉ ሁሉም ከዚያው ከቅርጫቱ ውስጥ ተርመስምሰው ለበላተኛ ይሰጣሉ። እንደዚሁም በጎጥ የሚተራመሱ ጎጠኛ ድርጅቶች ይህን አይመስሉም ብሎ የሚከራከር ሰው ይኖር ይሆን? አንዱን አንዱ እየጎተተ (ሰርጅቶ) በዚያው ተተራምሶ ይቀራል።

ኋላ ቀር ጎጠኞች በፈጠሩት የማጣላትና የማራራቅ ቀውስ ምክንያትም ተቃዋሚ ህብረ-ብሄር ድርጅቶች ተባብረው እንዳይታገሉ ከዓለም አቀፍ ኢምፔሪያሊስት ሃይሎች ጋር በመተባበር ጎጠኞች ልዩ ልዩ ተፅዕኖ አስደርገውባቸዋል። ህግ በሞተበት አገር ማንኛውም እንደ አዘበዘበ ግድግዳ ነው።

በአገር ውስጥ የከፍተኛ ትምህርት ዕድሉ በጣም የጠበበ በመሆኑ ተምሮም ሥራ በማግኘት በማዳገቱ ወደ ሰው አገር የተሰደደው ኢትዮጵያዊ እጅግ ብዙ ነው። ከዚሁ የጎሳ ትርምስ እያመለጠ ወደ ውጭ አገር የተሰደደው ውስጥ በጣም አነስተኛው በሰሜን አሜሪካና በአውሮፓ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ውስጥ ተምሮ ባገኘው ዕውቀት አገሩ ገብቶ ወገኖቹን እንዳያስተምር ጎሰኞች የዴሞክራሲን በር ዘግተው ስለ ያዙ ዕውቀታቸውን ለዚያው ለተማሩበት አገር አውለውታል።

በጣም የሚያሳዝነው የአገራቸውን ታሪክና ባህል በሚገባ ሳያውቁ ከተሰደዱት ታዳጊ ወጣቶች ተሰድደው ያሉበት አገር ወጣት ዜጎች በየኮሌጁ ገብተው ዕውቀት ለመሸመት ሲተራመሱ ኢትዮጵያዊያን ወጣቶች ግን አብዛኛውን ግዜአቸውን የሚያሳልፉት በየግዜው ቁጥሩ እየጨመረ በሚሄደው በመጠጥ ቤትና በጭፈራ ነው።

ኢትዮጵያዊያንን ለቀሳፊ ስደት የዳረጋቸው የጎሣ መመሪያ ተሰደውም ጥገኝነት በሚኖሩበት አገርም ተከትሎ ሂዶ እርስ በርስ እያተራመሳቸው በማጋጨት ላይ ነው። መስማማትና መፈቃቀር ጨርሶ ጠፍቷል። ይኸው የጎሣ በሽታ ከጎሣ አልፎ ወደ መንደርና ዞግ እየተሻገረ በመሄዱ የተማረውም ያልተማረውም ሃይማኖተኛውም ፖለቲከኛውም የቅራኔ ሰለባ ሆኗል። ሁሉንም ከማን አንሼ በሽታ ይዞት ጤናማ ሰው ማግኜት አልተቻለም።

ስለዚህ ነው ሰው ጠፍቶ እየተፈለገ «ጌታ ሆይ እባክህ ሰው ፍጠር አህያማ በቤትህ ሞልቷል» የተባለው። ማንኛውም ሃይማኖተኛ ለዕምነቱ የሚሰዋ?ከሞት ይልቅ ትዕዛዝን የፈራ ማን አለ ጀግና? ከግፈኞች አትተባበር። የሚል ትዕዛዝ አለና።

ይህ ትውልድ ፀጋው ስለተገፈፈ የነፍስ ገዳዮችንና የከሃዲ ወንበዴዎችን ጭካኔና ዝርፊያ ማስተዋል ተስኖታል። «ክፉ የሚያደርግ ሁሉ ብርሃንን ይጠላል ሥራውም እንዳይገለጽ ወደ ብርሃን አይወጣም» (ዮሃ.3:20) ተብሎ እንደተነገረው። በዚህ ሳይንሳዊ ቴክኖሎጂያዊ ዘመን ለራሱ የሚጠቅመውን እውነተኛ ህይወት የሚገኝበትን ጎዳና ከመከተል ይልቅ ምንነታቸውን ለካዱ በራሳቸው ታሪክ ላይ ለአመጹ ጎጠኞች አንገቱን ደፍቶ መግዛቱ ወንጀለኛ አድርጎ ያስፈርጀዋል።

-ንቃት አርነት፤ ንቃት ነፃነት ነው።
-ንቃት ሃብት፤ንቃት ጤንነት፤ንቃት ድፍረት ነው።
-ንቃት ስነ ጥበባት፤ ንቃት ጉልበት።
-ንቃት አእምሮአዊ መብራት ነው።
-ንቃት እምነት ነው።
-ንቃት አትንኩኝ ባይነት ነው።
-ንቃት አንድነትና ሉአላዊነት ነው።

ሳይንስና ሃይማኖት ጠቀሶች በባለሙያዎች ተዘጋጅተ
ው ራሳቸውን ችለው ትምህርታዊ በሆነ ዘዴ ተቀነባብረው
መገለጽ የሚገባቸው ናቸው። ይሁን እንጂ በዚህ ላይ እንደ
አብነት አድርጌ ለማንሳት የተገደድኩበት ዋነኛ ምክንያት የሰ
ለጠነው ዓለም ሕዝብ ያለበት ምድር (ፕላኔት) ጠቦት ሌላ
የማይታይና ያልታወቀ ዓለም ለመፈለግ አየራትን ሰንጥቆ በ
መጓዝ ሰማዩ ሰማያትን እየዳሰሰ በማጥናት ላይ በሚገኝበት
በዚህ አወንታዊ (ሳይንሳዊ) ዘመን ኢትዮጵያዊያን የኋሊት
በመጓዝ በጎሳና ቋንቋ፣ በሃይማኖትና በወገን እየተከፋፈሉ በ
ቅራኔ ማዕበል ውስጥ መስጠማቸው እጅግ አሳዛኝ፣ አስደንጋ
ጭና አሳፋሪም ነው።

የአንድ አገር ሕዝብ የታላቅነቱ ማስረጃና የማንነቱ መ
ለኪያ ባሕሉንና እምነቱን፣ ታሪኩንና ሰብዓዊ ክብሩን ብሎ
ም አገራዊ ሉዓላዊነቱን አጠንክሮ ይዞ ሲገኝ ነው። ኢትዮጵ
ያ በአሁኑ ግዜ በባዕዳን የተለያዩ እምነትና ባሕል እየተበዘበዘ
ችና እየጨቀየች ናት። ከድሮ ዘመን ጀምሮ የሚጠናወቷት
ዓረቦችና ፈረንጆች ተገንጣይ ጎሰኞች ሁኔታውን አመቻችተ
ውላቸው ከውስጧ ገብተው በተለያዩ ስልትና ዘዴ እያፈረሷ
ት ነው።

በድሮ ዘመን የሚዘምቱባት በተራቀቀ ዘዴ ሳይሆን ፊት
ለፊት በሚታይ ኃይልን በአዘለ እንቅስቃሴ ነበር። በአሁኑ ግዜ
ግን እጅግ በረቀቀ ዘዴ አንዳንድ የማምረቻ ድርጅቶችን ለሽ
ፋን እያቋቋሙ ወጣት ስፖርተኞችንና የኪነት ባለሙያዎችን
ከኢትዮጵያ ወደ አሜሪካ፣ ከአሜሪካ ወደ ኢትዮጵያ በቻርተ
ር አውሮፕላን በማጓጓዝ፣ እየደገሱ በማጋባትና በመናኛ ስጦ
ታ በማታለል እንደሠራቂያን በሰመመን ስበው በመውሰድ ጠ
ልቀው እየገቡ ነው።

እንደዚህ ያለውን የባሕልና የእምነት ሰለባ ለማስወገድ
ኢትዮጵያዊ ነኝ፣ አገሬን እወዳለሁ፣ በታሪኬ እኮራለሁ የሚ
ል ንቃተ ሕሊናውን በማዳበር፤ እስከ ዛሬ በግልጽ እንደታዩ
ው ይህን አድርግ፣ ይህን ሥራ፣ ይህን ተከተል እየተባለ እ
ንደ ዓይነ ስውር እየተመራ በጉትጎታ መሥራትን አስወግዶ
ሁሉም በየአለበት በራሱ ፈቃድና ኃላፊነት እየተንቀሳቀሰ የባ



ዕዳንን ተንኮል መቋቋም ይገባዋል።

በዚህ ሳይንሳዊ እውነት በተገለጸበት ዘመን ያለ ትውል
ድ መሠረቱን ሳይለቅ ብዙ እንዲመራመርና እንዲያጠና ወቅ
ቱ ያስገድደዋል። ከዘመኑ አስተሳሰብ ጋር አብሮ ለመራመድ
እንደ እንስሳ በመላሸ በመሳብ፣ በሰብከት በመታለል፣ እምነ
ትንና ባሕልን በመለወጥ አይደለም። መጽሓፍ ቅዱስ እንደሚ
ለው 'የከበረች አገርህን ከሚወርሱ ሰዎች ጋር ተካፋይ ትሆ
ን ዘንድ አይገባህም' (መቃ ፳፮፥ ፲፫) የራስን ኢትዮጵያዊ ባ
ሕልናእምነት፣ ነፃነትና የማንነት መታወቂያን አጠንክሮ በመ
ያዝ ነው ሁለመናው ሊሳካ የሚችለው እንጂ ለባዕዳን መሣሪ
ያ በመሆን አይደለም።

የባዕዳንን ወረራ አስመልክቶ የብጹዕ አቡነ መልከ ጼዴ
ቅን (አባ ሃብተ ማርያም) የብጽዓት ሥራ ለምሳሌ ያህል እ
ጠቅሳለሁ። የውጭ አገር ባዕዳዊያን ለብዝበዛ እንዲያመቻቸው
ና የራሳቸውን ባሕልና እምነት በአገሪቱ ውስጥ በማስፋፋት፤
ኢትዮጵያዊነትንና አገር ወዳድነትን ከሥሩ ነቅሎ ለመጣል አ
ስቀድሞ ለኢትዮጵያውያን ለሁለመናቸው መሠረት የሆኑትን
ሃይማኖትና ባሕልን ስልታዊ በሆነ ዘዴ ለማዳከም የጀመሩትን
ተንኮል ብጹዕ አቡነ መልከ ጼዴቅ በሚገባ ተረድተው ኢትዮ
ጵያዊ ሁሉ የማንነት መታወቂያዎቹን ባሕሉንና ሃይማኖቱን፣
ነፃነቱንና ሰብዓዊ ክብሩን ነቅቶ እንዲጠብቅ ትምህርት ቤቶች
ከፍተው ለማስተማር ከፍተኛ ጥረት በማድረጋቸው የሚደነቁ
ናቸው። ይሁን እንጂ ኋላ ቀር አስተሳሰብ ያላቸው (ቀኖና
ዊያን)፣ አርቆ ማዬት የተሳናቸው፣ በአገራቸው ላይ የተነፃ
ፀረውን አደጋ ማስተዋል ያቃታቸው፣ ንቃታቸው ከብጹዕ አ
ቡነ መልከ ጼዴቅ የብጽዓት ሥራ ጋር አብሮ መሔድ ያል
ቻሉት የግል ጥቅም አሳዳጆችና ምቀኞች የዕለቱን እንጂ የነ
ገውን የማያስተውሉ በብጹዕ አቡነ መልከ ጼዴቅ ርምጃ ላይ
እንቅፋት በመሆን ብዙ ጉዳት አድርሰዋል።

ምንም እንኳ ዕውነት የያዘ በአቸናፊነት የሚዘልቅ ቢ
ሆንም ለግዜው ግን እርስ በርሳቸው እየተመቀኛኙ አንዱ ሌላ
ውን ለመሠርጀት በመደባባት ሳያውቁት ለጠላት ሁኔታዎችን
እያመቻቹ በመስጠት አገራቸውን ለብርቱ አደጋ አጋልጠዋ
ል። እነዚህኑ ውስጣቸውን ገልበው ለጠላት የሚያሳዩትን ሕሊ
ና ቢስ ደካሞች አገር ወዳድ የሆነ ለባሕሉና እምነቱ ተቆርቋ
ሪ ሁሉ በየአለበት ነቅቶ ሊቋቋማቸው ይገባል። በአገር ጉዳይ
ወዳጅ ዘመድ ተብሎ ጥፋት ሊታለፍ አይገባምና። ቤት ሲ
ቃጠል ቅጠል ይዞ የማያጠፋ ማን አለ?

# ክፍል አራት
# የደርግ መንግሥትና ተቃዋሚዎቹ

## ምዕራፍ 17
## ደርግና አብዮቱ

ውንዳኑ ብዙኃኑን እያስቸገሩ እያሰቃዩ እየጨቆኑ የሚዘርፉና የሚቀጡት እንደ በግ የሚያጉሩት ከምን አንፃር ነው? የሚያስደንቀው ነቃ የተባለውም ሥልጡኑም ያልሰለጠነውም የተማረውም ያልተማረውም ሕዝብ በጣት የሚቆጠሩ ዴሞክራሲያዊ መብቱን እየነጠቁ ምፅዓት ሲያወርዱበት ሁሉም በአንድ ዓይነት በድንቁርና የሲኦል ጎዳና መትመሙ ነው።

በግልጽ የጤናቸው ሁኔታ ተመርምሮ የማይታወቁ የአእምሮ ቀውስ ያለባቸው ሰዎች በግዜው ሁኔታ ተጠቅመው በማታለል ወይም በማጭበርበር የመንግሥት ሥልጣን ሲይዙ የሕዝብን ሰብዓዊ መብት ማስከበር ሰላምና ደኅንነት መጠበቅ አመፅና ግፍን አስወግዶ ፍትሐዊ አስተዳደርን መዘርጋት ልማትን ማስፋፋት በሳይንስና ቴክኖሎጅ አገርን ለመገንባት ከመጣር ይልቅ ራሳቸውን ጣዖት አድርገው ለእነርሱ ያልስገደውንና ለእርኩስ ሥራቸው ተንበርክኮ ለጥ ሰጥ ብሎ ያልተገዛን በቆራጭ ፈላጭነት ያለ ፍትሕ አስረው ያሰቃያሉ፤ ይገድላሉ፤ ንብረቱን ይዘርፋሉ።

እንደ በግ መንጋ እንጂ እንደ እነርሱ እኩል አፈጣጠርና መብት ያለው መሆኑን ክደው ከመንጋ ውስጥ እየተመረጠ እንደሚታረድ በግ በጭካኔ ያርዱታል ያሰቃዩታልም። ስለ ሕገ ወጥ መሪዎች ጌታ እግዚእብሔር እንዲህ ይላል "እኔ ሕያው ነኝና እረኛ ስለሌላቸው እረኞችም በጎቼን ስለአልፈለጉ እረኞችም ራሳቸውን እንጂ በጎቼን ስለአልፈለጉ በጎቼ ንጥቂያ ሆነዋልና በጎቼም ለምድር አራዊት ሁሉ መብል ሁነዋልና እንሆ በእረኞች ላይ ነኝ በጎቼንም ከእጃቸው እፈልጋለሁ በጎቼንም ከማሰማራት አስተዋቸዋለሁ። ከዚያ ውዲያ እረኞች እራሳቸውን አያሰማሩም በጎቼንም ከአፋቸው አድናለሁ መብልም አይሆኑላቸውም" ይላል።(ሕዝ. 34 - 8፣-10)

እንዲሁም በትንቢተ ሕዝቅኤል "የደከመውን አላዳናትችሁም የታመመውንም አላከማችሁትም የተሰበረውንም አልጠገናችሁትም የባዘነውንም አልመለሳችሁትም የጠፋውንም አልፈለጋችሁትም በኃይልና በጭቆናም ገዛችኋቸው" (ሕዝ.34 - 4) እንዳለው ትንቢቱ በትክክል በሥራ ላይ ውሎ ታይቷል። ሕዝብን በማሰቃየት አሳድደውታል። በረኃብ ሲረግፍ አልረዱትም። በጦርነት እሳት ማግደውታል። ሰላማዊ ኑሮውን አደፍርሰውበታል። ከእምነቱ አፋልሰውታል። ደክሞ ያፈራውን ጥሪቱን ነጥቀውታል። ማሕበራዊ ኑሮውን አዛብተውበታል። ምን ያላደረጉት ነገር አለ?

አምላካዊ ትዕዛዝና ሞራል ያላገዳቸው እምነተ ቢስ ትዕቢተኞች በክፋትና ተንኮል ተወጥረው በድንቁርና ኃይል እየተንቀሳቀሱ እጅግ አሰቃቂ ተግባሮችን "ልብን ሁሉ የሚያቀልጥ እጆቹን ሁሉ የሚያደክም



ነፍስን ሁሉ የሚያዝል ጉልበትን ሁሉ እንደ ውኃ የሚያፈስ ኃያሉ አምላካችን እግዚአብሔር ከመሠረታቸው ከፍሏቸዋል ስማቸው የከፋ ታሪካቸው የከረፋ አድርጎ በዓለም ላይ ቅታቸውን አጥፍቶታል።

እነ ሂትለር ሙሶሎኒ ስታሊን ፓል ፖት ሕዝብ አሰቃይተውና ጨፍጭፈው የመሠረቱት ሥርዓተ መንግስት ጸንቶ ኖረ ወይ? ምን አተረፈ? አጥፍተው እንደ ጠፉት እንደዚሁም በመንግሥቱ ኃይለ ማርያም የተመራው ደርግ ታይቶና ተሰምቶ በማይታወቅ በአረመኔአዊ ጭካኔ ወገኖቹን ጨፍጭፎ መሠረትኩ ያለው ርዕየተ ዓለም አንድ ርምጃ ሳይሔድ ለምን ወድቀ? በቀይ ሽብር በመደዳ ጭፍጨፋ ገድሎ የሸጠው ሬሣ ለምን የብረት ዓምድ ሁኖ መንግሥቱን አላጸናም? የቀማው ርስትስ ለምን ተፋው? የዘረፈው ንብረትስ መሰላል ሆኖ ለምን አላዛለቀውም ኧረየት ደረሰ? እንደ በግ እየነዳ ያረደው የደም ጎርፍ ጠራርጎ ወሰደው ወይስ በነ ማርክስ ቴዎሪ የረገጠው ሃይማኖት እንጥሮጦስ አወረደው? ልጇን ገድሎ እስክስታ እንድትወርድ የተደረገች እናት እንባ የእንጥርጦስ ጎዳናን ጠርጎለት ይሆን? ወይንስ ጉልቁ መሳፍርት የሌለው የውጣቶች ደም ሁሉንም ገለባብጦ ጣለውን? ወይስ የዘር ማጥፊያ ዘመቻው ተፃርሮ ገፈተረው።

ይህ ሁሉ ሊሆን የቻለው እያንዳንዱ መብቱን ለማስከበር ተደራጅቶ ባለ መንቀሳቀሱ ነው። የነቃና የተደራጀ ቢሆን ኑሮ ደርግ ልጁን ገድሎ ከበራፉ አይዘርርም፤ ቤትና እርስቱን አይቀማም፤ ሰብአዊ ክብሩን አይረገጥም፤ ባሕሉና እምነቱን አይፌዝበትም ነበር። ደርግ ይህን የግፍ ሥራ በሚሰራበት ግዚያት ብዛቱ 120 ነበር የኢትዮጵያ ሕዝብ ግን በዚያን ጊዜያት 48 ሚሊዮን ሕዝብ ያህል ንበር። በዚህ ስሌት አንድ የደርግ አባል 400 መቶ ሺህ ሰዎች ይነዳ ነበር ማለት ነው። 400 ሺህ ሰዎች ቀርቶ አስር ሰዎች ቢተባበሩ ኑሮ ፍጅቱን አስቁመው መብታቸውን ማስከበር በቻሉ ነበር።

ለምን ሕብረተ ሰቡ ተደራጅቶ መብቱን አላስከበረም የሚል ጥያቄ ዘወትር ይነሳል። ነቅቶ በመደራጀት መብትን የማስከበር ጉዳይ እስከ ዛሬ ድረስ መፍትሔ ያላገኘ ብዙ ድካምና ጥረት የሚጠይቅ ነው። በዓዬው አገዛዝ ክብረ ነክ ዘለፋ እየተባለ አፉ ተለጉሞ ንቃተ ሕሊናው ደንዝዞ የኖረ ሕዝብ እንደ በግ እየተነዳ ቢታረድ አይፈርድበትም። በሺህ በግ መካከል አንድ ተኩላ ሲገባበት በርግጎ ይበታተናል እንጂ ተባብሮ ለመከላከል እንደማይችል፤ እንዲሁም ሰብዓዊ ፍጡር እንዳይደራጅ ከተከለከለ የሃሳብ ነፃነቱ ከተነፈገው አፉ እንዳይናገር ከተልጎመ ሰብአዊ ተኩላዎች ሲገቡበት ራሱን ለማዳን ከመፈርጠጥ ወይንም ዝም ብሎ ከመበላት በስተቀር በኃይሉ አይጠቀምበትም፤ ሌላም አማራጭ ፈልጎ ለመቋቋም አይታየውም። ከማኅበረ ሰቡ ውስጥ አንዳንድ የነቁ ግለሰቦች ቢኖሩም ድጋፍ ሲያጡ ሰልችተው ሲተውት ብዙዎች ለዕምነታቸው የተገዙት ብቻ ጸንተው ቂመዋል።

ደርግ በኮንጎ ዘማች አበል ምክንያት የተፈጠረ እንጂ የፖለቲካ ራዕይም አልነበረውም። የርዕዮተ ዓለም እምነት ወይም የሕዝብ ብሶት

አልፈጠረውም። በውሽልሺል ለሥልጣን ያበቃው ሂደቱን የጨረሰ የዓፄ ኃይለ ሥላሴ መንግሥት ነው። ደርግ የኮምዩንስትን ርዕዮተ ዓለም የተቀበለው በግፊት እንጂ እምነቱ አልነበረም።

አብዮቱን ማንቀሳቀስ የሚችለው የሠራተኛው ኃይል ሳይደራጅና አብዮቱን ተሸካሚ የነቃና የተደራጀ በባለቤትነት የራሴ ነው ብሎ የሚይዝ ኃይል ሳይኖር ማርኪሲዝምንና ሌኒንዝምን በአዋጅ ተግባራዊ ለማድረግ መሞከር ከፍልስፍናው ድኀነት ብቻ ሳይሆን ከድንቁርና ጭምር መሆኑን ያስረዳል። ደርግ ራሱን  በርዕሰ ብሔርነት ሰይሞ እራሱ የማያውቀውንና ለሥርዓቱ ተገዥ ሳይሆን በሕዝብ ላይ የጫነውን ርዕየተ ዓለም ሕዝብ መሸከም ቢያቅተው በግድ እንዲሸከም በመደረጉ መሸከም አቅቶት አውርዶ ጣለው እንጂ ተሸክሞ መጓዝ አልቻለም። ማኅበራዊና ሕሊናዊ ሁኔታዎችን ያላካተተ የሕግና ፍትሕ መድረኮችን የዘጋ ከዴሞክራሲያዊ አስተዳደር ጋር ያልተያያዘ በፖለቲካ ሥርዓት ሳይሆን በፍላጎት ንረት የተመራ አብዮት በመሆኑ በግንባሩ ተደፋ፤ እንደ ጉድፍ ተጣለ።

ደርግ ገና አንድ ርምጃ ወደፊት ሳይራመድ ይዣለሁ ይለው የነበረው የርዕሰ ብሔር ሥልጣን አስከሮት የዱሮ ባለሥልጣናትን እየሰበሰበ በሚያስርበት ግዜያት የዓፄ ኃይለ ሥላሴን መንግስት ልትገለብጥ አሲረሃል ተብሎ 5 ዓመት በዓለም በቃኝ ወህኒ ቤት የታሰረውን ኮሎኔል እምሩ ወንዴንም አስሮት ነበር። እሱን ለማስፈታት ወደ ደርግ ጽ/ቤት እመላለስ በነበርኩበት ወቅት በምክትል ርዕሰ ብሔርነት ተሰይሞ የነበረውን የሻለቃ ምንግሥቱ ኃይለ ማርያምን በዓፄ ኃይለ ሥላሴ መንግሥት በፖለቲካ ምክንያት ታስሮ የተሰቃዩን ኮሎኔል እምሩን ለምን አሰራችሁት? አብዮት እናካሔዳለን እያላ
ችሁ አብዮተኛውን ካሠራችሁ ከማንስ ጋር ልትሠሩ ነው እያልኩ በመመላለስ እጠይቅ ነበር።

በ25ኛ ሻለቃ ጅማ በልጅ ወታደርነት ሲቀጠር ጀምሮ በኋላም እድጎ ለአካለ መጠን ሲደርስ ሙሉ ወታደር ሁኖ ገነት (ሆለታ) ጦር ት/ቤት ገብቶ በመቶ አለቅነት ማዕረግ ተመርቆ ሲወጣ በመሣርያ ግምጃ ቤት ሻምበል ውስጥ ተዛውሮ በጥይትና ጠመንጃ እደላ ክፍል ተመድቦ ይሰራ ንበር። በዚያን ውቅት እኔ የ3ኛ ክፍለ ጦር የሁለተኛ መምርያ (የሎጂስትክ) ኃላፊ ስለ ነበርኩ በፖለቲካው ተጠርጥሬ ታስሬ ወደ አዲስ አበባ እስከ ሔድኩበት ግንቦት 30 ቀን 1957.ዓ.ም. ድረስ የሥራው ጠባይ ያገናኘን ስለነበር፤ መንግሥቱ ኃይለ ማርያምን ደኅና አድርጌ አውቀው ነበር። በዚያ ትውውቃችን መሠረት ነበር በግዜው የነበረውን የአብዮቱን ሁኔታ አንስተን ስንወያይ የክፍለ አገር አስተዳደር አድርገን የሾምናቸው ሲቪሎች ሳቦታጅ ያደርጉናል ያለኝ። እኔም ቀጠል አድርጌ አገሪቱን የሚያስተዳድር የጦር ኃይሉ ነው። ለምን መኮንኖችን አስተዳዳሪ አታደርጉም አልኩት። ችሎታ ያለው የለም ሲል መለሰልኝ። አገር ለማስተዳደር ችሎታ ያለው መኮንን ከሌለማ የዓፄ ኃይለ ሥላሴ መንግሥት በፖለቲካ ያሠራቸውን ያጋዛቸውንና ያሰደዳቸውን ለምን ከእናንተ ጋር እንዲሠሩ አታደርጉም



የሚል ሃሳብ ባቀርብለት "ክሬዲቱን እኛ መውሰድ አለብን" ብሎ መለሰልኝ። ለውጡን ያስገኘን እኛ ስለሆን የታሪክ ተሻሚ አንፈልግም ማለቱ ተሰማኝ። ለክሬዲት እንጂ ለዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ለፍትሐዊ አስተዳደር ደንታ የሌላቸው መሆኑን ለመረዳት ቻልኩ።

በሌላ ግዜ ለኮሎኔል እምሩ ጉዳይ ወደ ሻለቃ መንግሥቱ ኃይለ ማርያም ሂጄ ከቢሮው እንዳለሁ ጀኔራል ተፈሪ ባንቲ መጣና ሰላምታ ከተለዋወጥን በኋላ ተገናኘን። ከጀኔራል ተፈሪ በንቲ ጋር ወህኒ ቤት ከገባሁ ጀምሮ ተገናኝተን እናውቅም ነበር። "ያለ ግዜው ተነስታችሁ ተሰቃያችሁ" ስለ አለኝ መንግሥቱ " ክሬዲቱን እኛ መውሰድ አለብን" ያለውን ለማጣጣል አጋጣሚ አገኘሁና የዓፄ ኃይለ ሥላሴ መንግሥት ተቃዋሚዎች በየግዜው ባይገዘግዙት ኑሮ አሁን በቀላሉ ለውጥ ሊመጣ አይችልም ነበር ብዬ እቅጩን ስነግረው" መንግሥቱ ኃይለ ማርያም ይሰማ ነበር። ስለ" ክሬዲቱ " መናገሬ መሆኑ የገባው አይመስለኝም። የቀደመውን የነራስ ጉግሣን፤ ደጃዝማች ባልቻን፤ የእነ ሊጋባ በየነን፤ ብንዘለው እንኳ የዓፄ ኃይለ ሥላሴ መንግሥት ሊወድቅ የቻለው የክብር ዘበኛ መፈንቅለ መንግሥት ሙከራ ያደረገው የብሶት ቅስቀሳ ዋናው ሲሆን፤ በ1943 የነክቡር ቢትወደድ ነጋሽ እንቅስቃሴ፤ በ1954. ዓ.ም. የነፊታውራሪ ኃይሉ ከብረት እንቅስቃሴ፤ (እኔም ነበርኩበት፤ የጦር ኃይል ባልደረቦችን ያቀፈ)፤ በ1957.ዓ.ም. የጦር መኮንኖች እንቅስቃሴ (እኔም ነበርኩበት)፤ በ1962. ዓ.ም. የነ ክቡር ደጃዝማች ታከለ ወልደ ሐዋርያት እንቅስቃሴ በተለይ ክቡር ደጃዝማች ታከለ ወ/ሐ ያለ ማቋረጥ እስከ ሕይወታቸው ፍፃሜ የታገሉበት፤ ሌሎችም ግለ ሰቦች በተናጠል የታገሉበት፤ የዩኒቨርስቲ ተማሪዎች ደግመው ደጋግመው በሠላማዊ ሠልፍ ያሰሙት ተቃውሞ፤ እንዚህንና እነዚህን የመሳሰሉ በየግዜው የተደረጉ የተቃውሞ እንቅስቃሴዎች ድምር ውጤት ያመጣው ለውጥ እንጂ የጦር ኃይሉ የአበል ጥያቄ ያመጣው ለውጥ አይደለም።

እነዚህ በየግዜው የተደረጉ የተቃውሞ እንቅስቃሴዎች ቢከሺፉም ለሕዝብ ያስተላለፉት መልዕክት አልመከነም አፍርቷል። ከዚህም የተነሳ ነው ሕዝቡ የተቃውሞ እንቅስቃሴዎችን በተለይ ክብር ዘበኛ መፈንቅለ መንግሥቱ በራዲዮ ያሰማውን መልዕክት ሕዝብ ባለ መደገፉ ሲቆጭ ቆይቶ በ1966.ዓ.ም. የታክሲ ነጅዎችን የነዳጅ ዋጋ መናር የተማሪዎች ሴክተር ሪቪውን ተቃውሞ የጦር ኃይሉ ኑሮው እንዲሻሻልለት ያቀረበው ተቃውሞ ሕዝቡ ሊደግፈው የቻለው ባለፈው ቁጭት ነው።

ደርግ ያለ ውጣ ውረድ በሕዝብ ተቃውሞ ሳይደክም ያገኘውን መልካም እድሎቹን በራሱ የሥልጣን ስግብግብነት ቀብሯቸዋል። ደርግ ደም ሳይፈስ ያገኘውን ሥልጣን ራሱ መናድ የጀመረው ለአገራቸው ሉዓላዊነት አንድነት ሲታገሉና ሕዝብ ሲያስተባብሩ የነበሩትን የክቡር ጀነራል አማን አንዶም ሚካልን መኖርያ ቤታቸውን ከቦ በታንክና በከባድ መሣርያ ሲመታ ነው።የደርግ ውድቀት ከዚያ ጀምሮ በጀኔራል ታሪኩ ዓይኔ የተደመደመው።

ክቡር ጀኔራል አማን ሚካኤል አንዶም በርዕሰ ብሔር ሥልጣናቸው ቢቆዩ ኑሮ ሻዕቢያም ጀብሃም ወያኔና ኦነግ ሌሎችም ተገንጣይ ድርጅቶች ተከታይ አጥተው ያለ ጦርነት ጫጭተው በራሳቸው ይጠፉ ነበር። ምክንያቱም ጀኔራል አማን ለሕዝቡ በሚገባው ቋንቋ በትግርኛ በአማርኛና ዓረብኛ የመገንጠል አደጋን የአንድነት ጥቅምን ተንትነው ስለ አስረዱት ተገንጣዮችን ሕዝብ አንከተላችሁም ብሏቸው ነበር። የጀኔራል አማን ሞት ለተገንጣዮች ትልቅ የመጀመሪያው ድል ነበር።

ሻዕቢያና ወያኔ ታምራዊ እድገት ያገኙት ጀኔራል አማን ሚካኤል አንዶም ከተሰው በኋላ ነበር። ደርግ መቀጣጫ እያለ ያለ ፍትሕ የመደዳ ጭፍጨፋ በማካሄዱ ነፍሴን አውጪኝ እያለ ወደ ተገንጣዮች እየሔደ በመግባቱ ለሻዕቢያና ለወያኔ የሰው ኃይል ያጎረፈላቸው የደርግ እርሸና ነው። በተለይ የተማረውን የሰው ኃይል በውኃ ቀጠነ ይገድልና ያስር ስለነበር። ተገንጣዮች ፖለቲካውንና ኢኮኖሚውን የሚያቀነባብርላቸው የምሁራን ኃይል በማግኘታቸው ዕድላቸውን አቃንቶላቸዋል። በእርግጥ ሻዕቢያና ወያኔን ኮትኩቶ ያሳደጋቸው ደርግ ነው ቢባል ስሕተት አይሆንም።

ደርግ ለአገራቸው ዕድገት የሚያስቡትን አገር ወዳዶችና ዴሞክራቶችን እየገደለ በእየስር ቤቱ እያጎረና እያሰቃዬ ፀረ ኢትዮጵያ አቋም የያዙትን የትም አይደርሱ ብሎ በመናቅ ትኩረቱ በመኮንኖቹና በምሁራን ላይ ነበር። አገር ወዳዶችን በመግደል እንደ ትልቅ ጀብድ እየተቆጠረ ከካድሬ ጀምሮ እስከ ከፍተኛው ባለ ሥልጣን ገድሎ ለማሞገስ በየፊናው የግድያ ዘምቻውን ተያያዘው።

የግፉ ሥራ ምን ውጤት እንደ ሰጠው እስኪ እንመልከተው። በሰው ደም የተጨማለቀው ደርግ የአእምሮ መታወክ ደርሶበት የሲኦል ፈታውራሪዎች የእነ ኾርማን ኮኸን የነ ፖል ሄንዜ ምርኮኛ ሆነ።

- የመንግሥት ሥልጣን የተረከበው ተስፋዬ ገ/ኪዳን አትዋጉ መሣርያችሁን ደርድሩ ብሎ ለሠራዊቱ ትዕዛዝ ሰጥቶ ወደ ኢጣሊያ ኤምባሲ ገብቶ የተሞሸረው በማን ትዕዛዝ ነው? በእነ ኮኸን ወይስ በሻዕቢያ ትዕዛዝ ወይስ ወያኔ አዲስ አበባ በሰላም ስለገባለት የሙሽርነት ጊዜውን ሊያሳልፍ ጫጉላ ቤት መግባቱ ነው?

- ወያኔ ጥይት ሳይተኩስበት አዲስ አበባ ገብቶ ቤተ መንግሥትን ሲይዝ ለኢትዮጵያ ሠራተኛ ፓርቲ (ኢሰፓ) መሪዎች እጃችሁን ስጡ፤ ባትስጡ ግን ርምጃ ይወስድባችኋል ብሎ ወያኔ ሲያውጅ የኢሠፓ መሪዎች ተሠልፈው እጃቸውን ሰጥተው የታሠሩት የግፉ ድርጊት አስገድዷቸው ይሆን? አውሮፕላን በእጃቸው እያለ እንደ መሪያቸው ወደ ውጭ መኮብለል ሲችሉ እንደ በግ ተኮልኩለው እርጅ ውስጥ ገብተው የታጎሩት የግፍ ሥራቸው አለቃቸው ብሎ እንዳቸውም ሳያመልጡ እግር ከወርች አስሮ የሰጣቸው። የዓፄ ኃይለ




ሥላሴ መንግሥት ባለሥልጣናትን እጁን ያልሰጠ ሃብቱ ይውረሳል ብለው አታለው እጃቸውን በሰላም የሰጡትን በሥልጣን ላይ ሳሉ የሠሩትን በድል የሚመረምር ኮሚሺን አቋቁመው ቃላቸውን በመስጠት ላይ እንዳሉ ፍርድ ቤት ቀርበው ጥፋታቸው ሳይታውቅ በግፍ የተረሸኑት ብድር አይደለምን? ወያኔ በኢሠፓ መሪዎች ላይ የወሰደው ርምጃ በዓይነትም በይዘትም በድርጊትም በአፈጻጸምም ደርግ ያደረገውን ነው ወያኔ የደገመው። የውሻ ደም የማያስቀረው ታላቁ አምላካችን ልዑል እግዚአብሔር ዓይን በዓይን ጥርስ በጥርስ ይከፈላል ያለውን በትክክል በማይዛባ ፍርዱ ፈጽሞታል።

## አንበሳ በአህያ መሪነት፤የግዙፉ የደርግ ሠራዊት

ከም/መቶ አለቃነት እስከ ሜጀር ጀኔራልነት ማዕረግ የደርሱ ሠራዊቱን በጠቅላይ ኤታ ማዦርነት (ቺፍ ኦፍ ስታፍ) የመሩ ጀኔራል ግዛው በላይነህ አብዛኛውን ዕድሜያቸውን በሠራዊት አሰልጠኛነትና በአዛዥነት ያሳለፉ ንቁ መኮንን በሥነ ስርዓት አጥባቂነት የታወቁ በውትድርናው ሙያ ብቁ ችሎታ የነበራቸው ያልተልከሰከሱ ምርጥ መኮንን እንደ ነበሩ አውቃለሁ። ይሁን እንጂ በሠራዊቱ ላይ ስለ ደረሰው አሳፋሪ ውርደት በአንድ ጋዜጣ ወይም መፅሔት ላይ ቃለ መጠይቅ ተደርጎላቸው የሰጡት መልስ "ሠራዊቱ የደረሰበት ውርደት ሲያንሰው ነው" ያሉት ከቁጭት ይመስላል። ሆኖም በሰሜን ግንባር በመቶ ሺህ የሚቆጠር ሠራዊት አዛዥ የነበረው ጀኔራል ሁሴን አህመድ የሚያዘውን ጦር አጋልጦ በአውሮፕላን ወደ ጅዳ ሳኡዲ አረብያ ሲፈረጥጥ ያ ሠራዊት ከእርሱ ለሚያንሱ ተገንጣይ ሺፍቶች እጁን ለምን ሰጠ? በተማረው ትምህርት እስከ መጨረሻው ሰውና ጥይት አልተዋጋም ብሎ መፍረድ ይገባል ወይ? በጦር ሜዳ ተሰልፎ ሲዋጋ ከድቶ ለጠላቱ እጁን ባልሰጠ ሠራዊት ላይ ነቀፌታ መሰንዘር ወታደራዊ ሥነ ሥርዓትን ከሞራል ብቃት፤ የዕዝ ተዋረድን ያዛዥና የታዛዥ ግዴታዎችን እንደ መዘንጋት ይቆጠራል። ሠራዊቱ ያዛዦቻቸውን ትዕዛዝ ሲጠብቁ ሻዕቢያ አስመራ ሲገባ ጀኔራል ሁሴን አህመድ ጅዳ ሳውዲ አረቢያ ገብቷል። ያ ሠራዊት እኮ በውጊያ አልተቸነፈም። የውጊያ ትዕዛዝ ሰጥቶ የሚያዋጋው መሪ ባለ መኖሩ ሺፍቶቹ ስተት ብልው ገብተው ከተማውን ሲቆጣጠሩ የተፈጸመው እርክክብ እንጂ በውጊያ አቸናፊና ተሸናፊ አልነበረም። ቀደም ብሎ ደርግ ችሎታ የነበራቸውን የመምራትና የማዋጋት ልምድ የነበራቸውን በውኃ ቀጠነ እየረሸነ በእነርሱ ምትክ ብቃትና ችሎታ የሌላቸውን የሾመ ደርግ ለጥፋቱ ሁሉ ታሪክ ተጠያቂ ያደርገዋል።

ተገንጣዮች ሻዕቢያና ወያኔ ከኢትዮጵያ የጦር ኃይል የሚለዩት ከምዕራባውያን ኢምፔሪያሊስት አገሮች በሚቸርላቸው ምግብና ትጥቅ በመሳሰሉ ሎጀስቲካዊ አቅርቦት እንጂ በተዋጊነትና በሞራል ጥንካሬ ከአንድ ሥር የወጡ ስለሆኑ ስነ ልቦናዊ መሠረታቸው አንድ ስለሆኑ በምንም አይበላለጡም። እንዲያውም የጦር ኃይሉ ያለ በቂ ስንቅ



ጀግናው ደጃዝማች ጉግሣ አምባው



እየተራበና ችግርን ችሎ የተቋቋመ ከፍተኛ ወኔና ሞራል ነበረው።

ጀኔራል ግዛው በላይነህ ቁጭታቸውን ወደ መሪዎቹ ቢያዞሩ ይሻላቸዋል እንጂ "ቅጣቱ ሲያንሰው ነው" የሚለው ብያኔአቸውን ወታደራዊ ሳይንስ አይደግፈውም። ሠራዊት እኮ የሚታነጸው በአስተማሪዎቹ ነው። ጀኔራል ግዛው በላይነህ ሠራዊቱ ጥፋት አድርጓል የሚሉ ከሆነም በትክክል አላስተማሩም ማለት ነውና የጥፋቱን መድበል እርሳቸው ሊሸከሙት ግድ ይላቸዋል።

መንግሥቱ ኃይለ ማርያም አገራቱን ጥሎ ሲፈረጥጥ ሥልጣኑን የተረከበው ተስፋዬ ገ/ኪዳን በአዲስ አበባ ዙሪያ ይከላከል ለነበረው ሠራዊት አትታኮሱ መሣርያችሁን ደርድሩ ብሎ በአሻጥር ትጥቁን እንዲፈታ የተደረገ ሠራዊት በምንም ምክንያት በጥፋት ሊፈረጅ አይገባውም። የአዛገዦችን ትዕዛዝ በመፈጸሙ አይወነጀልም።

እኔም እንደ ማውቀው ከሆነ የኢትዮጵያ የጦር ኃይል እግረኛው የአየር ኃይልና የባሕር ኃይል ሌላውም ማናቸውም ታጣቂ በስልትና ዘዴ ይመሩት የነበሩትን አለቆቹን ደርግ በየግዜው ቢረሺንበትም ሽንጡን ገትሮ በምሥራቁና ሰሜን የውጊያ ሜዳዎች ተዋግቷል። ከሠራዊቱ ውስጥ የደርግን ጭፍጨፋ በመቃወም ከድቶ ለተገንጣዮች እጁን የሰጠ የለም። ብልሽቱ ከአናቱ ከመሪው ነው፡ እንጂ ከሠራዊቱ አይደለም።

የአንበሳ ጠረን በሩቅ ሲሸታት ፈርጥጣ ገደል እንደምትገባ እህያ እንዲሁም የደርግ ታማኝ ምርጥ ከፍተኛ መኮንኖች ከሚባሉት ውስጥ እንደነ ጀኔራል ሁሴን አህመድና መሰሎቹ አንበሳውን ጀግና ሠራዊት እንዲምሩ የተደረጉት የሞት ጠረን ሸተተኝ ብሎ አንበሳው ሠራዊት ጥሎ የፈረጠጠን ለደረሰው ጥፋት ሁሉ ተጠያቂ ይሆናል፡ እንጂ ሠራዊቱን አይመለከትም።

አንድ ትዝብት ልጨምር። ሜጀር ጀኔራል ግዛው በላይነህ የጦር ኃይሎች ጠቅላይ ኤታ ማዦር ሹም የነበሩ በ1969 ዓ.ም. ታጠቅ ጦር ሠፈር ሠራዊት ሰልጥኖ በሚመረቅበት ዕለት 80 ሺህ ጦር አሰልፈው ሻለቃ መንግሥቱ ኃይለ ማርያም በእስቴጅ ላይ ሲቆም "ለሊቀ መንበሩ በብረት ሰላም በል" ብለው ሰላምታ ሰጥተው ያነገሡት ያጠፋውን በሠራዊቱ ላይ መጫን የእምዬን ጥፋት በአብዬ ልክክ እንደ ተባለው ነው።

በመጨረሻም ጀኔራል ግዛው በላይነህ ነቢዩ ኤርሚያስ በምዕራፍ 46 ቁጥር 21 "ሸሹም በአንድም ከበለሉ አልቆሙም። የጥፋታቸው ቀን መጥታባቸዋለችና የመታሰቢያቸውም ግዜ" የሚለውን ከዱሮው መጽ ሐፍ ቅዱስ እንዲመለከቱት አሳስባቸዋለሁ።

በአጠቃላይ መልኩ ሲታይ እንዲያው ምክንያት ተደረደረ እንጂ የደርግ (ኢሰፓ) የአመራር አባላት የፈጸሙት አረመኔአዊ የግፍ ግፍ ብልሃትንና መላን ሰውሮባቸዋል። ሁለመናውን አጨልሞባቸዋል። የመንፈስ ሽብርና መርበትበት ከዞረባቸው የሚይዙትና የሚጨብጡት አጥተው የተፈጸመ ነው። ትንቢተ ሚልኪያስ ምዕራፍ 3 ቁጥር 2



ጀግናው ደጃዝማች ጉግሣ አምባው

"መልካሙን ጠልታችኋል ከፉውንም ወዳችኋል ቁርበታቸውንም ገፉችኋል ሥጋቸውንም ከአጥንታቸው ለይታችኋቸዋል፡ አጥንታችውንም ሰባብራችኋል" የሚለው ትንቢት በዘመናችን ደርሶ አይተናል። ትንቢትን ነገር ይቀድመዋል እንደተባለው፤ በዘመነ ደርግ ያልተደረገ የግፍ ዓይነት የለም። ለምሳሌ ያህል አንዱን የግፍ ድርጊት ከዚህ ላይ ልጥቀሰው። ኮሎኔል ምሩ ወንዴ በኮሎኔል ምንግሥቱ ኃይለ ማርያም ድጋፍ ከተፈታ በኋላ ወደ ኮሎኔል ምንግሥቱ ሄጄ ከጽሕፈት ቤቱ ስንነጋገር ኮሎኔል እምሩን የጎንደር አስተዳዳሪ ለማድረግ ሻለቃ ተፈራ ወልደ ተንሳኤን የባሌ ክፍለ አገር አስተዳዳሪ እንዲሆኑ አሰበናልና ምን ይመስልዎታል ብሎ አስተያዬቴን እንድሰጠው ጠየቀኝ። እኔም ኮሎኔል እምሩ ለማስተዳደር ብቃት አለው። ከሕዝብ ጋር ለመግባባት ይችላልና ትዕግሥት ስለ አለው ጥሩ አስተዳዳሪ ሊሆን ይችላል። ሻለቃ ተፈራ ወልደ ትንሳኤ ግን ከሕዝብ ጋር ተስማምቶ ለማስተዳደር ትዕግሥት የሚያንሰው ይመስለኛል ብዬ አስተያየቴን ሰጠሁት። እንዲያውም ካሉስ ብሎ ኮሎኔል መንግሥቱ ንግግሩን ሲቀጥል "ሻለቃ ተፈራ ወልደ ትንሳኤ የሲዳሞ አስተዳዳሪ በነበረ ግዜ ሰውን በሕይወቱ እያለ በቁመናው ሰውነቱን አስገፍፎታልና ርምጃ እንዲወሰድበት ብለው የደርግ አባላት ጠይቀው ነበር። እኔ ግን ለአብዮቱ አስተዋጽኦ አድርጓል ብዬ ከሲዳሞ አንስቼ አዲስ አበባ የወሀኒ ቤቶች አስትዳዳሪ አደረግኩት" ብሎ ነገረኝ። እንግዲህ ማንኛቸውንም የግፍ ድርጊት ከዚሁ ሊቀመንበር ከነበረው ንግግር መረዳት ይቻላል።

በ17 የፍዳ ዓመታት በዕየለቱ የተፈጸመውን ግፍ ምን ያህል እንደ ነበረ አኃዙን ይህን ያህል ነው፡ ብሎ ለመናገር ባይቻልም በሠራዊቱም ሆነ በሕዝብ ግፍ ሳይፈጸምበት በሰላም ያለፈች ከ6205 ቀናት ውስጥ ሊኖር አይችልም።

በትንቢተ ዕንባቆም ምዕራፍ 2 ቁጥር 7 - 8 " የሚያስጨንቁህ ይነቃሉ ለእነርሱም ብዝበዛ ትሆናለህ። የሰው ደም ስለ አፈሰስህ በምድሪቱና በከተማይቱም በእርሷም በሚኖሩ ሁሉ ላይ ስለ አደረግኸው ግፍ አንተ ብዙዎቹን አሕዛብ በዝብዘሃልና ከአሕዛብም የቀሩት ሁሉ ይበዘብዙኃል።" ተብሎ የተነገረው ትንቢት ከሁለት ሺህ ስድስት መቶ ዓመታት በኋላ እነሆ ደርሶ ደርግ ከሕዝብ የዘረፈውን ሁሉ ወያኔ ዘርፎታል። ወያኔም የደርግን ፈለግ ተከትሎ መጥፊያውን እየሠራ ነው። አይደርስም ብሎ ግፍ ማድረግ ተመልሶ በራስ ላይ ሲመጣ እየታየ ነው። የእግዚአብሔር ቃል አይሞትም፡ አያረጅም ለዘለዓለም ጸንቶ ይኖራል።

ደርግ ተቃዋሚውን ኢሕአፓን ከከተሞች ጠራርጎ ለማጥፋት የወሰደው የመደዳ ጭፍጨፋ (ቀይ ሽብር) ደመ ነፍሱን ቢያወጣ ያውጣኝ ባያወጣኝም ልጥፋ ብሎ የወሰደው ርምጃ ዓቅመ ደካማ ስለ ነበረ ነው። በመንገድ ቁሞ ያገኘውን ሁሉ እንደ አበደ ውሻ ሕፃን



ሽማግሌ ድኩማን ሳይል ያለ ልዩነት ይረሽን የነበረው ተስፉ በመቁረጥ ነው። ልጁንና ወገኑን የገደልኩበት ሕዝብ ሁሉ ሆ ብሎ ይነሳብኛል ብሎ ከመፍራቱ የተነሳ ነበር። ያን መሳይ አረመኔአዊ ጭካኔ ያደረገው መቼም በዚህ ዓለም እንደ ፈሪ ያለ ጨካኝ የለምና ደርግም ፍርሃቱን ነው የገለጸው፤ ደርግ ፈሪ ባይሆን ኖሮ ይህን መሳይ የዕብድ ሥራ አይሠራም ነበር።

ደርግ የመደዳ ጭፍጨፋውን ከማካሄዱ ትንሽ ቀደም ብሎ የከተማውን ሕዝብ መሣርያ ጠራርጎ ወስዶ ነበር። ከአዲስ አበባ ከተማ ምርጥ አውቶማቲክ መሣርያዎችና የቃታ ጠመንጃዎች ሰባ ሺህ፤ እንደዚሁም ጎንደር ከተማ 7(ሰባት ሺህ)፤ በድምሩ 77 ሺህ (ሰባ ሰባት ሺህ) ወስዶ ነበር። በዚያን ወቅት የጦር ሠራዊቱ በድምሩ በ 40.000 (በአርባ ሺህ) ክልል ውስጥ የነበረ ነው። የአዲስ አበባና የጎንደር ከተማ ሕዝብ ከያዘው መሣርያ ጋር ሲነፃፀር በግማሺ ያንስ ነበር።

ሕዝቡ መሣርያውን ቀደም ብሎ ባይነጠቅ ኑሮ ልጁ እየተገደለ ከበራፉ ሲጣል የሚታገስ አልነበረም። እጅግ የከፋ የርስ በእርስ ዕልቂት መነሳቱ አይቀርም ነበር። ደርግ ትጥቅ በማስፈታቱ የዕርስ በርሱ ውጊያ ያለቀለት ቢሆንም በሌላ በኩል ደግሞ ከፍተኛ ጉዳት አስከትሎበታል። የአገሪቱን ሉዓላዊነት ሲያስከብሩ የኖሩትን የጠረፍ ዘበኞች ነፍጠኞች እያለ ትጥቅ በማስፈታቱ ኢትዮጵያን በውጭ ኃይል አስደፍሯታል። ነፍጠኛው ትጥቅ መፍታቱን ተመልክታ ሶማሊያ አጋጣሚውን በመጠቀም ወረራዋን ቀጥላ እስከ ሐረር ከተማ ለመገስገስ አስችሏታል። በዚያን ወቅት ደርግ የገፈፈውን መሣርያ ለሕዝቡ ቢመልስ በሚያውቅበት ስልትና የመሬት አጠቃቀም የሶማሊያን ወራሪ ጦር መመለስ ይችልነበር። የኩባን ወታደራዊ ዕርዳታ መጠይቅ ባላስፈለገ ነበር።

## መብትና ግዴታ

አብዮት የሚያውቁ ተጠቅመውበታል። አብዮትን የማያውቁ ተጎድተውበታል። መብታቸውን ያወቁና የነቁ ግን ሕሊናዊ ዝግጅት በማድረግ ኃይላቸውን በማስተባበር ተደራጅተው መብታቸውን አስከብረዋል። ሰብዓዊ መብታቸው ሲረጋገጥ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ሲታፈን ሕግና ሥርዓት ሲጣስ ተባብረው ያልታገሉ ወይም አብዮቱን ደግፈው ያልቆሙ መብታችን ተነካ ክብራችን ተዋረደ ብለው ለመናገር ለሰላ እንደበት አልታደሉም። ሕሌናዊ ዝግጅት ሳያደርጉ ሳይደራጁ በግብታዊነት አብዮት ለማካሔድ የሞከሩም ራሳቸውንና አገርን ጎድተዋል።

ማናቸውም መንግሥታዊ ድርጅት ወይም ማኅበር ወይንም ግለ ሰብ ሕጋዊ መብቱንና ግዴታውን ማወቅ ይገባዋል። የሕዝብ እንደራሴዎች መክረው ከአጸደቁት ሕገ መንግሥት ድንጋጌዎች መሠረት ከድንጋጌዎች ሳይተላለፍ ሳይዛነፍ የአገርን ሉዓላዊነት መጠበቅ አገርን በማንኛቸውም ዘርፍ በእድገት ማራመድ ሕግና

ሥርዓት ማስከበር የሕዝብን ጤና መጠበቅ የየአንዳንዱን ዜጋ ብሔራዊና ተፈጥሮአዊ መብቶቹን የማስከበር ኃላፊነትና ግዴጅ አለበት። በአጠቃላይ መንግሥት ተብሎ የሚጠራው ድርጅት ሕዝብን እንዲያገለግል በሕዝባዊ ሸንጎ የተቀጠረ ዘበኛ ወይም የሕዝብ አገልጋይ ሎሌ ነው እንጂ ጣዖት ሁኖ የሚሰገድለት አምላክ ሁኖ የሚፈራ አይደለም። በዘልማድ ግን መንግሥት እንደ ጨካኝ ክፉ አውሬ ይታያል።

መንግሥት የሕዝብ አገልጋይነቱን ትቶ ሕዝብና አገር እንዲጠብቅ ባስታጠቀው መሣርያ ተመክቶ የሕግ ድንጋጌዎችን ጥሶ ከተራመደ መንግሥት ሳይሆን በጌታው በሕዝብ ላይ ያመፀ ወንበዴ ነው። በመሠረቱ ሕዝብ ያላቋቋመው መንግሥት ተብሎ አይጠራም። መንግሥት ተብሎ በሚጠራው ማኅበር ወንጀል የማይፈጸምበት አድሎ የማይደረግበት በጎሣና ቋንቋ በሃይማኖት የማይከፋፈልበት በሰው ልጅ መካከል ልዩነት የማይደረግበት ፍትሕ የማይዛነፍበት ዴሞክራሲያዊ መድረኮች የሚዘረጉበት ታሪክና ባሕል የሚጠበቅበት እንደ ፀሐይ ለሁሉም እኩል ብርሃን የሚሰጥበት እንደ ኦክሲጅን ለሁሉም እኩል የሕይወት ትንፋሽ የሚገኝበት ማለት ነው። መንግሥታዊ ድርጅት በሕግ ተደንግጎ በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ጠላት በአገር ላይ ሲነሳ የክተት አዋጅ ያውጃል በጦርነት ወቅት ለጦርነት ይጠቅማል በሚለው ሁሉ የመጠቀም መብት አለው።

የሕዝብ ግዳጅ እያንዳንዱ ዜጋ በሕግ የተመራ በሥርዓት የተገራ መሆን አለበት። በየፈናው ዴሞክራሲያዊ መብቴ ነው እያለ ከሥነ ሥርዓት ውጭ ለመሆን ሕግ አይፈቅድልትም። በተለይ በወታደር ማኅብረ ሰብ ውስጥ ሥነ ሥርዓት በጠበቀበት (ዲስፒሊን) ከሞት ይልቅ ትዕዛዝ በሚያስፍንበት የዕዝ ተዋረድ በተከበረበት ከታህሣሥ 1953.ዓ.ም. የክብር ዘበኛ መፈንቅለ መንግሥት ሙከራ ከከሸፈ በኋላ ሰጥ ለጥ ብሎ መታዘዝን ቸል እያለ ሥነ ሥርዓት እየላላ የበታች ለበላዩ የሚሰጠውን አክብሮት እየቀነሰ ወደ መናናቅ አድርሶት ነበር። በ1966.ዓ.ም. በእግዚአብሔር ተቀብቻለሁ የሚለውን የዓፄ ኃይለ ሥላሴ መለኮታዊ መንግሥት የሚተካ ድርጅት ሳይኖር በሥርዓት አልባነት በዘፈቀደ ሲቪሉ በአስተዳዳሪዎቹ ወታደሩ ባለቆቹ ላይ እያመጸ በሥርዓት አልባነት መሪዎቹን ከሥልጣን ለማውረድ አድማው በየቦታው ቀጠለ መንግሥታዊ አመራር ተቋረጠ።

ከዚያው ተያይዞ ደርግ የመንግስት ሥልጣን ይዞ ማርክሲዝምና ሌኒንዝምን (ኅብረተሰባዊነትን) መመሪያው አድርጎ ካወጀ በኋላ ሥነ ሥርዓትና የዕዝ ተዋረድ ሞተ ተቀበረም። ዕውቀት የሌለው ተራ ወታደር የአብዮቱ ታማኝ እየተባለ በካድሬነት እየተደለደለ የበላዮቹን የተማሩ መኮንኖችን ትዕዛዝ አልቀበልም እያለ በአዛዥ መኮንኖች ላይ እያደመ የማሰርና የመግደል መብት ከደርግ ስለ ተሰጠው ያለ እውቀት እየተመራ ያሻውን ያደርግ ነበር። ከዚያም የተነሳ በካድሬዎች ውሳኔ ሠራዊቱ በመመራቱና ዕውቀት ያላቸው አዛዥ መኮንኖች ሥልጣናቸው በመገፈፉ ኢትዮጵያን ለአሳፋሪ ውድቀት ዳርጓታል። ካድሬው



በእውቀት ማነስ ምክንያት ራሱ የሚጠፋበትን ነበር የሚሠራው። ያ ደርግ ያሰባሰበው ግዙፉ ሠራዊት ለሺፍታ ያውም ለተገንጣይ እጁን የሰጠው የአዛዥና ታዛዥ የመሪና ተመሪ ወታደራዊ ሥርዓት ጠፍቶ በየጦር ክፍሉ በነበረው ካድሬና ኮሚሳር ቆራጭ ፈላጭነት በመመራቱ ነበር።

በሲቪል መሥሪያ ቤቶችም በመሁራን ላይ የተሾሙ ከቀበሌ ጀምሮ እስከ ሚኒስትሩ መሥርያ ቤት የበላይ ሁነው ይመሩ የነበሩት ችሎታ የሌላቸው ደደቦች እራሳቸውን ማስተዳደር ያልቻሉ በዘፈቀደ ፎሪዎች የጎዳና ተዳዳሪዎች ጥሪት የሌሾች የአብዮቱ ታማኞች (ወዝ አደር) የሚል ቅጽል ስም የተሰጣቸው ማንኛውንም በበላይነት እንዲቆጣጠሩ ሙሉ መብት ተሰጡ።

በጣም የሚገርመው በየቀበሌውና በየ ማምረቻው ድርጅቶች ለአስተዳዳሪነት ለፀጥታ ጥበቃ የሚመረጡት ምንም ዓይነት ጥሪት የሌላቸው ቤት ንብረት ወይም ርስት የሌላቸው ሠርተው ሆዳቸውን መሙላት የተሳናቸው አብዛኛዎቹ ደረጃ አዳሪዎች የዱርዬ ጠባይ የነበራቸው ሞራላቸውን የጣሉ ተልከስካሾች ተራማጆች ተብለው በኃላፊነት ቦታ ይመደቡ ነበር።

ትንሽ ራስ የምታስገባ ጎጆና የከተማ ቦታ ያለው ታታሪውን ጭዋው አድኃሪ በዝባዥ ተብሎ ለቀበሌም ሆነ ለማኅጄመንት ሥራ ኃላፊነት አይመረጥም ነበር። ከዚያም ሌላ የቤተሰብ ኃላፊነት የተሸከመ የማይልከሰከስ ቤት ሠርቶ ኑሮውን በሥርዓት የሚመራ ጨዋ ሰው አድኃሪ እየተባለ በውኃ ቀጠነ ይታሰርም ይገደልም ነበር። ቆንጆ መልከ መልካም ሚስት ያለውማ ፈረደበት ሚስቱን ለመውሰድ ሲሉ ካድሬዎች ጸረ አብዮተኛ እያሉ ብዙዎችን አስረዋል ገድለውማል።

በሕዝብ ላይ የተሾሙ ወሮ በሎች የፈጸሙት ማስተዳደር ሳይሆን በቀል ነበር። በየመሥርያ ቤቱና በየፋብሪካው የነበሩ ጠንካራ ማናጀሮችና የክፍል ኃላፊዎች ዋልጌውንና መጋጣውን ሠራተኛ ሥራውን አክብሮ በትክክል የማይሠራውን ሲቆጣጠሩት ለምን ተቆጣጠሩኝ ብሎ የተቃውሞ ወረቀት ራሳቸው በትነው፣ በትነዋል እያሉ በሃሰት እየወነጀሉና ልዩ ልዩ ምክንያት እየፈጠሩ ያሳሰሯቸውና ያስገደሏቸው ብዙ ናቸው።

በተለይ በልማት ላይ ተሰማርተው ምርትን ያሻሻሉ ምሁራን እየተባረሩ በምትካቸው በነዚሁ ደርግ ወዝ አደር በሚላቸው ዕውቀት የሌሾች እየተተኩ በአመራር ጉድለት ምክንያት ብቻ የልማቱን እንቅስቃሴ ወደ ኋላ ጎትቶት ብዙ ማሣዎች ዳዋ እየለበሱ የአውሬ መፈንጫ ሁነው ታይተዋል። ደርግ ያለ ርኅራኄ በጭካኔ በመደዳ እየጨፈጨፈ ሬሣ የሸጠው የሕዝብን ድክመት አይቶና ሰልሎ ከመናቅ የተነሳ ነው።

- የድሮ ባለ ሥልጣናት 60 ያለፍትህ በአንድ ግዜ ሲረሸኑ።
- ንጉሡን አፄ ኃይለ ሥላሴን አስሮ አስሮና አንገላቶ ሲገድል፤
- ሠላማዊ ሠልፈኞችን ገድሎ ሬሣቸውን በገንዘብ ሲሸጥ፤
- የከተማ ቤትና መሬት የገጠር ርስቱን አታክልቱንና ንብረቱን

ሲቀማና የልማት ድርጅቱና ፋብሪካው ሲወሰድበት መብቴን አላስነካም ብሎ ተቃውሞ ባለማቅረቡና ሲገድሉት ሲያስሩትና ሲያሰቃዩትም ዝም ብሎ የሚወርድበትን መዓት በመቀበሉ ደርግ ቀይ ሽብር በሚል መፈክሩ የመደዳ ጭፍጨፋውን በድፍረት ቀጠለ።

ደርግ " ያለ ምንም ደም ኢትዮጵያ ትቅደም " የሚል መፈክር እያሰማ በአንፃሩ ግን በጭካኔ እያረደ አገሪቱን በደም ጎርፍ አጥለቅልቋት ነበር። አገርን ለመምራት ሕዝብንም ለማስተዳደር (የፖለቲካ) መሐይም የነበረው ደርግን ሁለት (ጠላቶች) ሰይጣኖች በርዕተ ዓለም ሁለተኛው ቂም በቀል ይዞ የተሰለፈው የአገር ውስጥ የጎሳ ኃይል ነበሩ ወደ ገደል የመሩት።

የመንግሥት ሥልጣን ከያዘ በኋላ ደርግ የአለበትን ኃላፊነትና ግዴታ በትክክል ባለማወቁ ዕውር ደንበሱን እየተመራ አገር ወዳዶችን እያጠፋ ፀረ አገር የሆኑትን ተገንጣይ የጎሣ ድርጅቶችን እየኮተኮተ አሳድጎ ምንም ዓይነት ጥይት ሳይጮኽባቸው አሥመራንና አዲስ አበባን በሰላም አስረከበ። የኮምዩኒስት መሪ የተባለው መንግሥቱ ኃይለ ማርያም ሠራዊቱን ለሻዕቢያና ወያኔ መቀበያ ፍሪዳ ሰጥቶ ወደ ውጭ አገር ኮበለለ።

ሌሎችም የኢትዮጵያ የሠራተኛ ፓርቲ (ኢሠፓ) መሪዎች የዓፄ ኃይለ ሥላሴን ባለ ሥልጣኖችን "እጃችሁን ስጡ ባትሰጡ ግን ንብረታችሁ ይወረሳል ብለው አውጀው ባለ ሥልጣኑ ሁሉ ንብረቱን እንዳይወረስበት እጁን በፈቃዱ የሰጠውን በእሥራት እንዳሰቃዩት እንዲሁም ወያኔ የኢሠፓ መሪ የነበሩትን እጃችሁን እንድትሰጡ ባትሰጡ ግን እርምጃ ይወሰድባችኋል" ብሎ ሲያውጅ የኢሠፓ የአመራር አባሎች እኔ እቀድም እኔ እቀድም እየተባባሉ ተጋፍተው እጃቸውን ሰጡ። ወያኔም እንኳን ደኅና መጣችሁ ብሎ ወህኒ ቤት አስገብቶ ፍዳቸውን እያስከፈላቸው ነው። ርጎራጌ ቢሶች ተስማምተው በአንድነት ነፍሳትን የበሉ ግፈኞች ከበርቴው ሰው እንዳለው የሞቱ ሰዎች ሁል ግዜ ጥሩ ናቸው በሕይወት ሳሉ የሞቱ ማለቱ ነው፡ ከሞት ይልቅ እኔን ይፈራሉና እንዳለው ያፈሰሱት ደም ያሰቃዩት ነፍስ በቁመናቸው መንፈሳቸውን ገድሎ ከሞት ይልቅ የወያኔን ትዕዛዝ ፈርተው ተኮልኩለው እጃቸውን ለጠላታቸው ሰጥተው በሠፈሩት ቁና እየተሠፈሩ ነው።

ቀይ ሽብር በሚሉት የመደዳ ጭፍጨፋ እየተገደሉ የተጣሉት በሥርዓት አልተቀበሩም። ወላጆች ለልጆቻቸው እንዳያለቅሱም ከልክሏል። እንደ ጉድፍ የትም ጥሏቸዋል። ከጥይት የተረፉትንም በራብ ገድሏቸዋል። በየትም እየረሸነ የጣላቸውን የሰማይ አሞሮች የምድር አራዊቶች በልተዋቸዋል። ይኸውና ብድሩ በዚያው ልክ እየተከፈለ ነው። ለጠላት እጅ ከመስጠት የበለጠ ውርደትና ሞት ፈጽሞ የለም።

ደርግ በማንኛውም በኮምዩኒስት አገሮች ያልተደረገውን የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የበላይ መሪ የነበሩትን ፓትሪያርኩን ብፅዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስን እየደበደበ አስሮ በግፍ ገድሏቸዋል።



እንዲሁም የመካነ ኢየሱስ ወንጌላዊ መሪ ቄስ ጉድናን ገድሏቸዋል።

ብፁዕ አቡነ መልከ ጻዴቅ ሊቀ ጳጳስን ደብረ ታቦርና ዳባት ትምህርት ቤቶች ከፍተው በማስተማራቸውና ድንቁርናን በመታገላቸው ወንጀል ሁኖባቸው ደርግ 8 ዓመት አስሮ አሰቃይቶአቸዋል። ሌሎችም የሃይማኖት መሪዎች የታሠሩና የተገደሉ ነበሩ። ወያኔም በተራው ባህታዊውንና ምዕመናንን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በጸሎት ላይ የነበሩትን ገድሏል። በወያኔና በደርግ መካከል ሃይማኖትን በተመለከተ አንድ ወጥ ናቸው። ልዩነታቸው ደርግ አስሮ ሲገድል፤ ወያኔ ደግሞ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ መግደልና እንዲሰደዱ ማድረጉ ነው። በፀረ ሃይማኖት ግን አይተናነስም።

## የደርግ ጠንካራ ጎን በተመልካች

ደርግ በአስተዳደር ዘመኑ የሠራውን በጆሮዬ ከመስማት በቀር በአይኔ አላየሁም። ይሁን እንጂ ሻለቃ ለማ ገብረ ጻድቅ የጹሮ ክብር ዘበኛ ባልደረባ የነበሩ ወደ አውራ ጎዳና ተዛውረው የመንገዶች አስተዳደር ኃላፊ ሁነው ሢሠሩ በየክፍለ አገሩ እየተዘዋወሩ በዐይናቸው የአዩትን የአብዮቱን የግንባታ ሥራዎች በጽሑፍ አረጋግጠውልኛል።

ሻለቃ ለማ "እንደ ኑዛዜ አንድ ነገር ልናገር ቢያምኑም ባያምኑም የኢትዮጵያ ሕዝብ ዓይኑን የከፍተው በደርግ የ17 ዓመት የአስተዳደር ዘምን ነው እላለሁ። ይህንንም የምለው ቀደም ብሎ የነበረውን ሁናቴና በኋላ በደርግ ግዜ የተፈጸመውን ስለ ተከታተልኩ ነው፡" በማለት በጽሑፋቸው ሲያብራሩ "ለዚህም የተሠሩትን እጅግ ረጅም የገጠር መንገድ ሥራዎች ክሊኒኮች የመንግሥት የእርሻ ልማቶች የመሠረት ትምህርት ቤቶች በገጠር የተሠሩ ጎተራዎች የንጹህ ውኃ ጉድጓድ ቁፈራዎች የከተሞች ዕድገት ለምሳሌ እንደ ነቀምቴ ደብረ ማርቆስ ባሌ ጎባ የአውሮፕላን ማረፊያዎች የባሕር ዳር በኢንተርናሺናል ደረጃ የተሠራውና የአሰብ በኢንተርናሺናል ደረጃ የተሠራውን መጥቀስ ይቻላል።እንዲሁም ጋምቤላ ከተማውን የሚያዋስነው ትልቁ የባሮን ወንዝ ላይ የተሠራው ድልድይ የኤሌትሪክ ማመንጫዎች በዋቢ ሸበሌ ወንዝ ላይ የተሠራው የመልካ ዋከና ትልቁ የኤሌትሪክ ማመንጫ ጣቢያ እስካሁን ከተሠሩት ሁሉ የበለጠ ነው። ፍፃሜ ሳያገኝ የቀረው የግልገል ግቤ ኤሌትሪክ ማመንጫ ጣቢያ ነው።

ከሁሉም በይበልጥ ታላቅ ሥራ ሁኖ የሚታየው የገጠር መንገዶች በሠፊው መዘርጋት ሲሆን በተከታታይ የመሠረተ ትምህርትና የገጠር ሠፈራን ማስፋፋት ለሕዝብ ታላቅ ጠቀሜታ የሰጠ ነበር። ለምሳሌ በውሎ ክፍለ አገር 12ቱም አውራጃዎች መንገድ እንደተሠራላቸዉ ተገልጿል። በልማት በኩል ደርግ የማይናቁ ሥራዎችን መሥራቱ ተነግሮለታል።

## ምዕራፍ 18
## የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ)
## የትግል ጎዳና

ምንም እንኳ ቀደም ብሎ ሕቡአዊ እንቅስቃሴዎችም ቢኖሩም ኢሕአፓ ተመዞ የወጣ በአብዮቱ ማግስት ነው። አብቶተኞች ሁኔታዎችን አይፈጥሩም ሁኔታዎችን የሚፈጥር ነባራዊ ሁኔታው ነው። ችግር ኮሙዩኒዝምን መፍጠሩ አዎንታዊ እንደሆነ እንዲሁም የአገሪቱ ፖለቲካዊ ኤኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ምስቅልቅሎችና ቀውሶች የነቁ አገር ወዳድ ኃይሎችን ወደ አብዮቱ ገፋቸው። የኢሐፓም አፈጣጠር ከዚሁ አንፃር ችግር የወለደው ነው። የኢሕአፓም አፈጣጠር እውነተኛ ኢትዮጵያዊ ሁኖ ነው።

የኢሕአፓ አነሳስ ከአገሪቱ ውጥረት አኳያ ሲሆን ይዞት የተነሳው ዓላማ ዓለም አቀፋዊ ርዕዮት ይሁን እንጂ ለአገራዊ ልዕልና ቅድሚያ የሰጠ ነበር። ለዚህም ማረጋገጫው ተጋዳይ ኃይሎችን በአገር ወዳድነት ማነጹና ሕዝብ ለመብቱ እንዲታገል መቀስቀሱ ነው።

ኢሕአፓ የቅርብና የሩቅ ግቦችን አቅዶ ሲነሳ ሊሠራቸው ያሰበው በቅርብ ግቡ ቀውሶችን በማስወገድ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ማስፈን ሲሆን የሩቅ ግቡ ደግሞ በእኩልነት ሥርዓት ላይ በተመሠረተ ሕዝባዊ መንግሥት አገር አቀፋዊ ልማትን ማሳደግ ሳይንስና ቴክኖሎጅ ማራመድ የመሳሰሉ እንደ ነበሩ በልሳኖቹ ገልጾታል።

ኢሕአፓ በአገር ውስጥ በጠባብ ብሔርተኞች በውጭ አገር በካፒታሊዝም ተፃራሪ የበዛበት ለሕዝብ መብትና ለአገር ሉዓላዊነት ሐቀኛ ሁኖ በመቆሙ ነው። የአገር ውስጥ ተፃራሪዎቹ ከአገር ይልቅ እራሳቸውን በሚያስቀድሙ ሥልጣን አፈንፋኞች ሲሆን በውጭ በኢምፔሪያሊስት አገሮች ደግሞ አገር ወዳድ በመሆኑ ነው። ኢምፔሪያሊስትና ወራሪ ኃይሎች የሚፈሩት ቢኖር አገር ወዳድን ነው። ምክንያቱም አገር ወዳድ ለማንም አይንበረከክም። የአገሩን ክብር አያስረግጥም። የአገሪቱን ሃብት አያስነካም። ኢምፔሪያሊስቶች ዓለም አቀፋዊ ርዕዮት የያዙውን ኮምኒዝምን አሻግሮ በሠፊው የሚያየው ቢሆንም ያገር ወዳድን ያህል ፈጽሞ አይፈሩትም። ማርኪስዝምንና አገር ወዳድነትን አጣምሮ የያዘማ ብርቱ ጠላታቸው ነው። ቡድኖች ቢተባበሩበት መንፈሱን አጠንክረው እንጂ አላላላውም። የኢሕአፓ አባላት በትግሉ ፀንተው የቆሙትም ሆኑ ለግዜው ገለል ያሉት ኢትዮጵያ በነሣ ተበጣጥሣ ክብሯ ተደፍሮ ሉዓላዊነቷን አጥታ ሕዝብ በዘር ተከፋፍሎ በቋንቋ ተራርቆ ማዬት የማይፈልጉ ናቸው። ኢሕአፓ ከምንም ነገር በላይና በበለጠ አገር ወዳድ ለመሆኑ በቅርብ ሁኜ ለመገንዘብ በቅቻለሁ።



የአገር መቆራረስ የሚያንገበግበው ኢሕአፓ ትላልቅ አይኖቹ በሠፊው አርቀው የሚያዩ ሠፋፊ ጆሮዎቹ ብዙ መስማት የሚችሉማናቸውንም የመንግሥት መሥርያ ቤቶች ድርጅቶች የሚተነፍሱትን የሚጠልፉ አንቴናዎች ነበሩት። በቢሮ ክራሲውና በሠራተኛው ማኅበር የሚያገናኙ ሳተላይቶች ነበሯቸው። ወደፊትም ይኖራሉ።

በድንገት የተከሰተው ማርክሲዝምና ሌሊኒዝም በአፍሪካ እንደቋያ እሳት ተቀጣጥሎ በነፃነትና በእኩልነት ላይ አንፀባራቂ ቴዎሪ የወጣቱን ጭንቅላት እንዳለ ውጦት ነበር። ወጣቶች በወላጆቻቸው ማፈር ብቻ ሳይሆን አብዮታዊ ርምጃ እንዲወሰድባቸውም ሚስጢራዊ ሰነዶች አሾልከው ያወጡባቸው ነበር። ወጣቶች አድኃሪ እንዳይባሉ ወላጆቻቸውን የነበራቸው የክብር ማዕረግ እንዲታወቅባቸው አይፈልጉም ነበር። የደጃዝማች የፊታውራሪ ወይም የሚኒስትር ልጅ መሆን የፊውዳል ልጅ ስለሚያሰኝ ያፍሩባቸው ነበር።

ወጣቶች የራሳቸው አገር በቀል የሆነውን የማዕረግ ስም እንዲጠሉ ያደረጉ የኢትዮጵያን ባሕል ወግና ሥርዓትን ሆን ብለው ለማጥፋት የዘመቱ ናቸው ለማለት ባይቻልም በተግባር የታየው ግን አብዛኛዎቹ ማርክሳዊ ቴዎሪ ጉዳትና ጥቅሙን ለይተው ጉድፉን ከጥራቱ አበጥረው አንጓለው አውቀው በፍጹማዊነት ተዋሕዷቸው ቢሆን ኑሮ ቀደም ብሎ ይሰጥ የነበረው ማዕረግ ለአገሩ ነፃነት ለታገለ ጀግና የሚሰጥ መሆኑን ዐውቀው ይኮሩበት ነበር። ለአገሩ አገልግሎ ማዕረግ የተሰጠው ሁሉ ጎታች አድኃሪ በሚባልበት ወቅት የተወናበዱ ወጣቶች ብቻ አልነበሩም። ታሪክ ይቅርታ ሊያደርግላቸው የማይገባ በዕድሜ የገፉ በመዓረግ የላቁ በከፍተኛ ሥልጣን ላይ የነበሩ ሁለት ፊታውራሪዎች አቶ በሉን ሲሉ ከልዑሎችም ታጋይ በሉኝ ያሉም ነበሩ።

በዚያን ወቅት ሰነፉ ጥሪት የለሹ በጎዳና አዳሪው የቀን ሞያተኛ የሌሊት ሰባሪው የአብዮቱ ታማኝ ተራማጅ እየተባለ ከችሎታው በላይ በከፍተኛ የሥራ ቦታ በኃላፊነት ሲመደብ አንገት የምታስገባ ቅልስ ጎጆ ያላቸው በዝባዥ ጨቋኝ እየተባለ ኃላፊነት ያለው ሥራ አይሰጠውም ነበር። ደርግ ራሱ ያብዮቱ ወገኖች ከሚላቸው ዱርዬዎች የተሻለ ዕውቀት አልነበረውም።

የኢሕአፓ ምልምሎች የመሬት ላራሹን መፈክር ይዘው ቢሰለፉም ደርግ ጨቋኝና በዝባዥ እያለ ያለ ልዩነት የድሆችን ቤት ጭምር መውረሱን ኢሕአፓ በልሳኑ ተቃውሞታል። ኢሕአፓ የደርግን ቶክራና ድንፋታም ከየዋህ ፖለቲከኛነት ማለት ከቂልነት ቆጥሮት ነበር። ምክንያቱም በመግደልና በማስቃየት በፕሮፓጋንዳ ማዕበል ኢሕአፓን ለማስጠም ያደረገው አረመኔአዊ ጭፍጨፋ በርዕየተ ዓለም አምኖ የተጠመቀን ሊያንበረክክ መሞከሩ በጭፍን ተጓዘ መሆኑን ያሳይ ስለ ነበር ነው።

በኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ) ተመልምለው የገቡ ወጣቶች ከምንም በላይ ከድርጅታቸው መመርያ

ውጭ እንዳያዩ አድርጓቸው ነበር። የድርጅቱን መመሪያ ተከትለው በትጋት ሌት ተቀን ያለ እረፍት በመሥራታቸው ድርጅቱን ከመጠን በላይ አሳደጉት። አለቃና ጭፍራ ተለይቶ በማይታወቅበት በድርጅት ሰንደቅ ብቻ እየተመሩ በቡድን እየተመካከሩ በጋራ የሚሠሩት ውጤታማ ነበር። ትጋታቸውንና ቆራጥኝነታቸውን ለሚያይ የሚያስቀና ምነው የኢሕአፓ አባል በሆንኩ የሚያሰኝ ሕሊናን ማራኪ ነበር። ዕድሜዬ ባይገፋና የመጣሁበት ማኅበረ ሰብ ባሕል ባይጫነኝ ኑሮ በዚያን ወቅት የኢሕአፓ አባል መሆንን እመርጥ ነበር። ስለዚህም ነው ድጋፌን ያልነፈግኋቸው።

የኢሕአፓ አባላት በጓዳዊ ፍቅር የተሣሠሩ በድርጅቱ ዓላማ የታመኑ "ትግል ነው ሕይወቴ" በሚል መፈክር ትግሉን ከግብ ለማድረስ መሷይት ይደፍሩ ነበር። ፍርሃትንና ጥርጣሬ ማመንታትና ልግመት በሰውነታቸው ውስጥ ሥፍራ አልነበረውም። የሚገርመው አብዮቱ በጋለበት ወቅት ሁሉም አባል መሷይት መድፈሩን በድርጊት መግለጹና መሷይት ለመሆን መሽቀዳደማቸው ነው።

ካድሬው ደርግ በሚቆጣጠረው አካባቢና በከተማ ምንም ዓይነት መከላከያ መሣርያ ሳይዝ ሕዝቡን እየቀሰቀሱ ያደራጁ ነበር። በካድሬው እጅ የሚገኙ በጨለማ ጉዞ በትርና በጠላት የተያዘ እንደሆን ህይወቱን የሚያሳልፍበት የተመረዘ ኪኒን ብቻ ነበር። የጦር መሳርያ ቀርቶ ጩቤና ሰንጢ እንኳ አይዙም ነበር። የዕለት ጉርስ የሚሆን ምግብ ከብርድ የሚከላከል ልብስ ከሾህ የሚከላከል ደጎና ጫማ (አይዙም) አልነበራቸውም።

የኢሕአፓ ቀስቃሺና አደራጅ ካድሬ ይዞ የሚጓዘው ቆራጥነትን ልበ ሙሉነትን ድፍረትን ፅኑዕ ተማኝነትን በጎ ፈቃድን ሰብአዊ እኩልነትን ፍቅርንና ወንድማማችነትን የመሳሰሉትን ብቻ ነበር። ለወዳጆቹ ለወላጆቹና ለግሌ የሚለው አልነበረውም። የኢሕአፓ የቅስቀሳና ያደራጅ ክፍሎች ከከተማ ወደ ከተማ ከወረዳ ወደ ወረዳ ከቀበሌ ወደ ቀበሌ በእግራቸው እየተጓዙ ስለሚያደራጁና ስለሚቀሰቅሱ ልብሳቸውን የሚያጥቡበት ግዜ አልነበራቸውም።
ንብ ማርን እንዲከብ ቅማልም በሰውነታቸው ላይ ሰፍሮ ሲመጠምጣቸው "ለስዕለት የሰጡት ገላ አያምም" እንደሚባለው አይሰማቸውም ነበር። የሞት መራራነት የማያስጨንቃቸው፤ ሁል ግዜ ራዕያቸው በሕሊናዊ መነጽር የሚያዩት ሕዝቡ ከጉስቁልና ኑሮው ተላቆ በእኩልነትና በወንድማማችነት በፍቅር ተሣሥሮ አእምሮው በእውቀት ኑሮው በሃብት በልጽጎ በሣይንስና ቴክኖሎጅ ተራምዶ ለማየት እንጂ ለራሳቸው ግላዊ ኑሮ ሃሳብ ፈጽሞ አልነበራቸውም። ይህ ያለ ምንም ተጋኖ በዓይኔ ያየሁት ነው።ሕያው ምሥክርነቴን ነው የምሰጠው።

ኢሕአፓ ማርክሲዝምንና ሌኒንዝምን እንደ ውኃ ግቶ በአገር ፍቅር ስለ አነፃቸው ፍልስፍናውን ተግባራዊ ለማድረግ ያሳዩት የነበረው ጥረት ከፍተኛ የመሳብ ኃይል ነበረው። ስለዚህም ነው ኢሕአፓ በወቅቱ የሕዝብ ድጋፍ አግኝቶ አገር አቀፍ እንቅስቃሴ ለማድረግ



አስችሎት የነበረው።

ከኢሕአፓ አባሎች አንዳንዶቹ ሁኔታው አስገድዶአቸው "ትግል ነው ሕይወቴ" ከሚለው መፈክር ማለት ከትግል ሜዳው ግዚያዊ ማፈግፈግ ቢያደርጉም ድርጅታዊና ጓዳዊ ፍቅር አልተለያቸውም። በዓመት አንድ ቀን የግንኙነት ምሽት አድርገው ድርጅታቸውን ያስታውሳሉ። "እምነት እስከ ሞት" ያሉ ቆራጦችም ትዳር ሣያምራቸው የግል ኑሮ ሳያቸንፉቸው የድርጅቱን ሕልውና ጠብቀው 27 ዓመት በተለያዩ የትግል ፈርጅ በመታገል ላይ ይገኛሉ።

ኢሕአፓ ለምን ተዳከመ የሚል ታሪካዊ ጥያቄዎችም መነሳታቸው አልቀረም። እኔ በቅርብ ሁኜ እንደተመለከትኩት፤ ኢሕአፓ ለኢትዮጵያ አንድነትና ሉዓላዊነት በመቆሙ በአገር ውስጥ ተገንጣይ ኀጠኞች በውጭ አገር ተስፋፊ ኢምፔሪያሊስቶች የተለያዩ አሻጥሮች አካሄደውበታል። ኢምፔሪያሊስት ኃይሎች ታሪክ ያለውንና በራሱ የሚመካ ሕዝብ ለብዝበዛ ስለማይመቻቸው ለአገር ሉዓላዊነት የቆመ ኢሕአፓን በተዘዋዋሪ መንገድ አዳከመውታል። በአገር ውስጥም ኋላ ቀር (ጠባብ) ኀጠኞችም የመገንጠል አላማቸውን ኢሕአፓ በብርቱ ስለሚቃወመው በድርጅቱ ውስጥ ሠርገው እየገቡ ብዙ ደባዎች አድርገውበታል።

* እንደ ኢሕአፓ ያለ ዴሞክራሲያዊ ድርጅት ያልተፈራ ማን ይፈራ?
* እንደ ኢሕአፓ ያለ ለዓላማው መሷይት ደፋሪ ያልተፈራ ማን ይፈራል?
* እንደ ኢሕአፓ ያለ ችግር አይበገሬ ያልተፈራ ማን ይፈራ?
* እንደ ኢሕአፓ ያለ በሕይወቱ ላይ የሞት ብይን ሰጭ ያልተፈራ ማን ይፈራ?
* እንደ ኢሕአፓ ያለ ሕብረ ብሔር ድርጅት ያልተፈራ ማን ይፈራ?
* እንደ ኢሕአፓ ያለ የሁሉንም ጉሳና የሁሉንም ሃይማኖት ተከታይ ያሠለፈ ያልተፈራ ምን ይፈራል?

*እንደ ኢሕአፓ ያለ ከወጣቱ እስከ ሽማግሌና ባልቴት ያሰለፈ ሁሉንም የሙያ ማኅበራት አርሶ አደሩን ያቀፈ የምሁራንን ኃይል ያሰባሰበና የሩቅ ዓላማ ያለው ያልተፈራ ማን ይፈራ ?

ኢሕአፓ እንደ ጠባብ ብሔርተኞች በንቃቱ ላይ ያልተኛ ነው። ድርጅቱም ይሁን አባላቱ ንቃታቸውን ያልገደቡ በመሆናቸው ግዜም ቢወስድ በኀጠኞች ላይ ተራምደው የሚያልፉ መሆናቸው የታመነና የተረጋገጠ ነው።

ኢሕአፓ ሠፊ ታሪክ ያለው በመሆኑ ገለልተኛ የሆኑ ሐቀኛ የታሪክ ሰዎች ወደፊት በዝርዝር ጽፈው እንደሚያወጡት ተስፋ አደርጋለሁ። ከዚህ ላይ አልፎ አልፎ የነካካሁት አንዳንድ ነገሮችን ለማውሳት ብዬ ነው። ከስንዴ መካከል እንክርዳድ እንደሚገኝ እንዲሁም ከኢሕአፓ አባሎችም ውስጥ ከቀን በኋላ አንዳንድ በዓይናቸው ላይ ውርግርግ/Cataract/ ያደረባቸው ጠባብ ብሔርተኞች ያጠመዱት መሰናክል እየጠለፈ የጣላቸው ቢኖሩም ተሰናክለው አይቀሩም።

"ባለ ሰፌ ሱሪ ጀግና እየተጎዳ
ባለ ጠባብ ሱሪ ሎሌውማ ከዳ
ቀድሞም ጋሻ ጃግሬ
ዛሬም ሆዱን ይሙላ እየሆነ ባንዳ"።

እንደተባለው የኢሕአፓ አባሎች ከነበሩት ውስጥ አንዳንድ ግለሰቦች ከፈጸሟቸው ስህተቶች ያየኋቸውን አንዳንዶችን ከራሴ የትግል መስመር ጋር የተያያዙትን መጥቀስ አስፈላጊ ነው። ኢሕአፓ ከፍ ብዬ እንደገለጽሁት ችግር ለማስወገድ የተፈጠረ ድርጅት በመሆኑ በግዜው ተከስቶ የነበረውን የደርግ ኢሰብአዊ ድርጊት በከተማም ሆነ በገጠሩ ተቋቁሞ ነበር። ብዙ መሿይትም ከፍሏል።

ድርጅቱ በራሱ አባሎች መካከል የአሠራር ችግሮችና የመስመር ልዩነቶች ቢኖሩበትም ለኢትዮጵያ ሉዓላዊነትና ለሕዝቡም ዴሞክራሲያዊ መብት መሿይት እየከፈለ መታገሉን አላቆመም።

እኔና ኮሎኔል እምሩ ሕዝባዊውን የኢትዮጵያን አገር ወዳዶች ዴሞክራሲያዊ ድርጅት እስከናቋቁም እስከ 1970 ዓ.ም. መጨረሻ የደርግን ግፋዊ ድርጊት በመቋቋም የሚያደርጉትን ትግል እንደግፋቸው ነበር። ደርግ እንዳበደ ውሻ ያለ ልዩነት የመደዳ ጭፍጨፋ በሚያካሔድበት ወቅት ኢሕአፓን ከመደገፍ በስተቀር ሌላ አማራጭ አልነበረውም።

የኢሕአፓ ያመራር አካላት የገጠርን የትጥቅ ትግልን በሚደግፉና የከተማን የትጥቅ ትግል በሚደግፉት መካከል ልዩነትና መከፋፈልን ፈጠረ። የከተማን የትጥቅ ትግልን በዋናንት የሚቃወሙ ጌታቸው ማሩና ብርሃነ መስቀል ረዳ ነበሩ። ይኸው አዲስ አበባ ውስጥ የተነሳው ችግር ወደ ገጠር ተዛምቶ አሲምባ የትጥቅ ትግል በሚያካሒዱት የአመራር አባት ላይ ችግር ፈጥሮ ነበር።

በዴሞክራሲ ሥርዓት መሠረት ችግራቸውን በመድረክ ተወያይተው ከመፍታት ይልቅ ሥራቸውን ትተው ቤተሰቦቻቸውን በትነው ሕይወታቸውን ለሠፊው ሕዝብ ጥቅም ለመታገል በፈቃዳቸው የተሠለፉት ፀሎተ ሕዝቅኤልና ይርጋ ተሰማ አንጃ ተብለው በመገደላቸው ፍትሕአዊ ባለመሆኑ በአባላቱ መካከል መጠራጠርና አለመተማመን ተከስቶ ድርጅቱን ጎድቶታል። ያን በመሰለ ድርጅታዊና ጓዳዊ ፍቅር መካከል ቀዝቃዛ ውኃ ቸልሰውበታል። ድርጅቱ በሻዕቢያና ወያኔ በተገንጣዮች መካከል ሁኖ ለመታገል አመች ባለ መሆኑ አሲምባን ለቆ ወደ ጎንደር ተዛወረ።

ኢሕአፓ ለወታደራዊ ስትራቴጂ አመች በሆነው በጎንደር ምዕራብና ሰሜን ከበለሳ እስከ ቋራ በጎንደር በሊቦ በሰሜን በወገራ በጭልጋ በአምስቱ አውራጃዎች ሕዝብ አቅፎት የሕዝብ ጦር ደግፎት ያለ ምንም ተጽዕኖ ሠራዊቱ እየተንቀሳቀሰ የደርግን ጦር ለማዋከብ የቻለው. ዘውዱ በላይ (ታደለ) ጎንደርና ጎጃም ባዋቀረው የካድሬ ኃላፊዎች እነ ሐቢቡ ታከለ (መሐባው) እነ አምሐ ተፈራ ( ደማስ)፡ እነ ሙሉ ደምሌ ( ታዬ በለሳ)፡ እነ ዳኘው ዓለሙ (ተሰማ) እነ ጥላሁን



( ማኦ) እነ መለስ (አዝመራው)፡ እነ ተስፋሁን (አያ እጅጉ)፡ እነ ኢያሱ አስካል (ብርሃኔ)፡ እነ ቄስ ፈንቴ እነ አገኘሁ ጥላሁን ወ. ዘ. ተ. ካድሬዎችን በየ ደብሩ በየጎጡና ታዋቂ ወደሆኑ ግለ ሰቦች እየላኩ ሕዝቡን ቀስቅሰውና አንቅተው ስለ አደራጁት ነበር።

የኢሕአፓ ሠራዊት የተፈጥሮ መከላከያ ባለው ለሺምቅ ውጊያ እጅግ አመቺ በሆነው ምድር ላይ ያለምንም ተጽዕኖ በመንቀሳቀስ ላይ እንዳለ በድርጅቱ ላይ ሰርጎገብ ሰላዮች መርዝ አፍስሰውበት መበጣጠስ ጀመረ። በለሳ ውስጥ ከነበሩት ታጋይ ኃይሎች ሰላሳ ያህሉ ከድተው ትግራይን ሊገነጥል ወደ እሚዋጋው የትግራይ ሕዝብ ነፃ አውጭ ግንባር/TPLF/ወያኔ ሒደው ገቡ። ወደ ማህል አገር ለመግባት ተስኖት የነበረው ወያኔም የኢትዮጵያ ሕዝብ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ (ኢሕዴን) ብሎ ሰይሞ በመሣርያነት ተጠቀመባቸው። ከነርሱ የተረፉት እጃችን ለገንጣይ ወያኔ አንሰጥም ያሉ ወደ ጎንደር ከተማና ወደ ደሴ እየሔዱ እጃቸውን ለደርግ ሰጡ " እምነት እስከ ሞት " ያሉ በአቋማቸው ጸንተው የድርጅታቸውን አርማ ተሸክመው ትግላቸውን እስከ ዛሬ እንደቀጠሉ ናቸው።

የኢሕአፓ አመራር በጎንደር ክፍለ አገር ሠራዊቱ የሚንቀሳቀስበትን አካባቢ በሬጅን ከፋፍሎ ሠራዊቱም በሻለቃ በኃይል በጋንታ ደልድሎና በማዕከላዊ እዝ እንዲመራ አድርጎ የሺምቅ ውጊያውን ቀጠለ። የጭልጋና የጎንደር አውራጃዎችን ሬጂን ሁለት ብለው ሰይመው በአንድ ዕዝ መምሪያ 6 ኃይሎች ነበሩት እነዚሁ ኃይሎች እየተከፋፈሉ በደርግ ሠራዊት ላይ አደጋ እየጣሉ ያዋክቡት ነበር። ያአካባቢው ሕዝብ ሠራዊትም አብሮአቸው እየተንቀሳቀሰ በውጊያ ብዙ መስዋዕትነት ከፍሎአል።ምንም እንኳ የኢሕአፓ ሠራዊት ከሕዝብ ምንም ነገር ባይፈልግም ሕዝቡ በፈቃዱ አንዳንድ ግዜ በምግብ ይረዳ ነበር።

ይሁን እንጂ ጤናማውን ድርጅት ሰርጎገብ ሰላዮች ስለ በከሉትና ስም የለበሱ ጉሰኞች ተስፋ የቆረጡ ወላዋዮችና ሳይታወቁ ውስጥ ለውስጥ አሻጥር ያደርጉ ስለነበር ከአባላቱ ውስጥ አንድ ሁለት እያሉ አንዳንዱ በሕጋዊ መንገድ እየተሰናበተ ሌላውም እየጠፋ በመሔድ የሬጅን ሁለት ሠራዊት እየተመናመነ ሔደ።

በመጨረሻም ሁኔታው አስከፊ ገጽታ እየያዘ በመሔዱ በጭልጋና አርማ ጭሆ ይንቀሳቀሱ የነበሩ ኃይሎች ወደ ሱዳን ጠረፍ ቀረብ ብለን ሰሚናር እናድርግ ብለው በማኅበረ ሥላሴ ማጠቢያ ወረዳ እስከኒት ከተባለው ቦታ ተሰባስበው ከተወያዩ በኋላ መሣርያችንን ቀብረን ሱዳን ውስጥ ተወያይተንና ተጠናክረን እንመለሳለን በሚል ሃሳብ ተስማምተው መሳርያውን ቀባሪ ቡድን ሰይመው መሣርያውን መሬት ቆፍረው ቀብረው ሁሉም ተጠቃለው ሱዳን ውስጥ መግባታቸውን ሊሰሙት የማይገባ አሳዛኝ መርዶ ነበር።

እኔ በዚያን ግዜ ሕዝባዊውን ጦር በማደራጀት አርማ ጭሆ ውስጥ ስለ ነበርኩ በሬጂን 2 ይንቀሳቀስ የነበረው የኢሕአፓ ሠራዊት መሳርያውን ቀብሮ ወደ ሱዳን ሔዷል የሚል አሳዛኝ ያልጠበቅሁት

ወሬ ስለሰማሁ በሁኔታው አዝኜ ቢቻል መክሬ ወደ ትግል ሜዳ እንዲመለሱ ባይቻል የቀበሩትን የጦር መሣርያ አጋልጠውት ለሔዱት ሕዝብ መከላከያ ይሆን ዘንድ ለአገር ወዳድ ታጋዮች እንዲሰጥ ለመጠየቅ ወደ ሱዳን ሔድኩ።

ሱዳን ገዳሪፍ እንደደረስኩ የኢሕአፓ የመዕከላዊ ኮሚቴ 4 አባላት ሳሙኤል አለማየሁ ( በላይ ) እያሱ አለማየሁ (ካሣሁን) ዘውዱ በላይ (ታደለን) ዮናስ አድማሱ (አድማሱ) አግኝቼ በጉዳዩ ተነጋገርን። ታጋዩ ወደ ትግል ሜዳ የሚመለስ አይመስልም መሣርያውን ለአገር ወዳድ ለመስጠት ፈቃደኞች ከሆኑ ጠይቃቸው በእኛ በኩል ግን ለአገር ወዳድ ቢሰጥ አንቃወምም። ወልቃይት ውስጥ ያለው የኢሕአፓ ሠራዊትም በቅርብ ቀን ወደ አርማጭሆ ይመጣልና መረዳዳት ይቻላል ስለ አሉኝና የኢትዮጵያ አገር ወዳዶች ዴሞክራሲያዊ ድርጅት አባል የነበሩት ኮሎኔል አለማየሁ አሰፋውንም ከዚያው ስለ አገኘኋቸው መሣርያው ለአገር ወዳድ ታጋዮች እንዲሰጥ ታጋዮችን ጠይቄያቸው ፈቃደኝነታቸውን ገልጸውልኛልና አንተም ጠይቃቸው ብለው በገለጹልኝ መሠረት ተጋዳዩ ወደ ሠፈረበት ዶካ ኡምራኩባ ወደ ተባለው መጠለያ ሠፈር ሔድኩ

በመጠለያውም ሠፈር ካለው ተጋዳይ ወኪሎች ጋር ተገናኝቼ ሕይወት በተከፈለበት መሣርያ እናንተ የማትታገሉ ከሆነ በትግል ላይ ያሉ አገር ወዳድ ታጋዮች እንዲታገሉበት ፍቀድሉን ብዬ ጠየቅኋቸው እነርሱም "በጦር ሜዳ አካላቸው የጎደለ መሥራት የማይችሉ ጓዶችን ተረክባችሁ በኃላፊነት የምትይዙአቸው ከሆነ መሣርያውን እንድትረከቡ በበኩላችን እንስማማለን የሴት ታጋይ ጓዶች ገዳሪፍ ያሉትን ጠይቁ " የሚል መልስ ሰጡኝ።

እኔም ከዑምራኩባ ወደ ገዳርፍ ሔጄ የሪጅን ሁለት ኮሚሳርና የፓርቲው አመራር አባል የነበረውን በትግል ስሙ ይመር ተብሎ የሚጠራውን አድማሱ የተባለውን አግኝቼ የሴት ጓዶችን አገናኘኝና ላነጋግራቸው፤ ዑምራኩባ ያሉት መሣርያው ለአገር ወዳድ እንዲሰጥ ተስማምተዋልና የሴት ጓዶችም ፈቃዳቸውን መጠየቅ አለብኝ አልኩት። እሽም እምቢም ሳይል ጊዜ ስለወሰደብኝ አንተ የሪጅን 2 ዋና ኮሚሣር የፖለቲካው ኮሚቴ አባል ስለሆንክ የተቀረው መሣርያ ለአገር ወዳድ ታጋዮች እንዲሰጥ ፈቃድህ ይሁን ብዬ ብጠይቀው መክሬ መልሱን መስከረም 12 ቀን 1973 ዓ.ም. እነግርሃለሁ ብሎኝ ስንለያይ ቅን አመለካከት አላየሁበትም ነበር።

ይመር (አድማሱ) በቀነ ቀጠሮው መልሱን ሳይሰጠኝ (ከማን ጋር እንደሚመክር አላውቅም) ጥሎኝ ከገዳሪፍ ወደ ካርቱም ሔደ። እኔም እስከ መስከረም 25 ቀን 1973. ዓ.ም. ከተቃጠርንበት ቦታ ጠብቄው ስለ ቀረ (እስከ 1934 ዓ.ም. ድረስ የኢትዮጵያ ግዛት ወደ ነበረችው ዛሬ በሱዳን ቁጥጥር ስር ወደ አለች) ቲያ ተብላ ወደ ምትጠራው ካቶ ወልደ ገብርኤል አስጌ ጋር ሔድኩ።

ይኸው ይመር ተብሎ የሚጠራ አድማሱ ተከታትሎኝ መጥቶ መስከረም 26 ቀን 1973 ዓ.ም አራት የሪጅን አመራር ኮሚቴ



አባላትን ይዞ እንነጋገር ብሎ ጠይቆኝ ፈቃደኛ ሆኜ ውይይት ጀመርን ውይይቱን የከፈተው ይመር (አድማሱ) ነው። እርሶ ኰሎኔል አስናቀ በማለት ንግግሩን ሲጀምር ብዙ የትግል ታሪክ ያለዎት አሁንም በትግል ላይ ያሉ ነዎት የተሰባበረ የማይረባ የተቀበረ መሣርያ ሊያወጡ መምጣትዎን ከተረጋገጠ ምንጭ ሰምቻለሁና ታሪክዎ እንዳይበላሺ እባክዎን የተቀበረውን መሣርያ እንዳያወጡ አለኝ።

እኔም እንዲህ ብዬ መለስኩለት ወደ ቲያ የመጣሁት ዘመድ ለመጠየቅ ነው። የተቀበረ መሣርያ ላወጣ አልመጣሁም። መሣርያውን እንድታስረክቡን በሕጋዊ መንገድ ጠይቀናችኋል። ተጋዳዩም መሣርያው ለአገር ወዳድ እንዲሰጥ ተስማምቷል፤ አንተም እንድትስማማ ጠይቄህ መልሱን መስከረም 12. ቀን 1973.ዓ.ም. መክሬ እነግርሃለሁ ባልክበት ቀን መልሱን ሳትነግረኝ ወደ ካርቱም ሔድህ። እኔም ተስፋ ቆርጬ ዘመድ ለመጠየቅ ወደ ዚህ መጥቼአለሁ። የሆነ ሆኖ የእኔ ታሪክ ለሕዝብ በማገልገሌ አይጠፋም። ይልቁንም እናንተ ሕይወታችሁን ያሰጋዋል። የጦር መሣርያውን ለመውሰድ የፈለገ አደጋ ሊያደር ስባችሁ ይችላል። በዚህ ላይ መሣርያው በአደገኛ ሁኔታ ላይ ይገኛል። አሁን በጋው እየተቃረበ ነው። ሣሩ ሲቃጠል መሣርያውን ደርግ ወይም ሱዳን ከእነርሱም ቢያመልጥ ሺፍታ ሊወስደው ይችላልና ከመወሰዱ በፊት በትግል ላይ ላሉ ለአገር ወዳድ ታጋዮች እንዲሰጥ ብታደርጉ ይሻላል የሚል መልስ ሰጥቻቸው ተለያየን።

ወዲያውኑ የጠረፍ ጠባቂ ወደ ሆነው የሱዳን መኮንን በይመር (አድማሱ) መሪነት ሒደው ኮሎኔል አስናቀ የተቀበረውን የኢሕአፓን መሣርያ ሊያወጣ መጥቷልና እሱን ብታስርልን ከቀበርነው ጠብመንጃ እንሰጠሃለን ብለው ቃል የገቡለት ይመስላል፡ የሱዳኑ መኮንን እኔንና አብሮኝ የነበረውን ወልደ ገብርኤልን በወታደር እንድንጠበቅ አድርጎ እነ ይመርን በመኪና አሳፍሮ መሣርያው ወደ ተደበቀበት ሲሔድ መንዶካ ከተባለው ከኢትዮጵያ ግዛት ውስጥ ሲደርስ የያዘው መኪና በመሰናከሉ የሱዳኑ መኮንን መሳርያው ከተቀበረበት ቦታ እስከኔት ሳይደርስ የደርግ ጦር መጣብህ ሲሉት ጣጥሏቸው ነፍሴን አውጪኝ ብሎ ወደ ጦር ሠፈሩ ሲመለስ ይመርና ተባባሪዎቹ የሱዳን ዋና ጦር ወደ አለበት ባሶንዳን አልፈው ሔደው በማመልከት የኢሕአፓ ቆራጥ ታጋዮች ተሰውተው የተገኘውን መሣርያ በነሱ መሪነት ሱዳን ከተቀበረበት ከኢትዮጵያ ግዛት ገብቶ አውጥቶ እንዲወስደው አደረጉ።

እኔ ሃያ ቀን ያህል በሱዳን ጦር ሠፈር ከታሰርኩ በኋላ ካርቱም የነበሩ ወንድሞቻችን ለሱዳን ባለሥልጣኖች አመልክተው ተፈታሁ። አቶ ወልደ ገብኤል አስጌ 25 ቀን ያህል ታስሮ ተለቀቀ። እነ ይመርም ሳይቀበር በእጃቸው የነበረውን ክላሺን ኮቭ ጠመንጃ በሦስት መቶ በአራት መቶ ብር ሸጠው በገዳሪፍ አድርገው ወደ ዋናው ከተማ ካርቱም ተሰባሰበው ሔዱ። ያን የሰው ሕይወት የተለወጠበትን መሣርያ ለሱዳን እንዲሰጥ ያደረገ ዋናው አቀነባባሪ ይመር (አድማሱ) ነበር። ሌሎቹ አሊጋዝ (ወሰኑ) ዮሴፍ (ቴዎድሮስ) ላብ አደር ይባል የነበረው

ደረጀ (ገንቱ) እና ገብሬ ጭላድ (ባዩ ካሣ) የተባሉት መናጆች ነበሩ።

ይኸው የሪጅን 2 አመራር ኮሚቴ እንደ አውሮጳ አቆጣጠር በ14 - 10 - 80.ዓ.ም. በአወጣው መግለጫ "የኢሕአፓ የበላይ አካል በሌብነት ንብረቱን በእጁ ለማስገባት ኮሎኔል አስናቀ እንግዳን በአቀናባባሪነት አንድ የቀባሪ ቡድን አካል ጠቋሚነት ንብረቱ እንዲሰረቅ ይወስናል" ይልና ሲቀጥል "መሣርያውና ጥይቱ ወልቃይትና አርማ ጭሆ ቢገባም እንደተለመደው ለከብት መንጃና ለሰው ሕይወት ማጥፊያ የሚውል ካልሆነ በስተቀር በአሁኑ ወቅት ለትግል የሚውልበት ሁኔታ እንደሌለ ይመለከታል" ይላል።

ጽሑፋቸውን ሲያራዝሙ " በዚያን ወቅት አማራጭ ባለመኖሩ ለሱዳን ማስረከብ ግድ ነበር ይልና መሣርያው በየዓይነቱ በጉድጓዶች ውስጥ ተቀብረው የነበሩ ንብረቶች የሱዳን መንግሥት ሊረከባቸው ችሏል" ይላል። የሌባ ዐይነ ደረቅ መልሶ ልብ ያወልቅ ሆነና ነገሩ የትናንቱ ኮምዩኒስት የዛሬው ዘረኛ ይመር (አድማሱ) ምርጥ አገር ወዳድ የኢትዮጵያውያን ሕይወት ያለፈበትን በትግል ላይ ለነበሩ ለጎንደር አገር ወዳድ ታጋዮች ከመስጠት ይልቅ ለባዕድ መንግሥት አሣልፎ መስጠት ምርጫው ሁኖ እኔን አሳስሮ ለምኖ አስረክቦ ተገደድሁ ይላል። ይመር (አድማሱ) አብሮት ሲታገል የነበረውን የጎንደር ታጋይ ለመጉዳት ያደረገው ሻጥር በመሆኑ በጦር ወንጀለኛነት የሚያስጠይቀው ነው። የመሣርያውን ዋጋም እንዲከፍል ሊገደድ ይገባዋል።

ከሁሉም የሚያሳዝነው እያበላና እያጠጣ አብሮ የተዋጋን ቤት ንብረቱ የተቃጠለበትን ሕዝብ መካድና እኛ ስንወድቅ መሣርያችንን አንስታችሁ ትታገሉበታላችሁ እያሉ የተናገሩትን ቃል መብላታቸው ብቻ ሳይሆን ከዚያ ለሰው ልጆች መብት ለፍትሕና ርትዕ ከታገለ ድርጅት ከኢሕአፓ ውስጥ መብቀላቸውና ከድርጅቱ ውስጥ ነበሩ መባሉ ነው።

ይመር/አድማሱ እና ኩባንያው የግለ ሰብ ሳይሆን የአገር ጠላቶች አሳፋሪ ጉዶች ስለሆኑ ማንም ኢትዮጵያዊ በጦር ወንጀለናነት ከሶ በሕዝብ ሸንጎ ሊያቀርባቸው ይገባል። ለጻፉት መግለጫ የሰጠሁት መልስ አባሪውን ይመልከቱ።

ከአዲስ አበባ ወደ አሲምባ ካሲምባ ወደ ጎንደር የተላለፈው በሺታ በአመራር አባላት መካከል እያከታተለ ያመጣው ልዩነት የፈጠረው ችግር ግለ ሰቦችን ለመበቀል አንዳንድ ያመራር አባሎች ሠራዊቱን ለመበተን በሕቡዕ ውስጥ ውስጡን የብተና ቅስቀሳ አድርገው የታጋዩን ቅስም ስለሠበሩት ተጋዳዩ ተስፋ በመቁረጥ አንዳንዱ በሕጋዊ ምንገድ እየተሰናበተ ሲሔድ ሌላው በፈቃዱ ወደ አሜሪካና ወደ አመቸው አገር ተሰደደ። ጥፋቱ ከአመራሩ እንጂ ከታጋዩ አልነበረም።

በድርጅቱ ውስጥ ሰርገው የገቡ ልዩ ተልዕኮ የነበራቸው በበለሳ ይታገሉ ከነበሩት ኃይሎችና ሕዝብ ከሚያደራጁ ካድሬዎች ውስጥ ሰላሳ ያህሉን አታለው ኢትዮጵያን ለማፈራረስ ለሚታገለው ተገንጣይ ብሔርተኛ " ሕዝባዊ ወያኔ ሓርነት ትግራይ (TPLF)" ገጸ በረከት



በመስጠት ግባቸውን ከመቱ በኋላ አንዳዶቹ ወደ ደርግ ተመልሰው ከፍተኛ ያመራር ቦታ ተሰጥቷቸዋል።

ኢሕአፓ በአውራጃና በቀጠና የተከፋፈለውን ኃይሉን አሰባስቦ ተጠናክሮ ተገንጣዩን ወያኔን ለመውጋት ዓቅዶ በሪጅን ሁለት ጭልጋና አርማ ጭሆ የነበሩትን ኃይሎች ወደ ጠገዴ እንዲጠጉ ጠለምት በለሳና ወልቃይት የነበሩ ኃይሎች ወደ ጠገዴ ተጠግተው በመሰባሰብ በወያኔ ላይ ለመዝመት ከበላይ አመራር የተላለፈውን ውሳኔ በሪጅን ሁለት አመራር መሪዎች እነ ይመር (አድማሱ) እምቢ ብለው ሰሚናር እናደርጋለን በማለት በማኅበረ ሥላሴ አስከኒት ተብሎ ወደ ሚጠራው ወደ ሱዳን ጠረፍ ሠራዊቱን ይዘው በመሔድ እቅዱን አከሸፈዋል።

ከጠረፉ አካባቢ አስካኒት ከደረሱም በኋላ ሰሚናሩን ሱዳን ውስጥ እናደርጋለን የሚል ሰበብ ፈጥረው መሣርያውን በጉድጓድ ውስጥ ቀብረው ሠራዊቱን እየመሩ ሱዳን ውስጥ አስገቡት። ሰሚናሩም ሳይደረግ ቀኑን ቀን እየገደለው ግዜው በከንቱ እያለቀ በመሔዱ ሠራዊቱ ከባድ ችግር ውስጥ በመውደቁ ከሰሚናሩ በኋላ ወደ ትግል ሜዳ ተመልሶ ለመታገል ቆርጦ የነበረው ሁሉ ሁኔታው እየተጣበበበት ከችግር ላይ ወድቆ እያዩ የሠራዊት መሪ የተባሉት እነ ይመር ተጋዳዩን የትም በትነው እነርሱ መሣርያ እየሸጡ በሱዳን ከተሞች በመንፈላሰሳቸው ተጋዳዩ ከችግር ብዛት የተነሳ ሳይወድ ወደ አውሮጳና አሜሪካ ተሰደደ።

እነ ይመር መሣርያ እየሸጡ ይጠቀሙ እንደነበረ ቲያ ኗሪ የነበረ ሹምዬ ንጋቱ የተባለ ከነ ይመር መሣርያ በመግዛት እየሸጠ ይጠቀም የነበረ "እርሰዎ በጉድጓድ የተቀበረውን መሣርያ አስወጥተው ሊወስዱ ነው ተብሎ ለሱዳን መሣርያው ከተሰጠ የእኔ ጥቅም መጓደሉ ነው። አንድ ክላሺንኮቭ ጠመንጃ በሦስትና በአራት መቶ ብር ገዝቼ በአምስት መቶ ብር እሸጥ ነበር" ብሎ ነግሮኛል።

ይህን መሣይ አሳፋሪ የክህደት ተግባር በኮምዩኒስት ሥርዓት በተጠመቁ ግለቦች መደረጉ በእጅጉ ቢያሳዝንም ድርጅቱ ግን እነርሱ በፈጸሙት አሻጥር አልፈረሰም። ከጠለምት ጊዜአዊ ማፈግፈግ አድርጎ በኤርትራ ባርካ አካባቢ ኃይሎቹን አጠናክሮ በወልቃይት በኩል ከወያኔ ጋር እየተፋለመ ወደ ውስጥ ገብቶ ትግሉን ቀጥሏል።

አቶ ክፍሉ ታደሰ የትግል ስማቸው (ታዬ)፤ ከኢሕአፓ መሪዎች አንዱ ነበሩ። እነ ይመር ይህን ነውረኛ አሳፋሪ ነገር ሲፈጽሙ በዚያው አካባቢ ነበሩ። ያደረጉትን ሁሉ ሰምተውታል፤ያውቁታልም። "The Generation" በሚለው አከታትለው በአወጧቸው ሁለት መጽሐፍት የነ ይመርን አሳፋሪ ድርጊት መግለጽ ይጠበቅባቸው ነበር። ለምን ሳይገልጹ እንዳለፉት አልገባኝም። የአገርን መከላከያ መሣርያ ለውጭ አገር መንግሥት አሳልፎ ከመስጠት የበለጠ ክፉ ድርጊት የለምና ታዲያ የታጋዮች ሕይወት የተለወጠበት መሣርያ እነርሱ ለተሰውልት ዓላማ ባለ መዋሉ አቶ ክፍሉ ጉዳዩን አቅልሎ ማዬት አይገባቸውም ነበር።

<u>ጠቅለል ባለ መልኩ፤</u>

" ማንም ፈሪና ድንጉጥ ሰው ቢኖር እርሱ ፈርቶ የወንድሞቹን ልብ ደግሞ እንዳያስፈራ ወደ ቤቱ ተመልሶ ይሂድ " (ኦሪት ዘዳግም 20-8) ኢሕአፓ የከተማን የትጥቅ ትግል አስመልክቶ ከላይ ባሉት በአመራር አካላት መካከል የሃሳብና የአቋም ልዩነቶች ተፈጥረው ጌታቸው ማሩና ብርሃነ መስቀል ረዳን የመሳሰሉ በከተማ ውስጥ የትጥቅ ትግል መካሔድ የለበትም የሚል አቋም በመውሰዳቸው በአንጃነት ተፈርጀው መለየታቸው በግልጽ መሰማት ሳይጀመር መለያየታቸውን ያልሰሙ አባላት ተጎድተውበታል ይባላል።

በዚያን ኢሕአፓ ባልተጠናከረበት ወቅት ምንም አስተማማኝ መካች ኃይል በሌለበትና በቂ ዝግጅት ሳያደርግ ርዕዮተ ዓለሙን በባለቤትነት ተቀብሎ የሚያስተናግድ ተሸካሚ የነቃ ኃይል ሳይኖር ጀሌዎችን አሳልፎ የትጥቅ ትግል ማካሔድ ትክክል ያልሆነ ከርዕዮተ ዓለሙ ጽንሰ ሃሳብ የራቀ ነው። የከተማው የትጥቅ ትግል ሁኔታዎችን ያላሟላና ያላገናዘበ ጥናት የጎደለው በስሜት የተሰባሰቡ ወጣቶችን (አንዳዶችን) ሽጉጥ አስታጥቆ ከብረት ጋር ተላተም ማለት ትልቅ ስህተት ነበር። በዚህ ላይ ጌታቸው ማሩና ብርሃነ መስቀል የወሰዱት አቋም የተሻለ ብስለት ነበረው ማለት ይቻላል።

ምንም እንኳ ደርግ ሳይጠናከርና ሥር ሳይሰድ በከተሞች የትጥቅ ትግል ማደረግ አስፈላጊነት ያለው መሆኑና ወቅታዊነቱን ቢያመለክትም ነባራዊ ሁኔታውም ወደ ትጥቅ ትግል መግፋቱ ቢታመንበትም ከበቂ ሕሊናዊ ዝግጅት በፊት መደረግ አልነበረበትምና የከተማውን የትጥቅ ትግል የመሩ ሰዎችን ከኃላፊነት የሚያሸሻቸው አይደለም።

በአቋም የተለዩ አንጃዎችም የድርጅቱን መዋቅር በሚያውቁት መንገድ በማጋለጥ በቅንነትና በየዋሕነት የተሰለፉትን እየጠቆሙ በማስያዝ ጉዳት ላይ ጥለዋል። የሚባሉት (ነገሩ እርግጠኛ ከሆነ) ከአብዮተኝነት ተራ የሚያወጣቸው ነው። ዳሩ ግን አንጃዎቹ መልስ ያልሰጡበት በመሆኑ ማረጋገጫ የለም። በዴሞክራሲ ሥርዓት መሠረት በመድረክ ተወያይቶ ብዙኃኑ በድምፅ ብልጫ ለሚወስኑት መገዛት ሲገባ የከተማ የትጥቅ ትግል ይካሔድ ያለውን የአመራር አካል አንጃ ከተባሉ አንዱ ጌታቸው ማሩ ላይ አሰቃቂ ግድያ ተፈጽሞበታል ተብሎ በግዜው ተወርቷል። ብርሃነ መስቀል ድርጅት አቋቁሞ በመንዝ አካባቢ ሲንቀሳቀስ ከደርግ ጦር ጋር ሲዋጋ ተማርኮ ከታሰረ በኃላ መ[illegible]ሹ የተረጋገጠ ነው። ለመበቀል ተብሎ የነበሩበትንና የታገሉበትን ድርጅት ለማፍረስ ንጹኃኑን አባሎች አጋልጦ መስጠትና ልዩ ልዩ አሻጥር ማድረግ የተነሱበትን ዓላማ እንደ መካድ የሚያስቆጥር ቢሆንም አንጃ የተባሉት አድርገዋል ብሎ በነሱ ላይ ወንጀል መከመሩ ለሕሊና ይከብዳል።

አብዮተኛ አምኖበት ለሚታገልለት ርዕዮተ ዓለም ምንም ምክንያት ቢፈጠር ሽብርና ብጥብጥ ቢነሳም ሁከትና ድብልቅልቅ ቢሆንም ከአቋሙ በምንም አይዛነፍም። እስከ ሞት ጸንቶ ይጓዛል



እንጂ። ደርግ ሥልጣን በያዘበት ሰሞን በማርክሲዝምና ሌኒንዝም ኮምዩኒስታዊ ርዕዮተ ዓለም ብዙ ድርጅቶች ተፈልፍለው (ከኢሕአፓ በስተቀር ሌሎቹ) ደርግን ስልታዊ ወዳጅ አድርገው በዙሪያው ተቋቋሙ። በማርክሲዝምና ለኒንዝም የተቋቋሙ ድርጅቶችም መላው ኢትዮጵያ ሶሻሊስት ንቅናቄ (መኢሶ ) ወዝ ሊግ፡ ኢትዮጵያ ኮምዩኒስት ፓርቲ (ኢኮፓ) የኢትዮጵያ ማርክሲዝም ሌኒንዝም ረቮሎሺነሪ ድርጅት (ኢማሌሪድ) የኢትዮጵያ ጭቁኖች አብዮታዊ ትግል (ኢጭአት) አብዮታዊ ሰደድ የተባሉ የግራ ሰልፈኞች ደርግን በአሻጥር ጥለን ሥልጣን እንይዛለን ብለው የተጠጉ ሲሆኑ የኢትዮጵያ ዴሞክራቲክ ኅብረት (ኢዴኅ) የቀኝ ሰልፈኛ ሁኖ ሱዳን ውስጥ በድሮ ባለ ሥልጣኖች መሪነት ተቋቁሞ የቀኝ መንገድ በብቸኝነት ይዞ ነበር።

ከነዚህም አገራዊ ድርጅቶች ሌላ ተገንጣይ የብሔር ድርጅቶች ተፈለፈሉ። ምንም እንኳን የኤርትራ አርነት ግንባር (ELF) እና የኤርትራ ሕዝባዊ ግንባር (EPLF) ቀደም ብለው የተቋቋሙ ቢሆንም እድገት ያገኙት ደርግ ሥልጣን ከያዘ በኋላ ነው። ተገንጣዩ ሕዝባዊ ሐርነት ትግራይ (TPLF) እና ሌላው ተገንጣዩ የኦሮሞ ነፃነት ግንባር (OLF - ኦነግ) በደርግ የሥልጣን ዘመን ተፈልፍለው ያደጉ ናቸው። የሚገርመው እነዚህ ሁሉ ድርጅቶች በኢሕአፓ ላይ ጤናማ አመለካከት አልነበራቸውም። ምክንያቱም ኢሕአፓ አገራዊ ድጋፍ በማግኘቱ ይውጠናል የሚል ሥጋት ስለ ነበረ ነው። ውድቀቱን እንጂ ዕድገቱን አይፈልጉም ነበር።

ደርግም በመጀመሪያዎቹ የሥልጣን ዘመናቱ ተገንጣይ የብሔር ድርጅቶች የትም አይደርሱ እያለ በንቀት እየተመለከተ ኢሕአፓ እና እዴኅን አገራዊ ድርጅቶችንና የነቁ የኅብረተ ሰብ ክፍሎችን በጥብቅ እየተከታተለ ለማጥፋት ዘመቻውን ቀጥሎ " ቀይ ሽብር " ብሎ በሚጠራው በከተሞች የመደዳ ጭፍጨፋውን በጭካኔ (ያለ ርኅራኄ) ቀጥሎ እየገደለ ሬሣ መሸጡን ተያያዘው። በዚህን ግዜ ለተገንጣዮች ሰርግና ምላሺ ሁኖ በነርሱ ላይ ይበልጥ ትኩረት ባለመደረጉ እንደ ፈለጉት ሁነው ለመደራጀት አስችሎአቸዋል። ወያኔም በተራው የጎሣ ድርጅቶችን በዙሪያው አሰልፏል።

ኢሕአፓን በሁሉም ዘንድ በጠላትነት የተፈረጀውና ወዳጂ ያሳጣው በአገር ውስጥ ብቻ አልነበረም። በሰፊ አመለካከቱ ይዞት በተነሳው አብዮታዊ ትግሉ እና በአገር ወዳድነቱ ምክንያት ተስፋፊ ኢምፔሪያሊስቶችና ኮሎኔያሊስቶች እስከ ዛሬ ድረስ እንደ ተቃወሙት ነው።

ኢሕአፓ በሰው ልጅ እኩልነት ላይ የተመሠረተ ድርጅት በመሆኑ አባል አድርጎ የተቀበላቸው በኢትዮጵያዊነት ብቻ እንጅ ሌላ ምንም ዓይነት መመዘኛ (ክራይቴሪያ) ስለዓልነበረው በድርጅቱ ውስጥ አንዳንድ ድርጅቱን ለማፍረስ ልዩ ተልዕኮ የነበራቸው ከደርግና ከተገንጣይ ድርጅቶች የተላኩ ገብተውበት በአሻጥር ድርጅቱን

ጎድተውታል። ታሪክ ከሚያስታውሳቸው ድርጅት አፍራሾች ውስጥ የመጀመሪያው ሰው አያሌው ከበደ የተባለ በለሳ ውስጥ ይታገሉ ከነበሩት የኢሕአፓ አባላት ሰላሳ ያህል ሰዎች አስከድቶ ለወያኔ አስረክቧል ተብሎ በብዙዎች ዘንድ ይነገራል። (እኔ እንኳ አላው ቀውም።) አያሌው ከበደ ለተገንጣዩ ወያኔ ታጋዮቹን አስረክቦ ወደ ሱዳን ሒዶ በካርቱም በኩል ወደ አዲስ አበባ ተጉዞ ደርግ መልካም አቀባበል አድርጎለት የሲዳሞ ክፍለ አገር ዋና ጸሐፊ አድርጎ ሹሞት እንደ ነበር በወቅቱ ተነግሯል። አያሌው ኢትዮጵያን ለካደ ወያኔ ከማስረከብ ይልቅ ወደ ደርግ ይዟቸው ቢገባ የተሻለ ነበር። ቢያንስ ደርግ ለኢትዮጵያ አንድነት ይታገል ነበርና።

ወያኔም አያሌው ከበደ ያስረከባቸውን 30 ሰዎች እነ ታምራት ላይኔን /ጌታቸው ማሞን/ የኢትዮጵያ ሕዝባዊ ዴሞክራሲ ያዊ ንቅናቄ /ኢሕዴን/ ብሎ ሰይሞ /ኢትዮጵያዊ ድርጅት በማስመሰል/ ወደ ማህል አገር ለመግባት ተጠቅሞባቸዋል። ይኸው ድርጅታዊ ነፃነት ያልነበረው ኢሕዴን አመታዊ ጉባኤ አድርጎ ባወጣው ያቋም መግለጫ "ኤርትራውያን የሚያደርጉት የነፃነት ትግል ፍትሃዊ ነውና ኢሕዴን ይደግፈዋል" ብሏል። ያው ወያኔ ያቀነቅነው የነበረውን ኢሕዴን የአቋም መግለጫ አድርጎ ያወጣው ወደ ወያኔ ተታለው ከገቡት ውስጥ ጠንካራ ኢትዮጵያዊ እምነት የነበራቸው ከወያኔ ጋር ሳይልከሰከሱ ወዲያውኑ ጥለው የወጡም ነበሩ። ወያኔ ሥልጣን ከያዘም በሁኋላ እነዚያኑ ኢሕዴን ብሎ አቋቁሞ እንደ ዕቃ ይጠቀምባቸው የነበረውን ብሔረ አማራ ድርጅት ብሎ እንደ ባርያ ስም እየለዋወጠ የጠባብ ዓላማው አገልጋዮች አድርጓቸዋል።

ሁለተኛው የኢሕአፓ አባላትን የበታተነው በጎንደር ምዕራብ በጭልጋ ጎንደር አውራጃዎች ተቋቁሞ የነበረው ሬጅን ሁለት ተብሎ ይጠራ የነበረው የሠራዊቱ የበላይ አመራርና ኮሚሳር የነበረው በትግል ስሙ ይመር (አድማሱ) የተባለ የኢሕአፓን የበላይ አመራር ትዕዛዝ አሻፈረኝ ብሎ በሰሚናር አሳቦ ወደ ሱዳን ወስዶ የበተነ በመሆኑ ጠላትነቱ ለድርጅት ብቻ ሳይሆን የአገር ጠላትም ነው። በአንድ ግዜ አከታትሎ ሁለት ወንጀሎችን ፈጽሞአል። አንደኛው ወንጀሉ ሠራዊቱን መበታተን ሲሆን ሁለተኛው ወንጀሉ የአገርን ንብረት ለውጭ መንግሥት ለሱዳን በማስረከቡ ከባድ ወንጀል ፈጽሟል። እኔንና አቶ ወልደ ገብርኤልን በማሳሰሩም ተጨማሪ ሁኖ የሚጠየቅበት ነው።

መቼም ከተደበቀ የወዳጅ ጠላት (በተለይም አብሮ በትግል ከተሰለፈ ጓድ) ይልቅ በግልጽ ፊት ለፊት የሚመጣ የታወቀ ጠላት ይሻላል። ምክንያቱም ጠላትን እንደ አመጣጡ መመከት ይቻላልና። በግልጽ እንደ ታየው ከሆነ የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ በውስጡ ከነበሩት አባሎቹ አንዳንድ ወስላቶች እየከዱ ያደረሱበትን ጉዳት ያህል የውጭ ጠላት አላደረሰበትም። ደርግንም ለውድቀት ያደረሰው በከፍተኛ ማዕረግና ሥልጣን ላይ ካስቀመጣቸው ከኢሠፓ አባሎች ውስጥ አንዳንዶቹ በፈጸሙት አሻጥር ነው።

ኢሕአፓ ጠንካራ ስነ ሥርዓት (ዲስፒሊን) ያለው ድርጅት



በመሆኑ በአንድ ወቅት ፊታውራሪ አየለ ተሰማ ኢሕአፓን በሁለት ነገሮች አደንቀዋለሁ አንደኛ በከተማ ውስጥ የነበረው ወጣት ጫትና ሐሺሽን ከመሰለ ናላን ከሚያዞር (ዕፅዋት) አላቆታል። ሁለተኛ ሴትና ወንድ (ያውም አፍላ ወጣቶች) አብረው እየተኙ በፍትወተ ሥጋ እንዳይፈላለጉ ማድረጉ በጣም ይገርመኛል።" ብለው ነገሩኝ።ይሁን እንጂ ልቅ በተሰደደ ዴሞክራሲ (ያለገደብ) የበላይና የበታች የዕዝ ተዋረድ ሳይጠብቅ ሁሉ የውሳኔ ተካፋይ በመሆኑ በድርጅቱ ላይ ጉዳት አድርሷል።

ማንኛውም ሰው ወደ አብዮታዊ ትግል ከመግባቱ በፊት አስቀድሞ ራሱን ፍጹማዊ ወደ ሆነ አብዮታዊ እምነት መለወጥ አለበት። ራሱን ሳይለውጥ ወደ አብዮቱ ሠፈር ቢገባ ግን የአብዮቱ አገልጋይ መሆኑ ቀርቶ አብዮቱ እርሱን እንዲሸከመው ይፍልጋል። ከንቃት በፊት አስቀድሞ በአእምሮው ውስጥ (የቀረጸው) ያስገባው ምናምንቴ ሽቀጥ ሥልጣን አፈንፋኝነት ልታወቅ ባይነት የግል ጥቅም አሳዳጅነት ሙገሳና ዝና ፈላጊነት ተንኮልና ምቀኝነት ወገናዊነትና ጎሰኝነት ስግብግብነትና ግብዝነት የመሳሰሉትን ጠርጎ አውጥቶ ሕሊናውን ንጹህ ሳያደርግ ወደ አብዮቱ ሠፈር ቢገባ አብዮታዊ ሁኔታዎችን ለመቀበል አይችልም። ምክንያቱም በንቃተ ሕሊናው አስቅድሞ ምናምንቴ ሸቀጥ የሞላበት በመሆኑ አዲሶቹን ራዕዮች ይተፋቸዋል አያስገባቸውም ስለዚህም ነው ራሳቸውን ሳይለውጡ ወደ አብዮቱ ሠፈር የገቡ መቋቋም እየተሳናቸው ተዝረክርከው ለአብዮቱም ለራሳቸውም ሳይሆኑ የትም ወድቀው የቀሩ ብዙ ናቸው። በተለይ ከዳተኛማ በሔደበት ሁሉ ይሰደባል። "ስመ ጥፉ" ስድብ ልብሱ ነውር ቀሚሱ" ይባላል።

አብዮተኛ ማለት በውስጡ ያለውን ቆሻሻ አጥቦ የተጣበቀበትን ጉድፍ አራግፎ አብዮት ሲዘራበት የሚያበቅል ንጹህ ሕሊና የያዘ እርምት የሌለበት ጥሩ የተንቀረቀበ የአብዮት ማሳ ማለት ነው። አብዮተኛ በራሱ አያዝበትም የአብዮቱ ዕቃ ነው። እንደ ዕቃ ሁኖ በጎደለበት እየሞላ ማገልገል የሚችል ፍጹም ቆራጥ መሿይት የሚደፍር ነው። አዲስ ፍጡር ሁኖ ካልተወለደ በስተቀር በስሜት ተገፍቶ በጓደኛ ተስቦ አብዮተኛ መሆን አይችልም።

ፀረ እድገት የሆኑት ጎታች ሥርዓቶችን ለማስወገድ የቆረጠ በመድረክ የተከራከረ በጦር ሜዳ የተፋለመ "እምነት እስከ ሞት" ብሎ በቃል ኪዳን የፀና ለቆመበት ዓላማ ብዙ መሱዋይት የከፈለ የኢሕአፓ ብቻውን (በዓላማው ፀንቶ) በኢትዮጵያዊነት ቁሞ ይገኛል። ሌሎቹ ኢትዮጵያዊ ሁነው ተፈልፍለው በደርግ ዙሪያ ተሰባስበው የደርግን ፍርፋሪ እየበሉ ውድቀቱን ሲመኙ ተያይዘው ጠፉ። አንዳንዶቹም እንደ ቂጣ እየተገለባበጡ የጎጠኛውንና የተገንጣዩን የወያኔ የጎሣ ፖሊሲ በመደገፍ ያበረታታሉ።

የኢሕአፓ ታሪክ ብዙ ቮሊሞች የሚወጣው እንጂ እንዲህ በአጭር ድርሰት የሚወሰን አይደለም። እኔ በዚህ እግር መንገዴን

ያነሳሁት በጎንደር ክፍለ አገር በዓይኔ ያየሁትን ብቻ ስለሆነ የኢሕአፓ አባሎች ያልተሟላ ታሪክ ጻፈ ብለው እንደማይቀየሙኝ ተስፋ አለኝ። እኔ እስከ ማውቀው ድረስ ኢሕአፓ ስሙን ከግብሩ አዋሕዶ የታገለ ድርጅት ነው።ኢሕአፓ ራሱን ከሥልጣን ለማውጣት ሳይሆን ሠፊውን ሕዝብ ወደ ሥልጣን ለማውጣት እንደነበር በትግል ሜዳ ያወጣቸው የነበሩ መፈክሮችና የሚያስራጫቸው በራሪ ጽሑፎች በግልጽ ያስረዱ ነበር። ኢሕአፓ ማኅበራዊና ኅብረተሰባዊነትን ይዞ በንቃት ተንቀሳቅሷል።

ኢሕአፓ መጀመሪያውን ካመሠራረቱና ከአነሳሱ እንደታዬው በመሬት ላራሹ እንቅስቃሴው ይገፋበት የነበረው ሕዝብን ከጢሰኝነትና ከገባርነት አላቅቆ እኩል የዜግነት መብትን ለማጎናጠፍና ፍትሐዊ አስተዳደር ለመመስረት እንደነበረ ይከተለው የነበረው ሕብረተሰባዊ መመሪያው ያረጋግጥለታል። ይህን ማንም ሊክደው የማይችል ሐቅ ነው።

ይህ ባይሆን ኑሮ መላው አባላቱ "የእኔ ደም መሰኖ ሁኖ ሕዝብን ያለምልም ከጉስቁልናና ከጭቆና ኑሮ ያላቅቅ" እያለ መሷይት አይደፍርም ነበር። የግል ሥልጣን ፈላጊነት ቢሆን ኑሮ ሕይወቱን ለሞት አሳልፎ አይሰጥም ነበር። ኢሕአፓ የሚታገለው ለሥልጣን ነው ሲባል እሰማለሁ። በእርግጥ ሕዝብን ወደ ሥልጣን ለማውጣት ታግሏል፤ እየታገለም ነው። እኔ ብቻ ልኑር እኔን ብቻ ይድላኝ ሁሉ ለእኔ ሳይል እየተቸገረና እየተሰቃዬ ለማንም ሳያነበድድ ኢትዮጵያዊ ድርጅት ሁኖ ያታገለና የታገለ ድርጅት መሆኑን ታሪክ ያውቅለታል።

# ምዕራፍ 19

## ሰው መሳይ በሸንጎ፤
## አገር አጠፋ በድርጅት ውስጥ መሽጎ።

አንዳንድ ሰው በንግግሩ የሰውን ሕሊና የሚስብ ቅን አሳቢ ራሱን ለሌሎች ጥቅም አሳልፎ የሚሰጥ መስሎ ይታል። እውነተኞችንና ደጎችን ለግል ፍላጎቱ መጠቀሚያ ወይም ለተገዛበት አገልግሎት እንደ እባብ ገላ ለስልሶ እንደበግ ገራም ሁኖ ይቀርባል። ከፖለቲካ ድርጅት ወይም ከሕዝባዊ ማኅበር ውስጥ ሸምቆ ገብቶ የሚፈልገው ከተሳካለት ከአንድ ሁናቴ በኋላ የተወሰኑ ሰዎችን ገንጥሎ በመያዝ የሕቡዕ ሥራውን ይቀጥላል። ለድርጅታቸው ታማኝ፤ በአቋማቸው ጠንካራ በምንም ነገር የማይደለሉ አገር ወዳዶችን ወደ ጎን ገፍትሮ በሕቡዕ መንገዱ በፖለቲካ ሸማቂነት ሲሠራ ብዙ ስህተቶች ሲያደርግ ታይቷል። እየተደረገም ነው።

" የጨነቀው እርጉዝ ያገባል!" እንደ ሚባለው የኢትዮጵያ ሁኔታ ከዕለት ወደ ዕለት እየተባባሰ በመጣበት ወቅት አደጋውን ተባብሮ ለመከላከል ኢትዮጵያዊ ነኝ ከሚለው ጋር እየተወያየን ችግሩን ለመፍታት በትግል ላይ የነበርነው ያልተቆጠበ ጥረት አድርገን ነበር።የአፄ ኃይለ ሥላሴ መንግሥት ኢትዮጵያን ወደ ገደል ሲመራት እንደታየው እንዲሁም ደርግ ኢትዮጵያን ይዟት እንደሚጠፋ በጉልህ ይታዩን ነበር።

በኢምፔሪያሊስት ኃይሎች ይደገፉ የነበሩት ተገንጣይ የጎሣ ድርጅቶችም ከዕለት ወደ ዕለት እየበረከቱና እየሰፉ በመሔድ ሌላው አሳሳቢ ጉዳይ በመሆኑ ጠንካራ ድርጅት መሥርተን በመታገል አገሪቱን ከውድቀት ለማዳን ሙሉ ፈቃደኝነት ስለ ነበረን አሜሪካ በጥገኝነት ኗሪ የሆኑ ኢትዮጵያውያን ወንድሞቻችን በማቴሪያልና በፖለቲካ ረገድ ይረዱናል በሚል ተስፋየድርጅታችንን መርሃ ግብር ልከንላቸው ነበር።

እነርሱም አብረን እንድንታገል ከፈለጋችሁ መርሃ ግብሩ እኛ በምንለው ከተስተካከለ አብረናችሁ እንታገላለን በማለታቸውና ለመታገል ሙሉ ፈቃደኝነታቸውን በመግለጻቸው እኛም ዋናው የትግሉ መካሔድ ነውና የሚታገሉ ከሆነ ስሙም ሆነ መርሃ ግብሩ አያከራክረንም ብለን መርሃ ግብሩንና የድርጅቱ መጠሪያ ስም ለእነርሱ በሚስማማ ሁናቴ ተዘጋጅቶ አገር ውስጥና ሱዳን የነበሩ አገር ወዳድ ታጋዮች መንቀሳቀስ ሲጀምሩ ተንኮሉ አብሮ እየተንቀሳቀሰ በአገር ውስጥና በሱዳን በትግል ላይ የነበርነውን ብዙ የትግል ልምድ ያለንንና ድርጅታዊ አሠራርን ጠንቅቀን የምናውቀውን ወደ ጎን ትተው በራሳቸው መንገድ በማያውቁት አሠራር ተጉዘው የአሥራ ስምንት ሰዎች ሕይውት አዲስ አበባ ውስጥ በከንቱ እንዲጠፋ አደረጉ። ለነዚያ በከንቱ ለተገደሉት ለነ ደጃዝማች አሰጋኸኝ ፎክተር መንገሻና ወይዘሪት ሃይማኖት ሌሎችም 18 ሰዎች ሕይወት እነ ደረጀ ዲሬሳን ያስጠይቃቸዋል።

ከኢትዮጵያ ሕዝቦች ዴሞክራሲያዊ አንድነት (እሕዴአ - EPDA) በአሜሪካና በአውሮጳ ከነበሩት ጋር እኛ በአገር ውስጥ በትግል



ኮ/ል አስናቀ እንግዳ ከታጋይ አያል ሰው ደስዬ ጋር ሲወያዩ




ላይ በነበርነው መካከል በተፈጠረው የአቋም ልዩ ነት ከተለያዩን በኋላ አሜሪካ ውስጥ የነበሩ የድርጅታችን አባሎች ኮሎኔል አለማየሁ አስፋው ሻለቃ ዮሴፍ ያዘውና ሻለቃ ጌታቸው የሮም እኛን ወክለው በዋሽንግተን ዲ. ሲ. ከሚገኙትአገር ወዳድ ምሁሮች ጋር ተነጋግረው ክተት በሚል ስም መርሃ ግብር ነድፈው ልከውልን በሱዳን የነበርነው አባላትም ተስማምተንበት ነበር። በክተት ውስጥ የተሰባሰቡ ምሁራን አቶ ክፍሌ ወዳጆ/ አቶ አያሌው ማንደፍሮ፣ ዶ/ር መክብብ፣አቶ ሚሊዮን ነቅንቅ፣ አቶ ሙሴ በትሩ፣ አቶ ዝበየሁ ወልደ ማርያም፣ ልጅ አምዴ አርዓያ፣ አቶ በላይ ብዙነህ መስራች አባሎች ነበሩ። ድርጅቱ አንዳንድ በራሪ ወረቀቶችን በአማርኛና እንግሊዝኛ ከመጻፍ አልፎ ምንም ዓይነት እንቅስቃሴ ሳያደርግ ከዓመት በላይ ቆይቶ እኛን ሱዳን ያለነውን ሳያማክሩ ከነ ደረጀ ደሬሳ ጋር ተዋሕደው ሥም መጥራት ሲጀምሩ በአሜሪካ በጉብኝት ላይ የነበሩት አያል ሰው ደስታና እኛም በሱዳን የነበርነው በአቋም ስንለይ እነ አቶ ደረጀ ድሬሳ ኮሞዶር ጣሰው ደስታ ዶክተር አደም አብደላ ሻምበል አስራት ደፈረሱ ከሲ አይ ኤ በዓመት 500000 ዶላር እየተሰጣቸው በዋሽንግተንና ለንደን የጦር ሜዳዎች አድርገው በመመላለስ ባካሔዱት ዘመቻ ትግሉን አጧጧፍን አሉ። በካርቱምም ካፒቴን ሐሰን ሰይድ የተባለውን ከጀርመን ወስደው በማስቀመጥ ስማቸውን ያስጠሩ ነበር።ለስሟ መጠርያ ቁና ሰፋች ነው። ቀደም ብሎ በሱዳን የነበርነው በአቋም ስንለይ ኮሎኔል እምሩ ከነርሱ ጋር አብሮ ለመሥራት ሞክሮ ነበር። ይሁን እንጅ በአመራር ባለመስማማት ብዙምሳይቆይ እሱም ተለይቶቸዋል።

አሁንም ተስፋ ባለ መቁረጥ አሜሪካ የነበሩ ወንድሞቻችን ምንም እንኳ ኢትዮጵያ ወዳጅ ኑሯት እርዳታ ማግኘት ባይቻልም ኢትዮጵያውያን ተሰባስበው በተቀናጀ መልክ ትግል የሚቀጥልበት ጥናት በማድረግ ላይ እንዳሉ የደርግ ( ኢሠፓ ) የእርዳታ ኮሚሽን ኃላፊ የነበረው ሻለቃ ዳዊት ወልደ ጊዮርጊስ ደርግን ከድቶ የአሜሪካንን ጥገኝነት ጠይቆ ተፈቅዶለት ለአገሩ ለመታገል ፈቃደኛነቱን ገልፆ "ነፃ የኢትዮጵያ ወታደሮች ንቅናቄ" የሚል ድርጅት እናቋቁም የሚል ሃሳብ በማቅረቡ ከነ ደረጀ በአቋም የተለዩት የድርጅታችን አባል የነበሩ መኮንኖች ተውያይተው በሃሳቡ ተስማምተውበት ነበር።

" የነፃ ኢትዮጵያ ወታደሮች ንቅናቄ " ዓላማና ተግባር " ሕዝባዊ ግንባር ኤርትራ (EPLF) በመባል የሚታወቀው 10 ሺህ የኢትዮጵያ ወታደሮችን በምርኮ ይዟል በመባሉ እነርሱን አስፈትቶ በማደራጀት ለመታገል ያነፃፀረ ነበር።

እኔም ልጆቼና ወዳጆቼ ጋብዘውኝ ከሱዳን ወደ አሜሪካ መጥቼ ስለ ነበር "ነፃ የኢትዮጵያ ወታደሮች ንቅናቄ" የሚል ድርጅት መሥርተናል ብለው ዓላማውንና አቋሙን በዝርዝር ገለፁልኝ። ዓላማውና ተግባሩ የሚደገፍ ነው፣ ዳሩ ግን ከዚህ በፊት እኔ እነ አቶ ደረጀ ዴሬሳን ምንነታቸውን መርምረን ሳናውቅ ከትግሉ አንፃር ብቻ በመመልከት በኢትዮጵያዊነታቸው ተማምነንና ከኢትዮጵያ ዲሞክራቲክ ኅብረት (ኢዲኅ) ተሰልፈው ስለ ነበር ተመክሮ አላቸው በሚል ተቀብለናቸው



ኮ/ል አስናቀ እንግዳ ከታጋይ አያል ሰው ደስዬ ጋር ሲወያዩ

በተንኮል ድርጅታችን አፈረሱብን። አሁን ደግሞ ሻለቃ ዳዊት ወልደ ጊዮርጊስ ከኋላው ምን እንዳስከተለ ሳናውቅ በየዋሕነት ከርሱ ጋር ድርጅት መመስረት ከጉዳት ላይ አይጥልም ወይ? ብዬ ኮሎኔል አለማየሁ አስፋውን ብጠይቀው "ደረጀ የራሱ የሆኑ ሰዎች አሉት፤ ዳዊት ግን ከእኛ በቀር ሌላ ሰው የለውም" አለኝ። ኮሎኔል ዓለማየሁ በተፈጥሮው ቅንና ደግ ሰው በመሆኑ የራሱን እምነት ገለጸልኝ እንጂ የሻለቃ ዳዊትን ምንነት በሚገባ ያወቀ አልነበረም። የሆነ ሁኖ ከአመናችሁት መልካም ነው አልኩ።

እንዳጋጣሚ ሁኖ ኒው ጀርሲ አቶ ገላጋይ በተባለ ሲቪል አማካኝነት ስብሰባ ሲያደርጉ ጋብዘውኝ ሄጀ ነበር። በዚህም ስብሰባ ዶክተር የመቶ አለቃ በርሔ የተባለ ትውልዱ ኤርትራ የሆነ የሐረር አካዳሚ ምሩቅ ነበር፤ (ለመጀመሪያ ያየሁት ሰው ነው) እንዲሁም ገላጋይ የተባለውን ሰው ለመጀመሪያና ለመጨረሻ ጊዜም ያየሁት የዚያኑ ዕለት ነበር።

ሻለቃ ዳዊት ወልደ ጊዮርጊስ የአውስትራሊያ " Community Aid ABROAD " የተባለው ዕርዳታ ሰጭ ድርጅት 50 ሺህ ኩንታል ዶቄት ሱዳን ውስጥ ሊያስረክበን ቃል ገብቶልኛል አሁን በፍጥነት ተረካቢ ያስፈልጋል። ሕዝባዊ ግንባር ኤርትራ በምርኮ ስም የያዛቸውን 10 ሺህ ሰዎች ከመረከባችን በፊት ምግባቸውን አስቀድሞ ማዘጋጀት ያስፈልጋል በማለቱ እኔ ወደዚህ አሜሪካ የመጣሁት ቤተ ሰቦቼና ወዳጆቼ ጋብዘውኝ ነው። ከእነርሱ ጋር አርፌ ወደ ሱዳን  መመለስ ያለብኝ ቢሆንም በእርግጥ ሕዝባዊ ግንባር ኤርትራ ( ሻዕቢያ ) በምርኮ ስም የያዛቸውን የሚያስረክብ ከሆነና የአውስትራሊያ የዕርዳታ ድርጅትም 50 ሺህ ኩንታል እህል የሚሰጥ ከሆነ የእረፍት ግዜዬን አቋርጩ ወደ ሱዳን ተመልሸ እረከባለሁ ብዬ ፈቃደኝነትን ገለጽሁ።

ልጆቼና ወዳጆቼም ብዙ ገንዘብ ከፍለን አስመጥተንህ ከእኛ ጋር ትንሺ ግዜ ሳትቆይ ወደ ሱዳን መመለስ የለብህም ብለው ተከራክረውኝ ነበር። እኔ ግን እንዲህ ያለ መልካም አጋጣሚ ሲገኝ መጠቀም አለብን። ዕድሉ ሳያመልጠን ወደ ሱዳን ተመልሸ እህሉን መረከብ አለብኝ ብዬ ተመለስኩ።

ምንም እንኳ የእርዳታው እህል ይገኛል ብዬ መቶ በመቶ ባላምንበትም በመቶ ሶስት (3%) ተስፋ ይዤ ወደ ሱዳን ስመለስ ሻለቃ ዳዊት አውስትራሊያ ድረስ ሒዶ ያነጋገረውን የባሕር ማዶ የእርዳታ ሰጪ ኃላፊ ስምና በሱዳን ያለው እርዳታ አከፋፋይ ስም በብጣሺ ወረቀት ላይ ጽፎ ሰጥቶኝ ወደ ሱዳን እንደተመለስኩ ከታጋይ አብዱል ቃድር ያሲን ጋር ወደ አውስትራሊያው  "Community Aid Abroad" ሔደን ብንጠይቅ ዋናው የእርዳታ ሰጭው ኃላፊ የነበረው ተለውጦ አሁን ያለው ሌላ አዲስ ሰው ነውና እንደ ገና ያቀዳችሁትን "Project" አዘጋጅታችሁ (Proposal) ለዋናው መሥሪያ ቤት አቅርባችሁ ካላስፈቀዳችሁ መስጠት አንችልም። የትግራይ ነፃ አውጪም ( TPLF ) የሚያስፈልገውን አዘጋጅቶ "Proposal" አቅርቦ ነው 50 ሺህ ኩንታል እህል የተፈቀደለት የሚል (STEPHPN Morrow የተባለ ( Community



Aid Aboroad) ኃላፊ የሆነ መልስ ሰጠን።

እኔም ወዲያውኑ ለሻለቃ ዳዊት ወልደ ጊዮርጊስ በሱዳን ያለው ያውስትራሊያ የእርዳታ እህል አከፋፋይ የሆነው የነገረኝን ዘርዝሬ በመጻፍ ፕሮፖሳል አዘጋጅቶ ለአዲሱ ባለሥልጣን ልኮ እንዲያስፈቅድ በደብዳቤ ገጥኩለት። ሻለቃ ዳዊት ለጻፍኩለት ደብዳቤ መልስ ሳይሰጠኝ በመካከሉ ሻለቃ ጌታቸው የሮም ከአሜሪካ ወደ ሱዳን መጣ። የመጣበት ምክንያት ሕዝባዊ ግንባር ኤርትራ በምርኮ ስለ ያዛቸው ወታደሮች ወደ ኤርትራ ሂጄ ከግንባሩ ባለ ሥልጣኖች ጋር ለመነጋገር ነው ብሎ ገለጸልኝ። ሻለቃ ጌታቸው ከግንባሩ ባለሥልጣኖች ጋር ተነጋግሮ ወደ ሱዳን እንደ ተመለሰ ሻለቃ ዳዊት ወልደ ጊዮርጊስ፤ ሻለቃ ስለሺ ፍስሐና ሻምበል ፀጋዬ ብሩ ተከታትለው ወደ ሱዳን መጥተው ከማንም ጋር ሳይገናኙ ሻለቃ ጌታቸውን ይዘው ወደ ኤርትራ ጉዞአቸውን ቀጥሉ። ከሕዝባዊ ግንባር ኤርትራ (EPLF) መሪዎች ጋር ተነጋግረው ሲመለሱ፤ ሻለቃ ጌታቸው እነ ሻለቃ ዳዊት ሊያነጋግሩህ ይፈልጋሉ ብሎ ወደ አረፉበት የሻዕቢያ ጽ/ቤት መርቶ ወሰደኝ ተገናኘኋቸው። ከነርሱም ጋር ስሙን የማላስታውሰው የሻዕቢያ ሰው አብሯቸው ነበር።

እነ ሻለቃ ዳዊት በካርቱም አልፈው ወድ ሕዝባዊ ግንባር ኤርትራ የሔዱት በሱዳን ከነበሩት ከድርጅቱ አባላትና ከእኔም ተሾልከው ነበር። ከኤርትራ መልሳቸው በኋላ ሊገናኙኝ የፈለጉት አሜሪካ የነበሩ ወንድሞቻችን ለምን አልተገናኛችሁትም ብለው እንዳይጠይቋቸው ለዩሉኝታ ያህል እንጂ ወደ ኤርትራ ስለ ሔዱበት ጉዳይ ምን አድርገው እንደ ተመለሱ ምንም ነገር ሊገልጹልኝ ስለ አልፈለጉ ምናልባት ያረፉበት የሻዕቢያ ጸ/ቤት በመሆኑ በየከፍሉ ቴፕ (TAPE)
አጥምደውበት ይሆናል ብዬ ወጣ ብለን እንወያይ ብዬ ሻለቃ ዳዊትን ብጠይቀው የሻዕቢያ ሰዎች ብቻችን እንድንሔድ አይፈቅዱልንም። ከተማውን ለማየት እንውጣ ብንላቸውም አብረን እንሒድ ነው የሚሉት የሚል መልስ ስለ ሰጠኝ ስለ ምርኮኞችም ሆነ ስለ ጠቅላላ የትግሉ ጉዳይ አንስተን ሳንወያይ ተለያዬን። ከዚያው ከሻዕቢያ ጽ/ቤት ሦስት ቀን ያህል ቆይተው ተልዕኳቸውን ፈጽመው ወደ መጡበት አሜሪካ ተመለሱ።

ቀደም ብሎም ሻምበል ፀጋዬ ብሩ ሕዝባዊ ግንባር ኤርትራ ገንዘብ ስለ ረዳን ለነፃ የኢትዮጵያ ወታደሮች ንቅናቄ በካርቱም የባንክ አካውንት ለመክፈት ነው የመጣሁ ብሎ አራት ቀን ያህል ካርቱም ቆይቶ በስዊዝም የባንክ አካውንት እከፍታለሁ ብሎ ወደ አውሮጳ ሔደ። ሻምበል ፀጋዬ በካርቱም ቆይታው የባንክ አካውንት ይክፈት አይክፈት የሚታወቅ ነገር አልነበረም። በዚያ በካርቱም የነበርነው የምናውቀው ሻምበል ፀጋዬ ብሩ ሕቡአዊ ተልዕኮውን ፈጽሞ መሔዱን ነበር።

የደርግ የዕርዳታ ማስተባበሪያ ኮሚሺነር ሁኖ የሠራ ሻለቃ ዳዊት ወልደ ጊዮርጊስና ተባባሪዎቹ የተልዕኳቸውን ምስጢር ለምን ከእኔ እንደሰወሩት አልገባኝም ነበርና ጉዳዩን እንዲያብራሩልኝ ዋሽንግተን ለነበሩ በትግል ለተፈተኑ አገር ወዳድ ወንድሞች ጠየቅሁ። እነርሱም ማንኛውንም ጉዳይ ከኮሎኔል አስናቀ ጋር ተመካከሩ ብለናቸው ነበር።

እንዴት እንዳልገለጹልህ ለእኛም አልገባንም። የሚል መልስ ሰጡኝ።

ለእኔ በደፈናው የተነገረኝ ያውም ቀደም ብሎ ከሔደው ከሻለቃ ጌታቸው የሮም ስለ ተማረኩት የጦር ወታደሮች ጉዳይ ለመወያየት የሚል እንጂ ሌላ ጉዳይ ያዘለ መሆኑ አልተገለጸልኝም ነበር።እነ ኮሚሽነር ዳዊት ወደ ኤርትራ ሒደው ከሕዝባዊ ግንባር ኤርትራ መሪዎች ጋር ያደረጉትን ውይይት ለማወቅ የቻልኩት የሻለቃ ስለሺ ፍስሐ "በአንድነት፤ ለአንድነት" በሚለው መጽሐፉ፤ " ከዚህ በፊት ያልተገለጹ ሰነዶች ይዟል" በሚል መንደርደርያ በገለጸው በገጽ 61 "ዳዊት ወልደ ጊዮርጊስ በውጪ አገር የሚገኘውን ነፃ የኢትዮጵያ ወታደሮች ንቅናቄ ከለንደኑ ስብሰባ በኋላ አገር ውስጥ ከሚገኙት የሠራዊቱ ከፍተኛ ባለ ሥልጣኖች ጋር በየጊዜው በስልክ በሚያደርገው ግንኙነት እንደቀጠለ ሲሆን መፈንቅለ መንግሥት ለማድረግ ከፍተኛ ዝግጅት ላይ እንዳለ ለዚህም አፈጻጸም ከኤርትራ ሕዝባዊ ግንባር ጋር በቅድሚያ ተወያይቶ ተጨባጭ የሆኑ ዋስትና እንደሚያስፈልግ ጠቆመ" ይላል።

ከዚያም አያይዞ በገጽ 62 "አዲስ አበባ መፈንቅለ መንግሥት በሚካሔድበት ወቅት ሕዝባዊ ግንባር እንዲሁም ወያኔ ከጀርባው እንዳይወጉትና አገሪቱ የበለጠ ሽብር እንዳትገባ የተኩስ ማቆም ስምምነት ዋስትና ያስፈልገናል ስለአሉን እዚያ ድረስ የመጣንበት ስለዚህ ለመወያየት ነው። እዚህ ጥያቄ ላይ ስምምነት ከሌለ ምንም ዓይነት ሙከራ የማያደርጉ መሆኑን በድጋሚ አሳስበውናል" ብሎ ዳዊት ለሻዕቢያ መሪዎች ማስረዳቱን ይገልጻል። ከዚያም አያይዞ "ዳዊት ይህንንም ጉዳይ አገር ውስጥ ላሉት በስልክ የምንነጋገረው ስለሺና እኔ ስለሆን እሱም እንዲሁ ሊጨምርበት ይችላል አለ" ይላል።

እኔም ይላል ሻለቃ ስለሺ " ወደ ዚህ ከመምጣታችን ከሁለት ቀን በፊት በስልክ ግንኙነት እንዳደረግነው ሁሉ እንደሚሉት ከሆነ የተለያዩ የጦር አዛዦች በሥራም ምክንያት አንዱ ሲገባ አንደኛው ደግሞ እየወጣ ሁሉም በአንድነት በአንድ ላይ መገናኘት ባይችሉም ጠቅላላ ዝግጅቱ የተጠናቀቀ መሆኑን በሚፈጽሙበት ግዜ እነማን እንደሚያዙና በቁጥጥር ስር እንደሚውሉ የስም ዝርዝር የወጣ መሆኑንና ይህንንም ሥራ ማን እንደሚያካሒደው ገልጸዋል። ዋናው ጥያቄ ጦርነቱ አሁን ያለበት ቦታ መቆም እንዳለበት ነው" ብለዋል ብሎ ሻለቃ ስለሺ ንግግሩን የአሳረገው "የመጣንበት ተልዕኮ የተሳካ ስለሆነ በደስታ ላይ ደስታ ጨምረን" ተመለስን ይላል። እነ ሻለቃ ዳዊት ከኤርትራ እንደ ተመለሱ ብዙም ሳይቆይ እ/አ የጀኔራሎቹ የመፈንቅለ መንግሥት ሙከራው ተደረገ።

ሻለቃ ዳዊት ወደ ሕዝባዊ ግንባር ኤርትራ የሔዱበትን ጉዳይ ያወቅሁት ሻለቃ ስለሺ ፍስሐ የተልዕኳቸውን ምሥጢር ዘክዝኮ ከጻፈ በኋላ ነው። እነ ሻለቃ ዳዊት ምስጢራዊ ተልኳቸውን ሱዳን ለነበረው ይቅርና "ነፃ የኢትዮጵያ ወታደሮች ንቅናቄን" አብረው ለመሠረቱት በዋሽንግተን ዲ.ሲ. አብረዋቸው ላሉት ወንድሞችም እንኳ ተልእኳቸው መፈንቅለ መንግሥትን በተመለከተ ለመወያዪት መሆኑን ያልገለጹላቸውና በስብሰባም የተወያዩባቸው በምርኮ የተያዙትን ወታደሮች ለማስፈታት ብቻ ነበር ብለው ገልጸውልኛል። ይህን ከባድ



ስሁተት የፈጸሙት በሻለቃ ዳዊት መሪነት ሻለቃ ስለሺ ፍስሐና ሻምበል ፀጋዬ ብሩ ሲሆኑ ምናልባትም ዋናው ኢንጅኔር ኤርትራዊው ዶክተር የሙቶ አለቃ በርሔ እንደ ነበር ድርጊቱ ወደዚያው ይመለሳል። ሻለቃ ጌታቸው የሮምን ለሽፋን ከተጠቀሙበት በኋላ አግልለውታል።

ከነሻለቃ ዳዊት ኋላም ሁኖ የሚያቀነባብርና የሚገፋ ፀረ ኮምዩኒስት የውጭ ኃይል ነበረበት ተብሎ ተገምቷል። የትግል ልምድ ከነበራቸው አገር ወዳድ መኮንኖችም ጉዳዩ እንዲሠወር የተደረገው የኢምፔሪያሊስቶች ከፋፋይ ፖሊሲና የሚያሽከረክራቸውን የጎሣ ድርጅቶችን ይቃወሙ ስለ ነበር ነው፤ እንጂ ምስጢሩን ለመጠበቅ አልነበረም።

እኛ በሱዳን የነበርነው ታጋዮችን በጣም ያናደደንና ያበሳጨን ነገር ቢኖር እነ ዳዊት ለምን ጉዳዩን ደበቁን ከሚል ሳይሆን ያገርን ውስጣዊ ጉዳይ ኢትዮጵያዊነታቸውን ክደው ለመገንጠል ከሚዋጉት ሻዕቢያና ወያኔ ጋር ስለ መፈንቅለ መንግሥት መወያየታቸው ነበር። ስማቸው እንደሚያመለክተው በዚያን ወቅት ይሁን ከዚያም በኋላ EPLF እና TPLF ኢትዮጵያውያን ድርጅቶች አልነበሩም። የአገርን ውስጣዊ ጉዳይ ከነርሱ ጋር መወያዪት ገመናን ገልጾ ለጠላት እንደ ማሳዪት ያለ ነበር።

ኸረ ለመሆኑ ኢትዮጵያ በደርግ ጭፍን አመራር በተዳከመችበት በዚያን ወቅት መፈንቅለ መንግሥት ማድረግ ይገባ ነበር ወይ? መፈንቅለ መንግሥት የሚደረግበት ኢሠፓ. እኮ ኢትዮጵያዊ ድርጅት ነበር። ሻዕቢያና ወያኔ ግን ኢትዮጵያዊያን ድርጅቶች አልነበሩም። ሻዕቢያና ወያኔ እኮ የለየላቸው ኢትዮጵያን ለማፈራረስ የተነሱ የኢትዮጵያ ዋና ብርቱ ጠላቶች ነበሩ። ታዲያ ከጠላት ጋር ማበር ትልቅ ስህተት ነው።

ኢትዮጵያን በጦርነት ከአደሟት ይበልጥ በዓለም አደባባዮች ኢትዮጵያ የምትባል አገር አልነበረችም ትናንት ምኒልክ የፈጠራት ናት ብለው ከነ ታሪኳ ከካዷት ጋር ተስማምቶ ኢትዮጵያዊውን ድርጅት ለማስወገድ ያደረጉት ውይይት ለተገንጣዮች አደፋፋሪና ሞራል ገንቢ በመሆኑ ጤናማ ሰው ያደርገዋል ብሎ ለማመን ያስቸግራል። በእርግጥም ነው ለማለት ያስደፍራል ምክንያቱም ኢትዮጵያን ለማፈራረስ አስቀድሞ አገር ወዳዶችን ማጥፋት ያስፈልጋል ተብሎ መፈንቅለ መንግሥቱ በረቀቀ ሰዓት ተቀይሶ የተደረገ ነው። ወደ ፊት ታሪክ ዘርዝሮ እንደሚያወጣው ተስፋ አለኝ።

እነ ሻለቃ ዳዊት ስልክ እየደወሉ በመነትነት ባደረጉት ግፊት ሳቢያ፤ ጀኔራል መኮንኖች በወሰዱት ግብታዊ ርምጃ ምክንያት ምን ግዜም የማይገኙ ጀኔራል መኮንኖች ሕይወት በከንቱ ጠፍቷል። የጀኔራሎቹ መገደል ለተገንጣዮች ለሻዕቢያና ወያኔ በጦር ሜዳ ያላገኙትን ሁለተኛውንና የመጨረሻ ድል አስገኝቶላቸዋል። ለኢትዮጵያ ግን ቀዳሚ ውድቀቷ ነበር። ተገንጣዮቹ ወያኔና ሻዕቢያ ቀዳሚውን ድል ያገኙት የጀኔራል አማን ሕይወት ሲጠፋ ነበር።

እነዚያ ባልተሳካ መፈንቅለ መንግሥት ሳቢያ የተገደሉት ጀኔራሎች በሕይወት ቢኖሩ ኑሮ ሠራዊቱም መሪ አጥቶ አይበተንም

ነበር። ሻዕቢያና ወያኔም በቀላሉ አሥመራና አዲስ አበባ መግባት አይችሉም ነበር። የሚሉ ብዙ ናቸው። የመፈንቅለ መንግሥቱ ሙከራ ሆን ተብሎ አገር ወዳዶችን ለማጥፋት የተደረገ ሤራ ነው የሚሉም አሉ።

"የማይተማመን ባልንጀራ በየወንዙ ይማማላል" እንደ ተባለው እነ ደረጀ ዴሬሳ፡ የቅስቀሳና የፕሮፓጋንዳ ሥራ በትግል ልምድ የቀሰምነውን ሰውረው የፕሮፓጋንዳ በራሪ ጽሑፎችንና ካሴቶችን እንደ ማንኛውም የሸቀጥ ዕቃ በእንዝላልነት በቀጥታ ወደ አዲስ አበባ ልከው 18 ሰዎችን እንዳስገደሉ እንዲሁም እነ ሻለቃ ዳዊት "ነፃ የኢትዮጵያ ወታደሮች ንቅናቄ"ን አብረው የመሠረቱትን መኮንኖች ሳያማክሩ የወሰዱት ርምጃ ሁሉ ለተገንጣዮች የእጅ አዙር ድል ሲሆን፣ ለኢትዮዮጵያ ግን መጥፊያዋ ነበር። "እጄን በእጄ ቆረጥሁት" ነው።

እነ ሻለቃ ዳዊት አገር ወዳዶች መሆናቸውን የሚክድ የለም። ይሁን እንጂ ግለ ሰብዕን መንግሥቱ ኃይለ ማርያምን ለማጥቃት እልሁን ተተው በዚያን ወቅት መፈንቅለ መንግሥት ቢደረግ ምን እንደሚያስከትል ቆም ብለው የሩቁንና የቅርቡን የኃይል አሰላለፍ የዓለም አቀፍ ተጽዕኖን በማመዛዘን ከርዕየተ ዓለምና ከኤኮኖሚ አንፃር የሚያስከትለውን ችግር ማየት ነበረባቸው። ይህን ባለማድረጋቸው ሦስት ስህተቶችን በአንድ ግዜ ፈጽመዋል።

1ኛ. ኢሠፓ በተዳከመበት በዚያን ወቅት መፈንቅለ መንግሥት ቢደረግ ለተገንጣዮች የሚያመች መሆኑን ሳይገነዘቡ አሜሪካ ሁነው ጀኔራሎቹ መፈንቅለ መንግሥት እንዲያደርጉ ማንም በሚጠልፈው ስልክ እየደወሉ መገፋፋት አልነበረባቸውም። ትልቅ ጥፋት ነው።

2ኛ. ስለ መፈንቅለ መንግሥት ከሻዕቢያም ሆነ ከውያኔ ጋር የሚወያዩበት ወቅቱ አልነበረም።

3ኛ. አብረዋቸው የተሰለፉትን የድርጅት አባሎችን አግልለው ትልቁን ያገር ጉዳይ በጋራ ውይይት ሳይደረግበት ለብቻቸው የወሰዱት ርምጃ ተገቢ አልነበረም። ይህም ቡድናዊ ሥራ ለኢትዮጵያ ውድቀት ያመጣ በታሪክ የሚያስጠይቅ ብርቱ ጥፋት ነው።

በሰሜን ኢትዮጵያ ክፍል ይካሔድ የነበረው ጦርነት ስሙ በተገንጣዮችና በደርግ ሠራዊት መካከል እንደ ነበረ ይነገርለት እንጂ ጦርነቱ የምዕራቡና የምሥራቁ የርዕየተ ዓለም ፍልሚያ ነበር። ጦርነቱ የውክልና (Proxy) ጦርነት ነበር ማለት ይቻላል።

የምዕራቡ ዓለም 30 ያህል ልዩ ልዩ ዕርዳታ ሰጭ ድርጅቶች ሱዳን ውስጥ በስደተኛው ስም አቋቁመው ለውጊያ አስፈላጊ የሆኑትን ሎጀስቲካዊ አቅርቦት ለሻዕቢያና ለወያኔ እንዲሁም ለኦነግ ቡድኖች ያከፋፍሉ ነበር። ያልተቆጠበ የፖለቲካ ድጋፍም ሰጥተዋቸዋል። በተለይም አሜሪካ፣ እንግሊዝ፣ ስዊድን፣ ጀርመንና አውስትራሊያ ግንባር ቀደምነቱን ይያዙ እንጂ መላው የምዕራቡ ዓለም ተሳታፊ ነበር።

ደርግ ወይም ኢሠፓ በመሣሪያና በኢንተልጀንስ በሶቪየት ኅብረትና በምሥራቅ ጀርመን ሲደገፍ ቆይቶ ጎርባቾቭ (Gorbachev) የሶቪየቶቹን ሥልጣን እንደያዘ (Perestroika & Glasnost) ግልጽነት በሚል መመሪያው ለኢትዮጵያ ይሰጥ የነበረውን ዕርዳታ ቢያቆምም፣



የኢትዮጵያ ሠራዊት ያለ ምንም የውጭ ዕርዳታ የምዕራቡን ኃያል ገትሮ ይዞ ነበር። ታዲያ በዚያን ግዜ መፈንቅለ መንግሥት ቢደረግ ማንን ነበር የሚጠቅም? በቀጥታ የምዕራባውያንን ጥቅም ነበር የሚያስከብረው። እነሆም ኢትዮጵያን ለመገነጣጠል ያሰቡት ተሳክቶ ኢትዮጵያን እንድትገነጣጠል እያደረጓት ነው።

በተደጋጋሚ እንደ ታዬው፣ አንዳንድ አገር ወዳዶች ኢትዮጵያን ካደጋ ለማዳን የፖለቲካ ድርጅት ይመሠርታሉ። በድርጅቱ ውስጥ ሁለት ልብ ይዘው የሚገቡ ድርጅትን ከላይ ለሽፋን እንደ "ትሮጃን ፈረስ" በማድረግ ይገቡና ስውር ዓላማቸውን በማካሔድ ብዙ ጉዳት አድርሰዋል። መንግሥቱ ኃይለ ማርያምን ከሥልጣን ለማውረድ ሲባል ይቅርታ የማያሰጡ ጥፋቶች ተደርገዋል።

ባዕዳዊያን ለራሳቸው ስትራተጂና ርዕየተ ዓለማዊ ጥቅማቸው እንሰሳ በመላሽ እንደሚታለል በዕርዳታ እያሳበቡ በመግባት ኢትዮጵያን በተለያዩ ዘዴና ስልት ሲጎዱት ኑረዋል። ምዕራባውያን በጦር ሜዳ ተሰልፈው ሳይዋጉ ድል የሚመቱበት ዘመናዊ ትልቁ መሣሪያ ዕርዳታ ነው። ለምሳሌ የኢትዮጵያ ሕዝቦች ዴሞክራሲያዊ አንድነት ( EPDA ) ድርጅት ውስጥ እነ ደረጀ ደሬሳ እናማክራለን በሚል ሰበብ በድርጅቱ ውስጥ ገብተው የራሳቸውን ዓላማ ያራምዱ ነበር።

እንደ ማስታውሰው ሚስተር ሐዋርድ የተባለ የሲ. አይ. ኤ.ሰው ነው ተብሎ የሚነገርለት አሜሪካዊ ወደ ካርቱም ሒዶ ከአረፈበት ሒልተን ሆቴል ኮሎኔል እምሩንና እኔን ጋብዞ አነጋግሮናል። ይኸው ሰው የጋበዘን ለስላሳ መጠጥ ስለ ነበር ሒሳቡን ለአሳላፊው ሰጥቶ የሚመለስለት የሱዳን 25 ፒያስተር ወይም 25 ሳንቲም እንበለው ሳይመልስለት ስለ ዘገዬ "አያሁድ ይመስል የሳንቲም መልስ ስትጠብቅ ግዚያችን ባከነ" የሚል ቃል ስሰነዝር ኮሎኔል እምሩ "እስል እንደሆነ ምን ታውቃለህ? አለኝ። የወጣ ቃል የማይመለስ ሁኖብኝ እንጂ ስህተቴን ወዲያው ተገንዝቤዋለሁ። የሆነ ሁኖ ሚስተር ሐዋርድ ወደ ገዳሪፍ ሒጄ ለ ኢ.ሕ.ዴ.አ.ፓ. (EPDA) አባላት ምክር እሰጣለሁና ከእኔ ጋር ገዳሪፍ የሚሔድ ሰው ያስፈልገኛል በማለቱ እኔና ቀኛዝማች አርዳሚስ ሳህሌ አብረን እንድንሔድ ተወስኖ ተለያዬን።

በማግስቱ ቀኛዝማች አርዳሚስ ስልክ ደውለው ወደ ገዳሪፍ ሊወስደን የነበረው ፈረንጂ መኪናው ስለ ተሰናከለበት ወደ ገዳሪፍ መሔዳችን ቀርቷል ብለው ከነገሩኝ በኋላ፣ ሚስተር ሐዋርድ ቀኛዝማች አርዳሚስን ብቻ ይዞ ከካርቱም 412 ኪሎ ሜትር እርቃ ወደ ምትገኘው ገዳሪፍ ሒዶ ተልዕኮውን ለመሸፈን ያህል ገዳሪፍ ከነበሩ ታጋዮች ጥቂቶቹን በቀኛዝማች አርዳሚስ አስተርጓሚነት አነጋግሮ ሲጨርስ ወደ ዋናው ተልዕኮው ሒዶ የኢትዮጵያ ፈላሾችን ጉዳይ ሂሠራ ሱዳኖች ደርሰውበት ወደ ካርቱም እንደተመለሰ ተባረረ። አብረውት የሔዱትን ቀኛዝማች አርዳሚስንና እነ መሳፍንትን የሱዳን የፀጥታ ክፍል ለተወሰነ ጊዜ በቁጥጥር ሥር አውሏቸው ነበር።

በራሳቸው ባህልና ታሪክ የሚመኩትን አገር ወዳዶች ባዕዳዊያን አይወዷቸውም። ምክንያቱም የፈለጉትን እንዲያደርጉ ስለ

ማይፈቅዱላቸው በጠላትነት ይፈርጇቸዋል። በሱዳን ቆይታዬ የታዘብኩት ዓቢይ ነገር ለኢትዮጵያ ሉዓላዊነትና አንድነት የቆሙትን ድርጅቶችና ግለ ሰቦች ለመርዳት ቀርቶ ለማነጋገር እንኳ ይቀፋቸው ነበር። እንዲያውም ለአገር ጥቅም ከቆመ ድርጅትም ሆነ ግለሰብ ይልቅ ሠፊ ዓለም አቀፋዊ ኮሚንስታዊ ርዕየተ ዓለማዊ ዝንባሌ ላለው ቅድሚያ ሲሰጡ ተመልክቻለሁ። ጎጠኞቹንማ የራሳቸው ድርጅት አድርገው ነበር የሚፈርጇቸው።

የምዕራባዊያን ኢምፔሪያሊስት አገሮችን ዕርዳታ ተማምነው ልባቸውን ሰጥተው የታለሉ ራሳቸውን ከፍ አድርገው እንዲገምቱ መደረጉ ከከባድ ስህተት ላይ ጥሏቸዋል። በጥፋት ሒደት ላይ እንዲጓዙ የገፋፋቸው አንድም በድክመታቸው ላይ ውይይት እንዳይደረግ በመፍራት ነበር። ፍፃሜውም "በሬ ሞኙ ሳሩን አይተህ ገደሉን ሳታይ፡ እበላ እበላ ብለህ ገደል ገባህ ወይ" ሁሉም ተያይዞ ወደ ገደል።

## ምዕራፍ 20
## በሞት ቀጣና ጉዞ

በአገር ውስጥ የሚታገሉ የኢ.ሕ.ዴ.አ. ኃይሎች አርማጭሆን ለመውረር የዘመተውን ጦር በመጀመሪያ ፳ሺህ ዳግመኛ ፲ሺህ ተዋግተው አቸንፈው መመለሳቸውን ፲፪ የጦር መሪዎች ሐምሌ ፪ቀን ፲፱፻፸፬ ዓ. ም. ለድርጅቱ በጻፉት ደብዳቤ ገልፀዋል፤ ከዚህም አያይዘው ዓርበኛውን ኃይል የሚያደራጁና መመሪያ የሚሰጡ ሰዎች በአስቸኳይ ይላኩልን የሚል ጥሪ ስለላኩ መንቀሳቀሻ ገንዘብ ስለአልነበረን ለድርጅቱ መገልገያ የተገዛችውን መኪና ሸጠን መሔድ ግዴታ ሆነብን።ምንም እንኳ መሣሪያ የታጠቀ ጉልበታም ሁሉ መንገድ ተላላፊውን እያሸመቀ ገድሎ ገንዘብ የሚነጥቅበት ተቆጣጣሪ በሌለው ምድረ በዳ መሣሪያ ሳይዙ መጓዝ ሕይወትን ለአደጋ አጋልጦ መስጠት መሆኑን ብናውቅም፣ የዓርበኞቹ የድረሱልን ጥያቄ ግዜ የማይሰጥ በመሆኑ ማንኛውንም አደጋ ለመቀበል ቁርጥ አሳብ አድርገን ኅዳር ፭ ቀን ፲፱፻፸፩ ዓም ኮ/አስናቀ እንግዳ፣ የመ/አለቃ አያልሰው ደስዬ፣ ታጋይ አብርሃም ጣሰው፣ ታጋይ ማንደፍሮ በፈቃዱ፣ ታጋይ ፀሐዬ መዓሾ ከገዳሪፍ ወደ አርማጭሆ ጉዞ ቀጥለን ከምሽቱ ፱ ሰዓት የሱዳን የጠረፍ መንደር በረኸት ኑሪ ደርሰን ከዚያው አደርን።

በማግስቱ ኅዳር ፰ ቀን ከሱዳን የፀጥታ ሠራተኞች ጋር ተገናኝተን ከተወያዩን በኋላ ታጋይ አያልሰው ከፈረንሳይ ድንበር የለሽ ሐኪሞች ያገኘውን ዕርዳታ ማለት ለሕዝቡ የያዝነውን መድኃኒት በአህያ ጭነን ኢትዮጵያንና ሱዳንን የሚያዋስነውንጓንግ የተባለውን ወንዝ ተሻግረን ከኢትዮጵያ መሬት አደርን።

ኅዳር ፫ ቀን ከሱዳን ወሰን እስከ አዋሳ ያለው ቀጠና የደርግ አደጋ ጣዮችና ወንበዴዎች የሚያሸምቁበት አደገኛ አካባቢ በመሆኑ ከሌሊቱ ሰባት ሰዓት ተኩል ጉዞ ቀጠልን። እንዳጋጣሚ ሁኖ ሱዳን ደርሶ የሚመለስ ሻምበል ዐወቀ ወልደየስን አግኝተን በርሱ መሪነት ተጉዘን ድሮ የግምሩክ ጣቢያ ከነበረች ጎደቤ ደርሰን እረፍት አድርገን ሁለት ሰዓት ያህል ከተጓዝን በኃላ ኮረምባዲ ከተባለ ቦታ ደርሰን ከመንገዱ ወጣ ብለን ከአስራ ሶስት ሰዓት ጉዞ በኋላ አረፍን። ወደ አገር ውስጥ መግባታችንንም የሰማ ሰለሞን የተባለ የኢ.ሕ.አ.ፓ አባል አንድ ስኳድ ይዞ ተከትሎን እንደነበር ሰማን።

ኅዳር ፲ ቀን ከአዋሳ በቅሎ እንዲላክልን ወረቀት ወልዴ በተባለ ሰው ልከን በዚያው እረፍት ባደረግንበት ቦታ ዋልን።

ኅዳር ፭ ቀን ከአዋሳ አታለል (ገበየሁ) የተባለ ወጣት በቅ
ሎ ይዞልን መጣና በዚሁ አደገኛ የሞት ቀጣና ጉዞአችንን
ቀጠልን።

ኅዳር ፮ ቀን ከወረንበዴ ወደ አዋሳ ተጉዘን ጎተቴ ከተባለ
ው ቦታ ስንደርስ የአዋሳ ታጋዮች ዉብቱ ቾኮለንና ክብረቱ
የተባሉ ከእነርሱ ጋር ሰዎች ጨምረው ተቀበሉን። (ለጊዜው
ሽፍታ መስለውን ደንግጠን ነበር።) ጉዞአችንን በመቀጠል
ድግዝግዝ ሲል አዋሳ ምድር (አዲስ ዓለም) ደርሰን ከክብረ
ት ቤት አዳር አደረግን።አስደሳች መስተንግዶም አደረጉልን።

ኅዳር ፯ ቀን ሻምበል አበበ ጀምበርና ታጋይ በላይ አድ
ማሱ ታጋዮችን አስከትለው መጥተው ተገናኝተን በነርሱ መ
ሪነት ጉዞ ቀጥለን ክርክራ ዉኃ ደርሰን ከፊታውራሪ ጥሩነህ
ቤት አደርን።

ኅዳር ፰ ቀን ጉዞ ቀጥለን ጀጎል አምባ ከነሻለቃ ዘለቀ ጀ
ምበር ሠፈር ደረስን። በዚያም የአርማጭሆ ተጋዳዮች በተደ
ጋጋሚ የዘመተባቸውን ጠላት በሚዋጉበት ግዜ በጎናቸው ተሰ
ልፎ የረዳቸውና የሞራል ድጋፍ የሰጣቸው አልነበረም።አሜር
ሪካ ለነበሩ የውጭ ኮሚቴ አባላትም የገንዝብ እርዳታ እንዲ
ልኩላቸው ቢጠየቁም ተዋጊ ጦር የለንም ብለው ዓይን ያወጣ
ክህደታቸውን በመረጃዎች በኩል አስተጋቡላቸው።'አብዮታው
ያን ባንዳች ታሪካ ወቅት ይከሰታሉ' እንደተባለው የመቶ አ
ለቃ አያል ሰው ደስዬ ባይሆን ለተጎዱት መዳሕኒት እንውሰ
ድላቸው ብሎ ከደንበር የለሽ ዶክቶሮች መዳሕኒት ጠይቆ ያ
ገኘውን ወስደን ለታጋይ ኃይሎች ሁሉ በዝሁ ቦታ አከፋፈል
ን።

ባዚሁ ቦታ እንዳለን የኢ.ሕ.አ.ፓ. መሪዎች ወደኛ መጥ
ተው ግንባር እንፍጠር ብለው ጠየቁን። እኛ ወደዚህ የመጣ
ነው የዓርበኛውን ኃይል ለማደራጀትና ለመርዳት እንጂ ግን
ባር ለመፍጠር ተልዕኮ የለንም። የድርጅታችን ዓላማ ግን ከ
ሁሉም ዴሞክራሲያዊ ኃይሎችና ድርጅቶች፤ ከዓለም ዓቀፍ
የሰላም ኃይሎችና ፀረ ደርግ አቋም ካላቸው ጋር ግንባር
መፍጠር የሚል መመሪያ አለውና በድርጅት መክረን እንገል
ጽላችኋለን የሚል መልስ ብንሰጣቸው ሳይደሰቱ ከፍቷቸው
ተመለሱ። ይህም የጥላቻ መጀመሪያው ነው።

ከዚያም እስከ ኅዳር ፳፱ ቀን ድረስ ሠፈራችንን በዚያው
አድርገን በታጋዮች ቁጥጥር ሥር ለነበረው ሕዝብ መተዳደሪ
ያ ደንቦችንና መመሪያዎችን እንዲሁም ጠላት ሲመጣ እንዴ



ት እንደሚከላከሉ፤ የጓዝ ጥበቃና በግንባር ለሚዋጋው ተጋዳ
ይ የምግብ አቅርቦት ስልታዊ መመሪያዎችን ስናዘጋጅ ቆዬ
ን።

ኅዳር ፴ ቀን አርዞ ሜዳ ከተባለው ቦታ ከሻለቃ በሪሁን
ገብረየሱስ፤ ከሻለቃ ዘለቀ ጀምበርና ከሻለቃ ደሴ አያልነህ ጋ
ር ተገናኝተን የመጀመሪያ ውይይት አደረግን።

ታህሳስ ፩ ቀን ዓርብ እሳት በተባለው ቦታ ሻለቃ በሪሁን
ና ሻለቃ ዘለቀ ዋና ዋና የጦር መሪዎችን ይዘው ሻለቃ ደሴ
በተገኙበት ከኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ(ኢሕአፓ)
ጋር ስለሚኖረው ሕዝባዊ ግንኙነትና በውጊያ ስለሚኖረው
አሰላለፍና ቅንጅት ሠፊ ውይይት ተደርጎ የጦር አዛዦች የ
ሕዝብ ሠራዊት ስለሆን ሕዝቡ በሙሉ ተሰብስቦ መወያዬት
አለበት ስለአሉ በማሰሮ ደንብ ታህሳስ ፳፱ ቀን ፷፰ ዓ.ም.
የአርማጭሆና የጭልጋ ሕዝብ እንዲሰበሰብ ተቀጠረ።

ታህሣሥ ፳፱ ቀን ፷፰ ዓ.ም. የታች አርማጭሆ፣ የላይ
አርማጭሆ፣ የዳዋ፣ የአዳኝ አገርና የጫቆ ሕዝብ ተወካዮች
ባሉበት ሕዝባዊ ስብሰባ ሻለቃ በሪሁንና ሻለቃ ዘለቀ ትግሉን
አስመልክቶ ለሕዝቡ ሰፊ ንግግር አደረጉ። ንግግራቸውም ያ
ተኮረው ከኢሕአፓ ጋር የሚኖረው ሕዝባዊ ግንኙነት ምን
መሆን እንዳለበት ሕዝቡ ይወስን የሚል ነበር። ከእነርሱም ቀ
ጥሎ ከሰባት ደብር ተወክለናል የሚሉ አራት ሰዎች አያናው
ተፈራ፣ ታላቁ አባተ፣ አባሆይ ሞላና መንግስቱ መራ ኢድ
ጎን እንወክላለን ብለው ንግግር ቢያደርጉም ሕዝቡ ሳይቀበላ
ቸው ቀረ። ከዚያም ጥሪ ሳይደረግላቸው በስብሰባው ከተገኙት
የኢሕአፓ አባሎች አበበ (ጸጋዬ ገ/መ)የተባለው የኢሕአ
ፓ ያመራር አባል ከሕዝቡ ጋር ተዋህደን አንድ ሁነናልና
አስተዳደሩን መሥርተን እንታገል የሚል ነበር። በዚህ ውይይ
ት ግዜ ከሱዳን ከኢ.ሕ.ዴ.አ. የተላከነው አስፈላጊ ሁኖ ስለ
አልታየን ንግግር አላደረግንም ነበር።

የተሰበሰበውም ሕዝብ የሁሉንም ንግግር ካዳመጠ በኋላ ለ
ሕዝባዊ ሠራዊት መሪዎችና ለኢ.ሕ.አ.ፓ. መሪዎች መክረን
እንነግራችኋለንና ገለል በሉልን ብሎ ከአገለለ በኋላ ተወ
ያይቶ ያሳለፈው ውሳኔ፤

፩. አስተዳደሩን ሕዝቡ ይዞ ታች አርማጭሆ በሻለቃ ዘለቀ
ጀምበር፤ ላይ አርማጭሆ በሻለቃ በሪሁን ገብረየሱስ ይመራ
ል፤

፪. መመሪያችንም ኢ.ደ.ኅ. ይዞት እንደነበረው ዓይነት ዴሞክራሲ ነው፤

፫.የመረጥናቸው ሻለቆች ይጠቅማል የሚሉትን ድርጅት መቀበል ይችላሉ፤ እነርሱ ያልተቀበሉትን ድርጅት አንቀበልም፤

፬. ከኢ.ሕ.አ.ፓ. ጋር ተባብሮ መታገል ያስፈልጋል፤ በአስተዳደር ውስጥ ግን አይገቡም እንጂ በምግብ ረገድ እንረዳቸዋለን የሚል ነበር።

ይህንኑ የጠቅላላውን ሕዝብ ውሳኔ ተግባራዊ ለማድረግ በስብሰባው ማግስት ታህሣሥ ፴ ቀን የሕዝብ አስተዳደሪና የጦር መሪዎች ማሰሮ ደንብ አካባቢ ስብሰባ አድርገው በሚወያዩበት ግዜያት ኢ.ሕ.አ.ፓ. ዎች ሳይጠሩ በስብሰባው ላይ በመገኘት እነዚያን የኢ.ዴ.ኅ. አባል ነን የሚሉትን አራት ሰዎች እንዲናገሩ ገፋፍተው አራቱም ሰዎች ያርማጭሆ ሕዝብ ኢ.ዴ.ኅን እንጂ ሌላ ድርጅት አይደግፍም በማለታቸው የሻለቃ ዘለቀ አብሬ የመሠረትኩትና ሶስት ሺህ ሕዝብ የፈረመበት(ኢ.አ.ወ.ዴ.ድ.) የአገር ወዳዶች ድርጅት አለኝ ሌላ ድርጅት አልቀበልም ብለው እቅጩን ተናገሩ። ሻለቃ በሪሁን ግን ቁርጠኛ አቋም ሳይወስዱ ሕዝብ የሚለኝን አደርጋለሁ ካሉ በኋላ ውይይቱ በዚሁ ተዘጋ። ኢ.ሕ.አ.ፓ. በዚያን ግዜ የኢ.ዴ.ኅ. አባል ከነበረው ከሻለቃ ኢያሱ አያልቅበት (ኪዳኔ) ጋር ግንባር መስርቶ ስለነበር በኢ.ዴ.ኅ. አሳቦ በመግባት ያስተዳደር መዋቅሩን ለመዘርጋት ያሰበ ይመስላል። ጉዳዩን በጥልቀት ሲመለከቱት በሁሉም በኩል ስህተት ነበር።

ምክንያቱም ሕዝቡ በአስተዳደር ውስጥ አትገቡም ብሎ ስለወሰነ ተበሳጭተው መግቢያ ቀዳዳ ፈልገው ያገኙት በኢ.ዴ.ኅ. ሥም መዋቅራቸውን መዘርጋት ነበር። ከድርጅታዊ ጥቅም ሌላ እልህም ታክሎበታል፤ ኢ.አ.ወ.ዴ.ድም አስታራቂ መንገዶች አልፈለገም።

ሕዝብ በጉባኤ አቋሙን ከወሰነ በኋላ የመቶ አለቃ አያልሰው ደስዬ የነበረውን ጠቅላላ ሁኔታ ለማስረዳት በሕክምና ይረዳን የነበረውን ይዞ ወደ ሱዳን ተመለሰ። እኔ ከሻለቃ ዘለቀ ጀምበር ጋር የታች አርማጭሆን፣ ማንደፍሮ በፈቃዱ ከሻለቃ በሪሁን ጋር በመሆን የላይ አርማጭሆን ሕዝብ በየደብሩ የአገር ወዳዶችን ዴሞክራሲያዊ ድርጅት መዋቅር በመዘርጋት በማህበር እንዲደራጅ በየደብሩ መንቀሳቀስ ጀመርን። ዮሴፍ የተባለው የኢ.ሕ.አ.ፓ. አመራር አባል እኛን እየተከተለ በኢ.ዴ.ኅ. ሥም ለማደራጀት ሞክሮ ሳይሳካለት ቀረ። ከዚህ ቀደም ብሎ ወደ ላይ አርማጭሆ ጉዟችንን ቀጥለን ነበር።



ታህሳስ ፳፫ ቀን ከጀጎል አምባ ተነስተን ጃንድባ አደርን። ታህሳስ ፳፭ ቀን ከፈልፈል ተነስተን በሳንኪ በኩል ወደ ጉራባ ተጓዝን።ታህሳስ ፳፮ ቀን ከጉራባ ተነስተን በማንተይ ጉራን ጉር መሬት አልፈን ደብረሲና ከተባለው ክልል በስተደቡብ ገደላማ መሬት አደርን። ታህሳስ ፳፯ ቀን ወደ እግዚአብሔር አብ ተጉዘን በ፬ ሰዓት ገደማ እግዚአብሔር አብ የሻምበል ናቃቸውን ተገናኝተን ትንሽ አርፈን ጉዞ ቀጥለን። ከቀኑ ፮ ሰዓት ከሻለቃ በሪሁን ጋር በደብሩ ተገኝተን ለደብሩ ሕዝብ አጭር ገለጻ ሰጠን። በዚህ ዕለት የደርግ ታጣቂ የነበሩ አማረ ገብረ ሕይወትና ልጃቸው ከፈተው አማረ ምህረት ጠይቀው ገቡ። በእግዚአብሔር አብ ምንም ተቃዋሚ አልነበረም። የደርግ ታጣቂ ሁሉ ምህረት ጠያቂ ነበር። ከታች አርማጭሆ በሻምበል ቸኮል የተላኩ መንገድ መሪዎችም ወደ ሠፈራቸው እንዲመለሱ አደረግን።

ታህሳስ ፳፰ ቀን ከእግዚአብሔር አብ ዳበዝዮን ሚካኤል አምርተን ከቀኑ ዘጠኝ ሰዓት ከሻለቃ በሪሁን የጦር መሪዎች ጋር ተወያይተን እንደጨረስን የአንገረባ ጽዮንና የጋምባራ ካህናት ስዕለ መስቀል ይዘው በመምጣት አዝመራችንን ለመሰብሰብ የአንድ ወር ግዜ ይሰጠን ብለው ጠየቁ። በዚያ አካባቢ ደርግን የሚደግፍ ተቃዋሚ አልነበረም።

ጥር ፮ ቀን ከሠፊ ባሕር ተነስተን ወደ ታች አርማጭሆ ተጉዘን ባርቡሺ ገባን። ወደዚያ የተመለስንበት ምክንያት ወደ ሱዳን በሚወስደው መንገድ ድርማ ከተባለው ወንዝ ፩፻፰ በሬና ፺ አህያ የደርግ ታጣቂዎች ከአብደራፊ ተነስተው አደጋ ጥለው ወሰዱብን ብለው ስለአመለከቱ ታጋዩን ኃይል አሰባስቦ አደጋ ወደ ተጣለበት ቦታ ሔዶ አጠፋውን ለመመለስና አካባቢውን ከደርግ አደጋ ጣዮች (ለመቆጣጠር) ነፃ ለማድረግ ነበር።

ጥር ፯ ቀን ፸፩ ዓ.ም. ከቦርቦሺ ወደ ጀጎል አምባ ጉዞ ቀጥለን መንገድ በመሳት ሰላሳ ደቂቃ ያህል ናውዘን መንገድ አግኝተን ጀጎል አምባ በደኅና ገባን። መንገድ የሳትነው የአካባቢ ተወላጆችን መንገድ መሪ ባለመያዛችን ነበር።መንገድ ካገር ልጅ፣ ስርቆት ከሹም ልጅ የሚባለውን አልተከተልንም።

ጥር ፲፩ ቀን ጀጎል አምባ ከነሻለቃ ዘለቀ ጋር የጥምቀትን በዓል አክብረን ዋልን።ጥር ፲፪ ቀን ከጀጎል አምባ ተነስተን በሳንኪ ወንበላ በር አልፈን ግዜው ስለመሸ ከመንገድ አድረን በማግስቱ በማሰሮ ደንብ በኩል አልፈን ስንኮት ገባን።

ጥር ፲፫ ቀን እነሻለቃ በሪሁን ቀጠሮውን አክብረው ስለአ
ልመጡልን ከዚያው አታላይ ከተባለ ሰው ቤት አደርን። ጥር
፲፬ ቀን ሻለቃ በሪሁን የላይ አርማጭሆን ተጋዳይ ይዘው ከ
ቀኑ ስድስት ሰዓት ሲሆን ደርሰው ወደ ሱዳን የሚወስደውን
ጎዳና ለማጽዳትና በዚያውም አብደራፊ ባለው የደርግ ጦር ላ
ይ አደጋ ለመጣል፣ በተጨማሪም ሕዝብ ጠርቷቸው ከሱዳን
የሚመጡትን መሪዎች ለመቀበል ሰፊ ውይይት ተደረገ።የው
ይይቱ ተካፋዮች ከሻለቃ በሪሁን በኩል ከላይ አርማጭሆ፤
፩. ሻለቃ በሪሁን
፪. ሻምበል አባሆይ መኮንን
፫. ሻምበል ማሞ ገብረ ሚካኤል
፬. ሻምበል ቆያቸው ለውጤ
፭. ሻምበል ባይተኩስ ቆለጭ
፮. መቶ አለቃ አሻግር ብዙነህ
፯. ታጋይ ወረደ ወልደ ሚካኤል ሲሆኑ
ከታች አርማጭሆ በሻለቃ ዘለቀ ጀምበር በኩል ተካፋይ የነ
በሩ፤
፩. ሻለቃ ዘለቀ ጀምበር
፪. መቶ አለቃ ወልዴ ፈለቀ
፫. ታጋይ ደምለው ፈረደ
፬. ታጋይ በላይ አድማሱ ነበሩ።
ወደ ሱዳን የሚወስደውን አውራ ጎዳና ነፃ ለማድረግና በ
ዚያውም አብደራፊ ያለውን የደርግ ጦር ለማጥቃት በታቀ
ደው ዘመቻ ኢ.ሕ.አ.ፓ. ጥሪ ተደርጎለት ነበር። ሆኖም ሥ
ራ አለን በማለት የብዙኃን ድርጅት ሠራተኛ የነበረውን ሰሎ
ሞን ተብሎ በትግል ስሙ የሚጠራ አባላቸውን መልዕክት እ
ንዲነግር ልከው በስብሰባው ሳይገኙ ቀርተዋል።
ለውይይት የቀረበው አጀንዳ፤
፩. የንግድ መገናኛ የሆነውን ወደ ሱዳን የሚያስገባውን መን
ገድና አካባቢውን ከደርግ ታጣቂም ይሁን ከደርግ ጦር ነፃ
ማድረግ፤
፪. ከአብደራፊ እየተነሳ አደጋ የሚጥለውን የደርግ ጦር አጥ
ቅቶ ቦታውን መቆጣጠር ይህም ባይቻል ከምሽጉ እንዳይወጣ
ማድረግ፤
፫. ታጋዩ ወደ አብደራፊ ሲዘምት ከጎንደር ጦር አዝምቶ ሕ
ዝቡን እንዳያጠቃ ተጋዳዩ ተከፍሎ ሕዝብን እንዲጠብቅ፤



፬. አዋሳ ለመተማ ቅርብ በመሆኑ ሕዝቡን አስተባብሮ ጥበቃ
ውን እንዲያጠናክር ማስተባበር፤
፭. የጫቆ ታጋዮች ወደ መተማ የሚወስደውን መንገድ እን
ዲቆጣጠሩ፤ በሕዝብ ለተመረጡት መሪዎች መመሪያ መስ
ጠት የሚሉ ነበሩ።
ጉባኤው ከተወያዩ በኋላ የተስማመበት፤
፩. ስለ መንገዱ ጥበቃና አሰሳ ከላይና ከታች አርማጭሆ የ
ተውጣጡ ፺ ሰዎች መንገዱን በቋሚነት እንዲጠብቁ፤
፪. ከሁሉ ቅድሚያ ሊሰጠው የሚገባ የምስራቁን ግንባር ገም
በራን፣ ማኺንንና ጃኒፈንቀራን አጠናክሮ እስከ ጎንደር ከተማ
መግፋት፣
፫. የጫቆ ተመራጮች ዕርዳታ ስለጠየቁ ለሻለቃ ደሴ ተጨ
ማሪ ኃይል ሰጥቶና አጠናክሮ ጭልጋ(አይከል)የሠፈረውን
ጦር እያዋከቡ ከምሽጉ ወጥቶ በሕዝብ ላይ አደጋ እንዳይጥ
ል ማድረግ በሚሉ ውሳኔዎች ላይ ተስማምተው ጉባኤው የዕ
ለቱን አጀንዳ ዘጋ።
በዚሁ በተጋዳዩ ጉባኤ ውሳኔ መሠረት አብደራፊ የሠፈረ
ውን የደርግ ጦር አጥቅቶ ወደ ሱዳን የሚወስደውን መንገድ
ለመቆጣጠር ተጋዳዩ በጋለ ወኔ ጉዞ በጀመረበት ወቅት ነበር
በነቢትወደድ አዳነ ላይ አደጋ መጣሉ የተሰማው። ከኢ.ሕ.
አ.ፓ. ጋር ቅራኔ የተፈጠረውም ከዚህ በኋላ ነው። ከዚያ በ
ፊትማ የኢ.ሕ.አ.ፓ. ሠራዊት ከሕዝቡ ጋር ሰምና ወርቅ
ሁኖ ተስማምቶ ይታገል ነበር።
የነቢትወደድ አዳነ መገደል በኢትዮጵያ ላይ ከፍተኛ ጉዳ
ት አድርሷል።
፩. ለአገር ሉዓላዊነትና ለፍትሕ የቆሙትን አገር ወዳድ ታጋ
ዮች እርስ በርሳቸው እንዲጋደሉ ምክንያት ሁኗል፤
፪. የተጋዳዩን ቅስም ሰብሯል፤
፫. ለኢትዮጵያ አንድነትና ፍትሕ የሚደረገውን ትግል አኮላ
ሽቶ ኢትዮጵያን ከአደገኛ ሁናቴ ጥሏታል፤
፬. ኢትዮጵያን ገነጣጥሎ ለማጥፋት ለሚታገለው ወያኔ ትግ
ራይ (ሕወሐት) ወደ ማህል አገር ገብቶ በመስፋፋት ሥ
ልጣን በመያዝ ኢትዮጵያዊያንን ለመከፋፈል ሁኔታዎችን አ
መቻችቶ ሰጥቶታል።

ታጋይ ዓርብኞች ለውጭ ኮሚቴዎች የላኩት ደብዳቤ ለ
ማስረጃነት ቀርቧል።

ሃምሌ ፪ ቀን ፩፱፻፹፬ ዓ. ም.
ለኢትዮጵያ ሕዝቦች ዴሞክራሲ አንድነት ድርጅት
ለውጭ ኮሚቴዎች
ባሉበት።

ጉዳዩም፤ በኢትዮጵያ ዴሞክራሲ ሕግና ዓላማ የሕዝቡን መብት በመርገጥ ፋሺስታዊ ተግባሩን በመቀጠል ለተዋህዶ ሃይማኖታችንና ለኢትዮጵያ ዴሞክራሲ ለመብትና ለነፃነት ክብር ሰንል ያለማቋረጥ በየግዜው ደማችንን እያፈሰስን በቅርቡ ግዜ ስለአደረግናቸው ውግያዎች በዝርዝር ለመግለጽ፤
፩ኛ፣ በሻለቃ በሪሁን ገ/ኢየሱስ የሚመራው ታጋይ ጦር በ ፪/፩/፹፬ ዓ.ም. በጭልጋ አውራጃ ዳዋ ዳንጉራ ከተማ አደጋ በመጣል መስሪያ ቤቱን አቃጥለን፣ ፀረ ሕዝቦችንም አሳደን በሻለቃ ዘለቀ ጀምበርና በሻለቃ ደሴ አያልነህ የሚመራው ታጋይ ጦር በአዳናጋሪ በመግባት ሰርዋ ከተባለው የምክትሉን መ/ቤት አቃጥለን ደምሰናል። ከዚያም ሕዝቡን አስተባብረን በ፳፬/፹፬ ዓ.ም. በ፫ቱ አውራጃ የዘመተው የጠላት ጦር ከሳንጃ ሰፊ ባህር ኪዳነ ምህረት ገብቶ በ፳፭/፹፬ ዓ.ም በጭልጋ አውራጃ ታጋዮች ወዳሉበት ጠላት ተሻግሮ አደጋ በመጣል ጠላት ከፍተኛ ጉዳት ደርሶበታል። ከወገን ታጋዮች ግን ታጋይ ተካ ደሴ ቆስሎ በ፳፯/፹፬ ዓ.ም. ማሰሮ ደንብ በሕዝብ ፊት ቁስለኛውን ረሺኖ ያካባቢውን ሰላማዊ ሕዝብ መሣሪያውን ላሙን በሬውን ፍየሉን እያረደ በላ። በ፳፰/፹፬ ታጋዮች ወዳሉበት አደጋ በመጣል በሻለቃ በሪሁን ገ/እየሱስ የሚመራው ታጋይ ጦር በሁለት በኩል ገብቶ ከወረዳው ቀንደኛ ተወርዋሪዎች አምስቱ ሲሞቱ ሰባት ቁስለኞች አንድ እጄ ሰሪና አንድ ክላሺን ማርከናል። በ፴/፹፬ በሻለቃ በሪሁን ገ/እየሱስ፣ በሻለቃ ዘለቀ ጀምበርና በሻለቃ ደሴ አያልነህ በሚመራው ታጋይ ጦር አደጋ በመጣል ከትግራይ ዘማቾች በከፍተኛ ደረጃ ሲሞቱ የተለያዩ መሣሪያዎች ስምንት ተማርከዋል፤ ከወገን ታጋይ ሻምበል ማሞ ማለዳና የመቶ አለቃ ስመኝ ምናለ ታጋይ ሹምዬ ሙጬ ተሰውተዋል። ቀላል ቁስለኛም ሻምበል ጫቅሌ አየለ፤ የመ/ መስፍን መለሰ፤ ጓድ አዲሳለም፤ ታጋይ አደገ፣ ታጋይ ጎዳናው በአጠቃላይ ፰ ቁስለኛ ሲሆን በ፩/፩/፹፬ ዓ.ም. ጠላት ከድቶ በመሸሹ ከሽብሩ ብዛት የወገን ታጋይ ጦር በአንድ በር ደፈጣ ይጠብቅ የነበረው ጠላት ወደ ጭልጋ አውራጃ በሌሊት ሲሄድ ተ



ኩስ በመክፈት ፸ እስረኛና ከሺህ በላይ የሚሆን የቀንድ ከብት አስጥሎታል። ጠላትም እርስ በእርሱ ሲማታና በመበታተኑ እስከ አምስት ቀን ሴቱም ወንዱም መሣሪያውን እንደእንጨት ለቅሞታል። በአጠቃላይ ከጠላት የተመታው ከ፹ በላይ ሲሆን የቆሰለውን ማወቅ አልተቻለም። የተማረኩት መሣሪያዎች ፩፻፶፯ ናቸው።
ከዚህም በኋላ ደርግ ያለማቋረጥ አምስት ቀን ባደረገው በአየር ድብደባ ፭ሰዎች ሲሞቱ ፲፪ ቆስሏል፤ ፶፪ ቤት ትቃጥሏል። እግረኛው ጦር ደግሞ ሳንኪ ፩፻፹ ቤቶች እስከመላ ንብረቱ አቃጥሏል። ታጋዩም አሰሳ ሲሄድ ተወርዋሪ በሆነው ፀረ ሕዝብ ሁለት ታጋዮች ታጋይ አማረ ባየውና በለው ገብሩ ሲሰዉ ከጠላት አጥፊው ፀረ ሕዝብ ተመትቷል። በአሁኑ ግዜ የጎንደር አውራጃ ታጋይ ሕዝብና የጭልጋ አውራጃ ታጋይ ሕዝብ የወገራ አውራጃ ታጋይ ሕዝብ በአንድ ላይ እየተገናኙ አንድነትን እየመሠረተ ኃይሉን እያጠናከረ በመስከብና በፋሺስቱ ደርግ ፍጹም የሆነ ቆራጥ እርምጃውን እየወሰደ ነው። ይህንንም ተመልክቶ ምዕራባዊ ዴሞክራት ረጂ መንግሥታት አውቆት እርዳታውን እንዲያፋጥንልን በዚህ መሠረት ለሱዳን መንግሥት ጸጥታ ክፍል አቅርባችሁ አቤቱታችንን እንድ ታስፈጽሙልን ሰንል ከትግል ሰላምታችን ጋር እንገልጻለን።
አሳሳቢዎች፤

(በየስማቸው እቅጣጫ ፊርማ አለው)
፩. የሻለቃ በሪሁን ገብረየሱስ፣
፪. የሻለቃ ዘለቀ ጀምበር፣
፫. የሻለቃ ደሴ አያልነህ
፬. የሻለቃ ጠጋ አገኘሁ
፭. የሻምበል ዋናው አዳነ
፮. የሻምበል መኮንን ለጋስ
፯. የሻምበል አወቀ ወልደየስ
፰. የመቶ አለቃ አማረ ዘውዴ
፱. የመቶ አለቃ አባተ ላቀው
፲. የሻምበል ቸኮል ሙጬ
፲፩, የሻምበል አይንየ በዛብህ
፲፪. ታጋይ ይፍሩ ገ/ሚካኤል

## ጥፋትን መቃወም መብት ወይስ ወንጀል?

የሰው ልጅ በዚህች ብቅ ብሎ ታይቶ ከመቅጽበት በሚሰ
ወርባት ዓለም ብዙ ፈተናዎች ይገጥሙታል። ሰው በዚህችው
ቅጽበታዊ ዓለም ሕይወቱ እንደ አሸን ታይታ የምትጠፋ መ
ሆኗን የሚያስተውልና የሚያሰላስል ቢሆን ኑሮ የመኖር ተስፋ
ው እየተቋረጠ ተጋብቶ መራባትን እያስወገደ የመኖር ተቃራ
ኒ በመሆን ዛሬ እሞት ነገ እሞት እያለ መንፈሱን በማስጨነ
ቅ ጥቅም ፍለጋ በመባዘን ወንጀል ለመሥራት አይጣደፍም
ነበር።

ዳሩ ግን ተፈጥሮ ሞትን እንዲረሣ እያደረገ ለዓለማዊ ኑ
ሮ እንዲማስን ያደርገዋል። ስለዚህም ነው የሞተ ዘመዱን ቀ
ብሮ ሲመለስ በሟቹ ንብረት አወራረስ በቤተሰብ መካከል
የእርስ በርስ መካሰስ የሚያስከትለው። ሞትንም በቅጽበት ደ
ራሽ መሆኑን ወዲያው ይረሳል።

እውነትን የተከተለ፣ የዓለምን ከንቱነት የተረዳ ጠላት ይበ
ዛበታል። የሥልጣን ብልግናንና ሙስናን የሚቃወምም ባለሥ
ልጣኖች ይቃወሙታል፣ ጤና አይሰጡትም። ሰው በወጣትነ
ቱ ዘመን በሥልጣን ክብር፣ በሃብት በልጽጎ ከሰው ሁሉ በላ
ይ ሁኖ ለመኖር ሕገ ወጥ ድርጊቶችን ይፈጽማል። ለግል
ሥልጣን ወይም በሃብት ለመበልጸግ የሌሎችን መብት ለመን
ጠቅ ክፉ ሥራዎችን ያቅዳል። ከዚያም ምኞቱንና ፍላጎቱን
ከግብ ለማድረስ እንደእርሱ እኩል ተፈጥሮ ያላቸውን ሰዎች
የተንኮል አሽከላዎችን እያጠመደ ጠልፎ በማስገባት ሌላውን
አጥቅቶ እየዘረፈ ለመኖር በሚያደርገው የሩጫ ወቅት ለዘለዓ
ለም ሕያው ሁኖ እንደሚኖር እንጂ እንደ እነዚያ እንዳጠፋ
ቸው ሰዎች እርሱ በተራው ጠፊና አላፊ መሆኑን አያስታው
ሰውም። እንዲያውም ጀብደኛ ሁኖ ይፈክርበታል።

ለምሳሌ እነ ሂትለርን፣ እነ ሙሶሊኒን፣ እነፖል ፖትን፣
እነ ኢዲ አሚንንና በመንግሥቱ ኃይለ ማርያም የተመራው
ደርግ አሰቃቂውን ዘግናኝ ግፍ የፈጸሙት በወጣትነት ትኩ
ስ መንፈስ ነው። ያም ብርሃን መስሎ የታያቸው የጭካኔ ድ
ርጊት ወደ ዘላለማዊ ጨለማ እንጦርጦስ ወርውሯቸው በግል
ጽ እየታዩ የነርሱን የጥፋት ጎዳና ተከትለው የነጎዱ የትግራ
ይ ወያኔና የኤርትራው ሻዕቢያ በግብረ ገብ ትምሕርት ታን
ጸው ባለማደጋቸው ምክንያት በራሳቸው አገርና ታሪክ ላይ



አምፀው በወገናቸው ላይ አረመኔአዊ ግድያና ግፋዊ ጭፍጨ
ፋ አካሂደዋል፤ አገራቸውንም በጎሣና ቋንቋ መከፋፈላቸውን
እንደ ትልቅ ጀብድ ቆጥረውታል።

ምድር አሰሱን ገሰሱን፤ ጉድፉን ሁሉ እየዋጠች ስታስገባ
ያ ከፍተኛ አይበገሬ ሥልጣንና ሰማይ ጠቀስ ብልጽግና ደል
ቦና ሰብቶ ስቡ ሲተናነቅ ገፍቶ ወደ አዘቅት ሲያስገባ እንጂ
ተከላክሎ ሲያድን አልታዩም። ከዚህም የተነሳ በዓፄው ሥርዓ
ት ሥልጣንና ሃብትን፤ ሙገሳንና ዝናን በነፍሰ ገዳይነት ፈ
ርጄ ለባዶ ከንቱ ነገር ማገልገልን አስወግጄ፣ የሕሊና ነፃነት
አግኝቼ ነበር። ሁኖም እነዚያ መሠረታዊ የሆኑ ሰብአዊ ክብ
ሮች እየተረገጡ፣ ሕሊናዊ ነፃነቶች እየተገሠሡ በአስከፊ ሁ
ኔታ ሕዝብ ሲጨቆን፣ ሲረገጥና ሲንገላታ፤ በዘር፣ በቋንቋና
በጎሣ እንዲሁም በሃይማኖት እየተከፋፈለ ወደ ባሰ ጨለማ ሲ
ጓዝ በማዬቴ ከዓፄው ክፉ ሥርዓት ራሴን በማግለል ያገኘኋ
ትን ሕሊናዊ ነፃነት አጥፍቶ በከባድ ጭንቀትና ሃሳብ ላይ ጥ
ሎኛል። ከአእምሮአቸው የተሰናበቱ፣ ዕውር ጀብደኞችን ለ
መፋለም የዕድሜዬ ሁኔታ ባይፈቅድልኝም እህል መብላት እ
ስከቻልኩ ድረስ ድንቁርናን የሚዋጉትን ኃይሎች በሚቻለኝ
ሁሉ እንድደግፍ ሁኔታዎች አስገድደውኛል። ስለዚህ ወደ ሕ
ሊናዊ ባርነት የመለሰኝን የወንበዴ ሥርዓት ከመታገል በስተ
ቀር ሌላ አማራጭ አላገኘሁም። ለእኔ ነፃነቴ ለመብት መከራ
ከሬ ነው። ለእኔ ሃብቴ ለእውነት መቆሜ ነው። ለእኔ ጽድቄ
ኀሰኛ ከፋፋይን መቃወሜ ነው።

ቀደም ብሎ በረጅሙ የአገልግሎት ዘመኔም በዘልማድ
'ሲሾም ያልበላ፥ ሲሻር ይቆጨዋል' በሚል የመዝረፊያ ዘይ
ቤ እየተመሩ በሥልጣናቸው መከታነት የሚያስተዳድሩትን ሕ
ዝብ የሚዘርፉትንና የሚጨቁኑትን፤ ፍትሕ ያጓደሉትን፣ ሥ
ርዓት ያዛነፉትን በመቃወሜ ሁለት ግዜ ቦምብ አስጥለውብኛ
ል፣ ሦሥት ግዜ የመግደል ሙከራ አድርገውብኛል። ከዚህ
ም ሌላ ሥልጣን ያለው ሁሉ በየተዋረዱ ከሳሽ የሚል የቅጽ
ል ስም አውጥተው በብርቱ ይከታተሉኝ ነበር። እንዲያውምባ
ንድ ወቅት ኮሎኔል አለሙ ቂጤሳ የተባሉ የመጅሊስ ሰው
እኔ ወዳለሁበት ሥንቅና ትጥቅ ተዛውረው ሲመጡ ከጄነራል
ኃይሌ ባይከዳኝ ጋር ተገናኝተው ወደ ሥንቅና ጥጥቅ ተዛው
ረው መሔዳቸውን ለኃይሌ ቢነግሩት 'ለምን አልጋ አልያዝ
ክም' ብሎ ይጠይቃቸዋል። ዓለሙ ቂጤሳም 'አልጋ ምን
ሊያደርግልኝ እይዛለሁ' ብለው ቢመልሱለት 'ከምትሔድበት
ክፍል አስናቀ አለና ከስሶ ያሳስርሃልና ወህኒ ቤት ስትገባ የ

ምትተኛበት ነው' ይላቸዋል። ኮሎኔል ዓለሙ በጣም ብልሀ
ና አርቆ ተመልካች በመሆናቸው ለኃይሌ ባይከዳኝ የመለሱለ
ት 'እኔ ወህኒ ቤት የምገባው ከሳሽ የለብኝም ብዬ ስልክሰክ
ስ ነው፤ከሳሽማ ካለ ተጠንቅቄ ስለምሠራ ወህኒ ቤት አልገባ
ም' ብለው መልሰውለታል። ይህን ለምሳሌ ያህል ጠቀስኩት
እንጂ በየትኛውም ክፍል የዚህ ዓይነት ድርጊት ይፈጸም ነበ
ር።

የመንግሥት ንብረት ያባከነን፣ ወይም በአስተዳደር የበደለ
ን ባለሥልጣን የተቃወመን ምክንያት እየፈጠሩ ያዋክቡት ነበ
ር። ከዚሁ በተያያዘ ሙስና የበዛበትን የዓፄ ኃይለ ሥላሴን
መንግሥት ለመገልበጥ አሲረሃል ተብዬ በጥርጣሬ በ፩፱፻፶፫
ዓ.ም. ፲ ወር ታስሬ ተፈታሁ። እንደገና በ፩፱፻፶፮ ዓ.ም.
ተይዤ አምስት ዓመት በዓለም በቃኝ ወህኒ ቤት ታስሬያለ
ሁ። መቼም ፍትሕና ርትዕ አይጓደል የሕዝብ ሕሊናዊ ነፃነ
ቱ አይታፈን፣ ሰብዓዊ መብት ይከበር ማለትን ከመንግሥት
ግልበጣ ጋር እያያያዙ በመክሰስ የሚሾሙና የሚሸለሙ ነበሩ
።ለአንዳንዶቹማ ክብረ-ነክ ዘለፋ እያሉ ወሬ በማቀበል መተ
ዳደሪያ ባጀት አድርገውት ነበር።

ሥልጣኔ በራሱ ኃይል እየገፋ በመሔድ በዓለም ላይ የብ
ርሃን ጨረር በፈነጠቀበት፣ እውነት በተከሰተበት፣ ሳይንሳዊ
ዘመን ሃሳብን ለመግለጽ ሕሊናዊ ነፃነትን፣ በማኅበር የመደራ
ጀትን፣ በመንግሥት የሥልጣን ተካፋይ የመሆን መብትን ተ
ነፍጎት፤ የምጣኔ ሀብት በጠመንጃ አፈሙዝ አሸንዳነት ለአን
ድ ቡድን እየተንቆረቆረ የሕዝብን ሕይወት በባሩድ ጢስ የጋ
ረደውን መራኸ ኃይል ለማስወገድ እያንዳንዱ ታጥቆ በመነሳ
ት ሰብዓዊ መብትን እንዲያስከብር፤የተበተነውን ለማሰባሰብ፣
የተራራቀውን ለማቀራረብ፣ የተቀያዬመውን ለማስማማት በጉ
ባዔ አበው ስም በጽሁፍም በመድረክም አሳስቤያለሁ።

ለረኃብና በሽታ፣ ለመጨቆንና ለመረገጥ ሕዝብን አሳልፎ
የሰጠ፣ በአንድነት ተሰብስቦ በሆነው መንገድ መብትን ለማስ
ከበር ጥረት ባለመደረጉ መሆኑን ሁሉም የሚክደው አይደለ
ም። በእርግጥ አንዳንድ የፖለቲካ ድርጅቶች ሕዝብን ለማሰባ
ሰብ ብዙ ውጣ ውረድና ልፋት አድርገዋል። በተለይም ኢ.
ሕ.አ.ፓ እና ከፋኝ የዓርበኞች ግንባር። ይሁን እንጂ አብዛ
ኛው በተለይ ከአገሩ ውጭ በስደት ያለው ኢትዮጵያዊ በጆሮ
ው የአገር አድን ጥሪን አልሰማበትም። በዓይኑም አይቶ በሕ
ሊናው አልሠራበትም። ወደ ፊትም ሆነ አሁን ያለው አገራ



ዊ ግዳጅ ለዴሞክራሲያዊ መብቶችና ለሕልውና ሁሉም ተባ
ብሮ ካልተነሳ ኢትዮጵያ የምትባል አገር ትጠፋለች እየተባ
ለ የተነገረው ማስጠንቀቂያ ወደ እውነትነት እንዳይለወጥ የራ
ስን ግላዊ ስሜት አስወግዶ ተባብሮ መነሳት ግድ ይላል። ወ
ቅቱ ኢትዮጵያዊ የሆነ ሁሉ ዓይነ ሕሊናውን ከፍቶ የአባቶቹ
ን የነፃነት ጋሻ በማንሳት ብሔራዊ የአንድነት ክንዱን አንዲያ
ነሳ የአበው መንፈስ ጥሪ ያቀረበበት ግዜያት ነው። ማንኛው
ምፍጡር የሚመካበት ጥግ ይፈልጋል፤ መመኪያ ጥግም ሊሆ
ነው የሚችልም የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ በትክክል ለፈጸመ -
በቻ ነው። ይኸውም 'ወንድሙን የሚወድ በብርሃን ይኖራል
።ማሰናከያ የለበትም፤ ወንድሙን የሚጠላ ግን በጨለማ አለ
፤በጨለማም ይመላለሳል፣ የሚሄድበትን አያውቅም፣ ጨለማ
ውዓይኖቹን አሳውረውታልና' (፩ኛ ዮሐንስ ፪ ፣፲-፲፩) ይላ
ልና እርስ በርስ መተቃቀፍና መረዳዳት ኃይልና ጋሻ ሁኖ
ከማናቸውም ስጋት ያድናል።ሰብዓዊ መብትንም ያስከብራል።

## ኢትዮጵያን የሚያሰጉ ሁለት ብርቱ ጠላቶች

፩. <u>የእምነት ነፃነት</u>፥- ምንም እንኳ ሃይማኖት የሕልውና ተ
ስፋ ሰጭነቱ የታወቀ ቢሆንም የየአንዳንዱ ሰው የእምነት ነፃነ
ቱ በሕግ ይጠበቅለት መባሉ በሃይማኖት ነፃነት እየተሳበበ የ
አገርን ሉዓላዊነት የሚፃረር (የሚንድ) የማንነት መታወቂያን
የሚያጠፋ፣ የባዕዳን ረቂቅ ሴራ በብዙ ጥፋቶች በታጀበ ተን
ኮል መሠረታዊ የሆኑ አገራዊ እምነቶችን ለማጥፋት ይዘመት
ማለት አይደለም። ስሙ የሃይማኖት ነፃነት ይባል እንጂ ዓይ
ን ያወጣ የፖለቲካ ሥርሠራ የባህል ቅኝ ግዛት ማስፋፋት ነ
ው። አገራዊ እምነትን ሰልቦ በሚያጠፋ ልዩ ልዩ አደንዛዥ
ስብከት፣ በገንዘብና በመናኛ ስጦታዎች በማታለል የኑሮ ጭ
ንቀት ያለበትን ሕዝብ ከመሠረታዊ የእምነት ነፃነትና ከሰብአ
ዊ ክብሩ እያፈናቀሉ ወደ አደገኛ ሃይማኖታዊ ባርነት እያስገ
ቡት ነው።

እስከ ዛሬ በታሪክ እንደታየው የአንድ አገር የመጥፋት ም
ልክቱ የሃይማኖት ነፃነትን መሣሪያ አድርገው ወደ አገር ው
ስጥ እየገቡ በሚያስፋፉት የባዕዳን ሃይማኖቶች ስብከት ነው።
የአሜሪካ ህንዶችና የሰሜን አፍሪካ በርበሮች፤ ግብጻውያን
ኮፕቶችና የሱዳን ኑባዎች የጠፉት ባዕዳውያን ባስገቡት ሃይማ

፪. ኢትዮጵያ ከታሪክ አንፃር ስትታይ
፫. ዩናይትድ ስቴት ኦፍ አሜሪካና የዓፄ ኃይለ ሥላሴ መንግስት
፬. የአሜሪካ ኋይት ሓውስና የኢትዮጵያ መንግሥት
፭. በማር የተሸፈነ መርዝ ወዳጅነት
፮. የኃያላን መንግሥታት መዳፍ በኢትዮጵያ ላይ
፯. የደርግ ጥራዝ ነጠቅ ኅብረተ ሰባዊነት
፰. ሕይወት አድን የምግብ ዕርዳታ
፱. ግቡን የሣተ ድርጅት
፲. የበግና የተኩላ ዝምድና
፲፩. ኦፐሬሽን ሞሰስ (ኢትዮጵያዊያን ፈላሾችን ወደ እስራኤል መውሰድ)
፲፪. ኦፐሬሽን ሼባ (ኢትዮጵያዊያን ፈላሾችን ወደ እስራኤል መውሰድ)
፲፫. የፖለቲካ ስደተኞች ሁኔታ ባጭሩ ሲታይ
፲፬. የጽሁፉን ዓላማና ይዘት የሚገልጽ ማጠቃለያ ሲሆን፤

ጽሁፉ ከተላኩላቸው ውስጥ ጀኔቫ የሚገኘው የተባበሩት መንግሥታት የስደተኞች የበላይ ኮሚሽነር ደብዳቤው የደረሰው መሆኑን ሲገልጽ ሌሎቹ በአደራ (በሬጂስተር) የተላከላቸውን ደብዳቤ መድረሱን እንኳ አልገለጹም። ምናልባትም በላቲን ፊደል በእንግሊዝኛ ቋንቀ ወይም በፈረንሳይኛ ቋንቋ ባለመጻፉ ንቀው ይሆናል። እኔም በአማርኛ ቋንቋ በግዕዝ ፊደል የጻፍኩት ለጉዳዩ ክብደት ይሰጡታል በሚል ሳይሆን ኢትዮጵያ ራሷን የቻለች የፊደልምሆነ የቋንቋ ተመጽዋች ያልሆነች፤ ኢትዮጵያ እንድትጠፋ ልዩ ልዩ ደባ ቢፈጽሙባትም የማትሞት ሕይወት ያላት ነፃ አገር መሆኗን በመግለጽ የአውሮፓ አገሮችን ደብዳቤ እንደሚያስተረጉሙት ሁሉ የኢትዮጵያንም ማስተርጎም ይገባቸዋል ከሚልም ነው።

ደብዳቤው የኑዛዜ ነበር ምክንያቱም እጅግ ዘግናኝ ድርጊት በሕዝብ ላይ ሲፈጸም እያዬሁ በዝምታ ማሳለፍን ሕሊናዬ ስለአልተቀበለውና ለኢትዮጵያ ሕዝብ የተሻለ ስርዓት ለማምጣት ሕይወቴን እሰጣለሁ ብዬ የገባሁትን ቃል ለመፈጸም፣ ልጆቼንና ባለቤቴን ትቼ የተሰለፍኩበት ትግል በልዩ ልዩ ምክንያቶች እየተሰናከለ በመቅረቱ ቢያንስ ቢያንስ ኢትዮጵያን ለማጥፋት የሚያሴሩትን ተንኮለኞች በሚያሳጣ ሁኔታ ራሴን ለመቅጣት ስወስን እስከ ሞት ድረስ ለማምነው ለቁርጠኛው ወዳጄ ለአያልሰው ገልጬለት ነበር። እርሱ ግን የሰጠኝ ሃሳብ



'ለአገር ጉዳይ መስዋዕት መሆን ይገባል። እኔም አምንበታለሁ፣ ዳሩ ግን መስዋዕት ሲከፈል ዋጋ ያለው መሆን ይገባልና ሌሎችን አማራጮች እየፈለጉ መታገል ይገባል፤ ነገ የተሻለ ሁኔታ ሊፈጠር ይችላል' ብሎ ስለ መከረኝ ሁኔታውን አውጥቼ አውርጄ ስሜቴን ብገታውም ወያኔ በየቀኑ የሚፈጽመውን እኩይ ድርጊቱን ስሰማ መንፈሴ ምንግዜም እረፍት አላገኘም።

## ጠቅለል ባለ መልኩ ሲታይ

የኢትዮጵያ የሶሻልና የኢኮኖሚ መዋቅር በበላይነት የተያዘው ተመሳሳይነት ባላቸው የውጭ ካፒታል ይዘው በገቡ የኢትዮጵያን ምስል (ማስክ) ባጠለቁ፤ ኢትዮጵያን ከመሠረቷ ለማናጋት ተልዕኮ ባላቸው ማስክ ለባሾች ነው። እነዚያው ማስክ ለባሾች ማንኛውንም ነገር በቁጥጥራቸው ውስጥ በማስገባታቸው እንደ እድገት ተቆጥሮላቸው ከምስጋናም አልፎ እየተመለከባቸውም ነው። በውጭ (ካፒታል) መዋዕለ ንዋይ የሚንቀሳቀሱ ኃይሎች በሚገባ ተሰናድተውና ተደራጅተው ግዜ ጠብቆ የሚፈነዳ ዳይነሚት በመቅበር ላይ ናቸው።

መቶ በመቶ ኢትዮጵያዊያን የሆኑ የአገር ተወላጆችን በራሳቸው አገር መፈናፈኛ አሳጥተው በከባድ ተፅዕኖ እንዲውሉ ተደርጎ ውስጥ ለውስጥ የሚካሄደው ፕሮፓጋንዳ የሰላቢዎችን ፍላጎት የሚያሟላ ነው። በልማት ሽፋን የሚካሄደው እንቅስቃሴ እያሸለበ የሚያስተኛ ምትሀት ነው። በተለይም በኢንዱስትሪውና በማዕድን ዘርፍ ያለተቀናቃኝና ተወዳዳሪ ልቅ ተሰደው በፈለጉት መንገድ እየተደራጁ ነው።

በማምረቻ ድርጅቶችና በኢኮኖሚው ላቂያ ያላቸው ፖለቲካውንም መቆጣጠር ስለ ሚያስችላቸው የኃይል መልሕቅን እየጣሉ የማኅበረሰቡን (አገር ወዳድ) ተቋም እየናዱት ነው። የአገር ወዳድነት ተቋም ከፈረሰ በኋላ የሚቀጥለው እርስ በርሱ አለያይቶ ማዋጋት ነው።

የመዋዕለ ንዋይ (የካፒታል) ዓዬዎች በአሁኑ ግዜ በድርጊት እንደሚያሳዩት የማምረቻ ድርጅቶችንና የማዕድኖችን መዋቅር በማስፋት ማንኛውንም ነገር በቁጥጥር ስር ማዋል ነው። ይህንንም ሆነ ሌላ የሚፈልጉትን ለማድረግ ከዚህ በፊት እንደተለመደው ወያኔ የሕዝባዊ ወያኔ ሓርነት ትግራይን የተ

ገንጣይነት የምስረታ በዓል ሲያከብር በየዓመቱ ብዙ ሚሊዮን ብር መስጠት ብቻ ነው።

ኅሰኛው ተገንጣይ ወያኔ በ፲፯ ዓመት ትግሉ ያተረፈው ነገር ቢኖር ፀረ ኢትዮጵያ ኃይሎች በጦርነት ለመውረር ሞክረው ያልተሳካላቸውን ዛሬ ወያኔ ባመቻቸላቸው ሁኔታ እየተጠቀሙ የኢትዮጵያን ሕዝብ ከነፃነቱ፤ ከአገር ወዳድነቱ፤ ከባህሉና ከእምነቱ አፈናቅለው ለማንበርከክ ማናቸውም ነገር ተመቻችቶላቸዋል።

## ጀግናውና ነፃነት ወዳዱ የኢትዮጵያ ሕዝብ ሆይ!!

ራስህን ለገንዘብና ለልዩ ልዩ ጥቅም የማትሸጥ መሆንክን ታሪክ ያረጋገጠልህን ዛሬ ነፃነትህንና ክብርህን የሚፈታተን ወጥመድ ተዘርግቶብሃልና፣ የጥፋቱን ማዕከል ተባብረህ ካላስወገድከው ግለ ሰብም ይሁን ድርጅት ከወጥመዱ ለማምለጥ አይችልምና ተባብረህ ተነሳ፤ መሰዋዕት ድፈር፤ መብትህን በደምህ አስከብር።

በክርስትና ላይ ክርስትናን፣ በእስልምና ላይ እስልምናን የሚደርቱትን ተቃወማቸው።

# ምዕራፍ 21
## ፍትሕ ጠያቂው አወዛጋቢ ግድያ

"አጥፊና ጠፊ ተፈላልገው ይገናኛሉ" እንደ ተባለው የኢጣሊያን ወራሪ ሠራዊት አምስት ዓመት ሙሉ በአርበኝነት የተቋቋሙ የጀግናው ቢትወደድ አዳነ መኮንንና የእነ ሻለቃ ዘለቀ ጀምበር በአልታሰበ አደጋ አወዳደቅ ዝርዝር ሁኔታዎች እንደሚመለከተው ቀርቧል።

ታኅሣሥ 29 ቀን 1975 ዓ.ም. ታች አርማ ጭሆ ማስሮ ደንብ ሕዝባአዊ ሸንጎ ተደርጎ ሱዳን ተቀምጠው ደብዳቤ እየላኩ የሚከፋፍሉንን ስለሆነ ወደፊት የሚልኩትን ደብዳቤ አንቀበልም፤ ከዚህ አገር ውስጥ መጥተው ዓላማቸውንና ድርጅታዊ መመሪያቸን ይግለጡልን፤ የሚስማማንን እንቀበላለን የማይስማማነን እንቃወማለንና ደብዳቤ ለራስ መንገሻ ሥዩም፤ ለጀኔራል ነጋ ተገኝ፤ ለቢትወደድ አዳነና ለኮሎኔል እምሩ ወንዴ አርማጭሆ ድረስ መጥተው በሕዝብ ጉባኤ አቋማቸውን እንዲገልጹ ደብዳቤ እንዲጻፍላቸው ተወስኗል። በዚህ ውሳኔ መሠረት በሕዝብ የተመረጡት የጦር መሪዎች የሻለቃ በርይሁን፤ የሻለቃ ዘለቀና የሻለቃ ደሴ ከላይ ስማቸው ለተጠቀሱት መሪዎች ጥር 30/75 ዓ.ም አርማጭሆ ድረስ መጥተው በሕዝብ ጉባኤ አቋማቸውን እንዲገልጹ ደብዳቤ ጽፈው፤ ፈርመውበት በታጋይ አያል ሰው ደሰዩ እጅ ተልኮ ነበር።

በዚሁ በሕዝብ ጥሪ መሠረት ይሁን ወይም አገር ውስጥ ገብተው ለመታገል፤ ክቡር ቢትወደድ አዳነ መኮንን ለታጋይ ትጥቅ ሊገዙ ወደ ሱዳን ከሔዱት ከነ ሻምበል አበበ ጀምበር ጋር አብረው ከሱዳን ጠረፍ ከብረከት ኑሪ ጥር 18.ቀን. 1975.ዓ.ም. ጉዞ ይጀምራሉ። ከስምንት ሰዓት ጉዞ በኋላ ከቀኑ 5 ሰዓት ዘመነ በሪቅ ከተባለው ወንዝ ደርሰው እረፍት ይደረጋል። የበረሃው ሙቀት በረድ ሲል ጉዞ ለመቀጠል ጭነት እንደ ጀመሩ ማንነታቸው ባልታወቀ ሰዎች ስለተተኮሰባቸው ነፍሴን አውጭኝ ብዬ በርሬ መጣሁ ብሎ ፈጠነ የተባለ ታጋይ ከነአበበ ጀምበር ጋር ሱዳን ሔዶ የነበረ ነገረን። ከእርሱ ጋር የነበሩ ሌሎች ሁለት ሰዎችም ፈጠነ የነገረንን ዓይነት ደግመው ነግረውናል።

መጀመሪያ እነ ፈጠነ የሰዎቹን ማንነት አናውቅም ብለው ነበር። በኋላ ግን ጥያቄ ስናበዛባቸው "ጭነት አራግፈን እንደ ተቀመጥን የኢሕአፓ አባሎች ወደኛ መጥተው ስንቅ ጨርሰናልና እርዱን ብለው ስለ ጠየቁን ከያዝነው ዱቄት ሰጥተናቸዋል። ወደ ሱዳን ከሚሔዱ ሰዎችም ማር ገዝተው የአስር ብር ምንዛሪ አበበን ጠይቀውት ዝርዝር የለኝም ብሎ አምስት ብር ሰጥቷቸው ማሩን ገዝተው ወስደው ሲበሉ አበበንም አብልተውታል። የኢሕአፓ አባሎች መሆናቸውንም



ሻለቃ ዘለቀ ጀምበር



አውቃለሁ፤ እንዲያውም አንዱ አለበል የተባለው 3 ወር ከነአበበ ጀምበር ቤት ተቀምጧል በማለት ፈጠነ ነግሮናል።ፈጠነ ይህን ቃል የተናገረው የሻለቃ ዘለቀ አደጋ ወደ ተጣለበት ቦታ ከሔዱ በኋላ ነው።

ጥር 19 ቀን 75 ዓ.ም. ሻለቃ ዘለቀ ለዕርዳታ ጥየቃ የመጡትን እነ ደምለው ፈረደን እና የጀጎል አምባን ታጋዮች አሰባስበው ሃያ ያህል ሰዎች ይዘው አደጋ ወደ ተጣለበት ወደ ዘመነ በረቅ ከምሽቱ 3 ሰዓት ተኩል ሔዱ።

ጥር 20 ቀን 1975.ዓ.ም. የኢሕአፓ የአንድ ጋንታ ጦር ከሻለቃ ዘለቀ ቤት መጥተው ስለ አረፉ የኢሕአፓ አባሎች ዘመነ በረቅ በነቢትወደድ አዳነና በነሻምበል አበበ ላይ አደጋ ጥለዋል ይባላል ወደ በረሃ ለአሰሳ የወረዱ ሰዎች አሉ ወይ ብሎ ሰለሞን የተባለውን ሰው ጠየቅሁት። የሻለቃ ኪዳኔ ሰዎች ይሆናሉ እንጂ የኢሕአፓ ጓዶች ወደዚያ የሄደ የለም ብሎ መለሰልኝ። ከኢሕአፓ ታጋዮች ወደዚያ የሔደ ከሌለ ሻለቃ ዘለቀ አደጋ ወደ ተጣለበት ሂደዋል። ሻለቃ በረይሁንና ሻለቃ ደሴም ወደዚያው ለመሔድ እየመጡ ናቸውና እናንተም አደጋ ወደተጣለበት ሒዳችሁ ወንጀለኞቹ እንዳያመልጡ እነ ሻለቃ ዘለቀ ጀምበርን ዕርዷቸው በማለት አሳሰቤአቸው ነበር።

እነርሱ ግን የኢሕአፓ ታጋዮች ያደጋውን ነገር እንደ ሰሙ በራዲዮ ተነጋግረው ወደ ስፍራቸው ሔዱ። የአደጋውን ሁኔታ ስነግራቸው በፊታቸው የድንጋጤ መልክ ይታይ ነበር። እነርሱ እንደ ሔዱ ከፈልፈል በነ ትልቁ ገብረ ማርያም ባንት ይርጋ የሚመራ፣ ከጃንሱማ በሞላ ተዋበ የሚመራ ከዕኩለ ቀን በኋላ አደጋ ወደ ተጣለበት ቦታ ሔዱ ሻለቃ በርይሁን ብዛት ያለውታጋይ ይዘው ከቀኑ 9 ሰዓት ጀጎል አምባ ደርሰው ከምሽቱ 2 ሰዓት ገደማ አደጋ ወደ ደረሰበት ዘመነ ባሪቅ ጉዞ ጀምረው ከማታው 5 ሰዓት ተኩል ወዲ ኑር ከተባለው ቦታ ደረስን እኔም አብሬ ነበርኩ ከዚያ ትንሺ እረፍት አድርገን በ6.30 ሰዓት ጉዞ ቀጠልን። ቱርካ ከተባለው ወንዝ በ4፡15 ሰዓት ስንደርስ ከወደ ዘመነ በረቅ የመጣ ሰው አግኝተን በዘመነ በረቅ ላይ የደረሰውን አደጋ አንድ በአንድ ዘርዝሮ ነገረን። ከቡር ቢትወደድ አዳነ መኮንና ሻምበል አበበ ጀምበር ሌሎች 5 ሰዎች በድምሩ 7 ሰዎች ተገድለዋል። ሁለት ቁስለኞች የሚያነሳቸው ጠፍቶ ወድቀው ያቃስታሉ ብሎ ነገረን። እንዲሁም እነ ሻለቃ ዘለቀ ዘመነ በረቅ ደርሰው ወደ ሠፈር ተመልሰዋልና እናንተም ተመለሱ ብለዋችኋል ስለ አሉን መራሩን ኃዘን ሰምተን ዘመነ በረቅ ለመድረስ ጥቂት ሲቀረን ተመለስን በ5 ሰዓት ተነስተን ከአደርንበት ወዲ ኑር አደርን በማግስቱ ጥር 21. ቀን 75.ዓ.ም. ከሌሊቱ በ10 ሰዓት ተነስተን 2.30 ሰዓት ጀጎል አምባ ገባን።

በዚሁ ዕለት ለሻምበል አበበ ጀምበር ታጋዮች በሚገኙበት ያካባቢው ሕዝብ ተሰብስቦ ኃዘኑን በመረረ አኳኋን ገልጿል። ሙሾና ቀረርቶም ቀጥሎ ውሏል። አበበ ጀምበር አስታዋይ ብልህ ትሁት ሰውን አክባሪ የማስተዳደር ችሎታ የነበረው ንቁ ታጋይ ነበር። እድሜ ያልጨረሰ ገና ወጣት ለአገሩ ብዙ ሊሠራ የሚችል ነበር።



ሻለቃ ዘለቀ ጀምበር



<u>ክቡር ቢትዎደድ አዳነ መኮንን</u>



ሌላው አሳዛኝ ደግሞ ቆስለው ዘመነ በሪቅ ወድቀው የቀሩ ሁለት ሰዎች የሚያነሳቸው ጠፍቶ እስከ ጥር 29. ቀን. 75.ዓ.ም. ድረስ ከዚያው ከወደቁበት የሚያቃስቱ መሆኑን አሰፋ የተባለ ወጣት ነግሮን የጀጎል አምባ ሕዝብ ሰው ልኮ እንዲያስነሳቸው ተማጥኜ ነበር። በኃዘኑ ምክንያት ፈቃደኛ ሁኖ የሚሔድ አልተገኘም። በኋላ እንደሰማሁት አንዱ ቁስለኛ ከዚያው ሙቷል፤ አንደኛውን የጠገዴ ሰዎች አንስተው ወስደውታል የሚል ሰማን።

ጥር 22. ቀን 1975.ዓ.ም. የኢሕአፓ መዓከላዊ ኮሚቴ የነበረው (የትግል ሥሙ ያፌት) መላኩ ተገኝ የተባለ በግል ለእኔ በጻፈልኝ ደብዳቤ " ጥር 13 ቀን 75 ዓ.ም. አስራ አንድ ከሃዲዎች ከመካከከለችን ብረትና ትጥቅ ይዘው ከድተው ነበር። ከሃዲዎች ከሆኑ አደጋ የጣሉት ኢሕአፓን ከአርማጭሆና ከጠገዴ ሕዝብ ጋር በማጋጨት ለመሆኑ ግልጽ ነው"፡ ብሎ የጻፈልኝ በአባሪ ተያይዟል።

ከኢሕአፓ ድርጅት ከድተው የሔዱ ናቸው የተባሉት 10 ወንዶችና አንዲት ሴት፤ በድምሩ 11 ሰዎች የጠለምት ተወላጆች ናቸው ተብሏል። እነዚህ ጥር 13 ቀን 1975.ዓ.ም. ከድርጅቱ ጠቅላይ ሠፈር ከጃንሱማ ከድተው ሔዱ የተባሉት በእርግጥ የከዱ ከሆነና ወደ ትውልድ ቦታቸው ወደ ጠለምት የሚሔዱ ከሆነ ወደ ሰሜን ምስራቅ አቅጣጫ ቀን በዱር ተደብቀው ሌሊት ጭለማን ተገን በማድረግ መሔድ ይገባቸው ነበር። እነርሱ ግን ወደ ምዕራብ በመሔድ የአዋሳ ጦር መሪ የነበረው በሻለቃ ዘለቀ የሚታዘዘውን የመ/አ ገዳሙ መንግሥቱን ለመያዝ ቤቱን በድንገት ከበው እሱን ቢያጡት ምናልባት ከብቱን እየጠበቀ ከበረሃ ይኖራል በማለት ሁለት ወንድሞቹን አስገድደው ከብቱ ወደ ተሠማራበት ቢሔዱም ሳያገኙት በመቅረታቸው ሁለት ቀን የእረኞችን ምግብ ሲመገቡ ቆይተው ገዳሙ መንግሥቱን ሱዳን ሄዶ ስለ አጡት በ3ኛው ቀን ወደ ጠገዴና ላይ አርማ ጭሆ የሚወስደውን መንገድ አሳዩን ብለው መርተን ወስደን ዘመነ በሪቅ ደርሰን ቦታውን በሩቅ ብናሳያቸው ከዚህ ተመለሱ ከእንግዲህ አታስፈልጉንም ብለውን ተመለስን። አርፈን እንደቆየን ተኩስ ሰምተን ሁኔታውን ለማጣራት ብንሔድ ቢትወደድ አዳነንና ሻምበል አበበ ሌሎችም የሞቱና የቆሳሰሉ ስለ አዩን ወደ አውሳ ሒደን ለሕዝቡ ተናገርን። ወዲያውኑ የአውሳ ሕዝብ ሁኔታውን እንድሰማ ወደ ዘመነ በሪቅ ሒዶ የሞቱትን ቀብሮ ተመልሷል።ቀደም ብሎ የተገደሉት አቀባበር ለታጋይ ፈጠነ ነግረውት የነበረውን ለእኔም ይኸንን አረጋግጠው ነግረውኛል።

ነፍስ ገዳዮቹን "ለምን መጣችሁ" ብለው ቢትወደድ አዳነ መኮንን ቢጠይቋቸው "በርሃውን ለማሰስ ነው የመጣነው" የሚል መልስ ስለሰጧቸው ቢትወደድም "መልካም ነው። እኔንም ትሸኙኣላችሁ" ብለዋቸው ነበር። ከቢትወደድም ከአበበ ጀምበርም የወሰዱትን ምግብ ተመግበው በግምት ከአንድ ሰዓት በኋላ ለመሔድ



ክቡር ቢትዎደድ አዳነ መኮንን

ጭነት አደላድለን መጫን ስንጀምር ተከፍለው ወደ አበበ ተከፍለው ወደ ቢትወደድ በመሔድ "ልትሔዱ ነው ወይ የሚል ጥያቄ ለአበበ አቅርበውለት አበበም "አዎ ሙቀቱ በረድ ስለአለ፤ ሕጻኑንም አያስቃየውም" የሚል መልስ ሰጥቷቸው አውቶ ማቲክ ጠመንጃውን ከግንድ አስጠግቶ በመጫን ላይ እንዳለ በመጀመሪያ በሱ ላይ የሩምታ ተኩስ ከፈቱበት። ወዲያውም አከታትለው በቢትወደድ አዳነ ላይ ተኩስ ከፍተው ከቢት ወደድ አዳነ በኩል እሳቸውና ሻምበል ይርጋ ጥጋቤና ሰሙ ያልታወቀ አንድ ሰው በድምሩ ሦስት ሲገድሉ ሦስት ቆስለዋል። ከአበበ ጀምበር በኩል እራሱ አበበ ጀምበር፤ አይንዬ በዛብህ፤ ይልማ ደሴ፤ ስሙ ያልታወቀ ሱዳን አገር ኑሮ አገሩ ለመግባት የመጣ በድምሩ አራት ተገድለዋል። ጠቅላላ ድምር የተገደሉት ሳባት የቆሠሉ ሦስት ናቸው። ሌሎቹ ተኩስ እንደተከፈተ ሩጠው ሲያመልጡ ከቦታው የቀረች ሕጻን ልጅ የያዘች የይልማ ደሴ ሚስት ብቻ ናት። እሷም ለሕክምና ሱዳን ከባሏ ጋር ሒዳ ታክማ በመመለስ ላይ የነበረች ናት። ባለቤቷ ይልማ ደሴ ተገድሎ በጫካ የታዘለች ሕጻን ልጅ ይዛ አሰቃቂ ፈተና ደርሶባት በመጨረሻ ወደ ሱዳን የሚሄዱ ነጋዴዎች ልጅ አዝላ በበረሃ ስትንከራተት አግኝተው ወስደዋታል።

ነፍስ ገዳይ ወንበዴዎች የፈጸሙት ዘግናኝ የግፍ ግድያ ሕሊናን የሚበጠብጥ አሳዛኝ ነበር። በተለይ ዓርበኛውን ቢትወደድ አዳነ መኮንን የ84 ዓመቱን ሽማግሌ መግደል የለዬለት ዕብደት ነው። ሌላው ደግሞ ባሏን ገድለው እልም ካለው በረሃ ሰው በአካባቢው በሌለበት ጨቅላ የያዘች መጫት እንድትቅበዘበዝ ያደረጉ ጨካኝ አረመኔዎች ናቸው።

ሰው በሰው ላይ የሚጨክንበት ምክንያቶች ይኖሩታል፤ እነዚህ 11 ሰዎች ግን ይህ ነው የሚባል ግልጽ ምክንያት አልነበራቸውም። የደርግን የመደዳ ጭፍጨፋ በመቃወም ለፍትሕና ሰብዓዊ መብቶች በመታገል ላይ የነበሩትን አዘናግተው ወዳጅ መስለው ቀርበው የገደሉ ሰዎች ከአእምሮአቸው የተሰናበቱ ሰውን በመግደል የሚደሰቱ እብዶች ናቸው።

ጥር 23 ቀን 1975 ዓ.ም. ፈልፈል እዳይት ባድማ በግፍ ለተገደለው ዓይንዬ በዛብህ ደመር / አጎበር) ተደርጎ ብዙ ታጋይና ሕዝብ በተገኘበት በፆሎት በኃዘንና ቁከራ ታስቦ ውሏል። በዚሁ ዕለት ከደመሩ የነበሩ ሻለቃ በሪይሁን ሻለቃ ዘለቀ ሻለቃ ደሴ በዘመን በሪቅና ማኀበር ሲጠጡ ፈልፈል አትኳ ከተባለው መንደር ስለ ተገደሉት ሰዎች ለተሰበሰበው ሕዝብ የግፉን አገዳደል በዝርዝር አስረድተዋል። ከኢሕአፓ አመራር አባል የተጻፈ ደብዳቤም ተነቧል።

የደብዳቤውም ይዘት "በዘመነ በሪቅ የተፈጸመውን ግድያ ያካሔዱት ጥር 13 ቀን. 1975 ዓ.ም ከእኛ ተገንጥለው የሔዱ ይሆናሉ እንጂ የድርጅታችን አባሎች አይደሉም በማለት የ11 ሰዎች ስም ዝርዝር ገልጸዋል። እነሱም የሜዳ ስማቸውና ትክክለኛ ስማቸውን በመዘርዝር የገለጿቸው፤ ከዚህ ቀጥሎ የተመለከቱት ናቸው።



| የሜዳ ስም | ትክክለኛ ስም! |
|---|---|
| 1. ደግለኝ | ብርሃኑ ደነቀው |
| 2. አለ በል | አለ በልአዲሱ |
| 3. ኃይለ ማርያም | ዘወልደ ማርያም |
| 4. ቀለመ ወርቅ | ሞላልኝ እንድርያስ |
| 5. እንዳልከ | ማሬ አዲሱ |
| 6. ሥራው ድንቅ | ኃይለ ማርያም አደራው |
| 7. አግደው | እሸቴ ሥዩም |
| 8. መሰለ | አስረሳኸኝ አየለ |
| 9. ብርሃኔ | ሠርጤ ተድላ |
| 10. ዓለም ነሽ | ትበርሕ ንጉሤ (ሴት) |
| 11. በዛብህ | አለምነህ ሰይፉ |

ከነዚህ ከተዘረዘሩት ውስጥ አለበል አዲሱ የተባለውን እነ ዘለቀና አበበ ጀምበር 3 ወር ከቤት አስቀምጠው መግበውታል።

በዚሁ ዕለት የጦር መሪዎች ከባድና መራራ ንግግር አድርገዋል። በተለይ ሻለቃ ዘለቀ ዕርር ትክን ብለው ያደረጉት ንግግር ሕዝብን ለውጊያ የሚቀሰቅስ ነበር። ከሕዝቡም መካከል በኢሕአፓ ላይ ይዘመትበት ብለዋል። በተለይ ፊታውራሪ ገብረ ማርያም የተባሉ አዛውንት ኢሕአፓ ሸሽቶ እንዳይሔድ በርበሩን ይያዝ ብለው ሃሳብ አቅርበዋል። በአጠቃላይ ከአርማ ጭሆና ከጭልጋ ለለቅሶ የተሰበሰበው ሕዝብ በኢሕአፓ ላይ እንዲዘመትበት ጠይቋል። በግፍ የተገደሉትን ወንድሞቻችንን ደም እንበቀላለን። እያለ ታጋዩ በቀረርቶና ፉከራ ስሜቱን ይገልጽ ነበር። ኢሕአፓ በበኩሉ ከግድያው የለሁበትም ከደሙ ንጹሕ ነኝ ብሎ በጽሑፍም በቃልም አስታውቋል።

ጥር 24 ቀን 1975.ዓ.ም ጫውራ ከተባለው ቦታ ውይይት ተደርጎ ሻለቃ በሪሁን የላይ አርማጭሆን ሕዝብ አስተባብረው ማለት ጦራቸውን አስከትለው እንዲመጡ ተደርጎ ጉዞ ሲቀጥሉ፤ ሻለቃ ዘለቀና ሻለቃ ደሴ ጦራቸውን ይዘው ወደ ሳንኪ ተጉዘው ወምበላ በር አደሩ።

ጥር 27 ቀን 1975 ዓ.ም ወደ ጀንድባ ጉዞ ተደርጎ ከቦታው ስንደርስ ዱባ ባሕር ሠፍሮ የነበረው የኢሕአፓ ሠራዊት ለቆ ሔዷል የሚል ወሬ ደረሰን። ጉዞአችንን ቀጥለን ጀጉል አምባ እንደ ገባን ከሻምበል ሞላ ተልኬአለሁ የሚል ሰው መጥቶ አንድ የኢሕአፓ አባል የሆነ ኮሎኔል አስናቀና ከሻለቃ ዘለቀ ጋር ለመነጋገር ይመጣልና ጥይት እንዳትተኩሱበት የሚል መልዕክት ይዞ መጣ። የተባለው ሰው ግን አልመጣም። ይልቁንም እኛ ከነበርንበት ጃንድባ ከሞላ ተዋበ ቤት የኢሕአፓ ሠራዊት መግባቱ ተነገረን።

ጥር 29 ቀን 1975 ዓ.ም. ፈልፈል ላይ የታጋይና የሕዝብ ስብሰባ ተደርጎ ዋለ። ከራስ መንገሻ ተልከናል የሚሉ ሦስት ሰዎች ዘሙተ በየነ፤ ቀኛዝማች አባተ ስጥ አርጋቸው፤ አለባቸው ይልማ የተባሉ በስብሰባው ተገኝተዋል። የስብሰባውም ዓላማ በዘመነ በሪቅ የኢሕአፓ አባሎች ስለ ገደሏቸው ታጋዮች ጉዳይ ተወያይቶ የመጨረሻ ውሳኔ ለመስጠት ነበር።

በዚሁ ስብሰባ ለተገኘው ሕዝብና በሦስቱ ሻለቆች ለሚመራው ታጋይ ሠራዊት እኔ በበኩሌ ያደረግሁት ንግግር "የኢትዮጵያ አገር ወዳዶች ዴሞክራሲያዊ ድርጅት ያለው አቋም ፀረ ደርግ አቋም ካላቸው ዴሞክራሲያዊ ድርጅቶች ጋር ሠፊ ግንባር መስርቶ በጋራ መታገል በሚል መርህ ላይ የተመሠረተ በመሆኑና እኛም ወደዚህ የመጣነው ለተለዬ ተግባር ስለሆነ የድርጅታችን አቋም ባልሆነ ጉዳይ ከኢሕአፓ ጋር የዕርስ በርስ ጦርነት መደረግ የለበትም። ጉዳዩ በውይይት ማለቅ አለበት የሚል ነበር። በዚሁ መሠረት ነገሩን አጣርተው የሚመጡ ሶስት ሰዎች ተሰየሙ። ኢሕአፓ ግድያውን የፈጸሙት ከእኛ ከድተው የሔዱ ሳይሆኑ አይቀሩምና ብለው በደ ብዳቤ በገለጹት መሠረት ሁኔታውን አጣርተው የሚመጡ ሦስት ሽማግሌዎች በአቶ ደምሴ ሰይፉ መሪነት ወደ ኢሕአፓ ተላኩ።

ጥር 30/ 75 ዓ.ም. አርዞ ሜዳ የተጋዳይ ሠራዊት ስብሰባ ተደርጎ ዋለ። ስብሰባውም ያተኮረው በኢሕአፓ ላይ ስለሚወሰደው እርምጃ ነበር።ስብሰባውም ተወያይቶ ያሳለፈው ውሳኔ " በኢሕአፓ ላይ እርምጃ ከመውሰዱ በፊት የላክናቸው መልዕክተኞች የሚያመጡትን መልስ መጠበቅ አለብን እስከዚያ ከኢሕአፓ ጋር ላለመጋጨት ተራርቆ መቆየት ያስፈልጋል ተብሎ ተወሰነ።

የካቲት 2 ቀን 75 ዓ.ም. ፈልፈል እንደገና የተጋዳይ ስብሰባ ተደርጎ ወደ ኢሕአፓ የተላኩት ሽማግሌዎች ኢሕአፓዎች ሠፈራቸውን ለቀው ስለተሰወሩ ልናገኛቸው አልቻልንም ስለ አሉ አሁንም ጉዳዩ በሽምግልና ማለቅ አለበት ተብሎ ሽማግሌዎች እንዲሔዱ በዳይት አድማ አዳር ተደረገ።

የካቲት 3 ቀን 1975 ዓ.ም. ጫውራ ላይ ዳግመኛ ስብሰባ ተደርጎ ወደ ኢሕአፓ መልዕክት ይዘው እንዲሔዱ የተመረጡት ሽማግሌዎች ይገድሉናል ብለው ፈርተው ሳይሔዱ በመቅረታቸው ሌላም ፈቃደኛ ሁኖ የሚሔድ ባለመገኘቱ የታጋይ መሪዎችና የኢሕአፓ መሪዎችን አቀራርቤና ችግሩ በውይይት እንዲፈታ ፈልጌ ወደ ኢሕአፓ ሔጄ የሕዝቡንና የታጋይ መሪዎችን የራሴንም ሃሳብ አቀርባለሁ አልኳቸው። የሻለቃ ዘለቀና የሻለቃ ደሴ "ትልቁን መሪያችን ቢትወደድ አዳነን አጥተን አሁን ደግሞ እርሶን ማጣት የለብ ንም አይሔዱም" አሉ። ሻለቃ በሪይሁን በኢሕአፓ አባልነት ጥርጣሪ ነበራቸውና በእኛ በኩል እንዲሔዱ አንፈልግልም በራስዎ የሚተማመኑበት ካለ መሔድ ይችላሉ" ብለው ተናገሩ"። "እኔም የተለዩ እምነት የለኝም ይሁን እንጂ እኔ ባለሁበት የእርስ በርስ ጦርነት ሲደረግ ማዬት አልፈልግም። ሽማግሌን መግደል የፖለቲካ ሃቅ ነው ካሉም ከጠቀማቸውም የፈለጉትን ያድርጉ ብዬ መለስኩላቸው። እነርሱም የጦር መሪዎቻቸውን ይዘው በቆይታ ለብቻቸው ተወያይተው አደጋ ስለሚኖር እኛ እርስዎ እንዲሔዱ አንፈልግም ሌሎች ሽማግሌዎች እንመርጣለን ብለው በቀኛዝማች ታረቀኝ ቦጋለ የሚመሩ 5 ሰዎች ተመርጠው ለመሔድ ፈቃደኛ ስለሆኑ ሦስቱ ሻለቆች በሕዝብና በታጋዩ ሠራዊት ስም ለኢሕአፓ መሪዎች ደብዳቤ ጻፈ። የተጻፈውም ደብዳቤ



6 ጉዳዮችን የያዘ ነበር እንደ ማስታውሰው።

1ኛ. ጥር 13 ቀን 1975 ዓ.ም. ከድርጅቱ ተገንጥለው የሔዱ ይሆናሉ ካላችሁ ከድተዋችሁ የሔዱ መሆኑን ተከታትለን እንድንይዛቸው ለምን አልገለጻችሁልንም።

2ኛ. በጥር 18/1975 ዓ.ም. በዘመነ በረቅ በነቢተወደድ አዳነ እና ሻምበል አበበ ጀምበር ላይ አደጋ ጥለው ሲገድሏቸው አድኖ ለመያዝ ለምን አልተባበራችሁንም?

3ኛ. ጥር 21 ቀን 1975 ዓ.ም. አትኳ ከቤት ውስጥ የማርያም ማኅበር በሚጠጡት ማኅበርተኞች ላይ የኢሕአፓ አባላት ተኩስ ከፍተው ሁለት ሰዎች ገድለው ጠመንጃ በወሰዱት ላይ ምንም ዓይነት ርምጃ አልተወሰደም።

4ኛ. በዘመነ በረቅና በአትንኳ በሁለቱም ቦታዎች ላይ የግድያ ወንጀል የፈጸሙትን ይዛችሁ ለሕዝብ ሸንጎ እንድታቀርቡ እንጠይቃለን።

5ኛ. በግፍ የተገደሉባቸው ዘመዶች ብድር ለመመለስ የእርስበ ርስ ግጭት እንዳይደረግ አባሎቻችሁ ወደ መንደር ከመሔድ እንዲቆጠቡ።

6ኛ. ሁኔታው ተጣርቶ እስኪ ታወቅ ድረስ ለግዜው ከቦታ ቦታ መዘዋወሩን አቁማችሁ ባላችሁበት ቦታ ጽኑ የሚል ነበር።

የካቲት 4 ቀን 1975 ዓ.ም. ማሰሮ ደንብ ታጋዩ ተሰብስቦ በሽማግሌዎች የተላከውን መልስ በመጠባበቅ ላይ እንዳለ፣ ሳንኪ ወንበላ በር የኢሕአፓ ሠራዊት ገባ ተባለ። ከማሰሮ ደንብ በግምት የአንድ ሰዓት የእግር ጉዞ ይሆናል። በዚህ ዕለት ሙሉ ኃይሌ የተባለ ከሻለቃ ኪዳኔ (ኢያሱ) ደብዳቤ ይዞ መጥቶ ለነ ሻለቃ ዘለቀ አስረከበ። የደብዳቤውም ይዘት ተገናኝተን ተወያይተን ኢ.ዲ.ኅን እናጠናክር፣ ከኢሕአፓ ጋር ሰላማዊ ውይይት ይደረግ የሚል ነው። ሻለቃ ዘለቀና ሻለቃ በሪይሁንም ለፅሁፉ መልስ ሰጥተዋል። ከሙሉ ኃይሌ ጋር 10 ሰዎች አብረው መጥተው ነበር። ሙሉ ኃይሌ የካቲት 5/ 1975 ዓ.ም. ቡቧት መጥቶ ከአደርንበት ቦታ አነጋግሮናል። ሁሉም ነገር ለሽማግሎች ተሰጥቷልና በውይይት እንዲፈጸም ኢሕአፓዎች ተስማምተዋል ብሎ ነበር።

ኢሕአፓዎች ግጭት እንዳይፈጠር ባላችሁበት ጽኑ ቢባሉም ማንም ከልካይ የለም ብለው እኛ ባለንበት ከንፈረ ማርያም ሻለቃ ዘለቃና ሻለቃ በሪይሁን በሠፈሩበት ማህል አቋርጠው በግምት አንድ መቶ ያህሉ ወደ ዳዋ ተሻገሩ። ለሽምግልና የተላኩት ቀኝአዝማች ታረቀኝ ቦጋለ፣ አቶ ደምሴ፣ አቶ ይርዳው በየነ፣ አቶ ዘስሉስ እሸቴና አቶ ዘኢየሱስ እሸቴ ሳይመለሱ መጋጨት አያስፈልግም ተብሎ ነው እንጂ ኢሕአፓዎች ወጥመድ ውስጥ ገብተው ነበር።

በዚሁ ዕለት ማሰሮ ደንብ ቅዳሜ ገብያ ለተሰበሰበው ገበያተኛ ሻለቃ በሪይሁን ሻለቃ ዘለቀና ሻለቃ ደሴ በየተራ ንግግር አድርገዋል። ስማ አገሬ የአርማጭሆ ሕዝብ እያበላ እያጠጣ በአስተናገደ አብሮ ደርግን እየተዋጋ በሞተና ቤት ንብረቱን በተቃጠለ ኢ.ሕ.አ.ፓዎች

በጠላትነት ተሠልፈው እየገደሉህ ነው። እሳት በጉያህ ይዘህ መኖር አትችልምና ተሰብሰበህ ምከር የሚል ነበር።

የካቲት 6/1975 ዓ.ም. ከማሰሮ ደንብ ምሥራቅ ከንፈር ማርያም ከተባለው ቦታ የታጋይ ስብሰባ ተደርጎ ኢሕአፓዎች የሰጡት መልስ ተሰምቷል። ለሽምግልና የተላኩት እነ ቀናዝማች ታረቀኝ ቦጋለ ተልኳቸውን አድርሰው ተመልሰው ኢሕአፓዎች ቀርበው ለመወያየት ተስማምተዋል ብለዋል። ንግግራቸውን በመቀጠል ሕዝቡ በመካከላችን አይግባ እኛና እነ በሪይሁን ዘለቀና ደሴ ከታጋዩ ጋር ይዋጣልን ብለዋል ብለው የሽማግሌዎቹ መሪ የነበሩት ቀኛዝማች ታረቀኝ ቦጋለ ለጦር አዛገሮቹ እኔ ባለሁበት የተባለውን ሁሉ በዝርዝር አስረድተዋል።

እኔም የርስ በርስ ግጭት ደርግን ከማስደሰትና ትግሉን ከመጉዳት በቀር የሚሰጠው አንዳች ጥቅም የለውም። ከሕዝብ መሪዎች ጋር ተገናኝታችሁ ችግሩ በውይይት መፈታት አለበት ብዬ ለኢሕአፓ መሪዎች የፃፍኩትን ደብዳቤ በሺማግሎቹ በእነ ቀኛዝማች ታረቀኝ ቦጋለ እጅ የላኩትን በትግል ስሙ (ዮሴፍ) ተብሎ የሚጠራው ሰጥቼው ተቀብሎ ጥርሱን ነክሶ ደብዳቤውን በእግሩ ረግጠው ብለው ቀኛዝማች ታረቀኝ ቦጋለ አስረድተውናል። ቀኛዝማች ንግግራቸውንም በመቀጠል ኮሎኔል አስናቀ እንግዳ አለመሔዳቸው በጀ እንጂ ቢሔዱ ኑሮ እኔ እንዳየኋቸው ከሆነ የኢሕአፓ መሪዎች በሕይወታቸው ላይ አደጋ ያደርሱባቸው ነበር ብለዋል።

ወንድማቸው ሻምበል አበበ ጀምበር ዘመነ በሪቅ ላይ የተገደለባቸው ሻለቃ ዘለቀ ጀምበር ከኢሕአፓ መሪዎች አንዱ የሆነው ዮሴፍ "ይዋጣልን" አለ የሚለውን ቃል ከተላኩት ሽማግሎች ከሰሙ በኋላ "ከኢሕአፓዎች ጋር በጦር ሜዳ አብረን ተሰልፈን ተዋግተን እየበላንና እየጠጣን ያስተናገድናቸው ስለሆነ እነ ቢትወደድ አዳነና እነ አበበ ጀምበርን ይገድላሉ ብዬ አላመንኩም ነበር። አቅፎ ከያዛቸው ሕዝብ ጋር አጣልቶ ትግሉን ለማኮላሸት የተደረገ ሤራ ነው" ብዬ ነበር። "ይዋጣልን" ካሉማ በርግጥ ግድያውን የፈጸሙት ኢሕአፓዎች ናቸውና እንውጋቸው በማለት ይወተውቱ የነበሩ ሻለቃ በሪይሁን ገብረ ኢየሱስ ብቻ ነበሩ። ሻለቃ ዘለቀ ግን "ይዋጣልን" የሚለውን ቃል እስከ ሰሙ ድረስ በጥርጣሬ ላይ ነበሩ።

የካቲት 8/ 1975 ዓ.ም. ከሠፌ ባሕር በስተ ሰሜን በኩል ከእየር አምባ ከገደምጌ ተራራ መካከል ከሚገኝ ቦታ ግራንጌ አድረን ወደ ኩልቢ ስንጓዝ ከራስ መንገሻ ከተላኩት ሰዎች ጋር ተገናኝተን ተወያይተናል።

በየካቲት 9/1975.ዓ.ም. ኩልቢ ባህታ ከአቶ አበራ ቁም ነገሬ ቤት እንደ አረፍን ከኢሕዴአ ካርቱም ካለው የውጭ አመራር አካል የተጻፈ ደብዳቤ ደረሰን። ደብዳቤው የሚለው "አገር ቤት ለምትገኙ አመራር ኮሚቴ አባላት ይህ ዴሞክራሲያዊ ድርጅት ታሪክ የጣለበትን ኃላፊነት ለመወጣትና የኢትዮጵያን ሕዝብ ትግል ትክክለኛውን አቅጣጫ ይዞ እንዲሔድ ለማድረግ ድርጅታዊ ይዞታውን ማጠንከር ይኖርበታል። ድርጅቱ ንቃት ያላቸውንና ለሐቀኛ የሕዝብ ነፃነት



ትግል ቆርጠው የተነሱ ታጋዮች ማሰባሰብ አለበት" ይልና ቀጥሎ "በአርማጭሆ የሚታገለው አርበኛ የራሱን ኑሮ እየገፋ የሚታገል ስለሆነ በሚገባ አደራጅቶ ማታገል ግዴታ ይሆናል። የወቅቱ የድርጅቱ ዋነኛ ተግባር ቋሚ ጦር በማቋቋም ላይ ያተኮረ በመሆኑ እናንተም በምትገኙበት አካባቢ ቀጥሎ በተመለከቱት ጥቆማዎች መሠረት ይሠራል።

ሀ. ለቋሚው ጦር ወታደራዊና ፖለቲካዊ አመራር ሊሰጡ ይችላሉ ብላችሁ የምታምኑባቸውን ታጋዮች መመልመል።

ለ. በቋሚው ጦርና በአርበኛው ጦር ተለይተው ሊታገሉ የሚችሉትን በየመልኩ መመዝገብ።

ሐ. ከገጠር ወደ ከተማ ሊኖር የሚገባውን ድርጅታዊ መሥመር በአስቸኳይ መዘርጋት።

መ. በሌሎች ወረዳዎችና አውራጃዎች አልፎም ከክፍል አገሮች የአርበኛውን ጦር ሊያንቀሳቅሱ ይችላሉ ተብለው የሚገመቱትን ግለ ሰቦች መገናኘት ያስፈልጋል " የሚል ነበር።

ካርቱም የነበረው አመራር ኮሚቴ ይህን መልዕክት ያስተላለፈው ኮሎኔል እምሩ ከአሜሪካ ስለ የኢትዮጵያ ሕዝብ ዴሞክራሲያዊ ድርጅት /ኢሕዴአ/ (EPDA) ጠቅላላ ስብሰባ አሜሪካ ሔደው እንደ ተመለሱ ነበር።

በ10/06/1975 ዓ.ም. ከኩልቢ ባህታ ወደ ባምብል ማርያም አምርተን ዓመት ሐርያ /ዓመተ ሐዋርያ/ ከተባለው ሠፈር ከአቶ አስናቀው ቤት አድረን በማግስቱ በ11/06/75 ዓቢይ ይርባ ወደ ተባለው አምርተን ከዚሁ ቦታ አርፈን እነ ሻለቃ በሪይሁንን ስንጠብቅ ሻለቃ ኪዳኔ /ኢያሱ/ ሻምበል ፀወቀ ወልደየስ ሻምበል ካሣው ደግ ታጋይ ሠራዊታቸውን እንደያዙ መጥተው ውይይት ስናደርግ ዋልን። በሻለቃ በሪይሁን መዘግዬት በዚያው ዓቢይ ይርባ አደርን።

በየካቲት 12/75 እኩለ ቀን ሲጠበቁ የነበሩት ሻለቃ በሪይሁንና ሻለቃ ዋግሹም ነወጠ ስለ መጡ ጠቅላላ የጦር መሪዎች ከዝቅተኛ እስከ ከፍተኛ ያሉት የጦር መሪዎች ሠፊ ውይይት አካሒደዋል። የውይይቱ ዋና ነጥብ ዘመነ በሪቅ ስለ ተገደሉት እነ ቢትወደድ አዳነና ሻምበል አበበ ጀምበር ነበር ሻለቃ ኪዳኔ /ኢያሱ/ በሕዝቡና በኢሕአፓ መካከል ያለው ቅራኔ በሽምግልና ይፈታ ብሎ በጻፈው ደብዳቤ መሠረት ነበር ውይይቱ የተካሄደው።በቀረበው ሃሳብ የሠራዊት መሪዎች ባለ መስማማታቸው ከቀኑ 12 ሰዓት ገደማ ያለ ምንም ውጤት ውይይቱ አበቃ። እኔና ማንደፍሮ ግን በውይይቱ ላይ ተካፋይ አልነበርንም።

ስብሰባው እንዳበቃ አርበኛው ሻለቃ ኪዳኔ ከኢሕአፓ ጋር ግንባር የፈጠረ በመሆኑ ከመካከላችን መኖር የለበትም የሚል ተቃውሞ በመነሳቱ ሻለቃ ኪዳኔ ላይ አደጋ እንዳይደርስ ሻለቃ ዋግሹም ወደ ሠፈሩ ያድርሰው ተብሎ ሻለቃ ኪዳኔን ሸኝቶታል።

ከዚሁ ቦታ እንዳሉ ከሻለቃ ኪዳኔ ጋር ከጠገዴ የመጣ ጫቅሌ እጅጉ የተባለ ሰው ኅዳር 6 ቀን 75 ዓ.ም. ኮሎኔል አስናቀና የመቶ አለቃ አያል ሰው ወደ አገር ውስጥ ገቡ ማለትን የኢሕአፓ አባል

የነበረው ሰለሞን ተብሎ የሚጠራ በመስማቱ ከሱዳን የጠረፍ መንደር ከበረኸት ኑሪ አንድ ስኳድ ታጋዮችን ይዞ በኅዳር 9/75 ሳያመልጡኝ እያለ ተከታተሏቸው ነበር።ቢያገኛቸው እንደነ ቢት ወደድ አዳነ አደጋ ይጥልባቸው ነበር ብሎ ለተሰበሰበው ታጋይ ተናግሯል። የራሱ ስሜት ይሁን ወይም እውነት ማረጋገጫ የለም። በዚሁ ዕለት ግዚያቱ ድንግዝግዝ ብሎ ስለ ነበር ጊደር ምጥ ከተባለው ተራራ በስተ ሰሜን ከተራራው ሥር ገመሮ ከሚባለው ከነ አቶ መኮንን ሠፈር አደርን።

የካቲት 14 ቀን.1975.ዓ.ም. ወደ ሳንኪ አምርተን ሰንበት ዳስ ውለን ወደ ምዕራብ አቅጣጫ በመጓዝ ሳንኪ አውራ ሜዳ አደርን በዚሁ ዕለት ከካርቱም ግዜአዊ አመራር ኮሚቴ የተላከልንን ደብዳቤ ለጦር አዛገሮች አንብበንላቸዋል። በዚሁ ቦታ እንዳለን ከግራዝማች ሥዩም ለቅሶ ቤት አቶ አቸናፊ የተባለ ሰው ወደ ጭልጋ የሔደው የኢሕአፓ ሠራዊት አይከል ከተማ ገብቶ አደጋ ጣለ ብሎ ነገረን።

የካቲት 17. 75 ጀጎል አምባ ከሻለቃ ዘለቀ ቤት አድረን የሟቹ የሻምበል አበበ ጀምበር 30ኛ ቀን ታሰበ። በዚሁም ዕለት የሻለቃ ዘለቀ ጀምበር ልጅ አሳመረች ዘለቀ ተዳረች።

የካቲት 18/75 ከጀጎል አምባ ወደ አዋሳ ጉዞ ቀጥለን ክርክራ ውኃን አልፈን አዋሳ ገባን።

የካቲት 20/75 አዋሳ ላም ማይ ከተባለው ቦታ ለተሰበሰበው ሕዝብ የደርግ ተባባሪ የሆኑ ግለሰቦች ነጋዴዎች ወደ ሱዳን ለንግድ የሚወስዷቸውን ከብቶች አደጋ ጥለው ዘርፈው ወደ አብደራፊ በመውሰዳቸው ሦስቱ የሻለቃ አዛገሮች ሻለቃ በሪይሁን ሻለቃ ዘለቀና ሻለቃ ደሴ አያልነህ ሠፊ ንግግር አድርገዋል። ወደ ሱዳን የሚወስደው መንገድም ጥበቃ ጉዳይ ተወስቷል። አዋሣዎቹ የጦር አዛገሮችን ንግግር ካደምጡ በኋላ የሰጡት መልስ፤ በሩን ከአርማጭሆ ታጋይ ጋር ሁነን እንጠብቃለን። አብረው እየተንቀሳቀሱ የሚታገሉ ልጆቻችንን እንሰጣለን። ዳሩ ግን እነ ገሪማ በወሰዱት ከብት የአዋሳ ሕዝብ ተጠያቂ አይደለም። እነ ገሪማን ለመበቀል በተወለድሽና በዝምድና የሕዝብ ከብት ቢወሰድ በትግሉ ላይ ጉዳት ያስከትላል። ብለው ሽማግሌች ተራ በተራ እየተነሱ አስረዱ። በመጨረሻም እኔ እነ ገሪማ ከደርግ ጋር የወገኑ በመሆኑ ቢቻል ወደ ወገኖቻቸው መጥተው እንዲቀላቀሉ ካልተሳካም በነሱ ላይ ተገቢ ርምጃ መውሰድ እንጂ ለመቀጣጫ ተብሎ የዘመዶቻቸው ሀብት መወሰድ የለበትም የሚል አስተያዬቴን በመስጠቴ የእነ ገሪማ ዘመዶች ሀብት እንዳይወሰድ ስምምነት ተደረገ።

የጭልጋና የጎንደር አውራጃ ታጋዮች ቀድም ብሎ የደርግን ግፋዊ አገዛዝ ተቃውመው በመዋጋት ላይ ነበሩ። በ1971 ዓ.ም. የኢትዮጵያ አገር ወዳዶች ዴሞክራሲያዊ ድርጅት አርማጭሆ ላይ ከተመሠረተ በኋላም ከድርጅቱ በሚሰጣቸው መመሪያ መሠረት ትግላቸውን በመቀጠል ላይ አንዱ ያልታሰበ ጠላቶች ከጉያቸው ተነሣባቸው። ሁለቱን ተቃዋሚ ጠላት ለመከላከል ተጨማሪ ኃይል ያስፈልጋቸው ስለ ነበር ቢያንስ 130 ሰዎች አስታጥቆ በጎናቸው



አሰልፎ ትግሉን ለማጠናከር እኔ ወደ ሱዳን ሔጄ ለጊዜአዊ አመራር ኪሚቲ ሁኔታውን አስረድቼ የመሣርያ መግዣ ገንዘብ ላምጣ ብዬ ሃሳቡን አቀረብኩላቸው። እነርሱም ነገሩ መልካም ነበር ነገር ግን አትመለስም ከዚያው ትቀራለህና አትሒድብን ከዚህ በሃሳብ ትረዳናለህ አሉኝ።

በ15 ቀን ውስጥ እመለሳለሁ እናንተን ጣብቂያ ውስጥ ትቼ አልቀርም የሚል መልስ ሰጥቻቸው የመሔዴ ነገር ቁርጥ ሆነ። ሱዳን ድረስ የሚሸኙኝ ሰዎችም አልሰጡኝም በውጊያ ላይ ስለ ሆኑና እኔም እንድሔድ ስለ አልፈለጉም ነው።

በዚሁ በየካቲት 20 ቀን 1975 ዓ.ም. አዋሳ አዲስ ዓለም ከሚባለው ከነ መቶ አለቃ ገዳሙ መንግሥቱ መንደር ከምሽቱ 2፡15 ሰዓት (ሁለት ሰዓት ከ15 ደቂቃ) ተነስተን ወደ ሱዳን ጉዞ ቀጠልን። እኔን ለመጠበቅ አቶ ይፍሩ ገ.ሚ እና አቶ ሥዩም ፈረደ በፈቃዳቸው መሣርያቸውን ይዘው ለመሸኘት ቆርጠው ተነሱ። አቶ በየነ የተባለውም በጀሌው አብሮን ተነሳ። አካባቢውን የሚያውቅ መንገድ መሪ አልነበረንም። አቶ ይፍሩ ገ. ሚ. የጠገዴ ሰው ነው። አቶ ሥዩም ፈረደና አቶ በየነ የጋይንት ሰዎች በመሆናቸው ችግር ላይ እንዳለን ምሕረቱ የተባለ የጃኒፈንቀራ ተወላጅ እስከ ሞገሴ ልረዳችሁ እችላለሁ ብሎ እስከ ሞገሴ ድረስ መራን። በጨለማ ጉዞአችን ቀጥለን 4፡15 ሰዓት ከተጓዝን በኋላ ከሌሊቱ 6፡30 ሰዓት በዱር ውስጥ አቋርጠን ስናልፍ ከምንገዱ ላይ የተጋደመ እንጨት አደናቅፎኝ በኃይል ሰወድቅ 3 ደቂቃ ያህል ሕሊናዬን ስቸ ነበር። ግራ ጡቴን ክንዴንና ቀኝ ጉልበቴን ጎድቶኝ ነበር። ለትንሽ ግዜም ቢሆን መተንፈስም ተስኖኝ ነበር። በሌሊት የምጓዘው ከፀጥታው አንፃር ነበር። አገላ ስንደርስ አረፍ ብለን ጉዞአችንን ቀጥለን ወራንበዴ አጠገብ አደርን። በማግስቱ ጉዞአችንን በመቀጠል ቀጭኔ ከተባለው ወንዝ አርፈን ዋልን።

የካቲት 22/75 ከሱዳን የጠረፍ መንደር ጓንግን ተሻግረን በረኸት ኑሪ ገባን።

የካቲት 24 ቀን 75 ዓ.ም. ከበረኸት ኑሪ ተነስተን ገዳሪፍ ከተማ ወደ ማታ ደረስን። ከዚያው አደርን። ገዳሪፍ በገባን በሁለተኛው ቀን ኢሕአፓ ከጭልጋ ተመልሶ የጦር አዛገሮች እኔን አዋሳ ድረስ ሸኝተው ሲመለሱ በድንገት ሳንኪ ላይ ተገናኝተው ተዋግተው የሞተው ሞቶ የተረፈው የኢሕአፓ ሠራዊት ወደ በረሃው ሲሔድ በነጋታው እነ ሻለቃ ዘለቀ ተከታትለው በመሔድ ማርሺ ከተባለው ቦታ ተጋጥመው ከሁለቱም በኩል ጥሩ ጥሩ መሪዎች ተመትተው ወድቀዋል። ከኢሕአፓ በኩል ሐዲሽ በየነ እና ደንጀር የተባሉ መሪዎች፤ ከነሻለቃ ዘለቀ በኩል ሻለቃ ዋግሹም ነወጠ ተመትቶ ወደቀ። ውጊያው ገብ ብሎ ኢሕአፓዎች ከውጊያው ሜዳ አፈግፍገው ሲሔዱ፤ እነ ሻለቃ ዘለቀ ጀምበር የውጊያውን ሜዳ ለቀው በመመለስ ላይ እንዳሉ ሻለቃ ዘለቀ ተመተው ወደቁ የሚል አሳዛኝ ወሬ ሰማን። ዋግሹም ነወጠ እነ ሻለቃ ኪዳኔን ትቶ ከነ ሻለቃ ዘለቀ ጋር የወገነ ነው። ቢትወደድ አዳነ አጎቱ

ስለሆኑ በእርሳቸው መገደል አዝኖ ነበር።

የካቲት 27/75 ወደ ካርቱም ጉዞ ቀጠልን ወደ ማታ ካርቱም ገባን በማግስቱ ኮሎኔል እምሩ ከአሜሪካ ተመልሶ መጥቶ ስለ አገኘሁት በአገር ውስጥ የነበረውን ሁኔታ አስረዳሁት። እንዲሁም ለጊዜአዊ አመራር ኮሚቴውም ሪፖርት በጽሑፍ አቀረብን። የመጣሁት ለ 15 ቀን ብቻ ነው፤ የመሣርያ መግዣ ገንዘብ ይሰጠኝ ብዬ አመለከትኩ።

የአመራር ኮሚቴው ተነጋግሮ ሦስት ጋንታ ጦር የሚያስታጥቅ መሣርያ ለመግዛት ስምምነት ላይ ተደረሰ። የመሳሪያውንም ዋጋ ቀኛዝማች አረዳሚስ ሣህሌ የየአንዳንዱን ዋጋ በየዓይነቱ አጥንተው እንዲያቀርቡ ተወሰኖ፤ ገዳሪፍ ሔደው የየአንዳንዱን ጠብመንጃ በየዓይነቱ ዋጋውን ዘርዝረው አጥንተው አቀረቡ። እኔም የመሣርያውን መግዣ ግምቱ ከታወቀ ወደ አገር ቤት ተመልሼ መሣርያውን ገዝቼ እንዳስታጥቅ ገንዘቡ ይሰጠኝ ብዬ ጠየቅሁ። በውጭ አመራር አካል የመጡ ኮሞዶር ጣሰው ደስታ በዛ ያለ ገንዘብ ይላከላችኋል ብለውኛልና ቢያንስ አንድ ሻለቃ ጦር ሊያስታጥቅ የሚችል መሣርያ መግዛት ያስፈልጋልና ታገስ የሚል መልስ በኮሎኔል እምሩ በኩል ተነገረኝ።

በዛሬ ነገ ግዜው እያለፈ በመሄዱ አንድ ቀን ምርር ብዬ ጦር ማስታጠቅ እንኳ ቢቀር ለድርጅቱ ሲታገሉ ለሞቱት ለነ ሻለቃ ዘለቀ ጀምበር የተዝካር ማውጫ ገንዘብ ይሰጠኝና ወስጄ ልስጣቸው ብዬ ገንዘብ ያዥ ለነበሩት ለኮሎኔል እምሩ ወንዴ ብጠይቃቸው ኢሕአፓዎች ይገድሉሃል። አይሆንም አትሔድም አሉኝ።

እኔም ትግል የጀመርኩት ሕይወቴን ልሰጥ እንጂ ትግልን እየሸሸሁ ከሞት አመልጣለሁ የሚል እምነት ስለ አልነበረኝ እነ ሻለቃ ዘለቀ ጀምበር ከመገደል የደረሱት ለድርጅታቸው /ኢ.ሕ.ዴ.አ./ በመቆማቸው ነው። በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ጃፓኖች ድል ሆነው እጃችሁን ስጡ ሲባሉ ወታደሮችን ከጠላት መርከብ ብረት ጋር ቦምብ ይዘው እንዲላተሙ እያደረግን አስጨርሰን፤ ለጠላት እጃችንን ሰጥተን በሕይወት መኖር አይገባንም በማለት ጀኔራሎቹ በራሳቸው ቆራጥ ውሳኔ ሰውነታቸውን በካራ እየወጉ የተሰውት የሞራል ግዴታ ስለ ነበረባቸው ነው። እኛም የድርጅት አባሎቻችንን አስገድለን በሕይወት እኖራለን ከምንል ይልቅ በእምነት ጸንተን የጽዋቸው ተካፋይ መሆን ይመረጣል። ብዬ ለኮሎኔል እምሩ መለስኩለት። ኮሞዶር ጣሰው ደስታ ከዚያው ስለ ነበሩ  የኮሎኔል አስናቀ ችግር ይገባኛል ብለው በነገሩ ሳይገፉበት ያቆማሉ።

የሆነ ሆኖ ኢ.ሕ.ዴ.አ. የውጭ አመራር አካል ገንዘብ በብዛት ይልኩልናልና በዛ ያለ ገንዘብ ይዘህ ብትገባ ይሻላልና ታገስ የሚል መልስ ኮሎኔል እምሩ ነግሮኝ ባዶ እጀን አልገባም ብዬ ስጠባበቅ ቆየሁ። ተስፋ ሳልቆርጥ ከዛሬ ነገ ገንዘቡን ይገኛ ወደ አገር ቤት ገብቼ መሣሪያ ገዝቼ ትግሉን በአዲስ መልክ ለመቀጠል ሳስብ እንዲያውም ይባስ ብሎ ሂስና ግለ ሂስ ሳያደርጉ እነ ደረጀ ደሬሳ ከጀርመን ካፒቴን ሐሰን ሠይድን ወደ ካርቱም ልከው የአገር ውስጥ ኮሚቴው ከእነሱ ጋር ተባባሪ የነበረውን ኮሎኔል እምሩን እንደ ዋንጫ ቂጥ አውልቀው ጥለው የግል ንግዳቸውን ቀጠሉ።



በነደረጀ ደሬሳ ቡድን የሚመራው የኢሕዴአ የውጭ ኮሚቴ እንደ ድርጅት መቀጠሉ ቀርቶ የለዬለት የቡድን መስመር እየያዘ ሔደ። የሲአይኤ /CIA/ ዳረጎትም ከሃያ ሺህ ዶላር ወደ 500000 ዶላር ከፍ ያደረገላቸው መሆኑን ዋሽንግተን ፖስት በአንድ ወቅት እትሙ ገልፆታል። ሱዳን ውስጥ የነበረውን ግንባር ቀደም አስተባባሪ ኮሚቴንና በአገር ውስጥ የነበረውን ታጋይ አግልለው እርስ በርሳቸው የሚደጋገፉ ቡድኖች (Clique) ተሰባስበው የአገር ቤቱ ትግል ድጋፍ አጥቶ እንዲዳከም በማድረጋቸው ወያኔ ዕድል አግኝቶ ወደ ማሕል አገር ገባ።

# ክፍል አምሥት
# የጎሣ ድርጅቶች

## ምዕራፍ 22
## ወያኔ ደግሞ ደጋግሞ ወደ ጥፋቱ ሲመላለስ

ወያኔ ግባቸው አንድ የሆኑ ስድስት የማጭበርበሪያ ስሞ
ች አሉት።
፩. ተጋድሎ ሕዝቢ ሓርነት ትግራይ (ተሕሓት)
፪. ሕዝብአዊ ወያኔ ሓርነት ትግራይ(ሕወሓት - TPLF )
፫. ማርክሲዝም ሌኒንዝም ሊግ ትግራይ (ማሌሊት)
፬. የኢትዮጵያ ሕዝቦች አንድነት ዲሞክራሲያዊ ግንባር
(ኢሕአደግ)
፭. የትግራይ ሪፑብሊክ መንግሥት
፮. የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ(ኢፌዴሪ)
በአንድ ራስ ስድስት ምላስ ይላሉ ይህ ነው።

-የወያኔ ስትራቴጂ - ጎሰኝነትንና ጎጠኝነትን ማስፋፋት
-የወያኔ ታክቲክ - በኢትዮጵያ ሉዓላዊነት ሕዝብን እየሸነገ
ለ የትግራይን ሪፑብሊክ መገንባት
-የወያኔ የኢኮኖሚ ፖሊሲ - ማንኛውንም መዋዕለ ንዋይ
ለትግራይ ልማት ማዋል
-የወያኔ የኢኮኖሚ ታክቲክ - አገር አቀፍ የልማት ዕቅድ
(ስትራክቸር) በስዕል ቀርፆ ማሳየት
የሚሉ ማታለያዎች በንድፈ ሃሳብ ደረጃ ማቅረብ።

ግንቦት ፳ ቀን ፲፱፻፹፫ ዓ ም ያለተቃዋሚ ሰተት ብ
ሎ አዲስ አበባ የገባው ሕዝብአዊ ወያኔ ሓርነት ትግራይ -
ሕወሓት ወያኔ እና በጎጥ የተሰየመው ማርክሲዝም ሌኒንዝም
ሊግ ትግራይ-ማሌሊት ሁለቱም ስሞች እስከ ዛሬ ተገንጣይነ
ትን እንደያዙ በትግራይ ማንአህሎኝነት የሚጠሩ ናቸው። ማ
ርክሲዝም ሌኒንዝምን ከዓለም አቀፋዊነት ወያኔ አጥቦ ወደ ጎ
ጥ አውርዶታል በሚል ምናልባት ማርክሲዝማዊያን የተቃው
ሞ ሠይፍ ካልመዘዙበት በስተቀር ማርክሲዝም ወደ ጎጥ ፍል
ሰፍና መዛወሩ ነው።

በዚያም ሆነ በዚህ የወያኔ የ፲፯ ዓመት ትግል ኤርትራ
ንና ትግራይን ለመገንጠል በጽሁፍ ያረጋገጡትን አሁንም በየ
ዓመቱ ተገንጣይነት የተመሠረተበትን በዓል በማክበር ላይ ይ
ገኛሉ። በዚሁ በወያኔ የ፲፯ ዓመት ትግል ኢትዮጵያ የምትባ
ል አገር ከተፈጠረች መቶ ዓመት አልሞላትም፣ የአማራ አ
ድኃሪ ምሁራን የፃፉት የተረት መጽሃፍ እንጂ ኢትዮጵያ ታ
ሪክ የላትም ብሎ ያቀነቀነ ወያኔ 'የኤርትራ ትግል ከየት ወ
ዴት' በ፲፱፻፸፱ ዓም በጻፈው መጽሐፉ የአረጋገጠ ሲሆን ኢ
ትዮጵያ ለወያኔ ምኑ ናት። ኢትዮጵያንና ወያኔን ሳይፈላለጉ
ያገናኛቸው አጋጣሚ እንጂ ሕልውናዋን የካደ ወያኔ በኢት



ዮጵያ ዓይን እንደ ውጭ ወራሪ የሚታይ ነው። በግብርም እ
ንደ ውጭ ወራሪ ሁኖ ሠርቷል፣ እየሠራም ነው።

ወያኔአዊ ቡድን ኢትዮጵያን በወራሪነት መያዙን በራሱ
ያረጋገጠው ራሱን እንደውጭ ወራሪ ቆጥሮ በኢትዮጵያ ደም
ተቀብቶ የድል ሓውልት በማቆም አረጋግጧል። በእርስ በርስ
ጦርነት የድል ሀውልት አይቆምም፤ የጀብድ ኒሻንም አይሰጥ
ም። ወያኔ ግን ወገናዊነቱን ክዶ ባዕድ ወራሪነቱን በግልጽ እ
ያሳዬ ነው። ሰው ሁኖ የማይሳሳት የለም፤ የወያኔ መሪዎች
ግን ስህተታቸውን ያላረሙ በስህተታቸው ተፀፅተው የኢትዮጵ
ያን ሕዝብ ይቅርታ ያልጠየቁ፣ የመንግሥት ሥልጣን ከያዙ
በኋላ እንኳ በስህተት ላይ የሚጓዙ ኃፍረት ቢሶች ናቸው።

የወያኔ መሪዎች ተነግረው የማይሰሙ፣ ድፍን ጆሮ ያ
ላቸው፣ ይሉኝታን በማያውቀው ሕሊናቸው በትግራይ ብዙ ት
ምህርት ቤቶች፣ ኮሌጆችና ዩኒቨርሲቲ ተቋቋሙ፤ መንገዶች
ተሠሩ፣ የማምረቻ ኢንዱስትሪዎች ተቋቋሙ፤ ጤና ጣቢያዎ
ችና ሆስፒታሎች ተሠሩ፤ የድል ሐውልት ተቋቋመ እያሉ
ስለትግራይ ልማት ብቻ የሚያቀነቅኑ የተገንጣይ ዓላማቸውን
ያላስወገዱ በጥፋታቸው የሚኮሩ ግብዞች አንድ ግዜ ዓረብ ነ
ን ሌላ ግዜ አፍሪካዊነት፣ ሲጠቡ ትግራዊይነት፣ ሲሰፉ ኢት
ዮጵያውያን ነን የሚሉ ናቸው።

የወያኔ መሪዎች እንደ ውጭ ወራሪ የሚፈረጁበት ዋና
ነጥብ፤
፩. ኤርትራን ማስገንጠሉ፣ አገርን በጎሳ መከፋፈሉ፣ 'እስከ
መገንጠል' የሚል ሐረግ በሕገ መንግሥቱ በመደንገጉ፤
፪. የአገር የመከላከያ ተቋምን ማፍረሱ፣ ሠራዊቱን መበተኑ።
ወያኔ ኢህአደግ ጎጃምን፣ ጎንደርንና ወሎን በወረረበት ግ
ዜ የሕዝብ ድርጅት ንብረት የነበሩትን የእርሻ መሳሪያዎች
ና የጭነት መኪናዎች ዘርፈው ወደ ትግራይ መውሰዳቸው፤
፫. የከተማ ቦታና ቤቶችን እየሸጠ ለግል መጠቀሚያ ማድረ
ጉ፣
፬. የማምረቻ ተቋማትንና ሆቴል ቤቶችን መሸጡ፣
፭. የታሪክ ሰነዶችን (መጻህፍትና መዛግብትን) ማጥፋቱ፣
፮. በኦሮሞ አካባቢ በላቲን ፊደል ትምህርት እንዲሰጥ ማድረ
ጉና የግዕዝን ፊደል ማዳከሙ፣
፯. ኢትዮጵያውያንን ለእስራኤል በመሸጥ መነገዱ፣ ዘመናዊ
ባርነትን ማስፋፋቱ
፰. ኢትዮጵያዊያት ልጃገረዶችን ለዓረብ አገልጋይነትና ጭን
ገረድነት በገሃድ የድለላ መሥሪያ ቤት አቋቁሞ መነገዱ፣
፱. ሃይማኖትን ደፍሮ በቤተ ክርስቲያንና መስጊድ ውስጥ
ምዕመናንን መግደሉ። ሃይማኖትን አርክሶ ባሕልን መርገ
ጡ፣
፲. ከጎንደርና ወሎ ክፍለ አገር ቆርሶ ያለ ሕዝቡ ፈቃድ ወ
ደ ትግራይ መመደቡ፣

፲፩. የትግራይን ሕዝብ ወደ ሱዳን ወስዶ በሽታ ከሚፈላበት
ቦታ አስፍሮ ከሰላሳ ሺህ በላይ የሚሆኑ ሰዎችን በበሽታ
ማስጨፍጨፉ፣

፲፪. የትግራይን ምሁራን የቻለውን ያህል ጨፍጭፎ ያልቻለ
ውን በአሻጥር ደርግ እንዲረሽናቸው (በሃሰት ወረቀት)
በማድረጉ

፲፫.የወልቃይትንና የጠገዴን ሕዝብ በትግራይ አስተዳደር አን
ቀረጥም በማለታቸው የአገር ሽማግሌዎችን መቀሌ ወስዶ
ማሰሩ፣ ከፋኝን ትደግፋላችሁ እያለ ንብረታቸውን መውረሱ፣

፲፬.በአሩሲና ሐረርጌ ኗሪ የነበሩ ሰላማዊ ሰዎችን ነፍጠኛ እ
ያሰኘ በኀላ ፖሊሲው ማስጨፍጨፉ፣

፲፭. የኤርትራን መገንጠል ተቃውመው የወጡ የዩኒቨርሲቲ
ተማሪዎችን በግፍ ማስጨፍጨፉ፣

፲፮.የሙያ ማኅበራት መሪዎችን አሰቃይቶ፣ አስሮ፣ መግደሉ፣

፲፯.የመምህራን ማኅበራት መሪዎችን ገድሎ የተረፉትን በእስ
ር ማሰቃየቱ፣

፲፰.ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ ርስት ማፋለሰና ለአቤቱታ አዲ
ስ አበባ የሔዱ የጎጃም ገበሬዎችን አስሮ ማሰቃየቱ፣

፲፱.በኀላ ፖሊሲው የጌዲዮንና የጉጂን ማኅበረሰብ ማጋደሉ፣

፳. ከአዲስ አበባ አንተነህ እውነቱ የተባለ ሰው እንደገለጸው
ለሕዝብ መታከሚያ መድኃኒት መግዣ የተቀመጠውን ፵
ሚሊዮን ብር፣ ደብረ ዘይት የነበረ ዘመናዊ የዳቦ መጋገሪያ
ፋብሪካ ከሥሩ ነቅሎ ወስዶ ትግራይ መትከሉ፤ ከቦሌ አው
ሮፕላን መጠገኛ እየነቀለ በመውሰድ መቀሌ ለሚሠራው የአ
ውሮፕላን ማረፊያ ማዋሉ፤ ለኤርትራ አየር መንገድ ዋጋቸ
ው ተከፍሎ ያላለቀ ሁለት አውሮፕላኖች መስጠቱ፣

፳፩.በማያገባው ገብቶ የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያ
ን የሲኖዶስ ሕግ ጥሶ በፓትሪያርክ ላይ ፓትሪያርክ ሹሞ ብ
ፁዓን ጳጳሳትና መነኮሳትእንድዲሰደዱ ማድረጉ፣

፳፪. ሹመት የተባለን ሁሉ ዕውቀት ለሌላቸው ካድሬዎቹ ሰ
ጥቶ ሕዝቡን ማሰቃየቱ፣

፳፫. የተቃዋሚ ኃይሎች ለብሔራዊ ዕርቅ ለውይይት የላኳቸ
ውን አባሎቻቸውን ማሰሩ፣

፳፬.አገራችን ኢትዮጵያን አናስገነጥልም፣ ሉዓላዊነቷንና አንድነ
ቷን እናስከብራለን ብለው የታገሉትን የኢትዮጵያ የጦር ኃይ
ሎች ተዋግቼ ድል አድርጊያለሁ ብሎ የድል ሐውልት ማቋ
ቋሙ፣

፳፭. ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን ማፈኑና ሰብዓዊ መብትን መ
ርገጡ፣

፳፮. የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላማ ማዋረዱ፣

፳፯. ኤርትራን ዋናውን ምድር አስገንጥሎ የበሬ ግንባር ለ
ምታህል ቁራጭ መሬት ሻዕቢያ ይዞብኛል ብሎ ብዙ ኢትዮ
ጵያዊያንን አዝምቶ በጦርነት እሳት ውስጥ ማግዶ የጥይት
መቆስቆሻ ጭራሮ ማድረጉና ማስጨረሱ ኢትዮጵያዊነትነውን?



ታዲያ ይህን መሳይ ድርጊት እየፈጸመ ወያኔ እንዴት
ኢትዮጵያዊ ሊሆን ይችላል? ወያኔ ሁሉንም አድርጓል፤ አገር
ገንጥሏል፤ በኀላ ከፋፍሏል፤ ንብረት ዘርፏል፤ በጦርነት እሳ
ት ውስጥ ማግዷል፤ አሁን የሚነግድባትን ኢትዮጵያን የስድ
ስት ሺህ ዓመት ታሪኳን ክዷል። አሁንም በተደራራቢ ጥፋ
ት ተጓዥ በመሆኑ መቆሚያው የት ነው? አንድም አጥፍቶ
መጥፋት አለዚያም አገር ወዳዶችን እየገደለ ኮትኩቶ አሳድጎ
ለሥልጣን እንዳበቃው እንደ ኢ.ሠ.ፓው መሪ እንደ መንግ
ሥቱ ኃይለ ማርያም የገፈፈውን ገንዘብ ይዞ መፈርጠጥ ካል
ሆነ በስተቀር የወያኔ መሪዎች ኢትዮጵያዊነትን ከመቀበል
ሰይጣን መልአክ ሆነ ብሎ ማመን ይቀላል።

ወያኔ በፖለቲካ፣ በኢኮኖሚና በማኅበራዊ ኑሮ አንድ አ
ይነት ሕይወት የነበረውን ሕዝብ የዘር ፋብሪካ አቋቁሞ ጎሳ
ን፣ ነገድን፣ ዘርንና ቋንቋን ያመረተው የከዳት ኢትዮጵያ ስለሆ
ነች ነው።ኢትዮጵያም ሳታውቀው ክዶ የገባባት ወያኔ ለሰው
ልጅ ያልተገደቡ መብቶቹን፣ ግላዊና ማኅበራዊ፣ ተፈጥሮአዊ ነ
ፃነቱን ወደ ጎን ገፍትሮ የጣለ በአንድ ጎሳዊ ድርጅት ቁራጭ
ፈላጭነት የሚመራ ኢትዮጵያዊ ሊሆን ከፈለገ መጀመሪያ ወ
ያኔ ኢትዮጵያዊ ዜግነቱን ማስቀደም ይኖርበታል።

ሕዝባዊ ወያኔ ሓርነት ትግራይ (ሕውሓት) እነ ማር
ክሲዝም ሌኒኒዝም ሊግ ትግራይ(ማሌሊት) መሰረዙን ሳያስ
ታውቅ፤ በኢትዮጵያውያን ደም መቀሌ ላይ ያቆመውን ሐው
ልት ሳያፈርስና ኢትዮጵያዊነቱን በይፋ አረጋግጦ ይቅርታ ሳ
ይጠይቅና ለተወዳዳሪዎችም የዴሞክራሲን በር ሳይከፍት፤ በ
ራሱ መዋቅር፤ በራሱ አስመራጭነት፤ በራሱ የጦር ኃይልና
ፖሊስ እያስፈራራ ተመረጥኩ ብሎ የሚያቋቁመው መንግሥ
ት በምንም ተዓምር ኢትዮጵያዊ ሊሆን አይችልም።

ለመሆኑ ወያኔ በኢትዮጵያውያን ደም የተከለውን ሐው
ልት እያዩ በወገናዊነት ይቀበሉኛል የሚል ከሆነ ተኩላን በግ
ነው ብሎ የማመን ያህል ነው። በምንም ሁኔታ ወያኔን ተ
ኩላነቱን ትቶ በግ ሁኗል ብሎ ኢትዮጵያዊ ሊቀበለው አይች
ልም። የወያኔ መሪዎች በየጊዜው በሚፈጽሙት ድርጊት አገ
ር ወዳድ ኢትዮጵያውያን እያፈሩበት ነው። 'የጎረቤት ጠላት
ዓይነ ሽውራራ ያደርጋል' እንደሚባለው የወያኔ መሪዎችንም
በወገናዊነት መቀበል ቀርቶ ማዬትም ያሳፍራል። የራሳቸው
ን አገር የካዱ፣ እገር ወጥ የሆነውን የማንነት መታወቂያፊደ
ልን በባዕዳን በላቲን ፊደል የተኩ፤ አገራቸውን ወግተው የድ
ል ሐውልት ያቆሙ፤ የራሳቸውን ቤት በኀላ ከፋፍለው ያፈ
ረሱ ጅሎች ስለሆኑ በይቅርታ የማይታለፉ እንደሹመት አባ
ቶቻቸው ኢሠፓዎች በከፋ መልክ የሚጠፉ ናቸው። መቼም
የወያኔ ጉድ ተነግሮ አያልቅም፤ እስቲ ሕሊናው ጤናማ የ
ሆነ ይፍረድ። የኢትዮጵያ አገራዊነት የተመሠረተባት፤ መንግ
ሥቷ የታነፀባት፤ ዋና አካሏን፤ መውጫና መግቢያዋን ኤርት
ራን ትገንጠል ብሎ ለተባበሩት መንግሥታት ደብዳቤ ጽፎአ
ስገንጥሎ የተደሰተ ዛሬ ድንበር ተጣሰ የኢትዮጵያ ሉዓላዊነት

ተደፈረ እያለ የዋሁን ባላገር እሳት ውስጥ መማገዱ ምንይ
ባላል? 'ሞኝ ባያፍር ጎረቤት ያፍር' ነውና በወያኔ መሪዎች
ጅልነት የጎረቤት አገሮች ሳይቀሩ እያፈሩ ነው።

'ጻድቅ ከምድር ጠፋ፣ በሰው መካከልም ቅን የለም።
ሁሉም ደም ለማፍሰስ ያደባሉ፤ ሰውም ወንድሙን ለማድማ
ት ይሮጣል' (ሚክ ፯፥፪) 'ከእርሳቸውም እሻላለሁ የሚለው
እርሱ እንደአማኬላ ነው፣ ቅኑም እንደ አቃቅማ (ኩርንች
ት)ነው። የተመልካቾችህና የመታሰቢያህ ግዜ መጣ። አሁን
ይሸበራሉ።'(ሚክ. ፯፥፬) ተብሎ በቅዱሳት መጽሐፍት የተነ
ገረውን ትንቢት የወያኔ መሪዎች ተግባራዊ አድርገውታል።
አፍኖ ወስዶ ድራሹን ማጥፋት፤ ያለ ፍትሕ በጭካኔ መግደ
ል፤ ቤቶችንናየማምረቻ ድርጅቶችን መውረስ፤ ገበሬውን ከር
ስቱ ማፋለስ የተደራረቡ የግፍ ድርጊቶች በመፈጸማቸው ነቢ
ዩ እንዳለው የግፉ ጽዋ ሞልቶ በወያኔ መሪዎች ላይ ሽብር
ለቆባቸዋል። የወያኔ መሪዎች የጅልነት መለኪያቸው ብዙ ና
ቸው። አንዳንዱ እንኳ ቢጠቀስ ወያኔ ጅል ባይሆን ራሱ የ
ሚጠቀምበትን የአገር ሃብት የጦር ካሳ ይገባቸው ነበር እያለ
ለሻዕቢያ አሳልፎ አይሰጥም ነበር። ደግሞስ በብዙ ሃብትና ድ
ካም የተገነባን የአገር መከላከያ ኃይል አያጠፋም ነበር። የመ
ሣሪያ ግምጃቤቶችን በእሳት አያቃጥልም ነበር።

የወያኔ መሪዎችን ጅልነትና ሞኝነት አጉልቶ የሚያሳየ
ው ሌላው ደግሞ ከጥንት ዘመን ጀምሮ በዘር፣ በባሕልና አ
ምልኮ ከትግራይ ጋር የተሣሠሩ የጋራ የኢኮኖሚ ሕይወት ያ
ላቸው፤ እንድ ታሪክ የተቀዳጁ የጎንደርና የወሎ ክፍላተ አገር
እንደ ጠላት ተቆጥረው የአስተዳደር ክልልን አፍርሶ ወያኔ
ታላቂቱን ትግራይ ለማስፋት ከተጠቀሱት ክፍላተ አገር መሬ
ት ቆርሶ ወደ ትግራይ አስተዳደር በማዛወሩ በስትራቴጂ ወዳ
ጆቹ ላይ የተከለው ቂም መነቀያ የለውም።

ጎንደርና ወሎ ለትግራይ ሕዝብ ግምጃ ቤቱንና ጎተራ
ውን ከፍቶ ሲያስተናግድ የኖረ እንጂ ጠላት አልነበረም። የ
ወያኔ መሪዎች ግን በኢትዮጵያዊነት እምነት ስለሌላቸው ትግ
ራይን ገንጥሎ መንግሥት ለማቋቋም ዓቅደው የተነሱበትን
ተግባራዊ ለማድረግ የትግራይ ቅኝ ግዛት ማስፋፋቱን ቀጥሏ
ል።

በተለይ ጎንደርንማ ወያኔ ልዩ ጠላት አድርጎ ፈርጆታ
ል። ከጎረቤት አገር ከሱዳን ጋር የሚያገናኘውን ለም መሬቱ
ን ያለ ሕዝቡ ፈቃድ ወደ ትግራይ ከልሎታል። ከእርሱ የተ
ረፈውንም በወለጋ ውስጥ ወዳለው ቤኒሻንጉል መድቦታል። የ
ጎንደር ክፍለ አገርን ሕዝብ ከመከፋፈሉም በላይ የልማት መ
ሬቶቹን ለወያኔ ካድሬዎች እየተሰጠበት ለችግርና ጉስቁልና
ኑሮ ተደርጓል።

ወያኔ ኢትዮጵያን ያለ ባሕር በር እንዳስቀራት እንዲሁ
ም ጎንደርን ከውጭ አገር ማለትም ከጎረቤቷ ከሱዳን ጋር እ
ንዳትገናኝ መሬቷን ከልሎ ወስዷል። ወያኔ የትግራይን ሪፑ
ብሊክን ሲያቋቁም ከውጭ አገር መንግሥታት ጋር በየብስ የ



ሚያገናኘው ስለአስፈለገው የጎንደርን መሬት ወደ ትግራይ ደ
ርቦ በሱዳን በኩል ከውጭ አገሮች ለመገናኘት መውጫ በር
ማዘጋጀቱ ነው እንጂ ጎንደርና ትግሬ በምንም የሚለያዩ አይ
ደሉም።

ወያኔ በጎንደር ላይ ሦስት በደሎችን አከታትሎ ፈጽ
ሟል። አንደኛ ያለ ኗሪው ሕዝብ ፈቃድ የወልቃይትን፣ የ
ጠገዴንና ጠለምት ሕዝብ ለዝንተ ዓለም አብሮት ከኖረው ወ
ገኑ ከጎንደር ሕዝብ ነጥሏል፤ ሁለተኛ የኗሪውን ሕዝብ መሬ
ት ወልቃይትና ሁመራ እየነጠቀ ለራሱ ካድሬዎች ሰጥቷል፤
ሶስተኛ የጎንደር ክፍለ አገር ሕዝብ ከጎረቤቱ ከሱዳን ጋር
እንዳይገናኝ ማድረጉ የተገንጣይነት ዓላማውን እያራመደ መ
ሆኑን በድርጊት እያሳዬ ነው። ወያኔ በኢትዮጵያ የትሮያን ፈ
ረስ ማለት ነው። የወያኔ ሌላው አስገራሚ ነገር ደግሞ በትግ
ራይ በየአውራጃውና ወረዳ እስከ ቀበሌ ከፍተኛ ኮሌጆችንና
የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችን እየሠራ፣ ሆስፒታሎችንና
የሕክምና ጣቢያዎች እያቋቋመ፤ ከመለስተኛ እስከ ከፍተኛ
የማምረቻና ማከፋፈያ ፋብሪካዎችን በአክሱም፣ በአድዋ፣ በ
አዲግራትና መቀሌ በብዛት እያቋቋመ፤ ትግራይን ከቀበሌ ወ
ደ ቀበሌ፣ ከወረዳ ወደ ወረዳ፣ ከአውራጃ ወደ አውራጃ የ
ሚያገናኝ መንገድ እየሠራ ሲያገናኝ በጎንደር ግን አንድም
ዓይነት የልማት እንቅስቃሴ አላሳዬም።

እንዲያውም ይባስ ብሎ ጎንደር ከከተማው ውስጥ አን
ድ የኤለትሪክ መብራት አመንጪ ሞተር ቢኖር ነቅሎ ወስ
ዷል። ለመንገድ ጥገና አገልግሎት ጎንደር የነበሩትን የአው
ራ ጎዳና ንብረት ቡልዶዘሮችንና ሌሎችም ወደ ትግራይ ወስ
ዷል። የጎንደር ከተማ መንገዶች ግን ጠጋኝ አጥተው በመበ
ላሸታቸው ከአዘዞ ጎንደር ፲፪ ኪሎ ሜትር መንገድ በመኪና
ለመሔድ ከአንድ ሰዓት በላይ የሚወስድ መሆኑን የዓይን
ምስክሮች ገልጸዋል።

የትግራይ ተማሪዎች ሁለመናው ተሟልቶላቸው በየት
ምህርት ቤቱ በኮምፒዩተር ሲማሩ የጎንደር ተማሪዎች ግን የ
ሚማሩበት በቂ መጽሓፍት የላቸውም። እንዲያውም የፋሲለደ
ስ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የመጸዳጃ ክፍሉ ተበላሽቶ
ባለ መሠራቱ ተማሪዎች በመስክ ላይ ይጸዳዳሉ።

ወያኔ ከቅኝ ገዥ በከፋ መልኩ ኢትዮጵያን በጎሣ ከፋ
ፍሎ እርስ በርስ እያጋደለ ሃብት ዘርፎ የሚወስድ ነው። ደር
ግ ያለ ፍትሕ በመደዳ ገዳይ ቢሆንም ለአገሩ ሉዓላዊነት ተ
ዋግቷል። ወያኔ ግን አገሩን ከዶ ገንጣጥሏል፤ ሰውንም ያለ
ፍትሕ ገድላል። ንብረትም ዘርፏል።

ወያኔ በጎንደር ክፍለ አገር ሕዝብ ላይ የበቀል ርምጃ
በመውሰድ ላይ ነው። ጎንደር ከተማና ደብረታቦር ከተማ
አናስገባም ብሎ ተቃውሞ ስለ ነበር እንደ ብርቱ ጠላት ቆጥ
ሮ በማንኛውም ረገድ ተጽዕኖ እያደረገ ነው።

ወልቃይትንና ጠገዴን ወደ ትግራይ አስተዳደር በማዛ
ወሩ ሕዝቡ ከፋኝ ብሎ ተቃውሞ በማንሳቱ ይህ ነው የማይ

ባል ግፍ ተፈጽሞበታል። ወያኔ እስከ ሰባት ትውልድ ዘር አ የቆጠረ ንብረት ወርሷል፤ ረሽኗል፤ እያሠረ አሰቃይቷል።

'ግፍ እስከ መቼ' ብለው ለአሜሪካ ሬዲዮ ጣቢያ ለ አማርኛ ዝግጅት ክፍል ወያኔ በወልቃይት፣ ጠገዴና ጠለም ት ሕዝብ ላይ የሚፈጽመውን ግፍ ለዓለም በሬዲዮው እንዲ ያሰሙላቸው የጻፉት ፫ ገጽ ደብዳቤ እንዲህ ይላል፤

ኢሕአዴግ 'ሰላምና መረጋጋት ቢልም በሰላም ፈንታ ጦርነት በመረጋጋት ፈንታ ብጥብጥ ሰፍኖ ይታያል፣ ይገኛል ም' ዴሞክራሲያዊ ነን እያሉ በቃላት ጋጋታ፣ ሃተታ፣ መ ግለጫ፣ አዋጅና መመጸደቂያ ልፈፋዎች ሊጋርዱት ያልቻሉ ት ሐቅ ካለ አገራችንና ሕዝባችን በአስከፊ፣ በጣም አደገኛ ሁኔታ ላይ እንዳለ ነው። ለዚህም ኢሕአዴግ ወያኔ የሚያደር ጉት ሁኔታ በዝርዝር

፩ኛ. በወልቃይት፣ ጠገዴ፣ አርማጭሆና ጠለምት ከ ፵፩ ዓመት ዕድሜ በላይ ያሉትን ታሪክ ዓዋቂዎች ናቸው በማለት እየተለቀሙ ለትምህርት እንፈልጋችኋለን በማለት ከ ጉድጓድ እስር ቤት በማስገባት የፀሐይ ብርሃንና ንፋስ ሳያገ ኙ እዚያው የዘለዓለም ሕይወታቸው ያልፋል። በሺህ የሚቆ ጠሩ አልቀዋል። ለዚህም ግህን እስር ቤት ይመስክር።

፪ኛ. አዛውንቱ ቀኛዝማች ገብረ ሕይወት ተስፋይ በስ ደት ገዳርፍ ይኖሩ የነበሩ የወልቃይት ተወላጅ በUNHCR ኃ ላፊነት ወደ ሁመራ ተልከው በሁመራ የሚገኙትን የትግራይ ሰዎች አሰልፈው በ፳፬ ሰዓት ውስጥ አስወጥተዋቸዋል። ምክን ያቱም ከወልቃይቶች እየተወሰደ ለትግራይ ሰዎች የተሰጠውን መሬት እንዳይቀናቀኑ ተብሎ ነው።

፫ኛ. የወልቃይት፣ የጠገዴና ጠለምት ሕዝብ የመጀመሪ ያ ቋንቋህ ትግርኛ ነው ለማንኛውም ነገር የግድ በትግርኛ መጠቀም አለብህ ተብሎ አዋጅ ታውጆ ተማሪዎች በትግርኛ አንማርም በማለት ትምህርታቸውን አቋርጠው ይገኛሉ።

፬ኛ. ከኢሕአዴግ ሕግ የወጣ፣ ያለው የሌለው፣ ቋሚ ና ተንቀሳቃሽ ንብረት ተወርሶ ለትግራይ ልማትና ለኢሕአዴ ግ ክብር መጠበቂያ እየሆነ ነው። ኢሕአዴግ ወያኔ በሌሎች የኢትዮጵያ ክፍል የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ እየተውለበለበ በወልቃይት፣ ጠገዴና ጠለምት አይውለበለብም። ለዚህም ሕዝ ቡ በሠላማዊ ሠልፍ ቢጠይቅ ምን አገባህና ትጠይቃለህ በማ ለት ስንቱ እስር ቤት ነው።

'ኢሕአዴግ ወያኔ በዚህ ክፍል ሕዝብ የሚያደርገውን ተጽዕኖ ወራሪው ፋሽስት ኢጣሊያ እንኳን አላደረገውም።የዚ ህን አገር ሕዝብ የኢሕአዴግ ወያኔ አመለካከት እንደ ውጭ ዜጋ አድርጎ በመመልከት በሰላም ፈንታ ጦርነት አውጇል።

ስለዚህ ይህችን መጠነኛ ደብዳቤያችን የአሜሪካ ሬዲዮ ጣቢያ ደርሳ በአንደበታችሁ ቅንብርነት የዓለም ዴሞክራሲያዊ ሕዝብ ሰምቶት ኢሕአዴግ ወያኔን የኢትዮጵያ ሕዝብ እንዲ ፈርዱንና ለዓለም ሰላምና መብት ጥበቃ እንድታስታውቁልን



በኢትዮጵያ አምላክ እንማጠናችኋለን።' የሰሜን ጎንደር የወ ልቃይት፣ ጠገዴና ጠለምት ሕዝብ' ይላል።

ከዚሁ አያይዘው በአባሪ ተጨማሪ አድርገው በላኩት ወልቃይት ውስጥ አንድ ሰሞን ከለቀሟቸው ሽማግሌዎች ው ስጥ ስማቸው በጣም የታወቁ ዕድሜያቸው ከ ፸፭ እስከ ፹፭ ዓመት የሆናቸውን ለመጥቀስ ያህል፤

፩ኛ. ግራዝማች ወልዴ የእኔሁን
፪ኛ. ባላምባራስ በሀታ ካሴ
፫ኛ. ሙሐመድ ነጋሽ
፬ኛ. ልጅ ዓለም ታዬ
፭ኛ. ፈረደ ዘርዓይ
፮ኛ. ሲሳይ ተስፋሁነኝ
፯ኛ. ቀኛዝማች ጸሃዬ ነጋ
፰ኛ. ግራዝማች አስማረ ታዳጊ
፱ኛ. ደምለው ገታው
፲ኛ. በየነ ገብረ ሚካኤል

ሌላው ቁጥር ስፍር የለውም። ይህ ሁሉ በወልቃይት ብቻ ሳ ይሆን በጠገዴ፣ በአርማጭሆና ጠለምት ላይ የተደረገ ነው በማለት በደብዳቤያቸው ገልጸውታል።

እንዲሁም ወያኔ በደብረታቦር ከተማና አካባቢው ያለ ውን ሕዝብ ጀኔራል ኃይሌ መለሰን ትረዳላችሁ በሚል ሰበባ ሰበብ ከመኖሪያ ቤታቸው ታፍነው እየተወሰዱ እስከዛሬ ድረስ የት እንዳሉ አይታወቅም። ያለ ምንም ማስረጃ የተገደሉትን ቤት ይቁጠረው። በእስር ቤት ታጉረው የሚሰቃዩ ብዙ ናቸ ው።ግህን በመባል የሚታወቀው የወያኔ የጉድጓድ እስር ቤት እጅግ በጣም ጠባብ፣ እግር የማያዘረጋ፣ በጎን የማያስተኛ፣ እግርን ኩድኩዶ (አጥፎ) የሚይዝ መሆኑን ሰቆቃው የተፈ ጸመባቸው ሰዎች ገልጸውታል።

## ጠላትን ማገልገል ስልት ወይስ ሎሌነት?

<u>የውጭ አገር ጠላት፡-</u> የአገርን ሉዓላዊነት የሚገስና ነፃነት ን የሚደፍር የውጭ አገር ወራሪ ይባላል።

<u>የአገር ውስጥ አምባ ገነን፡-</u>የሰውን የመናገር፣ የመስማት፣ የመሥራት፣ የማሰብ፣ የመደራጀት፣ ዴሞክራሲያዊ መብቶ ችን የሚያፍን፣ እምነትንና ባሕልን የሚረግጥ በወገኖቹ ላይ ያመፀ አምባ ገነን ይባላል።

የውጭ አገር ወራሪዎችም ሆኑ የአገር ውስጥ አምባገነ ኖች በሕዝብ ላይ የሚያደርሱት ግፍና ጭቆና ተመሳሳይ ነ ው።ልዩነቱ የአገር ውስጥና የውጭ አገር በመሆን ብቻ ነው። በአገራችን በኢትዮጵያ ተከስቶ እንዳየነው ማለት ነው። (በኢ ትዮጵያ የተከሰቱ ሁለት አምባ ገነኖች ደርግና ወያኔን ብቻ የሚመለከት ነው)

የውጭ አገር ወራሪ ጠላት የሰውን አገር ወርሮ፣ ዘር
ፎ፣ ዘራርፎ፣ ገድሎና አሰቃይቶ የራሱን አገር የሚያበለጽግና
የሚያሳድግ ነው። የአገር ውስጥ አምባገነን በሥልጣን ለመቆ
የት፣ ይቀናቀኑኛል የሚላቸውን የነቁ የሕብረተሰብ ክፍሎች
ያለ ምህረት በጭካኔ ይጨፈጭፋል፤ ራሱንም ከሕግ በላይ በ
ማድረግ በሕዝብ ንብረትና ሕይወት ያሻውን ያደርጋል።ያለ
ሕግ እየገደለ፣ ንብረት እየዘረፈ፣ የሕዝብን ኑሮ እያጫጫ፣ የአ
ገርን እድገት እያዳከመ ለችግርና በሽታ እየዳረገ በጉስቁልና
ኑሮ ላይ ይጥላል። ስለዚህ የአገር ውስጥ አምባገነንና የው
ጭ አገር ወራሪ ወያኔና ኢጣሊያ በአንድ ዓይነት ጥፋት ይ
ፈረጃሉ። ለነዚህ በመሣሪያነት የሚያገለግል ደግሞ ሎሌ ይባ
ላል። ሎሌነት ሁለት ዓይነት መልክ አለው። አንደኛው ሰል
ታዊ ሎሌ ሁለተኛው ሕሊና ቢስ ጅል ሎሌ ይባላል። ሰል
ታዊ ሎሌ ለጠላቱ ታማኝ መስሎ እያገለገለ ጠላቱን ሰርጅቶ
የሚጥልበትን ወጥመድ ያዘጋጃል። ወደ ዓላማው ለመድረስ
ሲገሰግስ የፈለገውን ማድረግ የሚያስችለውን ስልት እየቀየሰ
ለመታመን ወንድሙን ሳይቀር ለመስዋዕትነት አሳልፎ ይሰጣ
ል፤ ከከፍተኛ ባለሥልጣኖች ጋር የቀረበ ወዳጅነት ይመሠር
ታል፤ ከፍተኛውን ባለሥልጣን ወዳጅ ካደረገ ሰላዮች ስለሚ
ፈሩት ከሱ ይርቃሉ፤ በዚያን ግዜ ሥራውን እንደልቡ ይሠ
ራል።

ለምሳሌ ለአገሩ ክብር ለወገኖቹ ኩራት ራሱን የለወጠ
በጥንቷ ፋሪስ በዛሬዋ ኢራን በንጉሥ ዳሪዮስ ዘመነ መንግሥ
ት ከንጉሡ ለጥቆ ከፍተኛ ሥልጣን የነበረው ዞፕሮስ የተባለ
ው የፈጸመው አስደናቂ ድርጊት የሰልታዊ ሎሌን ምንነት ሊ
ገልጽ ይችላል።

የጥንቷ ባቢሎን የዛሬ ኢራቅ በፋሪሶች ትገዛ በነበረበት
ግዜያት የፋሪሶችን ገዢነት በመቃወም ባቢሎናውያን ከተማቸ
ውን አጠንክረው ከመሸጉ በኋላ 'እንግዲህ ወዲያ ፋርሶች በ
ቅሎ ካልወለደች በስተቀር በባቢሎናውያን አይገዙም ብለው'
በንቀት መናገራቸውን ትልቁ መኳንንት ዞፕሮስ በመስማቱ
በባቢሎናውያን ንቀት ተናዶ ሎሌውን ጠርቶ ምናልባት በቅ
ሎ በተዓምር ብትወልድ ወሬውን እንደሰማህ እንድትነግረኝ
ብሎ ያዘዋል።

ብዙ ዓመታት ካለፈ በኋላ ሎሌው በቅሎ ወለደች ብ
ሎ ሲነግረው የወለደችውን በቅሎ በዓይኑ ዓይቶ ሳያረጋግጥ
ዞፕሮስ ትንግርቱ ደረሰ ብሎ ልብሱን አውልቆ ሎሌውን እ
ንዲገርፈው አዞ ይገርፈዋል። ጆሮውንና አፍንጫውንም ያስቆ
ርጥና ደሙን እየዘራ ወደ ዳርዮስ በመሄዱ ዳርዮስም ጀርባው
ን የተገረፈ፣ አፍንጫውንና ጆሮውን የተቆረጠ ሰው በማየቱ
በገናናው መንግሥቴ ይህን ዓይነት ግፍ የፈጸመ ማንነው?
ማንነቱን መለየት ባለመቻሉ አንተስ ከወዴት ነህ? ማንስ ትባ
ላለህ? ብሎ ይጠይቀዋል። እኔ ዞፕሮስ ነኝ። ማንም በእኔ ላ
ይ እጁን የዘረጋ የለም። እኔ ራሴ ያደረግሁት ነው።



የባበሎናውያን ንቀት ለፋርስ ሕዝብ ውርደትና ቅስም
ሰባሪነውና ተሳድበው በጤና መኖር የለባቸውም።አሁን ንጉሡ
ዳርዮስ እኔ የምለውን እንዲፈጽምልኝ እለምናለሁ ብሎ እቅ
ዱን አንድ ባንድ ሲገልጽለት እንዲህ ይለዋል።

ለባቢሎናውያን ንጉሡ ዳሪዮስ ገርፎ ቆራረጠኝ ብዬ ነ
ግሬ አሳምናቸዋለሁ።ባቢሎናውያንም የሰውነቴን ሁኔታ አይተ
ው ወደ ምሽጋቸው ያስገቡኛል፤ከዚያም ዳርዮስ በሰውነቴ ላ
ይ ስለተጫወተብኝ እኔም አፀፋውን እመልሳለሁ፤የዳርዮስን የ
ውጊያ ጥበብና ስልት ደኅና አድርጌ አውቀዋለሁ። ጥቂት ተ
ዋጊ ጦር ብትሰጡኝ የእናንተንም የእኔንም ጠላት እበቀላለሁ
ብዬ እንዲያምኑኝ አደርጋለሁ ብሎ ስልቱን በዝርዝር ይገል
ጽለታል።

በመጀመሪያ ንጉሡ ካራ ብቻ የያዙ አንድ ሺህ ሰዎች
በከላውዲያን በር ይላክ እነርሱን ጨርሼ አጠፋለሁ። ሁለተኛ
በነነዌ በር ሁለት ሺህ ሰዎች ካራ ብቻ የያዙ ይላክ እነርሱን
ም ጨርሼ አጠፋቸዋለሁ።ሶስተኛ በሱሳን በር ሦስት ሺህ ሰዎ
ች ካራ ብቻ የታጠቁ ይላክ።እነርሱንም ጨርሼ እገድላለሁ።
በአራተኛው ንጉሱ ዳርዮስ ሠራዊቱን አስከትቶ በአራቱም የባ
ቢሎን ግንብ በሮች ይቅረብ ከዚያም እኔ አራቱን በሮች ስከ
ፍት ሠራዊቱ በአራቱም በሮች ገብቶ ባቢሎናዊያንን እንዲ
ጨርሱ ብሎ ሃሳቡን አቅርቦ ወደ ባቢሎን ግንብ ደሙን እየ
ዘራ ሔደ።

ባቢሎናውያንም የዞፕሮስን የተቆረጠ አፍንጫና ጆሮ፣
የተገረፈውን ሰውነት ሲያዩና ማንነቱን ሲነግራቸው የምሽጉ
ን በር ከፍተው ሲያስገቡት ዳሪዮስ የፈጸመበትን ግፍ አንድ
ባንድ ነግሮ እንዲያምኑ ያደርጋቸዋል።ባቢሎናውያንም መድኃ
ኒት በማድረግ ቁስሉን ፈውሰው 'እሾህ በሾህ ይወጣል' እን
ዲሉ በጠየቀው መሠረት ተዋጊ ጦር ሰጡት።

ከዚያም ከዳርዮስ ጋር በተነጋገሩት ዕቅድ መሠረት እ
ያከታተለ የላካቸውን ዞፕሮስ የራሱን ወገኖች በመጀመሪያ አ
ንድ ሺህ፣ በሁለተኛ ሁለት ሺህ፣ በሦስተኛ ሦስት ሺህ በድ
ምሩ ስድስት ሺህ የፋሪስ ተዋጊዎችን እንደገደለ በባቢሎናው
ያን ዓለም ከተፈጠረ ዘመን ከተቆጠረ እንደ ዞጥሮስ ያለ ጀግ
ና አልተፈጠረም ብለው ጀግንነቱን አድንቀው የሠራዊቱ ጠ
ቅላይ አዛዥ አድርገው ሹመው የአራቱንም የባቢሎን ግንብ
በሮች ቁልፎች ሰጥተው የባቢሎን መሪዎች ተዝናንተው ከቤ
ታቸው ተቀመጡ።

ንጉሡ ዳርዮስም ዞፕሮስ ባቀደው መሠረት ሠራዊቱን
አስከትቶ ወደ ባቢሎን ግንብ ሔዶ በአራቱም የባቢሎን በሮ
ች ጦሩን እንዳሠለፈ ዞፕሮስ አራቱንም በሮች ከፍቶ በማስገ
ባት ባቢሎናውያንን ያስጨረሳቸው መሆኑን የግሪኩ ታሪክ ጸ
ሐፊ ሔሮዶቱስ የጻፈውን ክቡር ብላታ መርስዔ ኃዘን ወ/ቂ
ርቆስ ባስተረጎሙት ተገልጿል።

በዳርዮስ ዘመነ መንግሥት ፋሪስ (ፔርሻ) ግዛቷ የሰፋ
ሕዝቧ የተከበረ ነበር። ዞፕሮስም በዳሪዮስ መንግሥት ትል

ቅ ሥልጣን የነበረው ሰው ሲሆን ባቢሎናውያን በፋሪስ ላይ
ያሳዩት ንቀት እንደ ትልቅ ውርደት ቆጥሮት የአገሩን ክብር
ና የፋሪስን ሕዝብ ታላቅነት፣ ጀግንነትና ቆራጥነት የራሱን
ሰውነት በመቆራረጥ አሳይቷል።

እንዲያውም ዞፒሮስ ሰውነቱን በመቆራረጡና መልኩን
በማጥፋቱ ንጉሡ ዳርዮስ አንድ ባቢሎን ቀርቶ ለምን መቶ
ባቢሎን አይቀርም፣ ከአእምሮህ ተሰናብተሃልን? እንደዚህ አደ
ርገህ ሰውነትህን ቆራርጠህ መልክህን ያጠፋህ ሲለው የመለሰ
ለት፤ 'የእኔ ሰውነትና መልክ የአገሬና የወገኔ ክብር ነው' ·
በሎ መልሶለታል።

ፍጹማዊ ባለ ልዕለ አእምሮ ለዓላማውና ለእምነቱ የሚ
ሰዋ፣ ለይሉኝታ (ምን ይሉኝ) የማይንበረከክ፣ ለግል ጥቅም
ለሥልጣንና ገንዘብ ራሱን የማይሸጥ በራሱ አብዮታዊነት የ
ሚተማመን፣ ወደ ጠላቱ ቀርቦ ፍጹም ታማኝ መስሎ እያገ
ለገለ የጠላቱን ብርቱና ደካማ ጎን እያጠና በደካማ ጎኑ ገብ
ቶ ጠላቱን ለመሰርጀት ዘዴዎችን እያበጃጀ አመቺ ሁኔታዎች
ሲፈጠሩለት ጠላቱን አጥቅቶ ወገኖቹን ከሥቃይ ኑሮ ያላቅቃ
ል።'ጅብን ሲወጉ በአህያ ታክ ነው' እንደተባለው ጠላት በ
አጭር ግዜ ለማጥቃት የሚቻለው ሲቀርቡት ነው። ነቀዝ አን
ዱን ትልቅ ግንድ የሚጥለው ከውስጥ ገብቶ በመቦርቦር ነ
ው። በውጭ ፈጽሞ አይታይም። ችብሃም ትልቁን ዛፍ የም
ትጥለው ከዛፉ ባላ ላይ በቅላ ምንም የማትጎዳ መስላ ተጠግ
ታ ሥሯን ወደ መሬት እየሰደደች ቀስ በቀስ ዛፉን ጠምጥማ
በመያዝ ሥጋውን በልታ ታጠፋዋለች። እንዲሁም ጠላትን ካ
ልቀረቡት ማናቸውም ነገሮች እየተሠወሩ ጉዞን ያራዝማል።

ሕሊና ቢስ ጅሉ ሎሌ - ክፉ ተናካሽ አውሬን ምግ
ብ እየሰጡ በማለማመድ ገራም ማድረግ እንደሚቻል ሁሉ ን
ቃት የሌላቸውን ደካሞች፣ ሕሊና ቢሶች በጥቅም ማታለል
ይቻላል። 'በሬ ሞኙ ሳሩን አይተህ ገደሉን ሳታይ' እንደተ
ባለውም ለጠላት መሣሪያ መሆን ምን ጉዳት እንደሚያስከት
ል ሳይመራመሩ በጊዜአዊ ጥቅም ታውረው ግፍ አድራጊዎች
ን ያገለግላሉ። የነርሱንም የግፍ ፖሊሲ ያራምዳሉ።

መላሾ እየሰጡ የሚገዟቸውን ጌቶቻቸውን ለማስደሰት
ይባስ ብለው የጥፋት ተዋናይ ይሆናሉ። ዛፎች ጉባኤ አድር
ገው 'መጥረቢያ እኛን የሚያጠቃው በምንድን ነው?
ከእኛ በሚወጣው ጠማማ እንጨት ለመጥረቢያ እጀታ በመሆ
ን ኃይል እየሰጠው ነው። መጥረቢያ ከጠማማው እንጨት እ
ጀታ ባይሰካ ኃይል ኑሮት አይቆርጥም ነበር' አሉ ተብሎ
እንደሚመሰለው እንደዚሁም የሰው ጠማሞች የወጡበትን መ
ኅበረሰብ ቋንቋ እየተናገሩ፣ ለሕዝብ የሚያስቡ፣ ተቆርቋሪ
መስለው በመታዩት የግፍ ድርጊት ተላላኪ ሎሌ በመሆን አ
ገርና ታሪክ ክደዋል። እንደነ ዳዊት ዮሐንስ ያሉ እነርሱ ባ
ልሠሩት ወንጀል የወያኔን ግፋዊ ደም ተሸክመው የሚቅበዘበ
ዙ ጅል ሎሌዎች አሉ። ጅል ያስያዙትን አይለቅም እንደ
ተባለው የወያኔ አፈ ጉባዔ ዳዊት ዮሐንስም 'ኢትዮጵያ የም



ትባል አገር ከተፈጠረች መቶ ዓመት አልሞላትም፣ የአማራ
ምሁራን የጻፉት የተረት መጽሐፍ ካልሆነ ኢትዮጵያ ታሪክ
የላትም' ሲል ቆይቶ በቅርቡ በ፲፱፻፺፪ ዓም ዋሺንግተን ዲሲ
የወያኔው አምባሳደር ባዘጋጀው ስብሰባ 'ኢትዮጵያ የጦር ሠ
ራዊት ኑሯት አያውቅም' በማለት ቅሌቱን ደግሞታል። ታዲ
ያ ከዚህ የበለጠ ጅልነት አለ ወይ? ወያኔን በራሱ አገርና
ጥቅም ላይ ሻዕቢያ ሲያጃጅለው እንደኖረ እነዳዊት ዮሐንስ
ደግሞ በራሳቸው አገርና ታሪክ ላይ ወያኔ እያጃጃላቸው የወ
ያኔን ፖሊሲ እያራመዱ ነው።

ዳዊት ዮሐንስ ሌላውንስ ይካድ እንዴት ኮሪያና ኮንጎ
የዘመተውን የኢትዮጵያ መደበኛ ሠራዊት ሊክድ ቻለ? የዓለ
ም ሕዝብ ይታዘበኛል አለ ማለቱ ምን ያህል ኅፍረተቢስ ቢ
ሆን ነው? ወያኔ እነዚህን እንደሰዓት የሚሞሉ ይዞ ነው አገር
እመራለሁ የሚለው።

ወያኔ ባሻው መንገድ እየተጓዘ የጎንደርን ሕዝብ በስል
ታዊ ዘዴ ዘር ከማጥፋት ባልተለዩ ሁኔታ እያጠፋው ነው።
የክፍለ አገሩ ሕዝብ በተለያዩ በሽታዎች ሲጠቃ መንግሥት
ተ`ብዬው ወያኔ አልተከላከለም። እንዲያውም ይባስ ብሎ ግ
ዜው ያለፈበት መድኃኒት እየላከ በመርዝ ለመጨረስ ያቀደ
ይመስላል። ግዜው ያለፈበትን መድኃኒት ለማደል ወደ ጎንደ
ርይዞ የሄደውን ሰው ግዜው ያለፈበትን መድኃኒት ለምን አ
መጣህ ተብሎ ቢጠየቅ ለጎንደር ሕዝብ የሚታደል ነውና ወ
ስደህ አስረክብ ተብዬ ታዝዤ ነው በማለት መልስ ሰጥቷል።

ይኸኑም ግዜ ያለፈበትን መድኃኒት ሲታደል ያዩ የ
ውጭ አገር ሰው ድርጊቱ ዘር የሚያጠፋ መሆኑን በመግለጽ
ለንደን በስብሰባ ላይ የተናገረው በቪዲዮ ተቀርጾ ይገኛል።
በድሮ ዘመን ወባ (ንዳድ) በቆላ እንጂ በደጋው አልነበረም።
ዛሬ በወያኔ አገዛዝ መድኃኒት ስለማይረጭ ወባው ወደ ደጋ
ው ወጥቶ በመራባት ሕዝቡን እያጠቃ ነው። ሌሎችም ኤድ
ስን የመሳሰሉት በሽታዎች በየቦታው ተስፋፍተው ሕዝብን እ
የጨረሱ ነው። ወያኔ ዓዲግራት ባቋቋመው የመድኃኒት ማም
ረቻ ፋብሪካ ምን እንደሚሠራ አይታወቅም።

እንደነዚህ እንደ ወያኔ መሪዎች የመሰሉትን ቅዱስ ጳ
ውሎስ'በመጨረሻው ቀን የሚያስጨንቅ ዘመን ይመጣል ይህ
ንን እወቅ ሰዎች ራሳቸውን የሚወዱ ይሆናሉ፤ገንዘብን የሚ
ወዱ፤ትምክህተኞች፤ቅድስና የሌላቸው፣እርቅን የማይወዱ፣
ሓሜተኞች፣ራሳቸውን የማይገዙ፣ ጨካኞች፣ ከዳተኞች፣ ች
ኩሎች በትዕቢት የተነፉ፣መልካም የሆነውን የማይወዱ፣ (ጢ
ሞ. ፫፡፩-፬) ይላቸዋል።ይህ የቅዱስ ጳውሎስ መልዕክት በት
ክክል በወያኔ ላይ ማንጸባረቅ ብቻ ሳይሆን ተዋህዷቸዋል።

ለጎንደር ሕዝብ ብሶቱን የሚነግርለት ተወላጅ ሰው በ
ሥልጣን ላይ ማስቀመጥ ቀርቶ በሕይወት እንዲኖር አይፈል
ግም። ሹመት የተባለውን ሁሉ ለወያኔ ከብት እረኞች ተሰጥ
ቶ ሕዝብን ማስተዳደር ቀርቶ ራሳቸውን እንኳ ማስተዳደር የ
ማይችሉ በመሆኑ የክፍለ አገሩን ልማት ገድለውታል። ለይስ

ሙሉ የተቋቋሙ ትምህርት ቤቶችም ዕውቀት ማግኛ ሳይሆን
የወያኔ ካድሬ ወይም የኮር አባል መመልመያ ነው።ተግባረ
ዕድ የሙያ ትምህርትማ ጨርሶ ስሙ አይነሳም። አስተዳደ
ርና ፍትሕ ተቀብሯል።

በዚያ አድልዎ በሠፈነበት በዓፄ ኃይለ ሥላሴ መንግ
ሥት እንኳ ጎንደርን የሚወክል በካቢኔው ውስጥ ባይኖርም የ
አውራጃና ወረዳ አስተዳዳሪዎች የክፍለአገሩ ተወላጆች ነበሩ።
በወያኔማ እስከ ምስለኔ የራሱን ሰዎች ሹሞበታል። ወያኔ የን
ቀቱ ንቀት ብዙ ሊቃውንት ባሉበት ለዚያ ብልህ ሕዝብ ለደ
ብረታቦር ዳኛ አድርጎ የላከው በግማሽ የትግራይ ተወላጅነት
ያላትን ያንደኛ ደረጃ ትምህርት ያላጠናቀቀች የዳኝነት ል
ምድ የሌላት መበለት ነው። ወያኔ በፍትሕ ላይ ያሳየው ቀል
ድ ድንጊያን በቅል የመስበር ያህል ነው።

ወያኔ ከጥፋት በቀር መልካም ነገር አይታየውምና ሕ
ሊና ያለው ሰው ሊያደርገው የማይገባውን ራሱን እንደ ው
ጭ አገር ወራሪ ቆጥሮ በኢትዮጵያውያን ወገኖቹ ደም የድል
ሐውልት መቀሌ ላይ በሰባ ሚሊዮን ብር ሠርቶ ሲያቆም የ
ሚገርመው ሠፊው የትግራይ ሕዝብ ዝም ብሎ ማየቱ ነው።
ይህ በኢትዮጵያዊያን ደም የቆመውን ሐውልት የትግራይ ሠ
ፊ ሕዝብ በፍጥነት እንዲፈርስ ካላደረገ በስተቀር አደጋ የሚ
ያስከትልበት ብርቱ ጠላት ነው። ትውልድ ሒዶ ትውልድ በ
ተካም በኢትዮጵያዊያን (በእርስ በርስ ጦርነት) የቆመን ሐ
ውልት በትዕግስት የሚያየው አይደለም ለትግራይ ሕዝብ ክፉ
ጠንቅ ነው። ስለ ፍትሕ አልባው ወያኔ አንድ ታሪክ
በምሳሌነት ይጠቀሳል። 'ሲሰማ የሞተን እያዩ ቅበረው' የሚ
ል ነው። ከዕለታት አንድ ቀን ሁለት የሚተዋወቁ ሰዎች ተገ
ናኝተው የኑሮን ሁኔታ አንስተው ሲወያዩ እንዲህ ያለ አገር
ሕግ የለም እንጂ ገንዘብ ይገኛል ብሎ ለአንደኛው ይነግረዋ
ል። በድኅነት ተጎሳቁሎ የሚኖር ሰው አምስት ልጆች ይዤ
በችግር ከምሰቃይ ወደዚያ ሕግ ወደ ሌለበት አገር ሒጄ
ለእኔም ለልጆቼ ይለፍልን። ሕግም ባይኖር እኔ ከሰው አልጣ
ላ፣ ከሰው ነገርም አልገባ፣ ከምንም ነገር አልደርስም ብሎ
ሚስቱንና ልጆቹን ይዞ ሕግ ወደሌለበት አገር ሔደ።

ከዚያም ሕግ ከሌለበት አገር ሠርቶ ገንዘብ አፍርቶ ከ
ችግሩ ተላቆ በምቾት መኖር ሲጀምር ከዕለታት አንድ ቀን
በአገሩ የታወቀ እጅግ ከበርቴ ወደ እርሱ ሒዶ ሰላምታ ከ
ተለዋወጡ በኋላ ከበርቴው ሰውዬ ወዳጄ ሆይ ብሎ ንግግሩን
በመቀጠል እግዚአብሔር ባለፀጋ አድርጎኛል የተትረፈረፈ ሃብ
ት አለኝ፤ ነገር ግን ባለመታደል እኔ ስሞት ሃብቴን የሚወር
ስ ልጅ የለኝም። አንተ ግን ዕድለኛ ሰው በመሆንህ አምስት
ልጆች አሉህ፤ መልካም ፈቃድህ ሁኖ ወራሽ የሚሆን ልጅ
ከሚስትህ እንድወልድ ፍቀድልኝ ብሎ ይጠይቀዋል።

ያም ሕግ የለም ወደ ተባለው አገር የሄደው ሰውዬ ከ
በርቴው ሰው በተናገረው ቃል ተናዶ ወደ ዳኛ ሄዶ የደፈረ
ውን ከበርቴ ሰውዬ ከሰሰው። ያቀረበበትም ክስ በሃብቱ ተመ



ክቶ ጥጋብ አደንዝዞት፤ ትዕቢት ወጥሮት አምስት ልጅ የወ
ለደችልኝን የሕግ ሚስቴን ልውለድባት ብሎ በድፍረት ጠይ
ቆኛልና ብርቱ ቅጣት ይቀጣልኝ፤ ስለ ደፈረኝም የሞራል ካሳ
ሊከፍለኝ ይገባል የሚል ነበር።

ዳኛውም ክሱን ከሰማ በኋላ ተከሳሹ ከበርቴ ፍርድ ቤ
ት እንዲቀርብ መጥሪያ ወረቀት ይልክለታል። ተከሳሹም ከበ
ርቴ ሰውዬ በቀኑ ቀጠሮው ፍርድ ቤት ይቀርባል። ዳኛውም
ከሳሽ ተከሳሽ መቅረባቸውን አረጋግጠ ክሱ እንዲሰማ ያደር
ጋል።

ከሳሽ ክሱን ሲያሰማ፤ እግዚአብሔር ያሳይዎ፣ መላክ
ይንገርዎ፣ ይህ ከበርቴ ሰውዬ በሃብቱ ተመክቶ፣ እግዜርን አ
ይፈሬ፣ ሰውን አያከብሬ' የአምስት ልጆቼን እናት የሕግ ሚ
ስቴን ልውለድባት ብሎ ስለ ጠየቀኝ ይቀጣልኝ፤ ለእኔም የ
ሞራል ካሣ ይክፈለኝ ብሎ ክሱን በድጋሚ ያሰማል። ከበርቴ
ው ሰውዬ ክሱን ከሰማ በኋላ መልስ ሲሰጥ 'የእኔን ሃብት
ሁሉ ያውቀዋል፣ ብዙ ንብረትአለኝ፣ ባለ መታደል ሁኖ ወ
ራሽ ልጅ የለኝም፤ እኔ ብሞት ሃብቴን የሚሰበስብ ወራሽ የ
ለኝም። የከሰሰኝ ሰው አምስት ልጆች አሉት፣ ሃብቴን የሚ
ወርስ ልጅ ከሚስትህ ልውለድባት ብዬ ብጠይቀው ወንጀለኛ
አድርጎ ሊከሰኝ አይገባውም፤ የሞራል ካሳም አያስከፍለኝም
ብሎ መልስ ሰጠ።

ዳኛው የከሳሽና ተከሳሽን ክርክር አዳምጦ የሰጠው ው
ሳኔ ከሳሽ አምስት ወራሽ ልጆች ካሉት፤ ተከሳሽ የሞላ የተረ
ፈ ሃብቱን የሚወርስ ልጅ ከሌለው የከሳሹን ሚስት ወስዶ ለ
ንብረቱ ወራሽ የሚሆን ልጅ ይውለድባት ብሎ በየነ።

ያ ሕግ የለም ሲሉት ሲሰማ የሞተ ከሳሽ ሰውዬ ሚስ
ቱን ከበርቴው ወስዶ እንዲወልድባት ዳኛው በመበየኑ በድንጋ
ጤ ታሞ ሲያቃስት ልጆቹ እናታችን ብትመለስ አባታችን
ይድናል ብለው በማሰብ ወደ ዳኛው ሄደው አባታችን በጠና
ታሟል። እናታችን እንድትመለስ ብታደርግ አባታችን ይድና
ል ብለው ዳኛውን ተማጠኑት።

ዳኛውም ሚስቱ ተወሰዳበት በድንጋጤ ወደ ታመመው
ሰው ቤት ሔዶ ቢያየው በሚስቱ መወሰድ ምክንያት የታ
መመው ሰውዬ በሽታው ጠንቶበት ሲያቃስት አገኘውና ነገ
ሥራ ነው ወይስ በዓል ብሎ ሲጠይቅ ነገማ ሥራ ነው ብለ
ው ሲመልሱለት፤ ነገ ሥራ ከሆነ መሞቱ ስለማይቀር ነገ
ሥራ ከሚያስፈታ ዛሬ በበዓሉ ቀን ይቀበር ብሎ በመወሰኑ
መቃብሩ ተቆፍሮ በሽተኛውን ሰውዬ ዓይኑ እያየ ቀበሩት።
በዚህን ግዜ አልቃሽ 'ሲሰማ የሞተን እያየ ቅበረው' ብለው
አንጎረጉረው ዓይኑ እያየ አፈርና ድንጊያ ከመሩበት።

የጎንደርም ሆነ የጎጃምና የወሎ ሕዝብ የዚሁ ሰው ዕ
ድል ገጥሞታል። ወያኔ ኢትዮጵያ የምትባል አገር አልነበረች
ም፣ ትላንት ምኒልክ የፈጠራት ገና መቶ ዓመት አልሞላት
ም። የአማራ አድርባይ ምሁራን የጻፉት ተረት ካልሆነ ኢት
ዮጵያ ታሪክ የላትም እያለ ኤርትራንና ትግራይን ለመገንጠል

እያወጀ ሲወጋ የነበረ ወያኔን እያወቀ ደርግን የጎዳሁ መስሎ
ት እየረዳ በማሳለፉ በቤተ ክርስቲያንና መስጊድ ውስጥ ሳይ
ቀር ምዕመናንን ጨፈጨፈ' ሲሰማ የሞተን እያዬ ቅበረው
እንደተባለው የወያኔን ብልሹ ታሪክ ሲሰማ በሕሊናው የሞተ
ዓይኑ እያዬ ይኸው ተቀበረ።

ሕዝቡ በድርጅትና ጎሣ መለያየቱን ትቶ ዳር እስከ ዳ
ር ተስማምቶ ከፋኝን፤ ኢህአፓን ወይም ሌሎችን በትግል ላ
ይ የነበሩ ሕብረ ብሔር ድርጅቶችን ደግፎ ቢነሳ ኖሮ ዛሬ
መብቱን ተገፎ ያለ ፍትሕ እየተገደለ፣ እየታሠረና እየተዘረ
ፈ ባገሩ ተደይኖ አይኖርም ነበር። ከወያኔ ፍትሕ መጠበቅ
ከዓይጥ ቤት ብቅል መጠበቅ ነው። የወያኔ ዴሞክራሲ ፍት
ሕ ሳይሆን ጥይት ነው። ይኸውም በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
ተማሪዎች፤ በጎንደር አደባባይ ኢየሱስ፤በአዲስ አበባ አኑዋር
መስጊድ የተፈጸመው ግድያና በእነ አሰፋ ማሩ ላይ በአደባባ
ይ የተደረገ ግድያ ያረጋግጣል።

የወያኔ ሕገ መንግሥት በጎሳ ከፋፍሎ እርስ በርስ ማ
ጋጨት ነው። ይኸውም በሲዳሞ በጌድዮና ጉጂ፤ በጋምቤላ፤
በጉራጌ ማኅበረ ሰብአት መካከል እንዲሁም በአሩሲና ሐረርጌ
በክርስቲያኖችና በአማራዎች ላይ የተፈጸመው ግፍ ያረጋግጣ
ል። የወያኔ የምጣኔ ሃብት መመሪያ(ፖሊሲ)የሕዝብን ሃብት
እየነጠቀ፤ ፋብሪካዎችን፣ሆቴል ቤቶችን ደርግ የወረሳቸውን
ቤቶችና የከተማ ቦታዎችን እየቸረቸረ ለወያኔ መሪዎች የንግ
ድ ኩባንያ ማቋቋምያ ነው ያደረገው።

የወያኔ ዲፕሎማሲ ከተቃዋሚ ኃይሎች ጋር ተወያይ
ቶ በጋራ ተስማምቶ ለመሥራት መፍትሔ ከመፈለግ ይል
ቅ፣ ይምጡና ይሞክሩን የሚል የይዋጣልን ፉከራ ነው። ወ
ያኔ·ማኅበራዊ ፖሊሲው ሕዝብን ከእርስቱ ማፈናቀል፣ በሃይ
ማኖት ጉዳይ ገብቶ የራሱን ካድሬዎች እየሾመ፣ የሃይማኖት
መሪዎችን መከፋፈል። የሙያ ማኅበራት መሪዎችን እያባረረ
የራሱን ካድሬዎች መሾምን የመሳሰሉ ናቸው።

በመጨረሻም ክቡር አቶ በላይ ዓባይ የዓድዋው ተወላ
ጅና የዓርበኛው የደጃዝማች ዓባይ ልጅ ዳይሌማ DILEMMA
ለው መጽሐፋቸው ኒው ዮርክ ታይምስ በ፫/፳፫/፺፱ የጻፈው
ን ጠቅሰው እንደ ገለጹት በሎንደኑ ጉባኤ የከፈሉትን አንድ
ሕዝብ ሻዕቢያና ወያኔ በባድመ፣ በዛላንበሳና ጾረና ምስለኔ
ዎች በአደረጉት የእርስ በርስ ጦርነት ወንድማማቾችን ማጋደ
ል እብደት ወይስ ጅልነት? ምን ይባላል?በውጊያው በሁለቱ
ም በኩል ፳ሺህ ወንድማማቾች በከንቱ እንዳለቁ ይገልጻል።

ኤርትራውያን ድንበራቸው ዛላንበሳ ወይም ባድመ አይ
ደለም፤ እስከ ሲዳሞው ሞያሌ፣ እስከ ኦጋዴኑ ፌርፌር ድረ
ስ ባለው በመላው የኢትዮጵያ ሠፊ ምድር ሲንፈላሰሱበት እ
ንደኖሩ ወደ ፊትም ይንፈላለሱበታል። ለኢትዮጵያወያንም በ
ትግራይና ኤርትራ መስተዳድሮች ክልል ሳይወሰኑ ቀይ ባሕር
ን ከዓረብ ጋር ይካፈላሉ። የሻዕቢያና የወያኔ የሁለት ምስለኔ
ዎች ግጭት የመሬት ገፋኸኝ ገፋኸኝ፣ ገበሬ ለገበሬ በእርሻ



መሬት በንብረት እንደሚከራከር እንጂ እንደ ሁለት አገሮች
ግጭት የሚወሰድ አይደለም። ሁለቱም ተፋላሚዎች የመንግ
ሥትነት ባሕርያት የላቸውም።

ወያኔ መላውን የኤርትራ ምድር አልፈልግም፣ ገንጥሉ
ልኝ ብሎ አስገንጥሎ ያሁኑ የድንበር ገፋኸኝ 'ሰድዶ ማሳደ
ድ ከፈለግህ ዶሮህን በቆቅ ለውጣት' ነው። ሻዕቢያም ትልቁ
ን አዳራሽ አልፈልግም ብሎ አፍርሶ ዛሬ ጓዳን ለማስፋት
ጦርነት መክፈት ሁለቱም ምስለኔዎች የሚያደርጉትን አያው
ቁም ማለት ነው። ሁለቱ ምስለኔዎች ወያኔና ሻዕቢያ የሚያካ
ሂዱትን የእርስ በርስ ውጊያ አእምሮ ያለው የማይደግፈው የ
ጅሎች ውጊያ ነው።

የኢትዮጵያ ሕዝብ የባህር መንገዶች ተዘግተውበት ሊ
ያገኝ የሚገባውን ሁሉ አጥቶ ኑሮ ተመሳቅቅሎበታል። ሕግ
በሌለበት አገር የሚኖር ሕዝብ ገንዘቡም፣ ሃብቱም፣ ርስቱም፣
ልጆቹም፣ ሚስቱም የእርሱ አይደሉም።ቤተሰብ መሥርቶ፣ ሃብ
ት አፍርቶ በሰላምና በጤና መኖር በማይችልበት አገዛዝ ገን
ዘብ ለማፍራት ከመጣር ይልቅ ከሁሉ አስቀድሞ ሕግ ከሁሉ
በላይ ገዢ ሁኖ የሚሠራበትን ሥርዓተ ማኅበር ቋሚ አድር
ጎ ለመትከል መጣርና መታገል ያስፈልጋል።

ገንዘብ የሚያገለግለው የሕግ ዋስትና ሲኖር ብቻነው።
ወፎች ጎጇቸውን የሚሠሩት በዛፍ ቅርንጫፍ ላይ ነው።
ምክንያቱም የዛፉ ቅርንጫፍ ከጠላታቸው እንደሚከላከልላቸው
በመተማመን ነው። በሕግ ጥላ ሥር ተከልሎ መዳን ካልቻለ
ሕይወቱም ገንዘቡም የእርሱ አይደለም።

ሕግ በማይሠራበት በሻዕቢያና በወያኔ አምባ ገነኖች ገ
ንዘብ ከሚጠቅም ይልቅ አስጠቂ ጠላት ሁኖ ሲያስገድል፣ ሲ
ያሳስር እና ለብርቱ አደጋ ሲያጋልጥ ታይቷል። ሕዝቡ ገንዘ
ብ ለማፍራት ያደረገውን መሯሯጥ ለፍትኃዊ አስተዳደር፣ ለ
ዴሞክራሲ ሥርዓት ቢያደርገው ኖሮ ሕይወቱንም ገንዘቡንም
ማጣትና የቤተሰብ ኑሮው የመፋለስ አደጋ አይደርስበትም ነበ
ር።

አእምሮ የጎደለው ወደ ፊት የሚደርስበትንና የሚያስከ
ትለውን ጉዳት ስለማይገነዘብ ጥቅም የሠጠ ሁሉ ይገዛዋል።
ለግል ጥቅም ራሳቸውን የሸጡ 'እናቴን ያገባ ሁሉ አባቴ ነ
ው' የሚሉ ወላጆቻቸውን ከማሳፈር አልፎ አገራቸውንና ወገ
ናቸውን ከጉዳት ላይ ይጥላሉ። ለአገር ውስጥ ወንበዴዎችና
ለውጭ አገር ወራሪዎች መሣሪያ በመሆን የሚያገለግሉ ለቤተ
ሰባቸውና ለመላው ሕዝብ ብርቱ አሳፋሪ ጠላቶች ናቸው።

ኃጢአት ምንድን ነው? ኃጢአት ማለት እንደ እርሱ
እኩል ተፈጥሮ ያለውን ሰው 'ከእኔ በቀር ሌላ አምላክ የለ
ም፣ ለፍጡር አትስገድ' የሚለውን መለኮታዊ ትዕዛዝ ጥሶ
ሕገ ወጥ ተግባር ለሚፈጽም ወንበዴ የጥፋት ተባባሪ በመሆን
የሚያጎበድድና የሚያገለግል ማለት ነው። ምንም አይነት ች
ግር ቢያጋጥም ክብሩን አዋርዶ እንዳይንበረከክና ሰብአዊ ክ
ብሩን ጥቅም በመቀላወጥ እንዳያዋርድ ሕሊናዊ ክብሩን እን

ዲጠብቅ 'ኩራት ራት ነው' የሚሉት ጎንደሮች ልክስክስነትን ለማስወገድ ነበር። ሰብአዊ ክብርን እየቸረቸሩ ለከርስ ላለመገዛት ነበር 'ኩራት ራት ነው' የተባለው።

ከርስ ሁል ግዜ የሚያስበው በሉሌነት፣ በአጎብዳጅነት፣ በተለማማጭነት፣ በአድርባይነት በሃሰተኝነት፣ በከዳተኝነት ሆድ መሙላት ብቻ ነው። አጋሰስ ተጭኖ ገፈራ፣ በሬ ታርሶ ገለባ፣ አህያ ተጭኖ ጥሬ እንደሚቀርብላቸው ከርሳሙም የኃጢአት መድበሉን ተጭኖ ያገለግላል።

በዓፄው ቤተ መንግሥት ባለሚሉ ሁሉ ጥፋት አጥፍቶ ተደብድቦ እንዲካስ ይፈልግ ነበር። ዓፄው ባለሚላቸው ሲያጠፋ በጥፊ ላጮሉት ወይም አዘው ላስደበደቡት በዛ ያለ ገንዘብ ይሰጡ ስለነበር በዱላ የተጠለዘው ካሳ ሲሰጠው ተደስቶ ይፈነድቅ እንደነበር ግልጽ ነው። ንጉሡ ውራጃቸውን የሰጡትማ የጦር ሜዳ የጀግንነት ኒሻን እንደተሸለመ ለአለፈ ለአገደመ ጃንሆይ የራሳቸውን ልብስ ሰጡኝ እያለ በማሳዬት ትልቅ ክብር እንዳገኘ ይቆጥር ነበር። ሰብአዊ ክብሩን አዋርዶ 'ኩራት እራትን' ግብአተ መሬት አውርዶ ሲመጻደቅ ያሳፍር ነበር።

የዚሁ ዓይነት ድርጊት በዘመነ ደርግም ተመሳሳዩ ተከስቷል። ደርግ ደጋፊዎች ናቸው ብሎ ከሾማቸው ውስጥ አንዳንዶቹን በውኃ ቀጠነ አስሮና አሰቃይቶ ቢለቃቸውም፤ ተመልሰው እየተለማመጡና እያጎነበሱ ይሾሙ ነበር። አህያ እየተገረፈች እንደምትጫን ማለት ነው።

አሁንም ያው ታሪክ እየተደገመ በተገንጣዩ የትግሬ ወያኔ የተሰደቡና የሕዝብ ተቃውሞ ያስነሳባቸው ከወያኔ የሥልጣን ፍርፋሪ የሚለምኑ አንዳንድ መንፈስ ደካሞች በገሃድ እየታዩ ነው። ሰብአዊ ክብራቸውን ለዕለታዊ ጥቅም ለውጠው ጸጋቸው የተገፈፈ የገፈራ ሰዎች ስለአገራቸው መፈራረስ ደንታ የላቸውም።

መንፈስ ደካማ ሰዎች ራሳቸውን በራሳቸው በሚሠሩት ተግባር ይጎዳሉ። ለትውልድ ለማይተላለፍ፣ አገርንም ሆነ ቤተሰብን ለማይጠቅም ለከንቱ ዕለታዊ ጥቅም ራሳቸውን ከብርቱ አደጋ ላይ ይጥላሉ። አንዳንዶችማ የድርጅትን ወይም የጓደኛን ስም በከንቱ ያጠፋሉ፤ ምስጢራዊ ሰነዶችን ለማይገባው ሰው አሳልፈው ይሰጣሉ።ማኅበረሰቡን በነገር ይነድፋሉ፤ የሚከፋፍል መርዝ ይረጫሉ። እነዚህና እነዚህን የመሳሰሉ ወስላታ ሰዎች ሳይሞቱ የሞቱ፤ ሳይቀበሩ የተቀበሩ ስለሆነ ማኅበረሰቡ ያለ ርኅራኄ ሊያስወግዳቸው ይገባል።

በማኅበረሰቡ የተተፋ ወስላታ በየደረሰበት ሲዋከብ ይሸማቀቃል፤ መድረሻ ሲያጣ የሠራው ጥፋት ትዝ እያለው ራሱን በፀፀት ይገድላል።

ሰው በአእምሮው ከተጠቀመበት በውስጡ ዕውቀት፣ ኀይል፣ ብልሃት፣ ገንዘብ፣ ሞራል፣ እምነት፣ ጀግንነት፣ ድፍረትና ክብርን የመሳሰሉ አሉት። እነዚህንና ሌሎችን ከራሱ አእምሮ መዞ በማውጣት መጠቀም ሲችል ለሌላው ሕሊና ማጎብደድ



የአእምሮ አለመብሰል ጅልነት ነው። የነቃ ሕሊና ነገሮችን አሰላስሎ የብልጦችን ወጥመድ በጣጥሶ ያልፋል እንጂ ሰብአዊ ክብሩን አዋርዶ ለአምባ ገነን መሪዎች አይንበረከክም። መቼም ለጥፋት አገልጋይ ባርያ ከመሆን የበለጠ ውርደት የለም።

የኢትዮጵያ ምድር በደም ተበክሏል። ሁለመናው እረክሷል። የእግዚአብሔርም ቅዱስ መንፈስ እንደ ሸማኔ መጠቅለያ ተጠቅሏል። የሕፃናት ደም ሲፈስ የአገሪቱ ግርማ ሞገስ ተገፏል። የአገር ወዳድ አዛውንቱ ደም ሲፈስ የአገሪቱ ኃይል ሲሟሽሽ የደጋግ ምእመናን ደም ሲፈስ ምድሪቱ ረድኤቷን ቀንሳለች። ፀጋዋን በደመናዎች ወደ ላይ ሰብስባለች። በምድሪቱ ፍቅርና ሰላም ቢጠፉ ረኃብና በሽታ ተስፋፉ። የእርስ በርስ ጦርነትና ስደት በአስከፊ ሁኔታ ቀጠለ።

በአገሪቱ ፍትሕ ነግሶ ነፍስ ገዳዮች ተቀጥተው ደም በደም ካልተመለሰ መቅሰፍቱ ሔደቱን ይቀጥላል፣ ማቆሚያ የለውም። ሕዝብ በትክክል መንፈሳዊ ሕይወቱን ካላገኘና መሪዎቹን መርጦ ካልሾመ ሰላም፣ ፍቅርና ረድኤት ምድሪቱን ፈጽሞ አይጎበኛትም።

በቅዱስ መጽሐፍ እንደ ተጻፈው በነቢዩ ኤልያስ ዘመን ፫ ዓመት ከ ፮ ወር በንጉሥ ዳዊት ዘመን ፫ ዓመት በእስራኤል ምድር ዝናብ ጠፍቶ በረኃብና በበሽታ ሕዝቡ የረገፈው በግፍ ኢዛቤል ባስገደለቻቸው ነቢያትና በጊብዓን ሰዎች ደም ምክንያት ነበር። ነቢዩ ኤልያስ የጣዖት ካህናትን፤ ንጉሥ ዳዊት በግፍ የገደለውን የንጉሥ ሳኦልን ፯ ልጆች እንዲገደሉ ከአደረጉ በኋላ የፈሰሰው ደም ብድር ሲመለስ ዝናብ ከሰማይ ወረደ፤ ከዚያበኋላ እግዚአብሔርም ስለምድሪቱ ተለመነ (ሳሙኤል ፳፩፡ ፲፬፤ መጽሃፈ ነገሥት ቀዳማዊ ፲፰፡ ፵) ይላልና ኢትዮጵያም ምህረት የምታገኘው የፈሰሰው ደም ብድር ሲመለስ ብቻ ነው። አለበለዚያ ረኃብና በሽታ ፈጽሞ አይወገድም። የአክሱምና የአድዋ ተወላጅ ነኝ ባዩ ወያኔ ለትግራይ ሕዝብ ተቆርቁሮ የተነሳ ከሆነ አክሱም የፈጠረችውን ፊደል በላቲን ፊደል ይለውጣልን? የአክሱም ነገሥታት የመሠረቷትን ኢትዮጵያንስ በጎሳና ቋንቋ ይከፋፍላልን? የአክሱምንስ ታሪክ ተረት ነው ይላልን? ኤርትራንስ የአክሱም አካል አልነበረችምና ገንጥሉልኝ ብሎ ለተባበሩት መንግሥታት ይጽፋልን? ስለዚህ ወያኔ አክሱማዊነቱንም ሆነ ኢትዮጵያዊነቱን የካደ ስለሆነ እንደዜጋ ለመቁጠር ፈጽሞ ያዳግታል።

የወያኔ መሪዎች ወያኔአዊነትን ካላስወገዱ በቀር ወያኔአዊነትና ኢትዮጵያዊነት ምን ግዜም የማይታረቁ ናቸው።

## የወያኔ አረመናዊ ጭካኔ በደብረ ታቦር ሕዝብ ላይ

እሰቲ አዲስ አበባ የሚታተመው 'አንድነት' የተባለው ጋዜጣ ተኀሳስ ፳፬ ቀን ፲፱፻፹፯ ዓም በግዜው ተከታትሎ

የመዘገበውን ታሪካዊ ሰነድ እንመልከት። 'ግንቦት ፳ ቀን ፲፱፻፹፮ ዓ ም በደቡብ ጎንደር በሽግግሩ መንግሥት አሰቃቂ ግርፋት፣ እስራት፣ ግድያ የተፈጸመባቸው ሰዎች ዝርዝር ከአካባቢው ዘጋቢዎች ደርሶናል። በኢሕአዴግ ሠራዊት ካምፕ ውስጥ እየታሰሩ በድብደባ በጥይት የተገደሉ፣ ብልታቸው እየታሠረ ከመሽናት ተከልክለው፣ ከሌላ የውስጥ አካላቸው ላይ ጉዳት ያገኛቸው፣ እንደ ፈረስ ለረጅም ግዜ ተለጉመው መንጋጋቸው የተሰነጠቀ፣ በድብደባ ጥርሳቸው የረገፈ፣ ዜጎች መኖራቸውን የገለጠው ይኸው ዘገባ አካባቢውን ለባርነት የዳረገ፣ ለግፍ የተከለለ አድርጎታል ነው የሚባለው። ይህን ዝርዝር እንደሚከተለው አቅርበነዋል።

ሀ/ በጥይትና በዱላ ተደብድበው አስከሬናቸው ተገኝቶ ቤተሰብ ያለቀሰላቸው፤

፩. አቶ ዘለዓለም መንግሥቱ አድራሻው ሓሙስ ወንዝ
፪. አቶ ሲሳይ ጎባው » ደረሂና ደብር
፫. አቶ መስፍን አያሌው » አትከና '
፬. አቶ ብዙአየሁ ፈንታ » ዋራባ
፭. አቶ ንጉሡ ጥበቡ » ግራሪያ
፮. አቶ ወንድማገኝ ገላው » ቃናት
፯. አቶ ዓለማየሁ ልየው » ቃናት
፰. አቶ አስፋው ባዩ » ደረሞ ሚካኤል
፱. አቶ መኩሪያ በላይ » አንድርጌ ገብርኤል

ለ/ በኢሕአዴግ ሠራዊት ተይዘው ተገድለው አስከሬናቸው ያልተገኘው

፩. 'አቶ አበባው ሙላት አድራሻው ሓሙስ ወንዝ
፪. አቶ ጌትነት ምስክር » እስቴ
፫. አቶ ተስፋ ፈለቀ » አንጦራ (ከባሕር ላይ የተጣለ)
፬. አቶ ሞላ ገበየሁ » ውቃራ ጊዮርጊስ
፭. አቶ ተስፋ » ኮኪራ
፮. አቶ ተስፋ ተገኝ » መቀጣዋ (ከሁለት ወንድሞቹ ጋር የተገደለ)
፯. አቶ አንዳርጌ ውበት » ሶራት
፰. አቶ ሙላት ገላዬ » ሊማዶ
፱. አቶ ታዬ ባይፈርስ » አየር ማርያም
፲. አቶ ዳኘው ታደሰ » አንጦራ
፲፩. አቶ ባዬ አስፋው » የደረሰበት ያልታወቀ

ብልታቸውን እየታሠሩ የተደበደቡና በአካላቸው ላይ ጉዳት የደረሰባቸው

፩. አቶ አራጋው ባዩ አድራሻው አንጦራ
፪. አቶ አያሌው ገላዬ » ማይነት
፫. አቶ ታዬ ከልካይ » ማይነት



፬. አቶ ይግዛው ምትኩ » ማይነት
፭. አቶ አራጋው ባዩ » ቅስናጥ
፮. አቶ ካሤ ዓለሙ » አንጦራ
፯. አቶ አበባው ካሤ » ማይነት
፰. አቶ ገበየ ዐወቀ » ቅስናጥ
፱. አቶ አላምረው አስረስ » ሶራት
፲. አቶ ልብሴነው መስፍን » ገንተኛ

አፋቸው በገመድ ታስሮ መንጋጋቸው የተሰነጠቀና እጃቸው ታስሮ ሽባ የሆነ

፩. አቶ ዓለሙ ከበደ አድራሻው ሐሙስ ወንዝ
፪. አቶ ልበይ ቦጋለ » ካምበሌ
፫. አቶ ጉልላት ላላ » መጋንዴ
፬. አቶ መንበሩ ሲሳይ » መጋንዴ
፭. አቶ ደስታ አድማሴ » ፋርጣ ቁስቋም

ጥርሳቸው በድብደባ የወለቀ

፩. አቶ ጌትነት ፈለቀ አድራሻው ማይነት

በጀኔራል ኃይሌ መለስ ሰበብ የተገደሉ የጎበዝ አለቆች

፩. አቶ ውበቱ አበበ አድራሻው አትከና
፪. አቶ መስፍን አያሌው ጊዮርጊስ ደብር
፫. አቶ ተስፋ ተገኝ እብናት
፬. አቶ አለባቸው ደበበ አጊሳ ደብር
፭. አቶ ዘለዓለም መንግሥቴ ገንተኛ ማርያም
፮. አቶ ጫኔው መንግሥቴ በመርፌ መርዝ ተወግቶ የተገደለ

በጥቅሉ ከዓማፂያን ወገን ናችሁ ተብለው የተገደሉት ፹፭ እንደሚጠጉ አመልክቷል' ይልና ሲቀጥል በአማፂያን ወገን ናቸው እየተባሉ በጋሳይና እብናት በእስር ላይ የሚገኙ (በአማራው ድርጅት አባልነት የተጠረጠሩ)

፩. አቶ አያሌው መድፉ
፪. አቶ በሪሁን መንግሥቱ
፫. አቶ ክንዱ ደረሰ ጋይንት
፬. አቶ መንበሩ ታዬ ጋይንት
፭. ቄስ መለስ ጨቁን ጋይንት
፮. አቶ ጮፌር ከበደ ጋይንት
፯. አቶ በዛብህ ኃይሉ ጋይንት
፰. አቶ ውብዓለም ከበደ ጋይንት
፱. አቶ ቢሆን መላኩ
፲. አቶ አላምነው ጌታሁን ይገኙበታል። ሪፖርተሩ ዘገባውን በመቀጠል በክልሉ በተነሳው ሕዝባዊ ዓመፅ ሳቢያ ንጹሃን ዜጎችን የኢሕአዴግ ታጣቂዎች የሽፍቶች ተባባሪ ነህ፣ ስንቅአ

ቀባይ ነህ፣ ዘመድ ነህ ወ.ዘ.ተ. እያሉ በማሰቃዬት ላይ እን
ደሚገኙ ገልጸዋል።

በተለይ የሽፍታ ልጆች ናችሁ፣ የሽፍታ ሚስት ነሽ እ
የተባለ በንጹሃን ዜጎች ላይ ግፍ እየተፈጸመባቸው መሆኑን እ
ስታውቋል በማለት አንድነት ገልጾታል።

ምንም በማያውቁ አርሶ አደሮች ላይ የተወሰደው የግ
ፍ እርምጃ በዚህ በአንድነት ጋዜጣ ላይ የተመለከተው ብቻ
አይደለም።በመንገድ የሚተላለፈውን አላፊ አግዳሚ በመያዝ፣
ከመኖሪያ ቤቱ አፍነው በመውሰድ ድራሻቸውን ያጠፏቸው ዘ
መዶች መራር ኀዘን እያሰሙ ናቸው።ወያኔ ትግራይ በደቡብ
ጎንደርና በወልቃይት ጠገዴ ሕዝብ ላይ የፈጸመው ግፍ የ
ጀርመኑ ናዚ በአይሁዶች ላይ ከፈጸመው ልዩ ልዩ ስቃይ ተ
ለይቶ አይታይም።

የወያኔ ዓይን ያወጣ በቀል በአፄ ቴዎድሮስና በአፄ ዮ
ሐንስ ዘመነ መንግሥት የኢትዮጵያ ዋና ከተማ የነበረች ደብ
ረ ታቦርን ከአፄ ሠይፈ አርዕድ ጀምሮ ለአካባቢው ሕዝብ አ
ገልግሎት ስትሰጥ የኖረች ከተማን ለማጥፋት ልዩ ልዩ አሻጥ
ር እያካሔዱባት ነው። ከተማዋ እንዳትለማ፣ አውቶቡስ እንዳ
ያድርባት አድርጓል። ተማሪዎቿ የወያኔ የኮር አባል ካልሆኑ
በስተቀር በትምህርታቸው ተጽዕኖ ይደረግባቸዋል።

ምንም እንኳ በአካባቢው የሥራ መስክ የተዘጋ ቢሆን
ም የአስተዳደሩና የዳኝነቱ ሥራ በወያኔ ሰዎች የተያዘ ነው።
በአጋጣሚ ተራ ሥራ የተገኘ እንደሆነም የወያኔ የኮር አባልነ
ት መታወቂያ ካላቀረበ ተራውም ሥራ ቢሆን አይፈቀድለት
ም።የወያኔ ተገንጣይ ሠራዊት ደብረ ታቦርን ለመያዝ በአደረ
ገው ጦርነት የደብረ ታቦር ሕዝብ በኃይል ተዋግቶት ስለነበ
ር የዚያን ብድር ገበሬዎችን በምፀዓታዊ መቅሰፍት እየተበቀ
ለ ነው።

### ሕዝብን ያለፍላጎቱ ማስገደድ የራስን ዕድል በራስ መወሰን ይሆን? ወይንስ የትግራይ ሪፑብሊክ ግዛትን ማስፋፋት?

በጎንደር ነገሥታት ዘመን ዛሬ ኤርትራና ትግራይ ተ
ብለው የሚጠሩት ክፍላተ አገር ትግሪኛ ተናጋሪዎች ተጠቃለ
ው በአንድ ስም በትግሬነት ይጠሩ ነበር። ትግሮች ጎንደር
ወደ ነገሥታቱ እየሔዱ ችግራቸውን የሚያሰሙት ከቤተ መ
ንግሥቱ ሰሜን ባለው ተራራ ላይ ውጥተው በመጮህ ነበር።
ያ ተራራ እስከ ቅርብ ግዜ ትግሬ መጮኼያ በመባል ይጠራ
ነበር።

ይህን ታሪካዊ ስም ጀኔራል ነጋ ኃይለ ሥላሴ የክፍለ
አገሩ አስተዳዳሪ በነበሩበት ግዜያት ጎንት ተራራ ብለው ሰይ
መውታል። ይሁን እንጂ ሕዝቡ አሁንም ቢሆን ትግሬ መጮ
ኼያ ብሎ መጥራቱን አልተወም። ወደፊትም ቢሆን ያ ተራ



ራ ታሪካዊ ስሙን ሊያጣ አይገባውም። የትግሬ ሕዝብ ታሪ
ክ ነውና።

ትግሬዎች በዚህ ተራራ ጩኸው በሚያሰሙት አቤቱ
ታ ጉዳያቸው ተፈጽሞላቸው በአገኙት ፍትሓዊ ውሳኔ ተደሰ
ተው ወደ ትውልድ ቦታቸው ይመለሱ ነበር። 'ሚች አውሬ
ገዳዩን ያስመሰግናል' እንደሚባለው ሚቹ ደርግ አገር ወዳዶ
ችን እየገደለ ኮትኩቶ ያሳደጋቸው ወያኔአውያን የዚያን ብድ
ር ለመመለስ ይመስላል የጎንደርን ሕዝብ በተለያዬ መንገድ
በማሰቃየት የግፍ ግፍ እየፈጸሙበት ያለው። አቤቱታ ቢያቀ
ርብ ሰሚ አጥቶ ይሰቃያል።

ለምሳሌ የጎንደር አካል የሆኑትን ወልቃይት፣ ጠገዴን፣
ጠለምትንና ሁመራን ወያኔ ነጥሎ ወደ ትግራይ ሪፑብሊክ
መንግሥት ሲመድብ አቶ ዳኜው ወልደ ሥላሴና አቶ ፍታዬ
አሰጉ የተቃውሞ ደብዳቤ ጽፈው ነበር። እኔም አከታትዬ ለ
ወያኔው ግዜአዊ ፕሬዚዳንት ለነበረው ለመለስ (ለገሠ) ዜና
ዊ ጥር ፲፭ ቀን ፲፱፻፹፯ ዓ ም እንዲሁም ለወያኔ ምክር ቤ
ት የካቲት ፲፪ ቀን ፲፱፻፹፬ ዓ ም የተቃውሞ ደብዳቤዎች
ልኬ ነበር። ዓዌ በጉልበቱ ከምንም ያልቆጠራቸው ደብዳቤዎ
ች በአባሪነት ተያይዘዋል።

ወያኔአዊያን የጎንደርን አራት ወረዳ ሕዝብ በአስተዳደ
ር ረገድ ታሪካዊ ግንኙነት ከሌለው ያለ ሕዝብ ፈቃድ በማስ
ገደድ በትግራይ እንዲቆረጥ ማድረግ የለዩለት የቅኝ ግዛት
አገዛዝን ማስፋት ነው። ወያኔ በዚህ ብቻ አልተወሰነም። በክ
ፍለ አገሩ ተከፍሎ በቀረውም ሕዝብ ላይ የሚፈጽመው በደ
ል ከመሳፍንቱ የተሠሪ ሥርዓት በእጅጉ የከፋ ነው። የተጠቀ
ሱት የ፬ ወረዳ ሕዝብ መቀሌ እየኼደ እንዲጮህ የተደረገው
ም የጎንደሩ ትግሬ መጮኼያ ብድር መመለሻ ነው።

በመሳፍንቱ የተሠሪ ሥርዓት ሕዝቡ በመኖሪያ ቤቱ ነ
ዋነቱን አጥቶ ግፍ ስለበዛበት ከጎንደር ከተማ ወጣ ብሎ በም
ዕራብ ሰቀልት ላይ ስብሰባ አድርጎ በመወያዬት ያንገፈገፈው
ን የተሠሪ ሥርዓት የሚያስወግድለት መሪ ፈልጎ ሲወያይ በ
ዚያን ግዜ የደንቢያና ቋራ ተወላጅ የሆኑ ካሣ የተባሉ በሱዳ
ን በኩል ከመጣው ቱርክ ጋር በመደጋገም ተዋግተው ድል
የተቀዳጁ ጀግና በአካባቢው ስለነበሩ ወደ ጉባኤው ተጠርተው
ቀርበው ጉባኤው የሚሰጥህን ትቀበላለህ ወይ ብሎ ጠይቋቸ
ው መቀበላቸውን ለጉባኤው ቃል በመስጠታቸው፤ ከቤታቸው
ያለውን መጠጥ እንዲያቀርቡ ተነግሯቸው ለግዜው በቤት
ውስጥ የተገኘች አንድ ገንቦ ጠጅ ወደ ጉባኤው ተወስዳ ለ
ሕዝብ የማታዳርስ በመሆኗ ሽማግሌዎች ጠጁን በጭራ እየነከ
ሩ ሕዝቡን በመርጨት ከዛሬ ጀምሮ አልቀንሃል፣ ልጆቻችን
ንም ሰጥተንሃል። ከዚህ አስከፊ የተሠሪ ሥርዓት አላቀን ብለ
ው መርቀው አሰናበቷቸው።ካሣም የጉባኤውን ውሳኔ ተቀብለ
ው ትግላቸውን በመቀጠል መሳፍንቱን ተራ በተራ ድል በማ
ድረግ የተሠሪውን ሥርዓት ከሕዝቡ ላይ አስወግደው እርሳቸ

ውም ዳግማዊ ቴዎድሮስ በሚል ስያሜ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ሆኑ።

እሁንም ጎንደሬውም ሆነ መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ከወያኔ የተሠሪ የጭቆናና የግፍ አገዛዝ ነፃ የሚሆንበትን ብልሃት መፈለግ ይገባዋል። ምክንያቱም ሕዝብ ሳይወድ በግድ ወደ ማይፈልገው ዓመጽ እየተገፋ ነውና። እስከ መቼ ነው በወያኔ ጀሌዎች እየተሰቃዩ የሚኖረው? የፖለቲካ ነፃነት፣ የኢኮኖሚ ተሳትፎ የሌለው መንፈሳዊ ሕይወቱን ያጣ ሕዝብ ምን ይጠብቃል። ከዚህስ የባሰ ምን ይመጣል? ሞት እንደሆነ የፖለቲካ ነፃነቱን ሲገፈፍ ሙቷል።ቀሪው ግብአተ መሬት ነው። እንደ ጃርት ታፍኖ ከመሞት የሞት ሽረት ትግል እንዲያደርግ ይገደዳል። ምን ዓይነት ትግል ለሚለው ብዙ አማራጮች አሉት። በሁሉም የትግል መስክ ወያኔን አዋክቦ ዴሞክራሲያዊ መንግሥት ካልመሠረተ አገሪቱም ሕዝቡም ተያይዘው ይጠፋሉ።

በአዲስ አበባ ከተማ የጀርመኖቹ የማርክስና ኤንግልስ የሶቪዬቱ ሌኒን (በስላሴ ተመስለው) የጣዖት ሓውልት አቁሞ ያሳልም የነበረ ደርግ ከነ ጣዖቱ አብሮ እንደተንኮታኮተው እንዲሁም ወያኔአውያን የሚመለኩበት መቀሌ ላይ በኢትዮጵያዊያን ደም የድል ሐውልት አቋቁመዋል። ይህ የወያኔመመለኪያ ሐውልት ካልፈረሰና ደም በደም ካልተመለሰ በስተቀር ፍቅርና ሰላም፤ አንድነት አይኖርም።

- ኢትዮጵያውያን በጎሳና ቋንቋ እየተከፋፈሉ እርስ በርሳቸው ይፋጃሉ፣
- ያገሪቱ ምጣኔ ሃብት ፈጽሞ ይንኮታኮታል
- ምድሪቱም በእርስ በርስ ጦርነት በደም ስትጨቀይ ረድኤቷን አትሰጥም፣
- ሕዝብ በረኃብና በበሽታ ከፍተኛ ጉዳት ይደርስበታል፣
- ምስቅልቅሉና ትርምሱ በከፋ መልኩ ይቀጥላል፣

ለዚህ ሁሉ ፍቱን መድኃኒቱ እግዚአብሔር እንዲታረቀንና በምድሪቱም ሰላም እንዲሰፍን በመንፈስ ውህደት፣ በዓላማ አንድነት፣ ትዕቢትንና ማን አህሎኝነትን አስወግዶ በመስማማት ወያኔን መስሎ አጎብድዶ፣ ተቃዋሚም ሁኖ በዲፕሎማሲና በፖለቲካ ተፋልሞ በሆነው ስልትና መንገድ ሁሉ ሥርዓትና ባህልየለሹን ወያኔን ተረባርቦ ማስወገድ ብቻ ነው።ይህ ካልሆነ መከራውና ፍዳው፣ ውርደቱና መንከራተቱ፣ ረኃብና በሽታው እየተራዘመ ይሄዳል።ወያኔ ከዕለት ወደ ዕለት በጥፋት እየገፋ ከሰማይ መቅሰፍት እየጋበዘ ነው። እረኞች ሳይቀሩ ራዕያቸውን እየገለጹ ነው።

ደርጎችን ዓይተው በደም ባሕር ሲሻገሩ
ወያኔዎች በጎሣ ዓዌነት እየተመሩ
በእንክርዳድ ጠላ ሰክረው መዘበሩ
ይኸው የእረኞች እንጉርጉሮ ያለፈውን አስታወሰኝ፤



በኢያሱ ዳቦ ነው ትራሱ
በዘውዲቱ ሬሳ ጎትቱ
በተፈሪ የለም ፍርፋሪ። ተብሎ እንደተገጠመ ሰምተናል። ከገጠሪቱ ኢትዮጵያ የመጣ ሰው በዘመነ ወያኔ የምናመርተው እህል ረድኤት የለውም፤ ጠግቦ የሚያድረው ከስንት አንድ ነው፣ ሰላቢ ገብቶበታል፤ የምትታለብ አራስ ላም ወያኔ ካያት ስለምትነጥፍ ሰው ሁሉ ከብቱን ወያኔ እንዳያይበት ያሸሻል። ሞትም በየቤቱ እያንኳኳ ይገባል' ብለዋል።

ወያኔ የኢትዮጵያን ሕዝብ ከአብዮታዊ ማማ ዘርጥጦ አውርዶ በአድኃሪ የጎሳ ቀፎ ከቶታል። ዛሬ በኢትዮጵያ የሚነገረው ስለአብዮታዊ እንቅስቃሴ፣ ስለሳይንስና ቴክኖሎጂ፣ ስለሕዝብ ኑሮ እድገት ሳይሆን ስለጎሳና ቋንቋ፣ ስለኤድስ በሽታና ስለረኃብ፣ ስለጦርነትናንብረት ሽያጭ፣ ስለ ኤርትራውያንመባረርና ስለ ትግራይ ልማት ብቻ ነው። ወይም በኢትዮጵያዊያን ደም ስለሚቆመው የድል ሐውልት ነው።

ወያኔ በከዳት ኢትዮጵያ ሥልጣን ከያዘ በኋላ በአንድ በኩል ኢትዮጵያዊ ለመምሰል እየሞከረ በሌላ በኩል ለሻዕቢያ ጥብቅናቁም ተበድለዋልና ካሣ ይገባቸዋል እያለ አሳልፎ ሲሰጥ ቆይቶ ዛሬ ሻዕቢያን ካላጠፋሁ እያለ ይደነፋል። ወያኔ አገሩን ኢትዮጵያን የከዳ ዛሬ ኮትኩቶ ያሳደገውን ሻዕቢያን ቢክድ የሚያስደንቅ አይደለም፤ ምክንያቱም የራሱን አገር ታሪክና ሰንደቅ ዓላማ ከመካድ የበለጠ ሊሆን አይችልምና። ኢትዮጵያን ያደማት ወያኔ የቁስሏ ጠባሳ ምን ግዜም ከታሪክ ገፅ የሚጠፋ አይደለም።

ደርግ በቀኝ አውለኝ ብሎ ባለመነሳቱ ግራ ገብቶት እግሮቹ እርስ በርሳቸው እየተላተሙ ካሰበበት ሳይደርስ መውደቁን ወያኔእያዩ ያለ አቅጣጫ መሪ ኮምፓስ ሳይዝ በሰሜን ኮከብ እየተመራ ሲሔድ ኮከቡ ወደ ምዕራብ ወስዶት በዚያ ሸመታው ቀንቶት ነበር። ያው የሰሜን ኮከብ ግራ ተጓዦች ወዳሉበት መርቶት የሙታንን ሃብት ለመውረስ ረድቶታል። በግራ ጉዞው (ማሌሊት የወረሰውን የግራዎችን ሃብት እየሸጠ ለመውሰድ ቢጠቅመውም በእምነት ደረጃ ሁለቱንም መንገዶች እከተላለሁ የሚለው ለጥቅም ብሎ እንጂ ሥርዓት ያላቸውን የቀኙም ሆነ የግራ መንገዶችን አይፈልጋቸውም።ሽፍታ ሥርዓት የለውምና።

ወያኔ ሥርዓት አልባ (አናርኪስት) በመሆኑ እያጭበረበረና እየዘረፈ በማመሰቃቀል መኖር የለመደ በሥርዓት ተገርቶ ለመያዝ ይጨንቀዋል። ሥርዓት ያላቸውን መንገዶች የሚጠላበት ዋና ምክንያት በቀኝ የሔደ እንደሆነ በዴሞክራሲ ሥርዓት መሠረት እየቀማና እየሸጠ የወሰደውን ሃብት ለባለቤቱ መልስ ተብሎ ይገደዳል። የግራውን መንገድ እንዳይመርጥ ዝርፊያን፣ ቅሚያንና የግል ሃብት ማካበትን ይቃወመዋል። ወያኔ ከትግራይ ሪፑብሊክ ውጭ እንዳያይ ዓይኑን ሸውራራ አድርጎበት 'ክንፍ የለው አሞራ፣ አይጽፍ ደብተራ' እንደ ተባለው ሁኖበታል።

ከወያኔ ተለዋዋጭ ባሕርይ አንዱ የዝንጀሮ ባሕርይ ነ
ው።ዝንጀሮ አንድን ክምር በልቶ ከጠገበ በኋላ ክምሩን አፈ
ራርሶና በታትኖ እንደሚሔድ ወያኔም ኢትዮጵያን አፈራርሶ
ሕዝብን ለያይቶ ታሪክንና ባሕልን ደምስሶ ለመጥፋት የቆረ
ጠ ነው።

ወያኔ ከመንግሥት ተራ ገብቶ መጠራት የማይገባው
ቢሆንም በጥፋቱ መነሳቱ አይቀርምና ዓፄ ኃይለ ሥላሴና ደር
ግ የገረፉበት ጅራፍ ለእርሱም ተላልፎለት መግረፊያ ጅራፉ
አንድ ዓይነት ነው። ልዩነቱ ገራፊዎቹ ናቸው። የሚገርፉበት
ጅራፍ ስሙ አፍን የሚባል ድንቁርና ነው። አፍን በሚባለው
ድንቁርና እየተለዋወጡ ገርፈውበታል። የሚገርፉበት ዓቢይ
ምክንያታቸው ተፈጥሮን በሕገ መንግሥታችን ውስጥ አውለን
እያለን መሰባሰብንና መደራጀትን፣ መናገርንና መቃወምን የ
መሳሰሉት የተከለከሉ ሲሆን፣ ለምን ትደራጃለህ? ለምንስ
ትናገራለህ? ለምንስ አስተዳደሩን ትቃወማለህ? በተለይም ደር
ግና ወያኔ ዘር በሚመትር አኳኋን እያሰቃዩ አባለ ዘርን አኮ
ላሽተዋል። እንስሳ አፉን እንደሚለጎም የሕዝብን አፍ ለጉመ
ው ምንም እንደማያውቅ እንስሳ አድርገው የ፳፩ኛውን ምዕተ
ዓመት ሰው ለመግዛት ከዓፄአዊ ሥርዓት በእጅጉ የከፋ ምዕ
ዓት አውርደዋል።

'ብልህ ያመቱን፣ ደንቆሮ የዕለቱን' እንደተባለው ዓ
ዋቂዎች ከሳንቃ በተሠራ ጀልባ፣ ደንቆሮዎች ከኩበት በተሠ
ራ ጀልባ ውቅያኖስን ለመሻገር ሲወዳደሩ በሳንቃ ጀልባ የተ
ሳፈሩት ውቅያኖስን ቀዝፈው ሲያቋርጡ፣ በኩበት ጀልባ የተሳ
ፈሩ በውቅያኖስ ላይ ጉዞ እንደጀመሩ በውኃው እርጥበት ኩ
በቱ ሲፈርስ ወደ እበትነት ተለውጠ በመፈረካከሱ ተሳፋሪዎች
እንዳሉ ሁሉም ተያይዘው እንደሰጠሙት እንዲሁም ወያኔ
(ማሌሊት) ሟቹ ደርግ አመቻችቶ በሰጠው የኩበት ዙፋን
ላይ የኩብቱ ጀልባ ውኃ ሲነካው ወደ እበትነት እንደተለወጠ
ወያኔም ወደ ነበረበት ሥርዓት የለሺነት አጋሚዶነቱ ተመል
ሶ ዓይን ባወጣ ዝርፊያ በአፈናና ግድያ፤ በጎሳና ቋንቋ መከ
ፋፈልን እንደ አብዮት ቆጥሮ ይመጻደቅበታል።

ከፊቱ ተፈረካክሶ የወደቀውን የኢሠፓን አወዳደቅ እን
ዳያስተውልም ልቦናው በትዕቢትና በማን አለብኝነት ተነፍቶ
የኢዲ አሚንን የቦካሳንና የሲያድ ባሬን ዕድል ይጠብቃል።
ነገ ምን እንደሚመጣ አያስተውልም።

# ምዕራፍ 23
# የኤርትራውያን ምስቅልቅል ሁኔታዎች

ኢጣሊያ ተባራ ኤርትራ በእንግሊዝ ሞግዚትነት ለ፲
ዓመታት ያህል ቆይታ የራሷን ዕድል በራሷ እንድትወስን በ
ተባበሩት መንግሥታት ሸንጎ በተወሰነላት መሠረት አብዛኛው
የኤርትራ ሕዝብ ከኢትዮጵያ ጋር ለመቀላቀል ያቀረበው ጥያ
ቄ ከታሪካዊ ግንኙነት፣ ከዝምድና ከኢኮኖሚ ግንኙነት፣ ከባ
ህል አንድነትና ከጋራ ታሪክ አንፃር እንጂ የኢትዮጵያ አስተ
ዳደር ስቧቸው አልነበረም።

ቀደም ብሎም በ፲፱፻፳፰ ዓ ም ኢጣሊያ ኢትዮጵያን
ስትወር ስመ ጥር ሐማሴኖች ስር መሠረታችን የሆነች ኢት
ዮጵያ እናታችንን አናስወርርም በማለት ኢጣሊያንን ከድተው
ከኢትዮጵያ ጎን ተሠልፈው ኢጣሊያንን የወጉ ኢትዮጵያ የታ
ሪካቸው መነሻ፣ የባህላቸው መፍለቂያ፣ የማንነታቸው መታ
ወቂያ በመሆኗ ነበር። የኤርትራ ደጋማው ክፍል ከኢትዮጵያ
ጋር ለመቀላቀል ያደረገው ተጋድሎ ስነ ልቦናዊ መሠረቱ አ
ንድ በመሆኑ ነበር። የኢትዮጵያ መንግሥትም ኤርትራን ወደ
ኢትዮጵያ ለመቀላቀል ፖለቲካዊና ዲፕሎማሲያዊ ትግል ማ
ድረጉ ግልጽ ነው። በሽምቅ ውጊያ የተሠለፉትን ከሠራዊ አ
ስረሳኸኝን፣ ከአካለ ጉዛይ ወልደገብርኤልን ይረዳ እንደ ነበር
የምናውቀው ነው።

ወደ ኢትዮጵያ አንቀላቀልም በሚሉ ስብስቦችም በእነ
ራቢጣ አል ኢስላሚያና ኤርትራ ለኤርትራ የሚለውን ሊበራ
ል ፕሮግሬሲብ ፓርቲና ፕሮ ኢጣሊያ ላይ ስነ ልቦናዊ
ሸብር በመልቀቅና በጉልበትም ጭምር የኃይል ሥራ ይካሔ
ድ ነበር። እነዚህ የተጠቀሱትን አሸባሪ መሪዎች ጎንደር በ፲
፱፻፵፱ ም መጥተው አይቻቼዋለሁ።

የኢትዮጵያ መንግሥት ኤርትራን ከኢትዮጵያ ለመቀላ
ቀል በውጭ አገርና በኤርትራ ውስጥ ያደረገውን ከፍተኛ ተ
ጋድሎ ድሮ አምባሳደር የነበሩ አቶ ዘውዴ ረታ 'የኤርትራ
ጉዳይ' በሚለው መጽሃፋቸው በሚገባ አብራርተው ገልጸው
ታል። የኤርትራ ጉዳይ የፖለቲካ መነታረኪያ እንዲሆን ያደ
ረጉት የተቋቋሙት ማኅበሮች ይገፉ የነበሩት ከግል ስሜት
አንፃር እንጂ በሕዝቡ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ዘላቂ ጥቅሞች
ላይ ያተኮረ አልነበረም። በኤርትራ በወቅቱ ተፈልፍለው ከነበ
ሩት የፖለቲካ ማኅበራት ውስጥ ታሪካዊነትን መሠረት አድር
ጎ ያቀደ 'የአገር ፍቅር የአንድነት ማኅበር' ብቻ ነበር ማለ
ት ይቻላል። የአገር ፍቅር ያንድነት ማኅበር ኤርትራን ከእና
ት አገሯ ከኢትዮጵያ ለመቀላቀል የታገለበት ዋና ምክንት
ማኅበራዊና ተፈጥሮአዊ የማንኙነት ማተብን ለአለመበጠስና
ኤርትራውያን ለብዙ ሺህ ዓመታት የኖሩትን ታሪካቸውን ደ
ምስሰው ኤርትራን ቅኝ ገዢ የመሠረታት አዲስ አገር አለመ
ሆኗን በተግባር ለማሳየት ነበር።